
በኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት
የአማራ ክልል የምክክር ግኝቶች አጭር ሪፖርት

(በፌደራል ደረጃ ከመጋቢት 9 – 11/ 94 አም ድረስ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ ለሚካሄደዉ ብሄራዊ የምክክር መድረክ ለዉይይት የቀረበ)



CRDA

የአማራ ክልል የድህነት ቅነሳ
ስትራቴጅ ቤክፊታሪያት

መጋቢት 1994 ባህር ዳር

ማዉጫ

ርዕስ		ገጽ
1	መግቢያ	1
2	የአማራ ክልል የህብት መሠረትና አጠቃላይ ሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ	1
3	በኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጃ ሰነድ ዝግጅት የአማራ ክልል የምክክር ግኝት	3
3.1	የምክክር መድረክሥች ሂደትና አፈፃፀም	3
3.2	የወረዳና ክልል አቀፍ የምክክር መድረክ ግኝቶች	5
	3.2.1 የድህነት ትርጉም	5
	3.2.2. የድህነት መንስኤዎች	6
	3.2.3. የድህነት ገፅታ	7
	3.2.4 በክልሉ ባለፉት አመታት የተካሄዱ ድህነት ተኮር የልማት እንቅስቃሴዎች ያስመዘገቡት ዉጤትና የነበረባቸዉ ችግር	9
	3.2.5 በክልሉ የመንግስት አስተዳደር መዋቅሮች እየሰጡት ያሉት አገልግሎቶችና የነበረባቸዉ ችግር	12
	3.2.6 በቀጣዩ ድህነትን ለመቀነስ ቅድሚያ ትኩረት አግኝተዉ መከናወን የሚገባቸዉ ተግባራት	13
	3.2.7 ብሄራዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂን ስኬታማ ለማድረግ መመቻቸት ያለባቸዉ ከባቢያዊ ሁኔታዎች	22
4.	በምክክር ሂደት የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎችና የተስተዋሉ የአፈፃፀም ችግሮች	23
5.	ማጠቃለያ	24

CCRDA

1. መግቢያ

በዚህ አመት ኢትዮጵያ ብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ ሰነድ ለማዘጋጀት በእንቅስቀሴ ላይ ትገኛለች። የስትራቴጅ ሰነድ ዝግጅቱ መላውን ህብረተሰብ ባሳተፈ መልኩ እንዲከናወን በማስፈለጉ እንደሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች በአማራ ክልልም በየደረጃው የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የሲቪል ማህበራት፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሀይማኖት ተቋማት ታዋቂ ግለሰቦችና እንዲሁም በተለያየ የኑሮ ደረጃ ከሚገኙ የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ ተሳታፊዎች በተገኙበት ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚቀረፀው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ ሰነድ ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦች ተሰባስበዋል።

ይህ ዕሁፍ ከሀገራዊው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ ሰነድ ዝግጅት ጋር በተያያዘ በአማራ ክልል የተከናወኑ የወረዳና ክልል አቀፍ የምክክር መድረኮች አመራር ሂደትና አፈፃፀምን አስመልክቶ ግንዛቤ ለማስጨበጥና በተከታታይም ለሀገር አቀፍ የምክክር መድረክ የውይይት መነሻ እንዲሆኑ በክልሉ በየደረጃው የተካሄዱ የምክክር ስብሰባዎች ላይ የተገኙ የምክክር ግኝቶችን በተጠቃለለ መልኩ በማቅረብ ለሀገር አቀፍ የምክክር መድረክ የውይይት መነሻ እንዲሆኑ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በዚህ ዕሁፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ የአማራ ክልል የኑሮ መሠረትና አጠቃላይ ሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታን ይዳስሳል። በመቀጠልም በኢትዮያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ ሰነድ ዝግጅት የአማራ ክልል የምክክር ግኝቶች ቀርበዋል። በዚህ ምዕራፍ የቅድመ ምክክር ስራዎች ሂደትና በተከታታይም በክልሉ በየደረጃው በተከናወኑ የምክክር መድረኮች ስለድህነት ትርጉም፣ መንስኤዎችና የድህነት ክልላዊ ገፅታ፣ ለማብራራት ተሞክሯል። ቀጥሎም ድህነትን ለመቀነስ ቅድሚያ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ተግባራት ተዘርዝረዋል። ሀገር አቀፍ የስትራቴጅ ሰነድ ተግባራዊነት ስኬታማ ከማድረግ አኳያ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትም በዚሁ ምዕራፍ ሥር ተጠቁመዋል። በመጨረሻም በየደረጃው የምክክር መድረኮችን ከማከናወን ጋር በተያያዘ የተስተዋሉ የአፈፃፀም ችግሮችና እንዲሁም ለወደፊት ለተመሣሣይ የምክክር ሂደቶች በጥሩ ተሞክሮነት የተስተዋሉ ነጥቦች ቀርበዋል።

2. የአማራ ክልል ሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል በሀገሪቱ የሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን በሰሜን ከትግራይ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በደቡብ ከኦሮሚያና በደቡብ ምዕራብ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልልና እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ከሱዳን ጋር ይዋሰናል።

ክልሉ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 15 በመቶውን ያህል ይሸፍናል። የክልሉ አስተዳደራዊ መዋቅርና አደረጃጀት ለልማት በሚያመችና የብሔረሰብ ዞኖችን ህገመንግስታዊ መብት ባገናዘበ መልኩ በ11 የዞን መስተዳድር በ114 የወረዳ መስተዳድርና እንዲሁም በተዋረድ በቀበሌዎችና መንግስታዊ ቡድኖች የተከፋፈለ ሲሆን በውስጡ የአማራ የአዊ፣ የህምራና የኦሮሞ ብሔረሰቦች በአንድነት የሚኖሩበት ክልል ነው። የክልሉ ህዝብ ብዛትም በ1993 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 16.8 ሚሊዮን እንደደረሰ ተገምቷል።

CCRDA

የክልሉ መልከአ ምድራዊ አቀማመጥ ከባህር ወለል በላይ ከ700 እስከ 4620 ሜትር ጉልህ የከፍታ ልዩነት ያለው ሲሆን የአየር ንብረት ፀባዩም የቆላ፣ የደጋ፣ የወይና ደጋና የውርጭ የአየር ንብረት ያካተተ ነው:: በመሬት አጠቃቀም ረገድ ከአጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ ውስጥ 27 በመቶ የሚሆነው ለእርሻ ስራ ተስማሚ የሆነ 14.7 በመቶው በደንና ቁጥቋጦ፣ 3.8 በመቶ በውሀ አካላት የተሸፈነ፣ 30 በመቶ ለግጦሽ የዋለና 5.3 በመቶ ለመኖሪያነት የዋለ ሲሆን ቀሪው በወቅቱ በጥቅም ላይ ያልዋለ እንደሆነ ይገመታል::

የአማራ ክልል ህዝብ የኑሮ መሠረት በዋናነት በግብርና ስራ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ይኸውም ከጠቅላላው የክልሉ ምርት (Regional Gross Domestic Product) ውስጥ 69 በመቶ የሚሆነው ከዚሁ ክፍለ ኢኮኖሚ እንደሚመነጭ ከ1986-89 ዓ.ም ባሉት አመታት በተደረገ ጥቅል የክልል ምርት ግመታ ጥናት ላይ ለማወቅ ተችሏል:: በስራ ስምሪት ረገድም ከጠቅላላው ነዋሪ ውስጥ ከ89 በመቶ በላይ የሚሆነው በእርሻ ስራ ተሰማርቶ የሚኖር እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ::

ክልሉ በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በተደጋጋሚ የሚጠቃ በመሆኑ ከአፈር መሸርሸር፣ ከድርቅና ከዝናብ ስርጭት አለመመጣጠን ጋር በተያያዘ ከጠቅላላ ወረዳዎች ውስጥ 48 የሚሆኑት ወረዳዎች በምግብ ምርት ራሳቸውን የማይችሉ በመሆናቸው በአብዛኞቹ ወራቶች ለምግብ እርዳታ ጥገኛ ሆነው ኑሮአቸውን እንዲመሩ ተገደዋል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው የተቀናጀ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በክልሉ ተግባራዊ እየሆነ ቢገፅም የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ በቀጣዮች አመታት ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ ተግባር ነው::

የማህበራዊ አገልግሎቶችን አቅርቦት በተመከተ በክልሉ የ1ኛ ደረጃ የትምህርት ሽፋን 51 በመቶ የደረሰ ቢሆንም እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ የክልሉ ህፃናት ውስጥ ግማሽ ያህሉ አሁንም የዘመናዊ ትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አይደሉም:: በመሠረታዊ ጤና ክብካቤ ረገድ በዋነኝነት በመካላከል ላይ የተመሠረተውን የጤና ፖሊሲን ለማስፈፀም በክልሉ ባሉ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመታገዝ የመሠረተ ጤና ክብካቤ ሽፋን በ1993 መጨረሻ 41 በመቶ ደርሷል:: ይሁን እንጂ ከክልሉ ህዝብ አሰፋፈርና የመሬት አቀማመጥ ወጣገባነት የተነሳ ከ60 በመቶ የማያንሰው ነዋሪ አሁንም በአቅራቢያው የመሠረተ ጤና ክብካቤ አያገኝም::

የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦትን በሚመለከት በገጠር የንፁህ መጠጥ ውሀ ሽፋን 23 በመቶ፣ በከተሞች 96 በመቶና አጠቃላይ የክልሉ የንፁህ መጠጥ ውሀ ሽፋን 28 በመቶ ላይ ይገኛል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለያየ የውሀ ወለድ በሽታዎች የሚጠቃው ህዝብ ቁጥር እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በሌሎች የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች ዙሪያ ማለትም በመንገድ አውታሮች ግንባታ፣ በኤሌክትሪክ ቴሌኮሙኒኬሽንና በሌሎች ለልማት ዋነኛ መሠረት በሆኑ መሠረተ ልማቶች እድገት እጅግ ወደኋላ የቀረ ክልል ነው ማለት ይቻላል:: :: የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማትን አስመልክቶ ባለፉት ጥቂት አመታት መጠነኛ መሻሻሎች ቢታዩም ክልሉ ያለበት የልማት ደረጃ አሁንም ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ እነኝህን ጥረቶች ይበልጥ አጠናክሮ መስራት የሚጠይቅ ይሆናል::

CGRDA

3. በኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ ሰነድ ዝግጅት የአማራ ክልል የምክክር መድረኮች ግኝት

3.1 የምክክር መድረክ ሂደትና አፈፃፀም

በኢትዮጵያ በዚህ አመት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ ሰነድ ለማዘጋጀት በየደረጃው የተለያዩ ማስፈፀሚያ መዋቅሮች የተዘረጉ ሲሆን በአማራ ይህን ብሄራዊ ተልዕኮ ለማከናወን በክልሉ በቅድመ ምክክር ምዕራፍ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

የምክክር ወረዳዎች ዝርዝርና የአመራረጥ ሂደት

በሀገር አቀፍ ደረጃ ምክክር ከሚካሄድባቸው 116 ወረዳዎች ውስጥ 23ቱ በአማራ ክልል የሚገኙ ሲሆን እነኚህ ወረዳዎች ወካይነት እንዲኖራቸዉ የወረዳዎችን የአየር ቀጣና፣ የምግብ ዋስትና ሁኔታ፣ የልማት ደረጃ ልዩነት፣ የብሔረሰብ ውክልና፣ የከተማና ገጠር ባህሪንና ሌሎች ልዩ ባህሪያትን /የጠረፍ ወረዳና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ/ መሠረት በማድረግ ምርጫው እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ በክልሉ ለምክክር የተመረጡ ወረዳዎች ዞናዊ ስርጭት በዋነኝነት ያሳቸውን የህዝብ ብዛተና የቆዳ ስፋት መሠረት በማድረግ ሲሆን በክልሉ ከሚገኙ 11 ዞኖች ውስጥ ከሰሜን ጐንደር /የመተማ፣ በለሣ፣ ጃናሞራና ጐንደር ከተማ/፣ ከደቡብ ጐንደር /እስቴና እብናት/፣ ከሰሜን ወሎ /መቄትና ቆቦ/፣ ከደቡብ ወሎ /ቃሉ፣ ጃማና፣ ደሴ ከተማ/፣ ከሰሜን ሸዋ /ቀወት፣ ላሎማማና አንሳሮ ዋዩ/፣ ከምዕራብ ጐጃም /አቸፈርና ሰከላ/፣ ከምስራቅ ጐጃም /ደጀን፣ ባሶሊበንና ሸበል በረንታ/፣ ከባህር ዳር ልዩ ዞን /የባህር ዳር ከተማ/፣ ከአዊ /የአንካሻ ጓጉሳ/፣ ከአርሚያ /ባቲ/ እና ከዋግ ኽምራ /የሰቆጣ/ ወረዳዎች በድምሩ 23 የምክክር ወረዳዎች እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡

- የወረዳ የምክክር ስብሰባ መሪዎችና የምክክር ተሳታፊዎች መረጣ

ከሰነድ ዝግጅቱ ጋር በተያያዘ በተከታታይ ለሚደረጉ የስብሰባ መድረኮች አመራርና አጠቃላይ የምክክር ሂደት ምን መምሰል እንዳለበት በቂ ግንዛቤን ለማስጨበጥና የተገኘውንም ግንዛቤ በሙሉ አቅም ይዞ ወደ ተግባር እንዲገቡ ለማስቻል ከየወረዳው ከማንኛዉም የመንግስት አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ነፃ የሆኑ ሶስት የስብሰባ መሪዎች ከየወረዳው እንዲመረጡ በማድረግ በድምሩ ከ23 ወረዳዎች የተውጣጡ 69 የስብሰባ መሪዎች (convenors) ተገቢውን የቅድመ ምክክር ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በምክክሩ እንዲሳተፉ ከየወረዳው የተወከሉ የህብረተሰብ ክፍሎችም ተገቢው ውክልና ኖሮአቸውና የሚነሱ ሀሳቦችም ሰፊ የህብረተሰብ መሠረት እንዲኖራቸው ለማስቻል የአመራረጥ ሂደቱ ከተለያዩ የህብረሰብ ክፍሎች የእድሜንና የፆታን ስብጥርን፣ የስራ ሁኔታ፣ የኢኮኖሚ መሰክ፣ የአኗኗር ሁኔታንና የመሣሠሉትን እንዲሁም ከሲቪል ማህበራት የቀበሌና የአገልግሎት የህብረት ስራ ማህበራት የህይማኖት ተወካዮች የግል ባለሀብቶችና በወረዳው ቀጥተኛ የልማት ተሳትፎ የሚያደርጉ የመንግስት አካላትና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማትና ርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እንዲውጣጡ በማድረግ በድምሩ 1150 ተሳታፊዎች የተገኙበት የምክክር ስብሰባዎች በወረዳ ደረጃ ተካሂደዋል፡፡ በምክክር ስብሰባው የሴቶችን ውክልና ለመጠበቅ ከጠቅላላው ተሳታፊ

CGRDA

አንድ ሶስተኛው ሴቶች እንዲሆኑ ተደርጓል። ከዚህም ሌላ በክልሉ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚንቀሳቀሱበት የሥራ አካባቢ በተካሄዱ የወረዳ ምክክሮች ተሳታፊ ሆነዋል።

- የወረዳ ምክክር አጀንዳ ቀረፃና ይዘት

በወረዳ ደረጃ ለተደረገው የምክክር ስብሰባ መነሻ የሚሆን የውይይት አጀንዳ ከየወረዳው ከተመረጡ የስብሰባ መሪዎች ጋር በመሆን የጋራና ወጥ የሆኑ አጀንዳዎች የተቀረፁ ሲሆን የአጀንዳዎች አጠቃላይ ይዘት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ማለትም የወረዳው ህዝብ የኑሮ መሠረትና የኑሮ ሁኔታ ምን ይመስላል? በወረዳው የድህነት ምንነት መንስኤዎችና ለድህነት ይበልጥ የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? በወረዳው ድህነትን የሚያባብሱ ባህላዊ፣ ማህበራዊና የግል ባህሪያት ምንድን ናቸው? በወረዳው ድህነትን ለመቀነስ ባለፉት አምስት አመታት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በመንግስትና በህብረተሰቡ የተከናወኑ የልማት ፕሮግራሞች ምንድ ናቸው? ያሉት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ተቋሞች ለህብረተሰቡ እየሰጡት ያሉት አገልግሎቶች ምን ይመስላሉ? ችግሮችስ ምን ነበሩ? በተለያየ ደረጃ በወረዳው ያሉ የመንግስት አስተዳደር መዋቅሮች ለህብረተሰቡ እየሰጡት ያሉት አገልግሎቶች ምን ይመስላሉ? ምን ችግሮች ነበሩባቸው? በወረዳው ድህነትን ለመቀነስ ወደፊት ቅድሚያ ትኩረት አግኝተው መከናወን ያለባቸው ርምጃዎች ምንድን ናቸው? ቅደም ተከተላቸውስ? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያጠነጠነ የመወያያ አጀንዳ ተቀርፆ ውይይቱ ተካሂዷል።

- የወረዳና ክልል አቀፍ የምክክር ስብሰባ ሂደት

በክልሉ ውስጥ በተመረጡት 23 የምክክር ወረዳዎች በ10 የምክክር ማዕከል ከተሞች በሁለት ዙር የምክክር ስብሰባው ተካሂዷል። የምክክር ሪፖርቱም አስቀድሞ የተቀረፀውን የመወያያ አጀንዳ ባካተተ መልኩ በየወረዳው አወያዮች አማካኝነት ተጠቃሎ ሪፖርቱ እንዲወጣ ተደርጓል።

የክልል ምክክር መድረክ በዋነኝነት ከወረዳዎች የተገኘን የምክክር ግኝት መሠረት ባደረጉ አጀንዳዎች ላይ በመወያየት ከምክክሩ የሚገኘው ውጤት ክልላዊ ባህሪያት ኖሮት ለሀገራዊው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ ሰነድ ዝግጅት ጠቃሚ ሀሳቦች የሚዘገቡበት መድረክ በመሆኑ በወረዳ ምክክር ግኝቶች ላይ በማተኮር ሰፊ ውይይት ተደርጓል። ከውይይቱ በፊት በሰነድ ዝግጅቱና አጠቃላይ በድህነት ጽነሰ ሀሳብ ላይ ግንዛቤን ሊሰጡ የሚችሉ ፅሁፎች ቀርበዋል። ከዚህም በመቀጠል በክልሉ በገጠርና በከተማ አጠቃላይ የድነት ገፅታና መንስኤ እና በክልሉ ልማትን ለማፋጠንና ድህነትን ለመቀነስ የተከናወኑ የልማት ስራዎች፣ ያስመዘገቡት ውጤት፣ የነበረባቸው ችግርና ወደፊት መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎች እንዲሁም የመንግስት መዋቅሮች ለህብረተሰቡ እየሰጡት ያሉት አገልግሎቶችና የነበረባቸው ቸግር ላይ ውይይት ተደርጓል። በመጨረሻም በክልሉ ወደፊት ቀጣይነት ያለው ልማት በማካሄድ ድህነትን በአስተማማኝ ለመቀነስ በአጭርና በረጅም ጊዜ መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎች እና ብሔራዊውን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዉን አፈፃፀም ስኬታማ ለማድረግ መወሰድ ያለባቸው ርምጃሞች በሚሉ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ ተጠናቋል ::

CCRDA

ወፍጮ ያለው፣ የቤት እቃው የተሟላ፣ የግል መኪና ያለው፣ የሚያከራየው ትርፍ ቤት ያለው፣ ዘመዶቹን አስጠግቶ የሚያኖር፣ ተመጣጣኝ ቤተሰብ ያለው፣ ሀይማኖቱን ጠብቆ የሚኖር፣ ወዘተ በሚል ተገልጿል። በአንፃራዊ መልኩ የመጥፎ ህይወት መገለጫዎች ከላይ ከተገለፁት ሁኔታዎች የተገለለና ለእነኚህ ነገሮች ያልታደለ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ የኑሮ ሁኔታው በመጥፎ ህይወት እንደሚፈረጅ ተዘግቧል።

3.2.2. የድህነት መንስኤዎች

የድህነት መንስኤዎች በገጠር ወረዳዎች፡-

የድህነት መገለጫው እንደየአካባቢው የኑሮ መሠረት ባህሪ የሚለያይ የመሆኑን ያህል በገጠር ወረዳዎች በተካሄደ ምክክር ለድህነት መንስኤ ሆነው ከተገለፁት ውስጥ የግብርና ምርትና ምርታማነት መቀነስ በክልሉ ያለውን የውሀ ሀብት ጥቅም ላይ አለማዋል /የአባይ ወንዝና ሌሎች ተፋሰስ/ የተፈጥሮ አደጋዎች በተደጋጋሚ ማከሰት /የሰብል ተባይ መከሰት፣ የዝናብ አጥረትና ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ/ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን /የአፈር ብክለት መባባስ፣ የአፈር ለምነት መቀነስ፣ የደን ሀብት መመናመን/፣ ጤናማጣት /የወባና የኤድስ መስፋፋት፣ የህዝብ ቁጥር መብዛት /ወላድነት፣ የቤተሰብ ምጣኔ አለመለመድ/ የማህበራዊ አገልግሎቶች በበቂ አለመሟላት /የትምህርት ተቋማት አለመስፋፋት፣ የጤና ጥበቃ ተቋሞች አለመስፋፋት/፡ የማምረቻ መሣሪያዎችና የካፒታል አቅም እጥረት /የእርሻ በሬ አለመኖር፣ በቂ የእርሻ መሬት አለመግር፣ በቂ ወረት አለመኖር/፣ የህይማኖትና ባህላዊ ተፅዕኖዎች (ከጐጂ ባህል አለመላቀቅ፣ ከአቅም በላይ መደግስ፣ ተስካርና ዝክር፣ ጣሊጋ፣ አጫሙየ፣ ወበራ፣ ግጥግጥ፣ አጐበር፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣ የግል ባህርያት ስራ መናቅ፣ የቤተሰብ ጭቅጭቅና ፍቺ፣ የስራ ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም፣ የመጠጥ ሱሰኝነት፣ የቁጠባ ባህል አለመዳበር)፣ ከአንድ በላይ ቤተሰብ መመስረት፣ /ቅምጥ/፣ በስርቆት መክበርን መፈለግ የሚሉ ተገልፀዋል።

የድህነት መንስኤ በከተማ ወረዳዎች፡-

በከተሞች ለድህነት መንስኤነት የተገለፁት ነጥቦች በገጠር ነዋሪው ከተገለፁት ሁኔታዎች ጋር በተወሰነ ደረጃ የተለየ ሲሆን ምክክር በተካሄደባቸው የከተማ ወረዳዎች የተገለፁት የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መሄድ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አለመስፋፋት፣ የኑሮ ውድነት፣ የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ዋጋ ታሪፍ መናር፣ ኢንቨስተሮችን የሚጋብዝ ምቹ ሁኔታ አለመኖር፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በከተሞች አለመስፋፋት፣ የሀገር ውስጥ ምርት የመጠቀም ባህል አለመዳበር፣ በተመሣሣይ የንግድ መስክ መሰማራት፣ የገንዘብ የመግዛት አቅም መውደቅ፣ የቁጠባ ባህል አለመለመድ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አለመስፋፋት የትምህርትና ጤና ተቋማት በበቂ አለመኖር የማይመጎት መስፋፋት፣ የተላላፊ በሽታዎች መበራከትና የመድሀኒት ዋጋ መናር፣ የማህበራዊ ዋስትና ሁኔታዎች አለመሟላት /የጡረታ ገቢ አለመስተካከል፣ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች አለመኖር፣ ለአካል ጉዳተኞች የሥራ መስክ አለመፈጠር/፣ የመንግስት ገንዘብ ብክነትና የቁጥጥር መላላት፣ የመንግስት ቢሮክራሲ መራዘም፣ ችግሮችን በግልፅ ያለመወያየት፣ ባህላዊና ማህበራዊና የግል

CCRDA

ባህርያት /ጠጭነት፣ ሴትኛ አዳሪነት፣ የስራ ጊዜ በአግባቡ አለመጠቀም፣ የአመጋገብ ባህል አለመለወጥ/ ህብረተሰቡ ለጋራ ልማት ያለው ግንዛቤ እናሳነት በሚል ተገልፀዋል::

3.2.3. የድህነት ገፅታ

ካለፉት አምስት አመታት ወዲህ በክልሉ የድህነት ገፅታ ምን አንደሚመስል በየደረጃው ውይይት ተደርጉበታል::

በገጠር የድህነት ገፅታ

በገጠር የድህነት ገፅታ የቀድሞውንና አሁን ያለውን ሁኔታ በተለያዩ አመልካቾች በመታገዝ ዉይይት ተደርጎአል:: በዚህም መሠረት በክልሉ ዝናብ አጠር አካባቢዎች የዋና ዋና ሠብሎች ምርታማነት መቀነስ፣ የነፍስ ወከፍ መሬት ይዞታ ማነስ፣ የደን ይዞታ እየቀነሰ መምጣት፣ የግጦሽ መሬት መጣበብ፣ የእንስሳት ሀብት በአይነትና በመጠን መቀነስ የቤት እንስሳት የውልደት መጠን መቀነስ የእለት ተረጂ ቁጥር እያደገ መሄድ የሚሉ ክስተቶች እንዳተስተዋሉ ተገልጿል:: የሰብል ምርት በተደጋጋሚ በሚከሰት ድርቅና ፀረ ሰብል ተባይ ምክንያት ቀድሞ ይገኝ ከነበረው የመቀነስ ሁኔታ እንደታየ ተገልጿል:: በአሁኑ ወቅት ከሚታየው የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የአፈር ክለትና ቀድሞ ይታረሱ የነበሩ መሬቶች በባዕድ አረሞች በመወረሳቸው ምክንያት የነፍስ ወከፍ የእርሻ መሬት ይዞታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰ እንደመጣ ተገልጿል:: የድህነት ገፅታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መሄዱን የሚያመለክቱ ሌሎች አመልካቾች ማለትም ለተጨማሪ የእርሻ መሬት አቅርቦት ሲባል በሚመነጠር ደን ምክንያት ቀድሞ የነበረው የደን ሀብት ይዞታ እየቀነሰ በመምጣቱ ይገኝ የነበረ ተጨማሪ ገቢ እየቀነሰ መምጣቱ ተገልጿል:: የእንስሳት ሀብት ይዞታ በመጠንና በአይነት እየቀነሰ መጥቷል:: ለዚህም መንስኤው በግጦሽ መሬት እጥረትና የእንስሳት በሽታ መበራከት ሳቢያ የእንስሳት ይዞታ መጠን እየቀነሰ መጥቷል:: ከዚህም ሌላ በመኖና የከብት መጠጥ ውሀ እጥረት ሳቢያ የእንስሳት የውልደት ምጣኔ ቀደም ሲል ከብት በየአመቱ እና ፍየል በአመት ሁለት ጊዜ ይወልድ የነበረው በአሁኑ ወቅት ከብት በየሶስት አመቱና ፍየል በአመት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚወልዱ ተገልጿል::

በሌላ በኩል በቂ የዝናብ ስርጭትና ለእርሻ ተስማሚ መሬት ባለባቸው የክልሉ ምዕራባዊ አካባቢዎች በቂ የሰብል ምርት ቢመዘገብም በአንዳንድ ሰብሎች የዋጋ መውደቅ ሁኔታ መከሰትና በተጓዳኝ የግብአት ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ ለአርሶ አደሩ የድህነት መባባስ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ተገልጿል:: ከገጠር ነዋሪው ህዝብ የኑሮ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በተለይም ድርቅ በሚያጠቃቸው የክልሉ አካባቢዎች የምግብ ፍጆታ አቅርቦት እየቀነሰ መጥቷል:: በዚህም ምክንያት የእለት ተረጂው ቁጥር ከቁድሞዎቹ አመታት እያደገ እንደመጣ ተገልጿል:: የነቀል ገበሬዎች ቁጥርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል:: በእርሻ በሬና መሬት እጦት ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማና ወደሌሎች አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚደረግ ስደትና መፈናቀል እየጨመረ እንደመጣ ተገልጿል::

በከተሞች የድህነት ገፅታ

ባለፉት አመታት በከተሞች አካባቢ የተከናወኑ በርካታ የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ስራዎች፣ የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት የስልክ የመብራትና የትራንስፖርት አገልግሎቶች እየተሻሻሉ እንደመጡ

CGRDA

ተገልጿል። ይሁን እንጂ አጠቃላይ የኑሮ ውድነት እየተባባሰ እንደመጣ ተገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ ቀደም ሲል በችግርነት ይፈረጁ ያልነበሩ አንዳንድ ሁኔታዎች አሁን በስፋት እየተከሰቱ እንዳለ ተጠቁሟል። ከእነዚህም ውስጥ በተማሪው ክፍል በተለይም በወጣቱ አካባቢ ትምህትን ጨርሶ ያለስራ መቀመጥ፣ ባልተማረው አካባቢም የስራ አጥነት ችግር፣ በህፃናትና ወጣቶች አካባቢ የጎዳና ተዳዳሪነት መበራከት፣ በሴቶች የሴትኛ አዳሪነት መበራከት፣ በወጣቶች ከቦታ ቦታ ፍልሰትና መፈናቀል በንግዱ ህብረተሰብ ንግድ ቤትን ዘግቶ የመሰደድ፣ የመኖሪያ ቤት አልባነት፣ ከፍሎ ለመታከም የአቅም እጥረት እና ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር መጨመር ሁኔታዎች እንደተስተዋሉ ተገልጿል። ከወጣቱ ስራ አጥነት ጋር በተያያዘ በምክንያትነት የተጠቀሱት ጉዳዮች ለተማረ የሰው ሃይል የስራ መስክ መጣበብና በተወሰኑ ወጣቶች አካባቢ ለትምህርት ያለ ፍላጐት በተወሰነ ደረጃ መሸርሸርና ከትምህርት ይልቅ በአጭር ጊዜ ሀብትን በሚያስጉኙ ሥራዎች ወደ መሠማራት የማዘንበል ሁኔታዎች ተገልፀዋል።

ከጐዳና ተዳዳሪነት መበራከት ጋር በተያያዘ በረሀብ ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት፣ የውልደት መበራከት ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ያላቸው የአስተዳደግ ቁጥጥር መላላት፣ አቅም የሌላቸው ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለተጨማሪ ገቢ ማስገኘነት ወደ መንገድ ማሰማራት ሁኔታ እየተባባሰ እንደመጣ ተገልጿል።

ከገጠር ወደ ከተማ ከሚደረግ ፍልሰት ጋር በተያያዘ በገጠር የእርሻ መሬት እጦት ለወጣት ገበሬዎች ፍልሰት ቁጥር መጨመር በምክንያትነት ተገልጿል። በሌላ በኩል በተለይም በንግዱ ህብረተሰብ በመካከለኛ ንግድ ተሰማርተው የሚኖሩ ነጋዴዎች በኪሳራ የመውጣትና አንዳንዶቹ ደግሞ ያለአቅም ከባንክ በመበደር ለመክፈል ባለመቻል የንግድ ቤቶቻቸውን እየዘጉ የመሠደድ ሁኔታዎች ተስተውለዋል።

ከመኖሪያ ቤት ችግር መባባስ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታን በቀላሉ ማግኘት ይቻል እንደነበረና በአሁኑ ወቅት ግን በማዘጋጃ ቤቶች አካባቢ ባለ ረጅምና አሰልቺ ቢሮክራሲያዊ አሠራር፣ ለቦታ ምሪት በሚጠየቀው የመያዣ ገንዘብ ከፍተኛነትና እንዲሁም በአነስተኛ ገቢ ለሚተዳደርና ለመንግስት ሠራተኛው በባንክ ብድር ቤት ለመሥራት የሚችልበት ሥልት አለመኖሩ በከተሞች የመኖሪያ ቤት ችግር እንዲባባስ ማድረጉ ተገልጿል።

የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መሄድ በከተሞች ለተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች መጣበብ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከተሞች ያላቸው የአገልግሎት አቅም አሁን ያለውን የህዝብ ቁጥር እድገት ተከትለው ስለማይሄዱ ከቀድሞዎቹ አመታት በተለየ ሁኔታ የሥራ መስክ መጣበብ፣ የትምህርትና ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች መጨናነቅ ተስተውሏል።

በገጠር አካባቢዎች የትምህርትና ጤና ተቋማት የማስፋፋት ስራዎች ባለፉት አመታት ቢተገበሩም በክልሉ ካለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት ጋር ጐን ለጐን የአገልግሎት አቅርቦቱ አለመስፋፋት ችግሩን ብዙም ፈቀቅ እንዳላደረገው ተወስቷል። ለአብነት ያህል የክልሉ የጤና አገልግሎት ሽፋን በ1992 ከነበረበት 43.5 በመቶ በ1994 ወደ 41 በመቶ ዝቅ ማለቱ የዚህ ችግር ነፀብራቅ መሆኑ በክልል ምክክር መድረክ ተነስቷል። የጤና ሁኔታን አስመልክቶ በከተሞች የጤና አጠባበቅ ተቋሞች

CCRDA

ቢኖሩም በመንግስት ተቋማት የአገልግሎት መጣበብ እየተስተዋለ መጥቷል። በግል ተቋማት አካባቢም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በሚመጣው የህክምናና የመድሀኒት ዋጋ መጨመር ምክንያት በዝቅተኛ ደረጃ የሚኖረው ነዋሪ ከፍሎ ለመታከም በማይችልበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ተገልጿል።

በከተሞች አካባቢም አነስተኛ የንግድ ሥራዎችን በምክር በማገዝና የካፒታል አቅማቸውን ለማሣደግ መጠነኛ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ በመደረጉ መደበኛ ካልሆነው ሴክተር የሚገኘውን ምርት በተወሰነ ደረጃ ለማሻሻል ተሞክሯል። በከተሞች የመሠረተ ልማት በመገንባት ረገድ ባለፉት አመታት ሰፊ ጥረት እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል። በሌላ በኩል በአንዳንድ የወረዳ ከተሞች የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ባለመኖራቸው ለትምህርት ማቋረጥ ዋነኛ መንስኤ እንደሆነና ችግሩም በአቅም እጥረት ሳቢያ እስካሁን እንዳልተፈታ ግንዛቤን አግኝቷል።

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፀው ሁኔታ በክልል ምክክር ያስማማ ቢሆንም በሌላ በኩል በክልሉ ባለፉት አመታት በገጠርም ሆነ በተከሞች አካባቢ ድህነት ተኮር የሆኑ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ሲተገበሩ የቆዩ በመሆኑ የድህነት መባባስ እስካሁን በክልሉ የተደረጉ የልማት ጥረቶች ያለዋጋ የሚያስቀር እንዳልሆነ በምክክር መድረኩ ተገልጿል። በተለይም የገጠሩን ህዝብ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በተግባር ላይ ያለውን የኤክስቴንሽን መርሀ ግብር የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲሻሻልና በቂ የዝናብ ስርጭት ባለባቸው የክልሉ ምዕራባዊ ዞኖችም በአብዛኞቹ የምርት ዘመናት ትርፍ ምርት ማምረት እንደተቻለና የምግብ እህል ቅርቦቱ እንደተሻሻለ ተገልጿል።

3.2.4. በክልሉ ባለፉት አመታት የተካሄዱ ድህነት ተኮር የልማት እንቅስቃሴዎች፣ ያስመዘገቡት ውጤትና የነበረባቸው ችግር

ባለፉት አመታት የገጠሩንም ሆነ የከተማ ነዋሪውን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻል በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በህብረተሰቡ አማካኝነት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

በገጠር አካባቢዎች የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሣደግ የኤክስቴንሽን መርሀ ግብር በመቀየስ በተለያዩ ፓኬጆች አርሶ አደሩ እንዲሳተፍ ተደርጓል። ከዚህም ሌላ ለአርሶ አደሩ የግብአት መግዣ፣ ለእንስሳት እርባታ ለእርሻ በሬ ግዥ የሚውል የአነስተኛ ብድር አገልግሎት ማግኘት እንዲችል በክልሉ አብዛኞቹ ወረዳዎች በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አማካኝነት በርካታ አርሶ አደሮች የብድር አገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል። በሬ የሌላቸው በሬ ገዝተዋል። ከምርት መጨመር ሳቢያ በአንዳንድ ቀበሌዎች ሳር ቤት የነበራቸው በቆርቆሮ ቤት ተክተዋል። አርሶ አደሩን በምክር ለማገዝ የልማት ጣቢያዎችን በማቋቋም ባለሙያዎች እንዲመደቡ ተደርጓል። በተወሰኑ አካባቢዎች የመስኖ ልማት ማስፋፋት ስራ ተካሂዷል። የእንስሳት ህክምና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተቋቁመዋል። የህብረት ስራ ማህበራትን የማቋቋምና የማጠናከር ስራዎች ተካሂደዋል። በዚህም ምክንያት በክልሉ የግብርና ምርትና ምርታማነት በተወሰኑ አካባቢዎች መሻሻልን እንዳሳየ ተገልጿል።

ይሁን እንጂ በግብርና ልማት ዘርፍ አንዳንድ ችግሮች እንዳሉ ተጠቁሟል። ከተጠቀሱት ችግሮች ውስጥ የእርሻ መሬት ጥበት፣ በዝናብ አጠር አካባቢዎች የምርት መቀነስ፣ የግብአት አቅርቦት በበቂ ሁኔታና በወቅቱ አለመድረስ፣ የልማት ጣቢያ ባለሙያ ቁጥር አነስተኛ መሆን፣ የገበያ ችግር፣

CCRDA

በገጠር የመንገድ አውታር አለመስፋፋት የእንስሳት ተዋፅዖ /የወተት ሀብትን/ እና የአሣ ምርትን በበቂ አለመጠቀም፣ አካባቢን መሠረት ያደረጉ የሰብል ዝርያዎች ምርምርና ስርፀት አለመጠናከር ፣ የከተማ ግብርና እንቅስቃሴን በምክር አለማገዝ የሚሉ ተገልፀዋል።

በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ረገድ በተለይም በደን ልማትና ጥበቃ የሚደረገው ጥረት አጥጋቢ ውጤትን ባያስገኝም በተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ በርካታ ስራዎች መከናወናቸው ተገልፀዋል። ይሁን እንጂ በክልሉ የደን ሀብት ልማትን በሚመለከት ሰፊ ችግሮች እንደሚስተዋልበት ተጠቁሟል። ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ አርሶ አደሩ የደን ሀብትን ለገቢ ማስገኛነት ለእንጨትና ለከሰል በማዘጋጀት ለግል ፍጆታና ለሽያጭ በማዋል ከፍተኛ የሆነ የደን ጭፍጨፋ ይካሄዳል። የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት ሲባል በህገወጥ መንገድ ደን ይጨፈጨፋል። በያመቱ በአብዛኖች ዝናብ አጠር አካባቢዎች የሚተከለው ችግኝ በዝናብ እጥረት ምክንያት ይደርቃሉ። በጋራ ላይ የሚተከሉ ችግኖች ለግጠሽ እየተባለ ችግኞቹን የማጥፋት ችግር ይስተዋላል። እስካሁን የተሰሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችም ያስገኙት ጠቀሜታ በየጊዜው ስለማይገመገም በዘርፉ ሊደረጉ የሚገባቸውን የአፈፃፀም ማስተካከያዎችን ዞር ብሎ ማየትና ርምጃ የመውሰድ እድሉን አደብዝዞት መቆየቱ ተወስቷል።

ከአደጋ መከላከል ጋር በተያያዘ ባለፉት አመታት በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የተለያዩ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ተከስተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የዝናብ እጥረት፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የምርት መበላሸት፣ የጐርፍ አደጋ፣ የተባይ ክስተት የአፈር መሸርሸር ወዘተ ሲሆኑ አደጋዎችን ለመቋቋም የተለያዩ የመከላከልና የመልሶ ማቋቋም ስራዎች መሠራታቸው ተገልጿል። የአደጋዎቹን ክስተት አስቀድሞ ለመተንበይ የሚያስችል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርአት ተዘርግቷል። በዝናብ እጥረትና በድርቅ ምክንያት በሚያጋጥም የምርት ቅነሳ የሚከሰተውን የምግብ እጥረት ለመቋቋም የተለያዩ የእርዳታ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ሆነዋል። በእርዳታ ፕሮግራሞች ከአካባቢ ዘላቂ ልማት ጋር ለማስተሳሰር የተለያዩ የስራ እድል የሚፈጥሩ /EGS/ ፕሮግራሞችን በመዘርጋት በእርዳታ እህል የተለያዩ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎች፣ የደን ልማት የምንጭ ማጐልበት የጢንዚዛ ለቀማ ወዘተ ስራዎች ተሰርተዋል። ይሁን እንጂ ከአደጋ መካላከል ተግባር ጋር በተያያዘ ተረጂዎችን በአግባቡ ያለመለየት፣ ወቅታዊ የሆነ የእርዳታ አቅርቦት አለመኖር፣ የእርዳታ ስርጭት አልፎ አልፎ ከእርሻ ስራ ወቅት ጋር የመጋጨት ችግሮች እንደተከሰቱ ተገልጿል።

በትምህርት አገልግሎት አቅርቦት ረገድ ካለፉት ጥቂት አመታት ወዲህ የትምህርት ሴክተር ልማት ፕሮግራምን መሠረት በማድረግ በርካታ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ለማዳረስ ረት እየተደረገ እንዳለ ተገልጿል። የተቋማቱን የሰው ሀይልና ለማሟላት በየአመቱ በርካታ መምህራንን በማሠልጠን ምደባ ተካሂዷል። የመፃህፍትና ሌሎች የመገልገያ ቁሳቁሶች አቅርቦት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና የጐልማሶች መሠረታዊ ትምህርትና ስልጠና ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ ይገኛል። ህብረተሰቡ ልጆቹን ወደ ት/ቤት እንዲልክ የቅስቀሳ ስራዎች ተካሂደዋል። ከዘረፉ ልማት ጋት በተያያዘ የሚነሳው ችግር በተለያዩ ምክንያቶች ህብረተሰቡ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ያለመላክ ችግር፣ በህብት ውስንነት ምክንያት የ1ኛ ደረጃና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በበቂ ያለመገንባትና በዚህም ምክንያት ከ8ኛ ክፍል በላይ ተማሪዎችን በአካባቢያቸው ማስተማር ያለመቻል፣ እና በከተሞች የሚታይ የተማሪዎች መጨናነቅን ችግር ለመፍታት የተጨማሪ ክፍሎች ማስፋፋት ስራዎችን በበቂ አለማከናወን፣ የሴቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣ የአፀደ ህፃናት ትምህርት

CGRDA

ተቋማት ግንባታዎች ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የተተወ በመሆኑ የአገልግሎቱ ውስንነትና የተሳትፎ ዝቅተኛነት፣ የጐልማሶች መሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ብልጭ ድርግም በሚል የዘመቻ ስራ የሚከናወን በመሆኑ የአገልግሎቱ መዳከም ወዘተ ችግሮች መስተዋላቸው ተጠቁሟል።

በጤና አገልግሎት ረገድ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረጸውን የጤና ሴክተር ልማት ፕሮግራም መሠረት በማድረግ በክልሉ የመሠረታዊ ጤና ሽፋንን ለማሣደግ የሚያስችሉ የተለያዩ የጤና ተቋሞችን የመገንባት መደበኛ ክትባት አገልግሎት ለእናቶችና ለህፃናት የመስጠት የወባና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የመከላከልና የማከም እና የመሰረተ ጤና አጠባበቅ ትምህርት የመስጠት ተግባር መከናወናቸዉ ተጠቅሶአል። በዚህም ምክንያት የተለያዩ የክልሉ የጤና ሽፋን ቀደም ሲል ከነበረበት ዝቅተኛ ደረጃ ከፍ ለማድረግ መቻሉ ተገልጿል። ይሁን እንጂ በተለያየ ጊዜ የሚገኑ የጤና ተቋማትን በወቅቱ በሰው ሀይልና በመገልገያ መሣሪያዎች የማደራጀት እጥረት በስፋት ጐልቶ የሚታይ ችግር እንደሆነ ተጠቁሟል። በመከላከል ዙሪያ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣ በከፍተኛ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የመድሀኒትና የህክምና ባለሙያዎች እጥረት ፍልሰትና ስራ መልቀቅ በከተሞች የጤና አገልግሎት መጨናነቅና የነፃ ታካሚ ቁጥርም በየጊዜው መጨመር ሌላው የዘረፉ ችግር እንደሆነ ተጠቅሷል። ከዚህም ሌላ ለክልሉ የጤና ልማት በአጥጋቢ ሁኔታ አለመድረስ በዋነኝነት የሚጠቀሰው ችግር ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት በጤና አገልግሎቱ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ ነው። ይህም አመታዊ የጤና በጀት እየናረ መሄድንና ከህዝቡ የእድገት ምጣኔ ጐን ለጐን የተቋማት ግንባታና አገልግሎት አቅርቦት በሚፈለገው ፍጥነት አለመሆን በክልሉን የጤና ሽፋን እድገት ላት ተፅእኖ እንዳደረ ተልጿል።

በመሠረተ ልማት ማስፋፋት ረገድ በተወሰነ ደረጃ የመንገዶች ግንባታ ቢከናወንም አሁንም ቀበሌዎችን ከቀበሌና ከወረዳ ለማገናኘት ለወደፊት ሰፊ ስራ የሚጠበቅ መሆኑ ተጠቁሟል።

በንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ረገድ አብዛኞቹ የክልሉ ከተሞች የንፁህ መጠጥ ውሀ ተጠቃሚ እንደሆኑ ተገልጿል። በገጠር አካባቢዎችም የመለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ የምንጭ ማጐልበትና የእጅ ጉድጓድ ቁፋሮዎችን በማካሄድ የገጠር መጠጥ ውሀ ሽፋንን በተወሰነ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም አሁንም በርካታ የሆኑ የገጠር ነዋሪ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አንዳልሆኑ ተወስቷል። በዚህ ዘርፍ ከተጠቀሱት ችግሮች ውስጥ በዋናነት በገጠር የተገነቡ የውሀ ተቋማት በጥንቃቄ አለመያዝና ተደጋጋሚ ብልሽት ማጋጠምና ከነጭራሹ የመዘጋት ሁኔታ በብዛት የሚከሰት ችግር እንደሆነ ተጠቅሷል። በከተሞች የውሀ ጥራት ቁጥጥር በብቃት አለመከናወንና ለውሀ ወለድ በሽታዎች የመጋለጥ ችግር እንዳለ ተጠቁሟል። በክልሉ የመጠጥ ውሀ ተቁማት የአጥሬሽንና ጥገና ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ አለመመራትና የእጅ ፓምፕና የመለዋወጫ አካላት አቅርቦት እጥረት አንዳለ ተገልጿል።

የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት በክልሉ ዋነኛ የጤና ችግር ቢሆንም በሽታውን ለመከላከል እስካሁን የተደረጉ ጥረቶች የበሽታውን ስርጭት እንዳልገታው ተወስቷል። በዚህ ዙሪያ የሚደረጉ ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶት እንዲያውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያስፈልገው ተግባር መሆኑ ተጠቁሟል። የችግሩ መንስኤዎች የህብረተሰቡ ግንዛቤ የባህሪ ለውጥን ሊያመጣ አለመቻሉ በዋናነት የተጠቀሰ ሲሆን በተለይም በከተሞች የአጉል ሱሰኝነት መበራከት፣

CCRDA

የመጠጥ ቤቶችና ምሽት ቤቶች መስፋፋት፤ በገጠሩ አካባቢ ደግሞ ከአንድ በላይ ሚስት /ቅምጥ/ የማስቀመጥ ባህል ለበሽታው መባባስ በምክንያትነት ተገልጿል::

በአጠቃላይ በክልሉ ባለፉት አመታት የተደረጉት የልማት ጥረቶች በርካታ ቢሆኑም በአፈጻጸም ሂደት የተከሰቱ ችግሮችን ማስወገድ እንደሚገባ በክልል ምክክር መድረክ ተጠቁሟል::

3.2.5. በክልሉ የመንግስት አስተዳደር መዋቅሮች እየሰጡት ያሉት አገልግሎቶች የነበሩባቸው ችግሮች

በክልሉ ባለፉት አመታት ከተከናወኑ የልማት ፕሮግራሞች ባሻገር በየደረጃው ያሉ የመንግስት አስተዳደር መዋቅሮች ለህብረተሰቡ እየሰጡት ያሉት አገልግሎቶችና ያጋጠሙ ችግሮች ላይ ውይይት ተካሂዷል::

በክልሉ የገጠርና የከተማ ወረዳዎች የሚገኙ የቀበሌ አስተዳደሮች ካከናወኗቸው በርካታ ተግባራት ውስጥ በቀበሌው የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የመፍትሄ ርምጃ መውሰድ፣ የትምህርትና የጤና ሽፋን እንዲጨምር ህብረተሰቡን በመቀስቀስና በማሣተፍ ፣ በተፈጥሮ ሀብት ስራዎች ህብረተሰቡን በማሣተፍ፣ አርሶ አደሩ በኤክስቴንሽን መርህ ግብር እንዲሳተፍ ራሳቸው አርአያ በመሆን በመቀስቀስና በማስተባበር፣ በቀበሌው የልማት እቅዶች ውስጥ በመሣተፍ፣ ግብር በማሠባሰብና የተለያዩ የልማት መዋጮዎችን በማሰባሰብ፣ የቀበሌውን ፀጥታ በማስጠበቅና የፍትህ አገልግሎት በመስጠት፣ የመንግስትን የተለያዩ መመሪያዎች በማስፈፀም፣ ለዘማች ቤተሰቦች ህብረተሰቡን በማስተባበር አስፈላጊው እገዛ እንዲደረግ ጥረት በማድረግ ወዘተ ተግባራትን ማከናወናቸው ተገልጿል::

ይሁን እንጂ ከቀበለና ወረዳ መስተዳድር ጋር በተያያዘ በርካታ ችግሮች እንደተሰተዋሉ ተገልጿል:: ከተጠቀሱት ችግሮች ውስጥ በተወሰኑ አካባቢዎች የሚገኙ የወረዳና ቀበሌ መስተዳድር አካላት የማስተዳደር አቅም ችግርና በየጊዜዉ የመለዋወጥ ችግር፣ በልማት ተግባራት ህዝቡን አስቀድሞ ያለማወያየት ችግር፣ በርዳታ ስርጭት ትክክለኛ ተረጂውን ያለመለየት ቸግርና የወል ርዳታ ስርጭት፣ በመስክ በመገኘት ለህብረተሰቡ ድጋፍ ዓለማድረግ፣ ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር የጋራ ምክክር ያለማድረግና የአስተዳደርና የልማት ጥረቶች ቅንጅት እጥረት፣ ከቀበሌው የሚመጡ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ አለመስጠት፣ ሁሉንም ስራዎች እኩል ትኩረት አለመስጠትና ለወቅታዊ ስራ ቅድሚያ ሰጥቶ መደበኛ ስራዎችን መዘንጋት፣ በከተሞች የማዘጋጃ ቤትና የወረዳ መስተዳድር ስራ መደበላለቅ፣ በከተማ የመኖሪያ ቤት የመሬት ጥያቄንና ፈጥኖ ያለማስተናገድ ፣ የአሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ በወገንና በዘመድ አዝማድ መስራት፣ ከክፍፍል የተረፈን መሬት ለግል ማዋል፣ በተለያየ ምክንያት የተነሳ ለሙስና መጋለጥና በአንዳንድ ጥቅሞች ላይ ራሳቸውን ከሁሉም በላይ ማስቀደም፣ የአካባቢውን ችግር ለመፍታት የራስን ጥረት ከማስቀደም ይልቅ የበላይ ድጋፍ ብቻ መፈለግና ትዕዛዝ መጠበቅ፣ ህብረተሰቡን የመቀስቀስ ችግር፣ የቀበሌ ስራ ማስኬጃ በጀት ችግር እንደሚስተዋል ተጠቁሟል::

CCRDA

በክልል ደረጃ የመስተዳድር አካላት መመሪያዎች በማውጣትና ወደታች በማውረድ ረገድ የተለያዩ ተግባራት ቢፈፀሙም የዞንና የወረዳ መስተዳድር አካላትን አቅማቸውን በመገንባት፣ በየጊዜው ግምገማ በማድረግና በማስተካከል ረገድና ወደታች ወርዶ የህብረተሰቡን የልብ ትርታ ለማወቅ ህዝባዊ ኮንፈረንሶችን እያዘጋጁ ስሜቱን ለማወቅ የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆኑ ተጠቁሟል።

3.2.6 በቀጣይ ድህነትን ለመቀነስ ቅድሚያ ትኩረት አግኝተው መከናወን የሚገባቸው የልማት ተግባራት

በአማራ ክልል በየደረጃው የተከናወኑ የምክክር መድረኮች በአሁኑ ወቅት የሚታየውን ድህነትና አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ዝቅተኛነት በቀጣይ የሚያሻሽሉና በክልሉ ውስጥ በከተማና በገጠር እንዲሁም በዝናብ አጠርና በቂ ዝናብ ባለባቸው የክልሉ አካባቢዎች መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ለይቷል። በቀዳሚነት ከተገለፁ የልማት ተግባሮች ውስጥ በሚከተሉት የልማት አቅጣጫዎችና ፕሮግራሞች ላይ በቀጣዩ አትኩሮ በመስራት በክልሉ ድህነትን መቀነስ እንደሚቻል በምክክር መድረኮች ተገልፆአል።

1. ከግብርና የሚገኘውን ምርት ከፍ በማድረግ የምግብ አቅርቦትን ማሻሻል

በክልሉ ምስራቃዊ ዞኖች ባለው አነስተኛ የዝናብ ስርጭት ምክንያት በርካታ ዜጐች ለምግብ እጥረት ተጠቂ ሆነው ይገኛሉ። በእነኚህ አካባቢዎች የሚገኙ ዜጐችን የምግብ እህል ፍላጐት ለማሟላት ቅድሚያ ትኩረት ከሚደረግባቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል እንደሚገባ በቀዳሚነት ተገልፆል። በዚህም መሰረት

- በክልሉ የዝናብ አጠር አካባቢዎች የሰብል ምርትና ምርታማነትን ከሚያሻሽሉ ተግባራት ውስጥ የመስኖ ልማት ስራወችን የማስፋፋትና ያለውን ውስን የውሃ ሀብት በተለያዩ የውሃ ማቆሪያ ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ በእነኚህ አካባቢዎች የሚታየውን የተለምዶ የአስተራረስ ዘዴ ለማሻሻል ዘመናዊ አነስተኛ የእርሻ መሣሪያዎች ማቅረብና ሌሎች የገጠር ቴክኖሎጂ ስራዎች ትውውቅና ስርጭት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። በአነስተኛ የመሬት ይዞታ በቂ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ የሰብል ዝርያዎችን በምርምር በማውጣት በስፋት እንዲለመዱ ማድረግና ድርቅን ለመቋቋም የሚችሉና በአጭር ጊዜ ሊደርሱ የሚችሉ የዝርያ አይነቶችን መጠቀም፣ የአርሶ አደሮችን ስልጠናዎችን በስፋት ማካሄድ፣ የግብአት አቅርቦትን ከዋጋና ከመጠን አንፃር ማሻሻል ቅድሚያ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል። በእነኚህ አነስተኛ የዝናብ ስርጭት ባለባቸው የክልሉ አካባቢዎች የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ጐን ለጐን አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ይሆናል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በክልሉ የሚታየውን የእንስሳት ህክምና መስጫ ተቋማትን በስፋት የማቋቋምና የባለሙያዎችን አቅርቦት ማሻሻል አስፈላጊ ይሆናል። የእንስሳት መኖ አቅርቦትን በማሻሻል ረገድ የመኖ ዘሮችን በስፋት የማሰራጨትና ያሉትንም ውስን የግጦሽ ቦታዎችን መከለል ያስፈልጋል። ከከብት መኖና መጠጥ ውሀ እጥረት ጋር በተያያዘ በክልሉ ምስራቃዊ ዞኖች የከብቶችና የፍየሎች የወሊድ ምጣኔ (Fucundity) እየቀነሰ እንደመጣ ተገልጿል። በምዕራቡም ሆነ በምስራቁ የክልሉ አካባቢዎች የወተት ሀብት መሸጫ ተቋማት አለመስፋፋትም ከምርቱ የሚገኝን ጠቀሜታ ማሻሻል አልተቻለም።

CCRDA

- በአንፃራዊ መልኩ የተሻለ የዝናብ ስርጭት ባለባቸው የክልሉ አካባቢዎችም የሚሠራውን የግብርና ስራ ከፍተኛ የምርት ጭማሪ በሚያስገኙ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ማገዝ አስፈላጊ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ሰብሎች እየተስተዋለ ያለው መጠነኛ የምርት ጭማሪ በገበያ እጦት መክንያት እነደይጨናገፍ የገጠር ግብይት ስርአትን ማጠናከር ትኩረት ሊደረግበት ይገባል። በምግብ ለስራ የሚቀርብ የእርዳታ እህል ከሀገር ውስጥ ገዝቶ መጠቀም ያስፈልጋል።

- ከገጠር ቴክኖሎጂ ምርምርና ስርፀት ጋር በተያያዘ እንደየአካባቢው ተስማሚ የሆኑ የዘመናዊ እርሻ መሣሪያዎችን ትውውቅና ስርጭት በገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከላት አማካኝነት ማጠናከር፣ ጉልበት ቆጣቢ የእርሻ ውስጥ የማምረቻና ማጓጓዣነት የሚያገለግሉ አነስተኛ ማኑዋል መሣሪያዎች ማስፋፋት ተገቢ ይሆናል።

- ከግብአት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የሚስተዋለው ችግር የማዳበሪያና ምርጥ ዘር ዋጋ በየጊዜው እየናረ መሄድና ያም ሆኖ የአቅርቦቱ ሁኔታ ወቅቱን ጠብቆ አለመቅረብና አቅርቦቱም ውስን መሆን /የዘር ወቅት በሀምሌ ሆኖ እያለ የማዳበሪያ ምዝገባ በሰኔ የማካሄድ ሁኔታ/ በያመቱ የሚስተዋል ችግር በመሆኑ የግብአት አቅርቦት ስርአቱን መፈተሽ ተገቢ ይሆናል። አቅርቦትን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ጐን ለጐን በሀገር ውስጥ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪዎችን ማሰብ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ መሆን ይኖርበታል።

- በከተሞች የምግብ ዋስትናን ከማሻሻል አኳያ የሀገር ውስጥ ሰብል ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማች ለማቅረብ የተጠናከረ የገበያ ኔትወርክ ማደራጀት ተገቢ ይሆናል። በአንድ አካባቢ ከፍጆታ የተረፈ የምግብ ሰብል ምርቶችን ወደ ሌላ አካባቢ በማጓጓዝ በተሻለ ዋጋ እንዲሸጡ ማድረግ አንዲቻል በማህበራት አማካኝነት የእህል ማከማቻ መጋዝኖችን መገንባት ያስፈልጋል። በክልሉ ካሉ የውሀ አካላት ሊገኝ የሚችለው የአሣ ሀብትም በሚገባ ጥቅም ላይ ያልዋለ በመሆኑ የአሣ ምርትን ማሣደግና ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች በጣና ሀይቅ ዙሪያ አካባቢ ማቋቋም እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል። የህዝቡንም የአመጋገብ ባህል መለወጥ ሌላው ትኩረት የሚደረግበት ተግባር ሊሆን እንደሚገባ ተገልፆአል።

2. በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ስራዎችን ማጠናከር

የአማራ ክልል የመሬት አቀማመጥ ወጣገባ እንደመሆኑ መጠን ከፍተኛ የአፈር መሸርሸር ችግር ይስተዋላል። ከዚህም ሌላ በክልሉ ያለው የደን ሀብት እጅግ ውስን ከመሆኑም ባሻገር የአጠቃቀም ችግር ይስተዋላል። በዚህ ዙሪያ ቅድሚያ ትኩረት አግኝተው መከናወን ካለባቸው ተግባራት ውስጥ፡-

- እስካሁን የተከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ያስመዘገቡት ውጤት በየጊዜው ለለማይገመገምና የአፈር ክለት መከላከል ስራዎችም የአንድ ወቅት ስራ አድርጐ የመመልከት ችግር እየተስተዋለ መምጣቱ ተግባሩን እንደሌላው የግብርና ኤክስቴንሽን ሥራ በመደበኛነት ማካሄድ ያስፈልጋል። በአፈር ጥበቃ ጠቃሚ ልምድ በሚገኝባቸዉ አካባቢዎች ትምህርታዊ ጉብኝቶችን እያዘጋጁ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

CCRDA

- የደን ሀብትን አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ እንዲያንሰራራ ለማድረግ ህብረተሰቡ በይዞታ መሬቱ ከሚያከናውነው የዛፍ ተከላ ባሻገር መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የደን ልማት ስራን በመደበኛ የስራ እቅዳቸው ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ይሆናል። የደን ልማትን ለማህበራትና ለግል ባለሀብቱ እየተው የመሄድ አቅጣጫ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ሲመዘን የተመዘገበው ውጤት እጅግም ነው።
- ከደን ሀብት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የማገዶ እንጨት አቅርቦት በሌላ አማራጭ የሀይል ምንጭ ደረጃ በደረጃ እንዲተካ የማድረግ ተግባራት በአጭር ጊዜ ተለይተው መተግበር ይኖርባቸዋል። የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም አካባቢንና ዘላቂ ልማትን መሠረት ማድረግም ይኖርበታል።
- የተፈጥሮ ሀብታቸው በተጐዳና የአፈር ለምነት መሸርሸር እጅግ ከፍተኛ ሆኖ የመሬቱ የማብቀል አቅም ሙሉ በሙሉ በተሟጠጠበት አካባቢዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሰፈራ ፕሮግራምን ተግባራዊ ማድረግ አማራጭ የሌለው መንገድ በመሆኑ በብዙዎች የችግሩ ተጠቂዎች ይሁንታን ያገኘ በመሆኑ ጥናቱን በፍጥነት መጀመር እና ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።
- ከውሀ ሀብት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በክልሉ የሚገኙ ታላላቅ ወንዞችን /አባይን ጨምሮ/ ለመስኖና የኤሌክትሪክ ሀይል ልማት ሊውሉ የሚችሉበት አማራጭ ማየት ሌላው ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው።

3. በአርሶ አደሩ ጉልበት ሊከናወኑ የሚችሉ የገጠር መንገዶችን ግንባታ በየቀበሌውና በየወረዳው ቀስ በቀስ ማካሄድ

- በገጠር አካባቢ ከመሠረተ ልማት ማስፋፋት ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የተነሳው ችግር የገጠር ቀበሌዎችን ከአቅራቢያ የወረዳ ከተሞች ጋር የሚያገናኙ መንገዶች ባለመኖራቸው የዘርፈ ብዙ ችግሮች መንስኤ መሆኑ ነው። በመሆኑም ከወረዳ ወደ ቀበሌዎችና ከቀበሌ ወደ ቀበሌ የሚያገናኙ የመንገድ አውታሮችን ማስፋፋት ትኩረት የሚደረግበት ተግባር ይሆናል። የመንገድ ግንባታን በአርሶ አደሩ ጉልበት ለማከናወን አነስተኛ የቅየሳ ተግባራትን የሚያከናውኑ ገበሬዎች ከአካባቢው በመመልመል በአካባቢ ሪሶርስና በቀላል የግንባታ መሣሪያዎች መንገዶችን ማስፋፋት እንዲቻል የአካባቢ አርቲዚያንስን በፕሮግራም ይዞ ማሰልጠንና በአነስተኛ የደሞዝ ክፍያ ህዝቡን እያስተባበሩ እንዲሰሩ መንግስት እገዛ ማድረግ ይኖርበታል።

4. በገጠር የንፁህ መጠጥ ውሀ ግኝትና አቅርቦትን ማሻሻል

- በገጠር ከመሠረተ ልማት ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው ችግር የመጠጥ ውሀ መገኛዎችን ከልሎ በማልማት በኩል ያለው እጥረት ነው። ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የገጠር ቀበሌዎች እየተከናወነ ያለው የእጅ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ የምንጭ ማጐልበት ስራዎችና የመለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮዎች አበረታች ቢሆንም ብዙዎቹ የውሀ ተቋማት በብልሽት ምክንያት አገልግሎት እያቋረጡ እስከነአካቴው የሚዘጉበት ሁኔታ ይስተዋላል። ይህ ችግር በብዛት የሚከሰት በመሆኑ በአማራጭነት በአንዳንድ ባይላተራል ድርጅቶች እየተከናወነ

CGRDA

ያለው የአካባቢ አርቲዝያኖች በቁፋሮ በኦፕሬሽንና ጥገና እያሰለጠኑ በየገጠር ቀበሌው አቅም የመገንባት ስራ በመንግስትም መከናወን ይኖርበታል። በፀሀይ ሀይል የሚሠሩ የውሀ ፓምፖች ተከላም በየቀበሌዎች ማካሄድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በውሀ ተቋማት አስተዳደር ዙሪያ ሴቶችን በስፋት የማሣተፍና ከአገልግሎቱ የሚገኘውንም ገቢ መልሶ ለእነኚህ ተቋማት ለማዋል የሚያስችል የስራ መመሪያዎችን እያዘጋጁ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

5. ቢያንስ የወረዳ ከተሞችን የኤሌክትሪክና የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ

በክልሉ የወረዳ ከተሞች ሰፊ የሆነ የመሠረተ ልማት ችግር ይስተዋላል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የወረዳ ከተሞችን ደረጃ በደረጃ ኤሌክትሪክና የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ፣ ደረጃቸውን በጠበቀ የመንገድ አውታሮች መደበኛ ትራንስፖርት አገልግሎት መመደብ፣ የገበያ ቦታዎችን በአግባቡ መከለል፣ የከብት መሸጫና ማሰሪያ ቦታዎች መከለል፣ ብዙ ህዝብ የሚኖርባቸውና በገበያ አካባቢዎች የመፀዳጃ ቦታዎች ግንባታ ማካሄድ በትኩረት ሊሰራበት የሚገባ ነው።

6. የዝናብ እጥረት ባለባቸዉ አካባቢዎች የአነስተኛና መካከለኛ የመስኖ ግንባታዎችን ማስፋፋት ያሉትንም በሙሉ አቅም መጠቀም

በገጠር ወረዳዎች የሚስተዋለው ሌላው ችግር የተገነቡ የመስኖ ግንባታ ስራዎችን በሙሉ አቅም አለመጠቀም ነው። እስካሁን የግንባታ ስራቸው ተጠናቆ ለአገልግሎት በደረሱ የመስኖ ግንባታዎች አካባቢ ከሚስተዋሉ ችግሮች ውስጥ የመስኖ ውሀን ለተወሰኑ ሰብሎች ብቻ የማዋል፣ የባለቤትነት ስሜት ባለመዳበሩ በተወሰነ ደረጃ የግንባታ ስራዎችን በአግባቡ ያለመጠበቅ፣ ሁኔታ ይስተዋላል። በመሆኑም በቀጣይ የመስኖ ውሀን ለተለያዩ ምርቶች መጠቀም የመስኖ ተጠቃሚዎች በማህበር የማደራጀት ተግባር ማጠናከር የአጠቃቀም ስልጠና ማካሄድና ባህላዊ የመስኖ ልማትንም ለማስፋፋት እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። በክልሉ የሚገኙ የመስኖ ውሀ ሀብቶችንም ጥቅም ላይ ለማዋል በተለይም የዝናብ እጥረት በሚታይባቸው አካባቢዎች ተጨማሪ ግንባታዎችን ማከናወን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

7. አገልግሎቱ ባልደረሰባቸው የገጠር ቀበሌዎች የተለያዩ ማህበራዊ ተቋሞችን መገንባት አገልግሎቱን ማስፋፋትና ያሉትንም ማጠናከር

- በገጠር በትምህርት አገልግሎት አቅርቦት ረገድ በክልሉ እስካሁን የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት የሌለባቸው ቀበሌዎች አሉ። በመሆኑም በአካባቢ አገልግሎቱን ከማግኘት አንፃር በየቀበሌዎች የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመገንባት ስራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በተጓዳኝም በየወረዳው የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መገንባት አስፈላጊ ይሆናል።
- በከተሞች አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የተማሪ መጨናነቅ ችግር ይስተዋላል። በዚህም መሠረት ተጨማሪ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን መገንባት፣ ነባር የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን አቅም ለማሣደግ የሴክሽን ብዛት መጨመር፣ የአፀደ ህፃናት ትምህርት ተቋማት ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ

CGRDA

የተተወ በመሆኑ አገልግሎቱ በግሉ ዘርፍ በስፋት እስኪለማ ድረስ መንግስት ተቋማቱን የማስፋፋት ተግባር ወደ ጐን መተው አይኖርበትም፣ በከተማ የማታ ትምህርትን ለማስፋፋት በሚደረገዉ ጥረት እንቅፋት የሆነው የትራንስፖርትና የመብራት ችግርን ደረጃ በደረጃ መቅረፍ፣ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሣደግ ጥረት ማድረግ፣ በህይማኖት ተቋማት የሚሠጥ የትምርት ስርአትን መደገፍ አስፈላጊ ይሆናል።

- በጤና አገልግሎት ረገድ በክልሉ የሚስተዋለው ሌላው ችግር የተቋማት እጥረትና ያሉትም በሰው ሀይልና በመሣሪያ አለመደራጀት ነው። በመሆኑም የጤና ተቋም በሌለባቸው የገጠር ቀበሌዎች የጤና ኬላዎችን መገንባት፣ በቁሳቁስና በሰው ሀይል ማሟላት፣ በጤና ኬላዎች የህክምና ሥራን ከመከላከል ተግባር ጋር ጐን ለጐን ማስኬድ፣ የህኪሞችን ቁጥር መጨመርና የሙያ ስልቹነትንም ማስወገድ፣ በከተማ ቀበሌዎች የህዝብ መፀዳጃ ሽንት ቤቶች መገንባት፣ በከተማ የአንቡላንስ እጥረቶችን ማቃለል፣ በቆላማ አካባቢዎች የወባ ቁጥጥርና ህክምናን ማጠናከር አስፈላጊ ይሆናል።

8. በከተማና በገጠር የኤች አይ ቪ/ ኤድስን ስርጭት መግታት፣ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎትና ቤተሰብ ምጣኔን ማስፋት

- በኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት ዙሪያ በአማራ ክልል ዋና ዋና ከተሞች የበሽታው ስርጭት እየሰፋ መምጣቱ ተስተውሏል። በሽታውን በመከላከል ረገድ የሚከተሉት ተግባራት መቷለትም የአባላዘር ምርመራ መታወቂያ ለሴተኛ አዳሪዎች መስጠትና የቤት ለቤት ቁጥጥር ማድረግ፣ ዝሙት መፈፀሚያ ማዕከላትን ስርጭት መገደብ፣ የፀረ ኤድስ ክበባትን ማጠናከር፣ በአቅም ማገዝ፣ በከተሞች እየተስፋፋ ያለን የአደንዛዥ እፅ /ጫት/ ልምድን በህግ መገደብ፣ በሽታው ያለበት መሆኑን እያወቀ ሌላውን በሚበክል ላይ ጥብቅ የህግ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።
- በስነ ተዋልዶ ትምህርትና አገልግሎት ረገድ በክልሉ የገጠርም ሆነ ከተማ አካባቢዎች ከፍተኛ የአገልግሎት ፈላጊ ቁጥር ቢኖርም የተፈለገው አገልግሎት በሚፈለገው ጊዜና ቦታ አይገኝም። በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች የሴቶች የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴን የመጠቀም ባህል እየዳበረ ቢመጣም አገልግሎቱን በቅርብ ካለመገኘት የተነሳ ላልተፈለገ እርግዝና እንደሚጋለጡ ተጠቁሟል። በመሆኑም በጥቂት የገጠር ቀበሌዎች የተጀመረውን የቤት ለቤት ትምህርትና የወሊድ መቆጣጠሪያ እደላ አገልግሎት ማስፋት፣ በስነተዋልዶ ጤናና ወሊድ ቁጥጥር የተሰማሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማበረታታትና ማገዝ፣ በክልሉ ራስ በራስ ልጅ የመውለድ ባህሪን ማስቀረት፣ የቀበሌ የልምድ አዋላጆችን ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና መስጠትና በቁሳቁስ ማደራጀት፣ የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትን በማንኛውም የልማት ምክር አገልግሎት ውስጥ እያካተቱ መስጠት /በግብርናና ልማት ጣቢያ ሰራተኞች ወዘተ/ ተገቢ ይሆናል።

9. በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ የመጣውን የክልሉን የህዝብ ቁጥር እድገት ለመግታት ትኩረት ማድረግ

ክልሉ በያመቱ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆን የህዝብ ቁጥር እድገት ይመዘገብበታል። በየአቅጣጫው የሚደረጉት የልማት ጥረቶች በህዝብ ቁጥር እድገት በእጅጉ እየተቦረቦር በመሆኑ

CCRDA

የወጣውን ብሔራዊ የስነ ህዝብ ፖሊሲ ለመፈፀም የመንግስት ቁርጠኝነት የመላላት ሁኔታ ባለፉት አመታት ተስተውሏል። በዚህም ምክንያት የህዝብ ቁጥር ቅነሳ እርምጃን ቀዳሚ አጀንዳ ማድረግ ያስፈልጋል። ለፈጣን እድገት ዋነኛ አማራጩ የህዝብ ቁጥር እድገትን መግታት እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን ለዚህም የቤት ለቤት የወሊድ ቁጥጥር አገልግሎትን ማስፋትና ለዚህ እንዲያግዝ የማህበረሰብ አቀፍ እደላ ሰራተኞች (CBD) በስፋት አሰልጥሮ ማሠማራት፣ የልማት ህብት አመዳደብ እና የልማት አቅጣጫም የህዝብ ቁጥር እድገትን በመከተለ አገልግሎቱን ማዳረስ ሳይሆን እድገቱን በመቀልበስ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ እንደሚሆን ተገልጿል።

10. በከተሞች ትናንሽና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋትና የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ ማበረታታት

መንግስት ከግብርና ዘርፍ ልማቱ ጐን ለጐን አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ጥረቱን በግል ባለሀብቱ ከማገዝ አኳያ ባለሀብቶች ላይ የሚጫንን ከፍተኛ የአገልግሎት ክፍያና የመሬት ኪራይና የሊዝ ገቢዎች በመንግስት እንደግብ አለመውሰድ አስፈላጊ ይሆናል። ይልቁንስ በተለያየ የስራ መስክ ለመሠማራት የሚመጣጠን የግል ባለሀብት እንደ ባለጉዳይ ሳይቆጥሩ መንግስት ራሱ ባለጉዳይ ሆኖ ባለሀብቱ በዚህ ዘርፍ የሚኖረውን ተሳትፎ በተለያዩ ማበረታቻዎችና በምክር ማገዝ እና ከግንባታም ሆነ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ በኋላ መንግስት ሊያገኝ የሚችለውን የረጅም ጊዜ የገቢ ግብር ማለም ብልጥነት ነው። በኪንስትራክሽን ዘርፍ የልምድ ተቋራጮችን ህጋዊ እውቅና ሰጥቶ በአቅም ማገዝ ሌላው ተግባር ሊሆን ይገባል። በኢንዱስትሪ ምርቶች የሀገር ውስጥ ምርትን ከውጭ ምርቶች የገበያ ተፅዕኖ መከላከል፣ በከፍተኛ ኢንቨስመንት ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ከሚገኘው የስራ መስክና የረጅም ጊዜ የገቢ ግብር ጠቀሜታ አንፃር በርካሽ የመሬት የሊዝ ክፍያ የመስጠት አካሄድ መከተል ያስፈልጋል።

11. በአገር በቀልና አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች የሚተገበሩ የልማት ጥረቶችን አቀናጅቶ መምራት

በክልሉ ባሉ በአንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተወሰኑ የሥራ ዘርፎችና በተወሰነ ቦታ ብቻ የመከማቸት ሁኔታ ይስተዋላል። መንግስት ከመያድ የሚፈሰውን ከፍተኛ መጠን ያለውን የገንዘብና የምግብ እህል ሪሶርስ ከአመታዊ እቅዱ ጋር አቀናጅቶ የመጠቀም አካሄድን አጠንክሮ መቀጠል ይኖርበታል። አመታዊ የለጋሾች የምክክር መድረኮችንም እያዘጋጁ መያድ ሊሳተፉባቸው የሚችሉበትን የልማት መስክ በመጠቆም ተግባራዊነቱንም የመከታተል ስራ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። የመንግስት የአቅም ግንባታ ተግባርም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንም ባካተተ መልኩ ማከናወን ያስፈልጋል።

12. የቀበሌ ገበሬ ማህበራትን በየደረጃው ማቋቋም ያሉትንም መደገፍ

ማህበራት ለገበሬው የሚሠጡት ጠቀሜታ በርካታ ሲሆን የገጠር የአገልግሎትና ህብረት ሥራ ማህበራት በማጠናከር አርሶ አደሩን በተቋማቱ አማካኝነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ

CGRDA

ይሆናል። በዚህም መሠረት የአነስተኛ ብድር አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲሆኑ የካፒታል አቅማቸውን በራሳቸው እስኪያሳድጉ መንግስት በመነሻ ካፒታል ማገዝ፣ በግብአት አቅርቦት ረገድ ለአባለሎቻቸው በተመጣጣኝ ዋጋ በመንደሩ አቅራቢያ ሊያሰራጩ እንዲችሉ የካፒታል አቅማቸውና የስቶሬጅ ፋሲሊቲ እንዲጠናከር ማገዝ፣ ገበያን በማረጋጋት ረገድ ማህበራት ሚናቸውን እንዲለዩ በማድረግ የምርት ስቶሬጅና የግምላሽያጭ እንዲያራምዱ በአቅም ማገዝና ጐን ለጐንም መንግስት ከፍተኛ ምርት በሚመዘገብባቸው አካባቢዎች ምርትን እስከወደብ አድርሶ ወደ ውጭ ገበያ የመላክ ሥራ Bulk carrier facility እንዲሰሩ የግል ባለሀብቱን ማበረታታት እንደሚገባ ተገልጿል።

ከዚህም ሌላ በየአካባቢው ያሉ ባህላዊ አደረጃጀቶችን በጐ ጐናቸውን በመለየት ለልማት ማስፈፀሚያ እንዲያግዙ ማድረግ ያስፈልጋል።

13. የቀበሌና ወረዳ አደረጃጀትን በአቅም ማሣደግ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማስፈን

ከአደረጃጀት ጋር በተያያዘ በወረዳ አካባቢ የሚታይን የአቅም ችግር ማስተካከል ተገቢ ይሆናል። የመስተዳድር አካላት በአካባቢው ለሚከሰት ችግር በራሳቸው አቅም መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ የበላይ አካላትን ውሳኔ የመጠበቅ ችግር ሊስተካከል ይገባል። በዚህም ምክንያት በየደረጃው ያለ አመራር ተጠያቂነትና ግልፅነት እንዲኖር ለአመራር አካላት ተግባርና ሀላፊነትን በግልፅ መለየት፣ በቀበሌ ደረጃ ለሊቀመንበር ብቻ የወር ደሞዝ ስለሚፈቀድ የሌሎች አካላትን ስራውን ወደ ጐን የመተው አዝማሚያ ማስቀረት፣ የቀበሌ መስተዳድሮችን በመንግስት በጀት ማገዝ፣ በቀበሌም ሆነ በወረዳ ደረጃ ህዝባዊ የምክክር መድረኮችን በየአመቱ በማካሄድ ችግርን መለየትና የህዝቡንም የልብ ትርታ ማዳመጥ ተገቢ ይሆናል።

በክልሉ ከመንግስት አስተዳደርና አገልግሎት አሠጣጥ ጋር በተያያዘ በመጠን አነስተኛ ቢሆንም የተለያዩ ሙስናዎች እንደሚፈፀሙ ተገልጿል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የተገለፀው በከተማም ሆነ በገጠር ቀበሌዎችና የወረዳ መስተዳድር አካላት በወገንና በዘመድ አዝማድ የመስራት፣ ተመራጮች በአንዳንድ ጉዳዮች የራሳቸውን ጥቅም የማስቀደም፣ በአጥፊዎች ላይ የሚወሰድ ርምጃ መላላት፣ የነፃ ህክምና ወረቀት በዘመድ አዝማድ መስጠት፣ የእርዳታ እህልን ስርጭት ለህዝብ ተመራጮች የስልጣን ማራዘሚያነት መጠቀም፣ የዞን ተመራጮች በልማት ስራ ሁሉንም ወረዳዎች በእኩል አይን አለማየት፣ የፍትህ አገልግሎት መራዘም ወዘተ እጥረቶች ይስተዋላሉ። በመሆኑም በህገሪቱ በአጠቃላይ ሙስናን ለመከለል ህገሪቱ የተጠናከረ ብሔራዊ የፀረ ሙስና ፖሊሲና ስትራቴጅ መቅረፅ ይኖርባታል። ሙስና በተደጋጋሚ የሚከሰትባቸውን የሥራ አካባቢዎች በየጊዜው እየለዩ የህዝብ ጥቆማን ማስተናገድ እና ክስተቱን መከላከል አስፈላጊ ይሆናል።

14. በመንግስት ተቋማት አደረጃጀትንና የሰው ሀይሉን የመፈፀም አቅም ማሻሻል

በክልሉ የሰው ሀይል ልማትና አቅርቦት የተስተካከለ እንዲሆን በየደረጃው ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚሠጡ የሰው ሃይል ስልጠናዎችን ማራመድ፣ ተቆርቋሪ ዜጋን ለማፍራት በየትምህርት ቤቶች የሥነ ምግባር ትምህርትን በካሪኩለም ማስገባት፣ በት/ቤቶች ለተማሪዎች የሚሠጡ ስልጠናዎች ከየአካባቢው ፍላጐትና ቅደም ተከተል አንፃር መቃኘት፣ ከሀገር ውጭ የሚደረግ የሀኪሞችን ፍልሰት ችግርን በጥናት መፍታት፣ በገጠር ለማንባር ቀደም የልማት ሀይሎች /መምህራን ጤና ባለሙያ ወዘተ/ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ላይ ትኩረት ማድረግና

CCRDA

እንዲሁም በመንግስት መዋቅራዊ አደረጃጀት ቶሎ ቶሎ የሚስተዋለውን ተለዋዋጭነት በማስቀረት የነባሩን አደረጃጀት ድክመቶች በውጤት ላይ ተመስርቶ ለውጡን ማከናወን ያስፈልጋል::

15. የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎች ተፈፃሚነት ላይ ትኩረት መስጠት፣ መሻሻል የሚገባቸውን እየገመገሙ ማሻሻል

አሁን በስራ ላይ ካሉት የመንግስት ፖሊሲዎች ውስጥ በዋነኝነት የተነሳና ውይይት የተደረገበት ከአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚነሳው ተቃውሞ በአፈፃፀም ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በመገንዘብ በተቃውሞዎች ላይ የሚደረግ ጫናን በጥናት መመለስ፣ ከአፈፃፀም ጋር የተያያዙትንም እንደየአግባባቸው ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ተገልጿል:: በሌላ በኩል መንግስት በፖሊሲ ያስቀመጠውን የስነ ህዝብ ፖሊሲ ለመፈፀም ቁርጠኝነቱን በተግባር ማሣየት፣ የማህበራዊ ደህንነትና የስራ ስምሪት ፖሊሲን ሁለንተናዊ አድርጐ በመቅረፅ ተግባራዊነቱን ማሻሻል ያስፈልጋል::

16 የልማት ፋይናንስ መገኛ ስልቶችን በጥናት ለይቶ ተግባራዊ ማድረግ

በክልሉ በአንዳንድ የወረዳና ንኡስ ወረዳ ከተሞች ህብረተሰቡ የራሱን ህብት በመዋጮ በማሰባሰብ የተለያዩ ተቋማት እንዲገነቡለት የመንግስትን ደጅ በተደጋጋሚ የሚረግጥ ቢሆንም በዚህ ዙሪያ ያለው እገዛ እጅግም እንደሆነ ተነስቷል:: መንግስት በክልሉ የሚያደርጋቸው የልማት ተግባራት የሚጠይቁት የህብት መጠን በየጊዜው እያደገ በመምጣቱ በተለይም በማህበራዊ አገልግሎቶችና ተቋማት ግንባታ ዙሪያ ህብረተሰቡ ወጭን የሚጋራበትን ስልት የመንደፍ ተግባር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: በመሆኑም በአብዛኛው የወረዳ ከተሞች ከህዝብ የሚነሱ የራስ አገዝ የት/ቤት ግንባታ የጤና ጣቢያ፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጀኔሬተሮች ተከላ፣ የመንገድ ግንባታ ጥያቄዎችን በተደራጀ አኳኋን ማስተናገድ እና በተለይም በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ግንባታ የሚነሳ የህዝብ ጥያቄ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ነው:: ከልማት በጀት አመዳደብ ጋር በተያያዘ ፍትህዊ የህብት ድልድልን ማስፈንና አፈፃፀሙም የተሻለ የልማት ደረጃ ላይ የሚገኘውን አካባቢ ባለበት ደረጃ ላይ በሚያስቆም መልኩ አለማከናወን ተገቢ ይሆናል::

17. የፍትህ አገልግሎትን ፈጣን ማድረግ፣ ፀጥታን ማስፈንና ሰብአዊ መብትን ማስጠበቅ

ከፍትህ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የአገልግሎቱ ፈጣን አለመሆን በተለይም በገጠሩ አርሶ አደር የስራ ጊዜ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳስከተለ ተገልጿል:: በወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤቶች የጉዳይ መቀበያ ጊዜያት በሳምንት ጥቂት ቀናት መሆንና ከህዝብ የሚቀርብ ያቄን ፈጣን ምላሽ አለመስጠት በስፋት ተነስቷል:: ከፍትህ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በክልሉ ምስራቃዊ ዞን ባለ አንድ አካባቢ አንድ የባለ 105 ብር የፍትህብሄር ክስ እልባት ሳያገኝ 25 አመት እንዳስቆጠረ በአብነት ተነስቷል:: በመሆኑም የፍትህ አሰጣጥ ስርአቱን ፈጣን ማድረግና በተለይም ለስርአቱ መሻሻል ህገራዊና ክልላዊ የፍትህ ሙያተኞች ቦርድ ማቋቋም አስፈላጊ እንደሆነ ተነስቷል:: ከፀጥታ ማስጠበቅ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች ከሚታዩ ግጭቶች በመነጨ የሚከናወኑ የግድያ፣ የሰብል ክምር ማቃጠል፣ ከብት

CCRDA

በጦር መውጋት ወዘተ ወንጀሎች በቀላሉ የሚታዩ ስላልሆኑ ተገቢውን የመከላከል ስራ መስራት ያስፈልጋል።

18. በከተሞች የሚታየውን የስራ አጥነት መበራከት ችግር ማቃለል

የስራ አጥነት በከተሞች በተለይም 12ኛ ክፍል ጨርሰው ያለስራ የሚቀመጡ ወጣቶች ቁጥር እየበረከተ እንደመጣ ተገልጿል። በገጠር አካባቢም ቢሆን ካለው አነስተኛ የመሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ አርሶ አደሩ በሙሉ አቅሙ በስራው ላይ ስለማይጠመድ የገጠር ስራ አጥነት (underemployment) ሰፊ ችግር ሆኖአል። በመሆኑም በገጠር አንዳንድ ከግብርና ውጭ ያሉ የገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲስፋፉ ጥረት ማድረግ፣ በአካባቢው በሰው ሀይል የሚከናወኑ የመንገድና የመስኖ ግድብ ፕሮጀክቶች ላይ ስራ የፈታውን አርሶ አደር በክፍያ ማሰማራት፣ የህዝቡን የስራ መናቅ ባህል በማስወገድ በከተማም ሆነ በገጠር የአነስተኛ እደጥበባት ማበራትን በማደራጀት የብድርና የምክር አገዛዎች ማድረግ ያስፈልጋል። በተመሣሣይ በከተሞች ትምህርታቸውን የጨረሱ ወጣቶችን በማደራጀት በተለያዩ ፕሮጀክቶች እንዲሰማሩ የመነሻ ካፒታል እያፈላለጉ ወደ ምርታማ ሥራ ማሸጋገር፣ ለዚህም የአስቸኳይ ጊዜ ተቋማዊ አደረጃጀት መዘርጋት አስፈላጊ ይሆናል።

19. የገጠር ብድር አገልግሎት ግኝትን ማስፋት

በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የገጠር ነዋሪዎችና በከተማ ወረዳዎች የሚኖሩ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ያለባቸውን የካፒታል አቅም እጥረት ለማስወገድ የተጠናከረ ሥራ መስራት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ወረዳ የራሱ የሆነ አመታዊ የአነስተኛ ብድር ፕላን ሊኖረው ይገባል። የሚቀረፀው ፕላን የብድሩን ምንነትና ተጠቃሚውን የለየ መሆን ይኖርበታል። አሁን በክልሉ ያለው የአነስተኛ ብድር አገልግሎት መስጫ ተቋም የብድር አሰጣጥ ስርዓቱ ማን በብድሩ ይሠራበታል ሳይሆን ማን መክፈል ይችላል በሚል መስፈርት የመመራት አካሄድ በተወሰነ ደረጃ የሚስተዋል በመሆኑ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱን መፈተሸና ማስተካከል ያስፈልጋል። በተጨማሪም ተበዳሪዎች የቅድመ ብድር የአጠቃቀም ስልጠና መስጠትም ያስፈልጋል። የማይክሮ ፋይናንስ ፖሊሲውን በተለይም የእንሰሳት ብድር መጠንና አጭር የመመለሻ ጊዜን ማሻሻል ያስፈልጋል። የገጠር ማህበራት ለአባሎቻቸው አነስተኛ የብድር አገልግሎት እንዲሰጡ በገጠር የቁጠባ ባህል እንዲስፋፋ ጥረት ማድረግና የመንግሥት ተቋማዊ አገልግሎትን ለማገዝ ማህበራትን በመነሻ ካፒታል ደረጃ በደረጃ እያገዙ መሄድና የአካባቢ ተቋማትን የመመስረት አካሄድ ተገቢ ይሆናል።

20. ሴቶችና ወጣቶችን የልማቱ ተጠቃሚ ማድረግ

ሴቶች ከክልሉ ህዝብ ግማሽ ያህሉን የሚወክሉ እንደመሆኑ መጠን እነኚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚያደርግ የልማት እቅዶች መተግበር ሌላዉ ቀዳሚ ተግባር መሆን ይኖርበታል። በገጠር የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት የሚያረጋግጥ የመርት ክፍፍል የተደረገ ቢሆንም በህብቱ ላይ ያላቸው ቁጥጥር አንም ጥያቄ ውስጥ ነው። በሌላ በኩል ሴቶችን ከቤት ውጭ ባሉ የሥራ መስኮች እንዲሰማሩ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ሴቶች የትምህርትና የሥራ እድል ተጠቃሚነታቸውን

CGRDA

ከወንዶች በተለየ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። ወጣቶችን በተለያዩ ሙያ በማሠልጠን እያደራጁ በተለያዩ የልማት መስኮች አጋዥ ሚና እንዲኖራቸው ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

21. ከግብርና ውጭ ያሉ የእድገት አማራጮችን ጎን ለጎን ማየት

ከተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ አማራጭ የሀብት መገኛዎችን /ማዕድን ፍለጋ፣ የኤሌክትሪክ ሀይል ኤክስፓርት፣ የቱሪዝም ሀብት ልማት፣ ኢንዱስትሪ ልማት ወዘተ /ከግብርና ልማቱ ጎን ለጎን ማካሄድ መዘንጋት የሌለበት ተግባር መሆን ይኖርበታል።

22. የልማት ጥረቶች አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ስርአትን በውጤት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ

በክልሉ በተካሄዱ የተለያዩ የምክክር መድረኮች የተነሳው ችግር የሚከናወኑ የልማት ጥረቶች በግብአቶቻቸው አፈፃፀም ስኬታማነትና በቁጥርና በክንውን መቶኛ ብቻ ላይ የተመሠረተ እንጂ ጥረቱ በህብረተሰቡ ላይ ያመጣውን የኑሮ ሁኔታ መሻሻል በሚለካ መልኩ ስማይገመገሙ ወደፊት የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ መመዘኛዎች ይህን ችግር በሚፈታ መልኩ እንዲሆን ተጠቁሟል። በህገራቱ በየሥራ ዘመኑ የሚከናወኑ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገቶች በየጊዜው መገምገም፣ የዜጎች የኑሮ ሁኔታን በተከታታይ የናሙና ጥናቶች እየተከታተሉ በህገር አቀፍ በክልል በዞንና በወረዳ ደረጃ አመልካቾችን እያወጡ ለእቅድ አውጭዎች ማስታወቅና በተከታታይም የመንግሥት ቀጣይ ጥረት የተመዘገበውን የልማት ክፍተት በሚሸፍን መልኩ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ እንደሚሆን ተገልጿል።

3.2.7 ብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂን ስኬታማ ለማድረግ መመቻቸት ያለባቸው አካባቢያዊ ሁኔታዎች

በሚቀጥሉት አመታት ተግባራዊ ለማድረግ የሚቀረፀው ብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂን ውጤታማ ለማድረግ የሚከተሉት የፖሊሲ የአደረጃጀትና፣ የአፈፃፀም ክትትልና የቁጥጥር ተግባራት ተጠናክረው መቀጠል እንደሚኖርባቸው ተጠቁሟል።

1. አሁን የሚታየውን የመንግሥት ፖለቲካዊና የመፈፀም ቁርጠኝነት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ። ለዚህም
   - የሚቀርፀውን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ በተግባር ለመተርጎም የመንግሥት ቁርጠኝነት እንዲቀጥል ማድረግ፣
   - ድህነትን ለመቀነስ በመንግሥት በአሁኑ ወቅት እየተከናወኑ ያሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባሮች፣ የተቀረፁ የልማት ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞችን አቀናጅቶ ጎን ለጎን ለመፈፀም የፈፃሚውን ሀይል ግንዛቤ ማጸበር ያስፈልጋል።
2. ተከታታይ የፖሊሲ ድጋፍን በየልማት መስኩ ማስፈን

CCRDA

- አሁን ያሉ የገጠር ልማት ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የስነ ህዝብ የማህበራዊ ደህንነት፣ የኢንቨስትመንት ወዘተ ፖሊሲዎችን ተግባራዊነትና ውጤታማነት በየጊዜው እየገመገሙ ችግሮቻቸውን ማስተካከል።
- በአፈፃፀም ሂደት ትኩረትን የሚሰቡ ጉዳዮችን እየለዩ በየወቅቱ የፖሊሲ ክለሳዎችን ማድረግ /የትምህርት ፖሊሲ፣ የሊዝ ዋጋንና የኪራይ ገቢ አወሰን/
- አዳዲስ የፖሊሲ ሀሳቦችን እንደየአስፈላጊነቱ ማስተናገድ /የግብርና ልማት ፖሊሲ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ/

3. የተቋማዊና መዋቅራዊ አደረጃጀቶችን በየደረጃው ማየት
   - ውጤታማ የማስፈፀሚያ መዋቅሮችን እንደአስፈላጊነቱ መዘርጋት፣
   - ያለበቂ ጊዜ ግምገማ የሚከናወኑ የአደረጃጀት ተለዋዋጭነቶችን ማስወገድ፣
   - ወረዳና ቀበሌዎችን በበቂ በጀት መደገፍና፣ በራሳቸው ልማት የመወሰን አቅማቸውንና መብታቸውን ማስከበር
4. ህብረተሰቡ ያመነባቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ፕሮግራሞችን ማራመድ
   - የህብረተሰቡን የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣
   - ህዝብን ከእቅድ እስከ አፈፃፀም ድረስ የሚሳተፍበትን የአሠራር ስልት ነድፎ ተግባራዊ የማድረግ አሰራርን በተጀመረው መልኩ አጠናክሮ መቀጠል እና የአካባቢውን የልማት ቅደም ተከተል በአካባቢው ነዋሪ እንዲወሰን ማድረግ
5. የልማት ፋይናንስ ግኝቶችንና አጠቃቀምን እያሻሻሉ መሄድ
   - የመንግሥት ገቢን የሚጨምሩ አማራጮችን /ህብረተሰቡን በማይጎዳ መልኩ/ ማየት
   - ከቀበሌና ወረዳ ነዋሪዎች የሚገኝን የገንዘብና የጉልበት ሀብት እያስተባበሩ የመንግሥትን ውስን ሀብት በእርሾ መልክ እየተጠቀሙ መሄድ

4. በምክክር ሂደት የተገኙ በጎ ጎኖችና የተስተዋሉ የአፈፃፀም ችግሮች

የልማት እቅድን ከታችኛው የህብረተሰብ ክፍለ በሚገኙ ሀሳቦች ተመስርቶ የተጠቃለለ የልማት እቅድ መቅረፅ በሀገራችን አንዳንድ ተሞክሮዎች ቢኖሩም በዚህ አመት በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት የተካሄደው ክልል አቀፍ የምክክር ሂደት ከመቼውም በተለየና በተሳካ ሁኔታ የተፈፀመ ቢሆንም በዚህ ሂደት በየአካባቢው በተደረጉ የምክክር ሂደቶች የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ከማንኛውም የመንግሥት ቢሮክራሲያዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ የነፃ ሀገራዊ የምክክር መድረኮች በመመራታቸው ህብረተሰቡ ያሉበትን ችግሮች ለማቅረብ ያሳየው ስሜትና ግልፀኝነት በሀገሪቱ ያለውን የዲሞክራሲ ስርአት ይበልጥ አረጋግጦታል።
- ከመንግሥት እይታ ውጭ ያሉ አንዳንድ የአፈፃፀም ግድፈቶችና የፖሊሲ ክፍተቶችን ዞር ብሎ ለማየት ለመንግሥት ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሯል።

CCRDA

- ተመሳሳይ ህዝባዊ የምክክር መድረኮችን ወደፊት ተከታታይነት ባለው መልኩ ማዘጋጀት ለመንግሥት የልማት እቅድ ዝግጅት ሂደት ጠቃሚነታቸው ለተገልጋዩ ህዝብም ሆነ ለአስፈፃሚው በጎ ግንዛቤን አስጨብጧል።
- የመያድ በምክክር መድረክ ተካፋይ መሆን ከመንግሥት ጋር ጎን ለጎን ለመሥራትና ለቀጣይ ቅንጅታዊ አሰራርና ውጤታማ የልማትና የርዳታ ሪሶርስ አስተዳደር ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮአል።

በሌላ በኩል በዚህ የምክክር መድረኮች አመራር አንዳንድ የአፈፃፀምና የፅንሰ ሀሳብ ችግሮች ተስተውለዋል። ከእነዚህም ውስጥ

- መንግሥት በየደረጃዉ ያደረገው የምክክር መድረክ ከውጭ ሀገር አለም አቀፍ አበዳሪ ተቋማት በመጣ ተፅዕኖ በመሆኑ ጥቂት የህብረተሰብ ክፍለች ሂደቱን በጥርጣሬ ተመልክተውታል።
- ህብረተሰቡን ብአቀደ የማሳተፍ ልምድ ቀድሞውንም ቢሆን በሀገሪቱ በተበታተኑ መልኩ ሲፈፀም የነበረ ቢሆንም ከዚህ ምክክር የተገኙትን የምክክር ግኝቶች ሀሳብ ይዞ በተግባር ለመተርጎም መንግሥት ከወትሮው በተለየ መልኩ ምን ያህል በአቅም ዝግጁ ነው የሚለው በአንዳንዶቹ የምክክር ተሳታፊዎች ጥያቄ ውስጥ ወድቋል።

ይሁን እንጂ በአጠቃላይ በክልሉ የተካሄዱ የምክክር መድረኮችና የተገኙ ሀቦች ሲመዘኑ በርግጥም ለውጥን ለማምጣትና ለጋራ ልማት ያለን ህዝባዊ ተነሳሽነት ይበልጥ የጎላ እንደነበር ተስተውሏል።

5. ማጠቃለያ

በሀገር አቀፍ ደረጃ በዚህ አመት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ከብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ጋር በተያያዘ በአማራ ክልል የተደረጉ የምክክር መድረኮች ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀዋል። በአማራ ክልል ለምክክር በተመረጡ 23 ወረዳዎች ከተደረጉ ምክክሮች የተገኙ የምክክር ግኝቶች በዋናነት በምግብ እህል አቅርቦትና በሌሎች መሠረታዊ የኑሮ ሁኔታዎች መሟላት ላይ ያተኮረ በመሆኑ የየወረዳዎች የተናጠል ግኝት አለም አቀፍ ሁኔታዎችንና የብሔራዊውን ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በተወሰነ ደረጃ በጥልቀት ያልዳሰሰ በመሆኑ የተነሱ የልማት ጥያቄዎች ከሀገሪቱ የፋይናንስ ግኝት፣ የቴክኖሎጂ እድገት ደረጃና የመፈፀም አቅም ጋር በብሔራዊ ደረጃ ማየትና መፈተሽ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ ተወስዷል። በመጨረሻም ይህ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶ ህዝቡ በየደረጃው እንዲሳተፍ መደረጉ ህዝቡን ለጋራ ልማት ያነሳሳና ተግባራዊነቱንም በናፍቆት እየተጠባበቀ እንደሆነ በውይይቱ ወቅት አፅንኦት ተሰጥቶታል።

CCRDA

በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት

የቤኒሻንጉል - ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የክልል ምክክር ማጠቃለይ ሪፖርት

CCRDA

የክልሉ ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

የካቲት 1994

አሶሳ

ማውጫ

ተ.ቁ	ርዕሥ	ገፅ
1	**መግቢያ**	**1-2**
1.1	*የክልሉ አጠቃላይ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ገፅታ*	*1*
1.2	*የተሳታፊዎች ሁኔታ / Back Ground*	*2*
1.3	*የምክክሩ አጀንዳ*	*2*
2	**የክልል ምክክር ሪፖርት**	**2-13**
2.1	*የድህነት መገለጫዎችና መንስኤዎች*	*2*
2.2	*የክልሉ የኑሮ ደህነት ሁኔታና ወቅታዊ ሁኔታ*	*3*
2.3	*ለደህነት ይበልጥ የተጋለጡ አካባቢዎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች*	*5*
2.4	*ባለፉት ዓመታት ድህነትን ለማስወገድ የተደረጉ ጥረቶች*	*5*
2.5	*መንግሥት የልማት ፕሮግራም በሕብረተሰቡ ኣይታ*	*6*
2.6	*መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ባለፉት 5 ዓመታየነበራቸው ተሳትፎ /የሕብረተሰብ ዕይታ/*	*7*
2.7	*በክልሉ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማካሄድና ድህነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀነስ መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎች*	*7*
2.8	*የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ አፈፃፀምን ስኬታማ ለማድረግ መዘርጋት ያለበት ስርዓት ወይም ስልት*	*13*

CGRDA

1. መግቢያ

1.1 የክልሉ አጠቃላይ ኢኮኖ ሚያዊና ማህበራዊ ገጽታ

የቤ/ጉ/ክልል በስተምዕራብ ከሱዳን፣ በሰሜን ከትግራይ፣ በሰሜን ምስራቅ ከአማራ፣ በምስራቅ አና በደቡብ ምስራቅ ከኦሮሚ፣ በደቡብ ምዕራብ ከጋምላ ሕዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ይዋሰናለ ። ክልሉ በሦስት ዞኖ ች፣ በሁለት ልዩ ወረዳዎች አና በ18 ወረዳዎች የተከፈለ ሲሆን 633 ቀበሌዎች ያሉት ። የቆዳ ስፋቱ ከ50,000 ካሬ ኪ.ሜ በላይ አንደሚሆን የሚገመት ሲሆን የክልሉ ማዕከለ አሶሳ ከአ.አ. በ687 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። ከክልሉ ግማት 75 በመቶ የሚሆነው ቆላማ አየር ንብረት ያለው ሲሆን ከ550 - 2731 ሜ. ከባህር ወለል በላይ ከፍታ ያላቸው ቦታዎችን ያካተተ ነው ። 55 በመቶ የሚሆን በተፈጥሮ ደን የተሸፈነ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ ። ክልሉ ከግንቦት አስከ ጥቅምት የሚዘልቅ የዝናብ ወቅት ሲኖ ረው ከፍተኛ የሙቀት መጠኑ ከ20 - 25 ዲግሪ ሴልሺየስ የሚደርስ ሲሆን በበጋ ወቅት ከፍ ብሎ ከ28 - 34 ዲግሪ ሴልሺየስ ይደርሳል ።

የክልሉ ህዝብ ቁጥር በ1987 ዓ/ም በተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ስሌት መሰረት በ1994 ዓ/ም 558, 541 አንደሚደርስ ይገመታል ። ከዚህ ውስጥ 49.4 በመቶው ሴቶች ናቸው ከጠቅላላው የክልሉ ነዋሪ 91.5 በመቶው የገጠር ነዋሪ ነው ። የክልሉ ህዝብ ቁጥር ከ1987 - 1992 በአማካይ ግማት 2.66 በመቶ ዕድገት አሳይቷል ። በክልሉ የሚኖ ሩ ብሄረሰቦች ስርጭትን በተመለከተ በርታ 26.7 በመቶ፣ ጉሙዝ 23.4 በመቶ፣ አማራ 22.2 በመቶ ፣ኦሮሞ 12.8 በመቶ ፣ሺናሻ 6.9 በመቶ ፣ ማኦ ኮሞ 0.8 በመቶ አና ሌሎች ብሄረሰቦች ናቸው ።

የክልሉ ዋነኛ ገፅታ አጅግ የከፋ ድህነት ሲሆን የዚህም ሀቅ ዋነኛ መገለጫዎች በአመዛኙ ህዝቡ በኋላቀር የኑሮ ሁኔታ መስማራቱና ከዚህም ሚገኝ ምርትና ገቢ አጅግ ዝቅተኛ መሆን፣ በዚህም መሠረት በክልሉ ከድህነት ወለል በታች የሚኖ ረው ህዝብ ከጠቅላላው ህዝብ 47.6 በመቶ ነው ።የአፍሪካ ልማት ባንክ በ1993 ባጠናው መሠረት/ በክልሉ ከፍተኛ የመሃይምነት ደረ ያለ ሲሆን ይኸውመ 82.1 በመቶ /1987 ዓ/ም፣ ንፅህ ያለበኖ ውሃ አቅርቦት 27.4 በመቶ ፣ስኢቴሽን 19 በመቶ /1987 ዓ/ም ፣ አማካይ የአድሜ ጣራ 48 ፣ ከፍተኛ የህፃናት ሞት ይኸውም በህይወት ከሚወለዱ 1000 ህፃናት መካከል አንድ ዓመት ሳይሞላቸው የሚሞቱት 130 ይደርሳሉ ።

አንደተቀሩት የሀገራችን ክፍሎች የቤኒሻንጉል - ጉሙዝ ክልል ሁለት የማይጣጣሙ አውነታዎችነ ያቀፈ ነው ። ይኸውም በአንድ በኩለ ሰፊና ምቹ የተፈጥሮ ሀብት ያለው ሲሆን በሌላ በኩል ግን የክልሉ ህዝብ በተለይ ነባሩ ህብረተሰብ በአመዛኙ አጅግ ኋላቀር የኢኮኖ ሚ አንቅስቃሴዎች ላይ ሚውን የመረሠተ መሆኑ ነው ። በክልሉ ግብርና ዋነኛ የኢኮኖ ሚ ዘርፍ ነው ። 93.2 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ነዋሪ በግብርና ዘርፍ የተሰማራ መሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ ከዚህ ውስጥ አብዛኛው በአነስተኛና ኋላቀር የግብርና ዘዴ የተሰማራ ነው ። የንግድ አንቅስቅሴን በተመለከተ ክልሉ ሰፊና የተጠናከረ የኢኮኖ ሚ አንቅስቃሴ የሌለበት አንዲሁም ለንግድ ዘርፍ የሚያስፈልጉ የገበያና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች ያልተስፋፋበት ሲሆን በዚህ የተነሳም የንግድ አንቅስቴ ደካማ አና በአመዛኙ ልማዳዊ ነው ። በኢንዱስትሪ ዘርፍም ያለው ገፅታ የክልሉ ኋላ ቀርነት ነፀብራቅ ሲሆን የሚገኙት ጅምር አነስተኛ የኢንዱስትሪ አንቅስቃሴዎችም የዳቦ መጋገሪያ፣የአህል ወፍጮ የዘይት መጭመቂያና የቤትና የቢሮ አቃዎች ማምረቻዎ አና የመሳሰሉት ናቸው ።

የክልሉነ የመንገድ ሁኔታ በተመለከተ በክልሉ የሚገኙ መንገዶች ደረጃቸውን ያልጠበቁና አብዛኞቹ መንገዶች በክረምት ወቅት አገልግሎት የማይሰጡ ናቸው ። አጠቃላይ የክልሉን መንገዶች ኔት ወርከ ስንመለከት ዞኖ ችን ወረዳዎችን ከክልሉ አንዲሁም ዞኖ ችን ከወረዳዎቹ ጋር የሚያገናኝ መንገድ የለም ።

የክልሉ ማህበራዊ ሁኔታም አንደኢኮኖ ሚው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በትምህርት መስክ ከ1986 ዓ/ም በፊት በክልሉ በጣም ዝቅተና ደረጃ ላይ የነበረ ሲሆን ከ1986 ዓ/ም ወዲህ ግን ከፍተኛ ዕድገት አያሳየ መጥቷል ።ጤናን በተመለከተ ክልሉ ቀደም ሲል በዘርፉ የተካሄደ ጉልህ የሚባል እንቅስቃሴ የማስፋፋት አንቅስቃሴዎች ባለመኖ ራቸው ክልሉ የተለያዩ በሽታዎች ተጋልጦ የቆየ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የክልሉ ጤና ሽፋን 50.4 በመቶ ላይ ደርሷል ።

CCRDA

የተሳታፊዎች ሁኔታ

ከየካቲት 4 - 6/1994 በተካሄደው የክልል ምክክር የተሳታፊዎች ብዛት 180 የነበረ ሲሆን ምክክሩ በክልሉ ከሚገኙ የክልልና የዞን ሴክተር መ/ቤት ተወካይዮች ባለሙያዎች፣ የክልል ም/ቤት ስራ አስፈፃሚ አካላት ከዞን ም/ቤት ተወካዮች የወረዳ ምክክር መሪዎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ተወካዮች የልማት ማህበራት የሙያ ማህበራት የክልሉ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የሃይማኖት ተቋማት የግል ባለሀብቶች ታዋቂ ግለሰቦች ትምህርት ተቋማት ተወካዮች ከሚዲያ ሰዎች እና ሌሎቹንም ያካተተ ነበር።

የምክክሩ አጀንዳ

የምክክሩ አጀንዳወች
1/ለማዘጋጀ የሚረዱ ፅሁፎች
የኢትዮጵያ ጊዚያዊ የድህነት ማቃለያ ስትራቴጅ ዋናዋና ይዘት
የድህነት ሁኔታ እና የልማት አጀንዳ በኢትዮጵያ
በክልሉ የድህነት ቅነሳስትራቴጅ ሰነድ ዝግጅት ሂደት
በክልሉ ልማትን ለማፋጠንና ድህነትን ለመቀነስ የተከናወኑ ዋናዋና የልማት ስራወች
2/ በወረዳ ደረጃ የተካሄደው ምክክር ዋናዋና ይዘት
3/በክልሉ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማካሄድና ድህነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀነስ በአጭርና በመካከለኛ ዘገዜመዉሰድ ያለባቸው አርምጃወች
4/የድህነት ቅነሳ ስትራቴጅ አፈፃፀምን ስኬታማ ለማድረግ መዘርጋት ያለበት ስርአት ወይም ስልት
የሚሉ ነበሩ
በአነዚህ አጀንዳወች ላይ በሶስት ተከከታይ ቀናት ሰፊ ውይይት በማድረግ በተለይ የወረዳ ምክክር ግንቶችን በማጥራትና ነማጠናከር ከዚሁም በሌሎች ተጨማሪ አጀንዳወች ላይ ገንቢን አመላካች ሀሳቦች ን በማካተት ውይይቱ ተጠናቃል

2. የክልል ምክክር ሪፖርት

የክልል ምክክር ተሳታፊዎች የክልሉን የድህነት መገለጫዎችና መንስኤዎች እንደሚከተለው አስቀምጠዋል ።

2.1 የድህነት መገለጫዎችና መንስኤዎች

2.1.1 የድህነት መገለጫዎች

መሠረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላት / ምግብ ልብስና መጠለያ/፣ በቤተሰብ ደረጃ በምግብ እህል ራስን አለመቻል ፣ አንድ ቤተሰብ ሁሉንም ልጆች ማስተማር አለመቻል ፣ የማይምነት ደረጃ ከፍተኛ መሆን፣ከዘመናዊ የህክምናአገልግሎት ይልቅ ባህላዊ ህክምናን በስፋት መጠቀም፣ የህብረተሰቡ የነፍስ ወከፍ ገቢዝቅተኛ መሆን፣ ጉልበትን ሸጦ ማደር ወይምለሌላ ሰው ተቀጣሪ ሆኖ መስራት፣አማራጭ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ስራዎችን ለመፍጠርአለመቻል፣የገንዘብ ስርጭትና ዝውውር /Money Circulation / ደካማ መሆን።

2.1.2 የድህነት መንስኤዎች

ከፍተኛ የአስተራረስ ዘዴና ህብረተሰቡ በተበታተነ ሁኔታ መስፈሩ፣ ገበሬው የሚያመርተው ምርት ገበያ ተኮር አለመሆን፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ማስፋፋት፣ ፀረ ሰብል ተባዮችና አረሞች መስፋፋት፣ በከፍተኛ ደረጃ የሰው እና የእንስሳት በሽታ መስፋፋት /ወባ ፣ገንዲ፣ ኤድስ/፣የምርት ዋጋ መቀነስ የግብዓቶች ዋጋ መጨመር የግብዓቶች አቅርቦት ችግር፣ የቤተሰብ መብዛት የወሊድ ቁጥጥር አለመኖር፣

CCRDA

የብድር አገልግሎት አለመስፋፋት፣ለምርት ሽያጭ ገበያ አለመኖርና የተመረተን ምርት ገበያ አውጥቶ የመሸጥ ልምድ አለመኖር፣ በቂ ያልሆነ የመሰረተ ልማት አውታሮች አለመስፋፋት፣አነስተኛ የጎጆ ኢንዱስትሪዎችና ንግድ አለመስፋፋት ፣ የስራ ባህል ደካማ መሆን፣ከአቅም በላይ ለድግስ ወጪ ማውጣት።

2.2 <u>የክልሉ የኑሮ ድህነት ሁኔታና ወቅታዊ ሁኔታ ያለፉት 5 ዓመታት ግምገማ የመሰረታዊ ፍላጎት ፍጆታ</u>

⇒ <u>የምግብ ፍጆታ</u>

ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ የኤክስቴንሽን መርሀ ግብር መካሄድ በተወሰኑ አካባቢዎች ምርትን የጨመረ ቢሆንም ከታች የተዘረዘሩት ችግሮች በግብርናው አንቅስቃሴ ላይ ባስከተሉት ተፅዕኖ በምግብ ፍጆታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበራቸው ። እነሱም:-

ጥሩ የአስተራረስ ዘዴ፣ የፀረ ሰብል ተባዮችና አረሞች መስፋፋት፣አነስተኛ የመስኖ ልማት ስራዎች አለመስፋፋት፣ያለውን መሬት በአገባቡ አለመጠቀም፣ አማራጭ የገቢ ምንጮች አለመኖር፣ የምርት ሽያጭ ገበያ ችግር፣ የምርት ዋጋ መቀነስና የግብአት ዋጋ መጨመር፣ የስራ ባህል ዝቅተኛ መሆን፣ከግብርና ስራ ውጭ በተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ አለመሰማራት።

⇒ <u>የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት</u>

በክልሉ የነበረውን ከፍተኛ የመጠጥ ውሀ ችግር ለመቀነስ ባለፉት አምስት ዓመታት ብዙ ጥረት የተደረገ ቢሆንም ከታች የተዘረዘሩትን ችግሮች በንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል። .

በቂ የውሃ መገኛ ጥናት አለመከናወን፣የተገነቡት ተቋማት በአጭር ጊዜ ለብልሽት መዳረግና ጥገና አለማግኘት፣የተገነቡት የውሃ ተቋማት ንፅህናቸው የተጠበቀ አለመሆን፣ህብረተሰቡ የውሃ ተቋማትን ዘለቄታ ባለው መንገድ አለመጠቀም፣ የምንጭ ማጎልበት ስራ አነስተኛ መሆን፣ለእንስሳት ሀብቱ የውሀ ገንዳዎች በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት ።

⇒ <u>የቤተሰብ ጤና ሁኔታ / የህፃናት እና እናቶች / ፣ጤናና ኤድስ</u>

ባለፉት 5 ዓመታት በአርዕስቱ የተገለጹትን ሽፋን ለማሳደግ ከጤና ተቋቀማት ግንባታ በተጨማሪ የጤና ትምህርት አገልግሎት በየደረጃው አየተሰጠ የመጣበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም ከታች የተዘረዘሩት ችግሮች ባለፉት ዓመታት የሴክተሩ ችግሮች ነበሩ። እነሱም:-

የጤና አጠባበቅ ትምህርት አለመስፋፋት፣ በተገነቡ የጤና ተቋማት ህብረተሰቡ የመጠቀም ልምዱ አነስተኛ መሆን፣የህክምና ተቋማት በቂና አስፈላጊ መድኃኒት አንዲሁም ባለሙያና በህክምና መሳሪያዎች አለመሟላት ፣ በጤናው ዘርፍ የባለሙያዎች የአቅም ብቃት ውስን ተነሳሽነትና የስነ ምግባር ችግር መኖር፣ የኤድስ እና አባለዘር በሽታዎች በተመለከተ በህብረተሰቡ ዘንድ የግንዛቤችግር መኖ ርና በሽታዎቹም በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት፣

CCRDA

⇒ የትምህርት አገልግሎት

ባለፉት 5 ዓመታት የትምህርት አግልገሎት አና ሽፋን ለማሳደግ ብዙ ትምህርት ቤቶች በየአከባቢው የተስፋፉ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሴክተሩ የሚከተሉት ችግሮች ነበሩ ።

የትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን በተለይም በነባሩ ህብረተሰብና በገጠር ፣ ህብረተሰቡ ለትምህርት ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን አንዲሁም ለትምህርት ተቋማት የባለቤትነት ስሜት ዝቅተኛ መሆን፣ወላጆች ያላቸው የኢኮኖ ሚ አቅም አነስተኛነት ሳቢያ ልጆቻቸውን ማስተማር አለመቻል ፣ በራስ ቋንቋ ትምህርት ለመስጠት ያለው ትኩረትና አንቅስቃሴ አነስተኛ መሆን፣የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ከወንዶች አንፃር ዝቅተኛ መሆን የተማሪዎች ከትምህርት ማቋረጥና መድገም ከፍተኛ መሆን፣

⇒ የአንስሳት ጤና

ባለፉት 5 ዓመት የአንስሳቱን ጤና ሽፋን ለማሳደግ የተወሰኑ የአንስሳት ጤና ተቋማት ግንባታ የባለሙያ ስልጠና የተደረገ ቢሆንም ከታች የተጠቀሱት ችግሮች በከፍተኛ ሁኔታ መኖር በአንስሳት አርባታ ላይ ተፅዕኖ አስከትሏል።.

1. የአንስሳት በሽታ ስርጭት በከፍተኛ ፍጥነት መስፋፋት / በተለይ የገንዲ በሽታ / ፣
2. የአንስሳት ጤና ተቋማት በበቂ መድኃኒት መሳሪያዎችና ባለሙያዎች አለመሟላት ፣
3. በተገኑት የአንስሳት ጤና ተቋማት ህብረተሰቡ የመጠቀም ልምዱና ግንዛቤ አነስተኛ መሆን፣
4. የአነስሳት ጤና ባለሙያዎች አውቀት አነስተኛ መሆንና የስነ ምግባር ችግር፣

⇒ የመገናኛ ፣ የመንገድና የመብራት አገልገሎት

በርዕሱ የተገለጹትን አውታሮች በተመለከተ ባለፉት 5 ዓመታት በክልሉ ያለውን ከፍተኛ የመንገድ ችግር ለመቅረፍ በርካታ የመንገድ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ሌሎች አውታሮችን በተመለከተ የረባ ስራ ተሰርቷል ለማለት አይቻልም በአጠቃላይ ከታች የተዘረዘሩት ችግሮች በአጠቃላይ በርዕሱ በተጠቀሱት አውታሮች የነበረውን ሁኔታ ያመለክታሉ ።

1) ከማዕከል ወደ ክልል የሚያስገባው መንገድ ደረጃውን ያልጠበቀ መሆን አና መሰረታዊ ጥገና አለማግኘት፣
2) በክልሉ ርዕሰ ከተማ ወደ ዞኖች አና ወረዳዎች ብሎም ከወረዳ ወረዳ የሚያገናኝ መንገዶች አለመኖር አና ያሉትም ቢሆን በአብዛኛው የበጋ ብቻ መሆን ፣
3) ወረዳና ቀበሌን አንዲሁም ቀበሌን ከቀበሌ የሚያገናኝ በህብረተሰቡ የሚሰራ የገጠር ጥርጊያ መንገዶች አለመኖር፣
4) የባንክ አገልግሎት አነስተኛ መሆን አንዲሁም የአነስተኛ ብድር ተቋማት አለመስፋፋት፣
5) የመገናኛ አውታርን በተመለከተ / በተለይ ስልክ ፖስታ / በአብዛኞቹ ወረዳዎች አለመኖር ያሉትም ቢሆን ደረጃቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በየጊዜው አየተበላሹ አገልግሎት ማቋረጥ፣
6) በክልሉ የመብራት አገልግሎት በጣም ዝቅተኛ መሆን፣

CCRDA

2.3 ለድህነት ይበልጥ የተጋለጡ አካባቢዎችና የህብረተሰበብ ክፍሎች

◊ **አካባቢዎች**

የከተማና የገጠር አካባቢዎች በተለይም የገጠሩ፣ በጦርነት የተጎዱ ጠረፋማ አካባቢዎች፣ዓመታዊ የምግብ ፍጆታቸውን መሸፈን ያልቻሉ አካባቢዎች።

◊ **የህብረተሰብ ክፍሎች**

ወላጅና አሳዳጊ አልባ ህፃናት፣ ሚሪ የሌላቸው አረጋዊያን ፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች፣አካል ጉዳተኞች፣ ረጂ የሌላቸው በተለያየ በሽታ የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ሰዎች፣ዓመታዊ የምግብ ፍጆታቸውን ሊሸፍኑ ያልቻሉ የህብረተሰብ ክፍሎች፣የአርሻ መገልገያ መሳሪያ የሌላቸው ገበሬዎች፣ደካማ የስራ ባህል ያላቸው ሰዎች ።

2.4/ ባለፉት ዓመታት ድህነትን ለማስወገድ የተደረጉ ጥረቶች

በክልሉ ተንሰራፍቶ ያለውን ድህነት ለመቀነስ ባለፉት ዓመታት በርካታ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በወረዳም ሆነ በክልል ምክክር ወቅት ተሳታፊዎች በሕብረተሰቡ በመንግስት አና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተከናወኑትን ተግባራት አንደሚከተለው አስቀምጠዋል ።

በህብረተሰቡ

1/ የተፈጥሮ ማዳበሪያ አና የክብት ፍግን በመጠቀም የመሬት ለምነትን ለማሻሻል ጥረት ተደርጓል፣
2/ ሰብልን አያፈራረቁ በመዝራት የመሬት ለምነትን ለመጠበቅ ተሞክሯል፣
3/ አረምን ነቅሎ በማቃጠል ለመቀነስ ተሞክሯል፣
4/ አፈር አንዲይሸረሸር የአፈር ጥበቃና ክትር ስራ ተሰርቷል፣
5/ ወንዞችን በባህላዊ ዘዴ በመጥለፍ አነስተኛ መስኖ ስራ ተጀምሯል፣
6/ በተለያዩ የህብረት ስራ ማህበራት የአህል ወፍጮዎች ተቋቁመዋል፣
7/ በስነ- ተዋልዶ አና ኤድስን በመከላከል ረገድ ጥረቶች ተደርገዋል፣
8/ ለልማት ማነቆ የሆኑ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶቸን ለማስወገድ ጥረት ተደርጓል፣
9/ በአካባቢው በተቋቋሙ ማህበራዊ ተቋማት/ አቁብ፣ አደር፣ ማህበራት ወዘተ/ ገንዘብ በማስባሰብ ችግርን ለማቃለል ጥረት ተደርጓል።

CCRDA

ሀ/ በመንግስታዊ ተቋማት የተከናወኑ ተግባራት

1/ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለያዩ የኤክስቴንሽን ፓኬጆች ተግባራዊ አንዲሆኑ ተደርጓል፣

2/ የመሰረተ ልማት ችግሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ የኢኮኖ ሚ እና ማህበራዊ አገልግሎት ጥቅም የሚሰጡ የመንገድ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የንፁህ መጠጥ ውሃና ሌሎች አገልግሎቶች ሰጭ ተቋማት ተቋቁመዋል፣

3/ ህብረተሰቡ አነስተኛ የብድር አገልግሎት አንዲያገኙ ጥረት ተደርጓል፣

4/ በተለያዩ መስኮች የተሰማሩ ባለሙያዎችን በመቅጠርና በማሰልጠን በልማት ስራ አንዲሳተፉ በማድረግ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖ ሚያዊ ተጠቃሚነት አንዲሰፉ ተደርጓል፣

5/ ኤድስን ለመከላከል ረገድ በክልሉ የሴክሬትራያት ፅ/ቤት ተቋቁሞ የቅስቀሳ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ አየተሰራ ነው።

6/ ህዝቡ እና የግል ባለሀብቶች በልማት ስራ ላይ አንዲሳተፉ ጥረት ተደርጓል

ለ/መግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተከናወኑ ተግባራት

በክልሉ ያሉት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አነስተኛ ሲሆኑ ንፁህ የመጠጥ ውሃን በማስፋፋት፣ የብድር አገልግሎት በመስጠት በግብርና፣በጤና፣ በትምህርት ዘርፎች ህብረተሰቡን በመጠኑ አየረዱ ይገኛሉ።

25 / የመንግስት የልማት ፕሮግራም በህብረተሰቡ ዕይታ

ሀ/ በፕሮግራም አፈፃፀም

አሁን ያለው የልማት ስራዎች/ፕሮግራሞች/ በቂ ነው ባይባልም ቀደም ሲል ከነበረው ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው።

- የፕሮጀክቶች ሽፋን አያደገ የመጣ ሲሆን በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ያለው ሽፋን ከህበረተሰቡ አድገት አና ብዛት አንፃር ዝቅተኛ ነው፣
- የአንዳንድ የልማት ፕሮግራሞችን ተግባራዊነት በተመለከተ በወቅቱ አና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ተግባራዊ አየተደረገ አይደለም፣
- የአንዳንድ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች አገልግሎት አሰጣጥና ብቃትን በተመለከተ የባለሙያ አጥረት፣ የውስጥ ድርጅት አለመሟላት አና የተፈለገው ግብአት አለመኖር ብቃቱን ዝቅተኛ አድርጎታል፣
- የመንግስት የማስፈፀም አቅም ግምት ውስጥ ያላስገቡ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መሆን፣
- የአንዳንድ ፕሮጀክቶች በወቅቱ አለመጠናቀቅና ለአገልግሎት አለመብቃት ችግሮች ይታያሉ፣
- በፕሮግራምና ፕሮጀክት ዝግጅት አንዲሁም ተግባራዊነት ክትትል አና ግምገማ ወቅት የህብረተሰቡ ተሳትፎ ዝቅተኛ ሲሆን በተወሰኑ ሴክተር መ/ቤቶች ብቻ ተግባራዊ ሆነዋል።

CCRDA

ለ/ በተለያዩ የአስተዳደር አርከኖች መካከል ያለው ግንኙነት

- በወረዳና ቀበሌ ያለው የአስተዳደር መዋቅር ያልተጠናከረ መሆን፣
- በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን አና በክልል መስተዳድሮች መካከል የግንዛቤ ማነስ ፣የብቃት ችግርና የስልጣን አርከን ጠብቆ አለመስራት፣
- የመስተዳድር አካላት ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ አለመግባት፣
- በልማት ህዝቡን ማሳተፍና ዲሞክራሲያዊ መብቱን አንዲገነዘብ በየደረጃው ባሉት የመስተዳድር አካላት የተደረገ ጥረት አነስተኛ ነበር።

2.6 /መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የህብረተሰቡ አይታ

- ክክልሉ ፍላጎት አንፃር በክልሉ ያሉት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ የሰጡት አገልግሎት አነስተኛ ነው፣
- በፕሮግራም /ፕሮጀክት/ ዝግጅት መረጣና ትግበራ ወቅት ህበረተሰቡን ያሳተፉ፣
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከመንግስት የስራ አቅድ ጋር በቅንጅት አለመስራት፣
- ድሃውን ማዕከል በማድረግ ወደ ገጠሩ ዘልቀው ለህብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት አነስተኛ መሆን፣

2.7 /በክልሉ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማካሄድና ድህነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀነስ መወሰድ ያለባቸው አርምጃዎች

ቀጣይነት ያለው ልማት ለማካሄድና ድህነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀነስ መወሰድ ያለባቸው አርምጃ በሚለው አጀንዳ ሥር በክልል ምክክር ተሳታፊዎች መወሰድ የሚገባቸውን ርምጃዎች በዋና ዋና ሴክተር በመለየት አርምጃዎቹን በአጭር አና በረዥም አስቀምጧል

CGRDA

ሀ. ግብርና

በአጭር ጊዜ	በረዥም ጊዜ
• አዳዲስና ተስማሚ የግብርና ቴክኖ ሎጂዎችን እና ግብዓቶችን በመጠቀም የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነትማሳደግ፣	◆ የግብርና ሙያ ብቃትን ለማሻሻል የአርሶ አደሩን አጠቃላይ ዕውቀት ማሳደግ/አርሶ አደሩን የ1ኛ ደረጃ ትምህርት አንዲያገኝ ማድረግ፣
• የተበታተነው ህብረተሰብ በፈቃደኝነት አንዲሰበሰብ በማድረግ በበረሃ አንዲያርስ ማድረግ፣	◆ የግብርና ምርምር ተቋማትን ማቋቋምና ማስፋፋት፣
• ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞችን ማዳበር፣	◆ የኤክስፖርት ኘሮሞሽን ስትራቴጂ መዘርጋትና ገበያን ማፈላለግ፣
• አነስተኛ የብድር ተቋማት አንዲስፋፉ ማድረግ፣	◆ ለኤክስፖርት የሚሆኑ ሰብሎችን በማምረት ወደ ገበያ ማቅረብ፣
• በክልሉ የግብርና ምርምር ተቋማትን ማቋቋምና በምርምር የተገኙ የግብርና ውጤቶችን ለገበሬው ማቅረብ፣	◆ የህብረት ሥራ ማኅበራትን በማስፋፋት ንግድ ተኮር የግብርና ሥራ አንዲያከናውኑ ማድረግ፣
• የተሸሸ ቴክኖ ሎጂ ማዕከል ሥራ ማስጀመር፣	◆ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፣
• ለገበሬው ኢንፎርሜሽን አንዲያገኝ ተቋማትን ማስፋፋትና ማጠናከር፣	◆ በክልሉ ያለው የተፈጥሮ ሀብት ዓይነትና መጠን በማጥናት በአግባቡ ጥቅም ላይ አንዲውል ማድረግ፣
• የመሬሙያ አቅም መገንባት፣	◆ የግብዓት አቅራቢ ድርጅት በክልሉ አንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
• ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን በመፍጠር የግል ባለሀብቶች በግብርናው ዘርፍ አንዲሳተፉ ማድረግ፣	
• ህብረተሰቡን በህብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጀት	

CCRDA

ለ. ጤና

በአጭር ጊዜ	በረጅም ጊዜ
◆ የክትባትና መስጫ ተቋማትን ማስፋፋትና የጤና አገልግሎት ብቃቱን ማጠናከር፣	◆ የጤና አገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ፣
	◆ የማሰልጠኛ ተቋሙን አቅምና ብቃቱን ማሳደግ፣
◆ ሆስፒታሎች በዘመናዊ መሣሪያዎች ማጠናከር ና ማደራጀት	◆ ልዩ ፋርማሲዎችን በሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች አንዲከፈቱ ማድረግ
◆ ከክልሉ የተገኘውን የመለስተኛ ጤና ባለሙያዎች ማሰልጠና በሰው ኃይልና ቁሳቁስ አንዲሟላ ማድረግ	◆ ሆስፒታሎችን በአስፈላጊ ባለሙያዎችና መሣሪያዎች በማሟላት ወደ ሪፈራል ሆስፒታል ማሳደግ፣
◆ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት፣	◆ የጤና ተቋማቱን በሰው ኃይል ማደራጀትና የአገልግሎት ብቃታቸውን ማረጋገጥ
◆ ባለሙያ፣ የመድኃኒትና የህክምና መሣሪያዎችን አቅርቦት ማሻሻል፣የሥርጭትና የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት አንዲሁም ጥራቱንና ሚዘናዊነቱን መጠበቅ፣	◆ የመድኃኒት አቅርቦት በክልሉ የሚገኝበትን መንገድ ማመቻቸት፣
	◆ ሙያዊ ሥነ ምግባር የተላበሰ ባለሙ ማፍራት፣
◆ መድኃኒት ሥርጭትና ቁጥጥር ሥልቱን መቀየስና ማሻሻል፣	◆ በጤና ተቋማት ግንባታና ህክምና ላይ የግል ባለሀብቶች አንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር
◆ ህብረተሰቡ ስለ ጤና አጠባበቅና በሽታ መከላከል ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ	
◆ ኤድስ በሽታን በተመለከተ ህ/ሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፣ አንዲከላከል ማድረግና የምርመራ አገልግሎት ማጠናከር፣	
◆ ጤና አገልግሎት ክፍያን አጥንቶ ማሻሻል፣	
◆ ኤድስ ክበባትን ማቋቋምና ማጠናከር፣ ለኤድስ ታማሚዎች የካውንስሊንግ ማዕከል ማቋቋም፣	

CCRDA

ሐ. ትምህርት

በአጭር ጊዜ	በረጅም ጊዜ
▪ የክልሉን ነባር ብሔረሰቦች የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ፣	◆ መሠረታዊ ትምህርት ለሁሉም ማዳረስና የህብረተሰቡን ተሣትፎ ማረጋገጥ፣
▪ የትምህርት ጥራትን መጠበቅ በጥራት ዙሪያም ጥናቶችን ማካሄድ፣	◆ መካከለኛና ከፍተኛ የትምህርት ባለሙያዎችን ማፍራት፣
	◆ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትንና አዳሪ ትምህርት ቤቶችን መገንባት፣
▪ የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን አቅም ማሳደግ፣	◆ የአፀደ ህፃናትና ልዩ ትምህርትን በክልሉ ማስፋፋትና ማጠናከር፣
	◆ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች አንዲማሩ ማድረግ፣
▪ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋምን ሥራ ማስጀመር፣	◆ የመጀመሪያ ሳይክል ት/ቤቶችን በማጥናት ደረጃቸውን ማሳደግ፣
▪ ትምህርት ቤቶችን በውስጥ ድርጅትና በባለሙያ ማሟላት፣	◆ ኤድስና የሥነ ምግባር ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት አካቶ መደበኛ ትምህርት አንዲሰጥ ማድረግ፣
	◆ የመምህራን መመልመያ መስፈርትን አጥንቶ ማሻሻል፣
▪ የትምህርት ግብዓት አቅርቦትን ማስፋፋትና ማጠናከር፣	◆ የግል ባለሀብቶችና የሃይማኖ ት ድርጅቶች በትምህርት ዙሪያ ተሣታፊ አንዲሆኑ ማበረታታት፣
▪ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሱ ግንዛቤን በህብረተሰቡ ማሳደር፣	
▪ ወላጆች ለትምህርት ያላቸውን ግንዛቤን በህብረተሰቡ ማሳደር፣	
▪ ቤቶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ ልዩ ትኩረት መስጠት፣	
▪ መሠረተ ትምህርት አንዲስፋፋ ማድረግ	
▪ የሁለ ቧጋ ትምህርት በተጠናከረ መልኩ መስጠት፣	
▪ የትምህርት መገናኛ ዘዴዎችን በክልሉ ማስፋፋት፣	
▪ ትምህርት ለሚያቋርጡ ተማሪዎች አነስተኛ የሙያ ሥልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር፣	
▪ የማንበብ ክህሎት ሥልጠና ማዕከላትን ማጠናከር	

CCRDA

መ. ንፁህ የመጠጥ ውሃ

በአጭር ጊዜ	በረጅም ጊዜ
• ንፁህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎትን ማስፋፋት፣ • የተሸሉ የመጠጥ ውሃ ተቋማት በዘለቄታው፣ በህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ጥገና ማድረግ፣ የውሃ ጥራቱንም መጠበቅ • የውሃ ተቋማቱን ህብረተሰቡ እንዲንከባከብ ማስተማርና ስለ ውሃ አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ፣ • የመጠጥ ውሃ ተቋማት መለዋወጫ ዕቃዎች በገልም ሆነ በመንግሥት በቅርቡ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት • የሚቆፈሩ የእጅ ፓምፖች ሲበላሹ በህብረተሰቡ እንዲጠገኑ ሥልጠና መስጠት • የሚገነቡ የውሃ ተቋማት ህብረተሰቡን ማሳተፍ፣ • የሚገነቡት ውሃ አቅርቦትን ማመቻቸት፣ • የሳኒቴሽን ያዎችን አቅም መገንባት፣ • የውሃ ተቋማትን አስተዳደር በወረዳ ደረጃ ማጠናከር፣ • የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተቀናጅተው የውሃ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲታዩ ማድረግ፣	◆ የውሃ ግኝት ጥናት ማካሄድ፣ ◆ የውሃ ሴክተር አቅም ግንባታ ማስፋፋትና ማሳደግ፣ ◆ ለጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ማሟላት

ሠ. መንገድ

በአጭር ጊዜ	በረጅም ጊዜ
• የገጠር መንገድ ግንባታ ማስፋፋትና የተሰሩትን ጥገና ማድረግ፣	◆ ወረዳን ከወረዳ፣ ወረዳን ከዞን፣ ዞንን ከክልል የሚያገናኙ መንገዶችን ደረጃ በደረጃ መገንባት፣
• ማሬን ከቀበሌና ቀበሌን ከወረዳ የሚያገናኝ የጥርጊያ መንገዶች ግንባታ ላይ ህብረሰቡ እንዲሳተፍና እንዲገነቡ ማድረግ፣	◆ ኢኮኖ ሚ ጠቀሜታ ያለውን መንገዶች በመለየት ቅድሚያ አየሠጡ መሥራት ◆ የገጠር መንገድ ጽ/ቤት በሰው ኃይልና በማሽነሪ ማሟላት፣
• መሠረታዊ የመንገድ ሥራ ትምህርት ህብረተሰቡ እንዲጨብጥ ማድረግና ለሥራው አጋዥ የሚሆኑ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶችን ድጋፍ ማድረግ፣	

CCRDA

ረ. መገናኛና መብራት

በአጭር ጊዜ	በረጅም ጊዜ
• የፖስታና የስልክ አገልግሎት በየወረዳው አንዲስፋፋ ማድረግና ጥራቱንም ማሳደግ፣	◆ የዞንና የወረዳዎች ርዕሰ ከተሞች የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ
• የሞባክ አገልግሎት የሚስፋፋበትን መንገድ ማመቻቸት፣	◆ በዞኖ ችና የወረዳ ከተሞች የቴሌቪዥን አገልግሎት ማስፋፋት
• የክልሉን ርዕሰ ከተማ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማሻሻል፣	◆ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት በክልሉ ባለሀብቶች አንዲስፋፉ ማበረታታትና ሌሎች የትራንስፖርት አማራጮችን ህብረተሰቡ አንዲለምድ ማድረግ /ሳይክል፣ ሞተር ሳይክል፣ ጋሪ ወዘተ/

ሰ. አቅም ግንባታ

በአጭር ጊዜ	በረጅም ጊዜ
• የክልሉን የልማት ኃይሎች አቅም ለመገንባት ማቀታይ ሥልጠና መስጠትና ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፣ የሰው ኃይል ሥልጠናና ሥምሪት ጉዳዮች ላይ / Need based/የተመሰረተ ማድረግ • አደረጃጀትና አሠራርን በየጊዜው መገምገምና አንዲሻሻል ማድረግ፣ • የአቅም ግንባታ ሥራን ተቋማዊ / institutional/ ማድረግ • የገጠ መሰበሰብ አቅምን ማጎልበት፣ • ከውጪ የሚገኙ የፋይናንስ ፍላጎትን ለማሟላት የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ማዘጋጀት	◆ የማሰልጠኛ ተቋማትን ማጠናከር ◆ አደረጃጀትና አሰራሮችን በየጊዜው በመገመገም ማሻሻል

መደበለ ዘርፍ

በረጅም ጊዜ

• የኢንቨስትመንት ዕምቅ ሀብቶችን በዘርዝር በማጥናት ተግባር ላይ ማዋል • የድንበር ንግድ ሥራን በጥናት ላይ ተመሥርቶ ማካሄድ • ዝርና ከተማን የሚያስተሳስርና ተደጋጋፊ አንዲሆኑ የሚያደርግ ሥርዓት መፍጠር

CCRDA

2..8 የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ አፈጻጸምን ስኬታማ ለማድረግ መዘርጋት ያለበት ሥርዓት ወይም ሥልት

⇒ *ከአደረጃጀት አኳያ*

- ◊ ቀበሌን አና ወረዳን ማዕከል ያደረገ አደረጃጀት መፍጠር አና ማጠናከር ፣
- ◊ ግልጽ የሆነ አሠራርና ተጠያቂነትን የሚያጸብር አደረጃጀት መፍጠር፣
- ◊ የልማት ኃይሎችን በቅንጅት የሚሰሩበትን አደረጃጀት መፍጠር።

⇒ *የልማት ኃይሎችን አቀናጅቶ ከመጠቀም አኳያ*

- * የልማት ኃይሎችን ለልማት በቅንጅት የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- * የልማት ኃይሎች የልማት አቅጣጫ ድህነት ተኮር አንዲሆን ማድረግ።

⇒ *ከአቅም ግንባታ አንፃር*

- * ፍላጎት ተኮር አና የክልሉን አቅም በሚፈጥር መልኩ ለሀሉም የልማት ኃይሎች የአቅም ግንባታ ሥራ ማከናወን፣
- * የአቅም ግንባታን ሥራ ከአለብን የአቅም ችግርና ከምናካሂደው የልማት ፕሮግራም አኳያ መዘርጋት፣
- * የማሰልጠኛ ተቋማትን አቅም ማጠናከር አና የሚያደርጉት የአቅም ግንባታ ድህነት ተኮር አንዲሆን ማድረግ።

⇒ *ከክትትልና ግምገማ አንፃር*

- * ክትትልና አና ግምገማ በየደረጃው ሥርዓት ባለው መልኩ ግልጽነት ተጠያቂነትና ኃላፊነት በያዘ ሁኔታ ማደራጀት፣
- * ፍትህ አና አስተዳደርን በማሻሻል አና አቅም በመገንባት የክትትልና ግምገማውን ሂደት ማጠናከር ።

CCRDA

የድሬዳዋ አስ/ካው/ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ /PRSP/ የመረዳዎችና የክልል ምክክሮች ማጠቃለያ ሪፖርት/Summary Report/

ለፌዴራል የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ምክክር ስብሰባ የቀረበ

CCRDA

የድሬዳዋ አስ/ካው/ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት

ድሬዳዋ፤

የድሬዳዋ አስ/ካው /የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ /PRSP/የወረዳዎችና የክልል ምክክሮች ማጠቃለያ ሪፖርት /summary report/

መግቢያ፣

1.1. አጠቃላይ የክልሉ ገጽታ

የድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል አቀማመጡ በአገሪቱ የምስራቅ ክፍል የሚገኝ ሲሆን የክልሉ ርዕሰ ከተማ የሆነችው ድሬዳዋ በስተምስራቅ አቅጣጫ ከአዲስ አበባ 515 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እና ከጅቡቲ ሪፑብሊክ መንግስት የወደብ ከተማ ከሆነችው ጂቡቲ ደግሞ በ313 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በመሀል ትገኛለች። ክልሉም በስተሰሜን ከሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሆነው የሽኒሌ ዞን እንዲሁም በስተደቡብ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሆነው ከምስራቅ ኦሮሚያ ዞን ጋር ይዋሰናል።

የአስተዳደር ካውንሰሉ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 1977 ካሬ ኪ.ሜትር እንደሚደርስ የሚገመት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 90.5 በመቶ ገጠር እና 9.5 በመቶ ደግሞ የከተማ ክልል እንደሆነ ይገመታል።

የክልሉ አብዛኛው ክፍል ቆላማ የአየር ንብረት ሲኖረው አማካይ አመታዊ የሙቀት እና የዝናብ መጠኑም እንደቅደምተከተላቸው 25.4^0C እና 604 ሚ.ሜ ነው።

በ1986 በተደረገው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ትንበያ መሰረት በ1994 የክልሉ ሕዝብ ቁጥር 330000 እንደሚሆን ሲገመት ከዚህ ውስጥ 72 በመቶው በድሬዳዋ ከተማ የሚኖርና ቀሪው 28 በመቶ ደግሞ በገጠር የሚኖር ነው። እንዲሁም ዓመታዊ የሕዝብ ዕድገት መጠኑ በከተማ 4.11 በመቶ በገጠር 2.23 በመቶ ነው።

የአስተዳደር ካውንስሉ ሕዝብ የኑሮ መተዳደሪያን በተመለከተ የክልሉ አብዛኛው ሕዝብ ኗሪ በሆነበት የድሬዳዋ ከተማ ዋና የመተዳደሪያው መሰረት ንግድ፤ትራንስፖርት፤ኢንዱስትሪ፤ ኮንስትራክሽን፤ የመንግስት ሥራዎች እና በተለያዩ የአነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ላይ ተሰማርቶ የሚተዳደር ሲሆን በገጠር የሚኖረው 28 በመቶ ሕዝብ ደግሞ በግብርና ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ የሚተዳደር ነው።

CCRDA

የድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል በአወቃቀሩ የፌዴራል መንግስት ተጠሪ ሲሆን አስተዳደራዊ መዋቅሩም በ4 ክፍተኞችና 25 ቀበሌዎች ባሉት የከተማ አስተዳደርና በዙሪያው የሚገኙ 29 የገጠር ቀ/ገ/ ማህበራትን ያቀፈ ነው።

1.2. የወረዳ እና የክልል ምክክሮች አጠቃላይ ሂደት

1.2.1. ቅድመ ምክክር ዝግጅት

በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ (PRSP) የወረዳና የክልል ምክክርን በተሻለ ደረጃ ከማሳካት አንፃር በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- የክልሉን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የስትሪንግና የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ማደራጀትና የሴክሪታሪያት ኃላፊውን በመመደብ በወቀቱ ለፌዴራል ሴክሪታሪያት እንዲተላለፍ ተደርጓል።

- በክልሉ ገጠርና ከተማ ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናር ለመስጠት የሚያስፈልገውን የማስፈፀሚያ ወጪ ከፌዴራል መንግስት እስኪለቀቅ ሳይጠብቅ ከአስተዳደር ካውንስሉ በጀት በማስፈቀድ በወቅቱ እንቅስቃሴውን ለመጀመር ጥረት ተደርጓል።

- በዚህም መሰረት በወረዳና በክልል ለማካሄድ ስለታቀደው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ የምክክር ስብሰባዎች አብይ ዓላማ፤ ለማስፈፀም ስለተቀየሰው ስልት፤ ከሕብረተሰቡና በየደረጃው ከሚገኙ አካላት ስለሚጠበቀው ተሳትፎና የኃላፊነት ድርሻ አስመልክቶ በገጠር በ3ት የተለያዩ የአግሮ ኢኮሎጂካል ማእከላት ለ148 እና በከተማ በሁለትዙር ለ173 በድምሩ ለ321 የሕብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

- በግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ላይ የተሳተፉት ወደ መጡበት አካባቢ ተመልሰው በተዋረድ ለሕብረተሰባቸው ስለ ድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የወረዳ ምክክር አላማ እንዲያስጨብጡና ተገቢውን ምክክር አድርገው ሕብረተሰቡን ወክለው በወረዳ ምክክር ስብሰባ ላይ የሚሳተፉትን ከሀገር ሽማግሌ፤ ከሴቶች፤ ከወጣቶች፤ ከጎልማሳ፤ ወዘተ ተገቢውን ስብጥር በጠበቀ መልኩ ሕብረተሰቡ መርጦ እንዲወክል አድርገዋል።

CCRDA

- በተሳታፊነት የተመረጡትም ሕብረተሰባቸውን በማወያየት በወረዳ ምክክር ላይ እንዲንፀባረቅለት የሚፈልገውን አብይ የድህነት ችግሮቹንና አንገብጋቢ የልማት ፍላጎቶቹን እንዲያቀርብ በማድረግ አስተያየቶችና ሀሳቦች አሰባስበው በጽሁፍ ይዘው በምክክር ስብሰባው ወቅት እንዲቀርቡ ተደርጓል።

- በፌዴራል ሴክሬታሪያቱ በእያንድንዱ የወረዳ ምክክር ላይ 50 ተሳታፊዎች እንደሚኖሩና ከዚህ ውስጥ 30 የሕብረተሰቡ ተወካዬች ይሆናሉ የሚለውን የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ለማስፋትና ለማጎልበት ከአስተዳደር ካውንስሉ ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ 30 የነበረውን በእጥፍ በመጨመር 60 እንዲሆንና በአንድ ወረዳ 80 ተሳታፊዎች እንዲመረጡ ተደርጓል።

- የወረዳና የክልል ምክክሩን በሰብሳቢነትና በራፖርትነት (convenors)እንዲመሩ የተደረጉትን በቴክኒክ ኮሚቴው በወጣው የመምረጫ መስፈርቶች መሰረት ይሄውም ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት አባልነት ነፃ ወይም ገለልተኛ የሆኑ፤ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነት ያላቸው፤ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ቋንቋ፤ ባህልና ስነልቦና የሚያውቁ፤ የመድረክ መምራትና የተግባቦት ክህሎት ያላቸው፤ ወዘተ መመዘኛዎች አማካይነት ከሕብረተሰቡ መሀከል በጥንቃቄ እንዲመረጡ በመደረጉ የምክክር ስብሰባዎቹ ነፃና ዲሞክራቲክ በሆነ መልኩ እንዲካሄዱ አስችሏል።

- ከፌዴራል ሴክሬታሪያቱ ጋር በቅንጅት ለወረዳና ለክልል ምክክር ሰብሳቢዎችና ራፖርተሮች ተገቢው ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።

- በክልሉ ምክክር የሚካሄድባቸውን 2ት ወረዳዎች ለመምረጥ የድህነት ችግሮቹ ዓይነት፤ ስፋት፤ ጥልቀት፤ ውስብስብነት፤ ወዘተ በባህሪው የከተማና የገጠሩ የተለያየ መሆኑን በዋነኛነት ግንዛቤ ተወስዶ የድሬዳዋ ከተማን እንደ አንድ ወረዳ የገጠሩ ክፍል ደግሞ አንድ ወረዳ አድርጎ በመውሰድ ምክክሩ እንዲካሄድ ተደርጓል።

- በሌላ በኩል የገጠሩ ክፍል አንድ የምክክር ወረዳ ተብሎ የተወሰደ ቢሆንም በክልሉ ገጠር የሚገኙ የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ አርብቶ አደሮችና የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪ አርሶ አደሮች በራሳቸው ቋንቋ እንዲወያዩ ሁለት የተለያዩ መድረኮች እንዲመቻችላቸው ተደርጓል።

CCRDA

- በፌዴራል ሴክሬታሪያቱ የተዘጋጁ የመወያያ ሰነዶችን፤ ከኢንተር አፍሪካ ግሩፕ የተለገሱ መጽሄቶችን፤ በክልሉ የቴክኒክ ኮሚቴ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን፤ ወዘተ ለተሳታፊዎች ከምክክር ስብሰባው በፊት በቅድሚያ እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

- የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት ዋነኛ ትኩረትና ዓላማውን ሊያስተላልፉ የሚችሉ የቅስቀሳ 800 ፖስተሮችና 300 ኬፖች በአሮሚኛ፤ በሶማሊኛ፤ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች በማሳተም በአካባቢው እንዲለጠፉና እንዲሰራጩ ተደርጓል።

- በወረዳ ደረጃ የተካሄደውን ምክክር፤ የሕብረተሰቡን የተሳትፎ ደረጃና የተሰጡ አስተያየቶች ምን እንደሚመስል የክልል ምክክር ተሳታፊዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኙ ከወረዳው ማጠቃለያ ሪፖርት በተጨማሪ በወቅቱ የተቀረፀውን የቪዲዮ ምስል አሳጥሮ በማዘጋጀት እንዲመለከቱት ተደርጓል።

- የቡድን ውይይት አስመልክቶ በገጠር የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተሳታፊዎች ካለው የባህል ተጽእኖ አኳያ ከሦስቱ የስብሰባ ቀናቶች አንዱን በያታ በመከፋፈል የቡድን ውይይት ያደረጉ ሲሆን እንዲሁም በክልል ምክክር ስብሰባም በመጨረሻው አንድ ቀን ተሳታፊዎችን በሶስት ቡድን በመክፈል እንዲወያዩ በመደረጉ በርካታ ጠቃሚ ሀሳቦችና አስተያየቶች እንዲቀርቡ አስችሏል።

1.2.2. የምክክር ተሳታፊዎች ሁኔታ

1.2.2.1. የወረዳ ምክክር ተሳታፊዎች ይዘት

- የገጠርና የከተማ የወረዳ ምክክር ስብሰባ ከጥቅምት 30 እስከ ሕዳር 2/1994 በድሬዳዋ ከተማ የተካሄደ ሲሆን ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተወከሉ 81 የገጠር፤ 74 የከተማ በድምሩ 155 ተሳታፊዎች ተገኝተዋል። ከነዚህ ውስጥ 46 ወይም 29.7 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።

- የገጠሩ የምክክር ወረዳ በሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ አርብቶ አደሮችና በአሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ አርሶ አደሮች ተብሎ በመለየት በሁለት መድረኮች ተከፍሎ በራሳቸው ቋንቋ የተካሄደ ሲሆን፤

  እንደቀደም ተከተላቸው 23 እና 58 ተሳታፊዎች ነበሯቸው። የሴቶች ተሳትፎም በተመሳሳይ 21.7 በመቶ እና 26 በመቶ ድርሻ ነበረው።

CCRDA

1.2.2.2. የክልል ምክክር ተሳታፊዎች

- የክልል ምክክሩ ከጥር 30 እስከ ሕዳር 2/1994 በድሬዳዋ ከተማ የተካሄደ ሲሆን ከተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች፤ መ.ያ.ድ/NGOs/፤ ከሲቪክ ማህበራት፤ ከግሉ ዘርፍ፤ ከሕብረተሰቡ፤ ወዘተ የተወከሉ 211 ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን የሴቶች ተሳታፊ ድርሻ 11.4 በመቶ ነው።

1.2.3. ያጋጠሙ ችግሮች

- ከፌዴራል በወቅቱ በጀት ያለመተላለፍ ችግር
- የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በመ/ቤታቸው ተደራራቢ ሥራዎች ያሏቸው በመሆናቸው ያሳደረው የሥራ ጫናና በስብሰባዎች ተሟልቶ ያለመገኘት ችግር
- በፌዴራል የወረዳና የክልል ምክክሮቹ እንዲካሄዱ የተሰጠው የጊዜ ገደብ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ በቂ ቅድመ ዝግጅቶችን ለማድረግ ያላስቻለ መሆኑ
- አጠቃላይ የምክክሩ ሂደት የመጀመሪያና አዲስ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የተመክሮ ማነስና ወጥነት ያለው አሰራርን ለመከተል አለማስቻሉ

2. የወረዳዎች ምክክር ዋና ዋና ግኝቶች

2.1. የድህነት ገጽታ በገጠርና በከተማ በሕብረተሰቡ ዕይታ

2.1.1. በገጠር

ሀ. አርሶ አደር

- ቤተሰቡን የሚመግብ በቂ ምርት አለማግኘት
- በቂ የእርሻ መሬት፤ የእርሻ በሬና መሣሪያ አለመኖር
- በእርሻ ሰዓት በጉልበት ሥራ መስማራት
- የምግብ ፍላጎቱን በልመናና በማገዶ ሽያጭ የሚያሟላ

ለ. አርብቶ አደር

- መተዳደሪያውን የገቢ ምንጭ የሆኑት እንስሳት በተለይ የግመል፤ የወተት ላም፤ የበግና የፍየል የመሳሰሉትን እጅግ በጣም አነስተኛ ቁጥር ያለውና የሚያረባ
- ለሰውና ለእንስሳት የመጠጥ ውሀ አገልግሎት በበቂና በቅርብ ርቀት ማግኘት አለመቻል
- ለተደጋጋሚ የተፈጥሮ ድርቅ ተጠቂ በመሆን የራስንና የቤተሰብን ፍላጎት ማሟላት አለመቻል

CCRDA

- በተለይ በሴቶች ፅይታ በአርሶ አደሩም ሆነ በአርብቶ አደሩ የወተት ላምና ለተለያዩ ማጓጓዣዎች የአህያ ባለቤት አለመሆን

2.1.2. በከተማ

- የሚላስ የሚቀመስ ማጣትና የቤተሰብን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት አለመቻል
- አባት የሌላቸውን ልጆች ማሳደግ
- በራፍ ላይ ተቀምጦ መቸርቸር፤ አመቺ የሥራ ቦታ አለመኖር
- የገቢ አነስተኝነት፤ አስተማማኝና አማራጭ የገቢ ምንጭ ማጣት
- ዘላቂ የሥራ ዋስትና ማጣት

2.2. በገጠርና በከተማ ድህ የሚባለው የአኗኗር ሁኔታ

ሀ. አርሶ አደር

- በአካባቢው አመጋገብ ሥርዓት በቀን ሁለቴ መመገብ የተሳነው
- በአመት አንድ ጊዜ የራሱንና የቤተሰቡን ልብስ ማሟላት የማይችልና ከአመት አመት ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ያለበት
- በአንድ ጎስቋላ ቤት ውስጥ ከእንስቲቱ ጋር የሚኖርና ለመኝታው አንድ ቆዳ ችግሮች እየቆረቆረው በባዶ መደብ ላይ የሚተኛ

ለ. አርብቶ አደር

- አነስተኛ የእርባታ እንስሳት ያለው ወይም ምንም እንስሳት ላይኖረው በሌሎች የማሕበረሰቡ አባላት እየተረዳ የሚኖር
- በአብዛኛው እንጨትና ከሰል በመሸጥ የቤተሰቡን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚፍጨረጨር

2.2.2. ከተማ

- የፅለት ጉርሱና የዓመት ልብስ የማያገኝ
- በጎዳና ላይ የሚኖርና የቀን ገቢ የሌለው
- በእንጨት ለቀማና በጉልበት ሥራ የሚተዳደር
- መስራት እየቻለ ሥራ በማጣቱ በልመና ላይ የተመሰረተ ኑሮ የሚገፋ

CGRDA

- ተስፋው የጨለመበትና ራዕይ የሌለው
- ፍትህ በጊዜ የማያገኝ፤ የሚናቅና አስተዋሽ ያጣ

2.3. በገጠርና በከተማ ለድህነት በይበልጥ የተጋለጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች

2.3.1. በገጠር

ሀ. አርሶ አደር

- በርካታ ልጆችን የማሳደግ የኃላፊነት ቀንበር የተሸከመች ሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪ
- የእርሻ መሬታቸውን የሚያርስላቸው ልጅ የሌላቸውና ሚሪና ደጋፊ ያጡ አረጋዊያን
- ከወላጆቻቸው የእርሻ መሬት የመካፈልና የማግኘት ዕድል ተስፋ የሌላቸው የገጠር እረኞችና ወጣቶች

ለ. አርብቶ አደር

- ባሏ በመሞቱ ሳቢያ በርካታ ልጆችን በማሳደግ ከፍተኛ የቤተሰብ ኃላፊነት ቀንበር የተሸከመች የገጠሯ ሴትና ሕፃናቶች
- ከአርብቶ አደሩ የአኗኗር ሁኔታ አንፃር ከሥፍራ ሥፍራ ለመንቀሳቀስ አቅም የተሳናቸው አረጋዊያን

2.3.2. ከተማ

- በአነስተኛ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩና በዝሙት አዳሪነት የሚተዳደሩ በተለይ የቤተሰብ አስተዳዳሪ የሆኑ ሴቶች
- ወላጅ አልባ ሕፃናት የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናትና ሥራ አጥ ወጣቶች
- ደጋፊ የሌላቸው የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ሕመምተኛ
- አካል ጉዳተኞችና የተበተነ የቀድሞ የደርግ ሰራዊት

2.4. የድህነት ሁኔታ ባለፉት ዓመታት የነበረው ገጽታ

በገጠርም ሆነ በከተማ ባለፉት ዓመታት በአጠቃላይ ሲታይ የሕብረተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ከዓመት ዓመት እያሽቆለቆለ እንደሄደና የድህነት ሁኔታውም እየተባባሰ እንደመጣ የወረዳ ምክክር ተሳታፊዎች የገለፁ ሲሆን ለድህነቱ እየተባባሰ መሄድ አስተዋጽኦ ያደረጉ አበይት መንስኤዎች ናቸው ያሏቸውንም እንደሚከተለው አቅርበዋል።

CCRDA

2.4.1. በገጠሩ ክፍል

ሀ. አርሶ አደር

- በከፍተኛ መጠን በየዓመቱ ከሚጨምረው የሕዝብ ብዛት አንፃር በቂ የእርሻ መሬት ያለመኖር
- የእርሻ መሬት ይዞታ አነስተኛና የተበጣጠሰ ከመሆኑ ባሻገር የአፈር ለምነቱ የተሟጠጠ መሆን
- የእርሻ በሬና የእርሻ መሳሪያ እጦት

ለ. አርብቶ አደር

- የከብቶች ብዛትና የግጦሽ መሬት አለመመጣጠን
- በተደጋጋሚ በሚከሰተው ድርቅ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቃና የውሀና የመኖ እጥረት ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መሄድ
- በኮንትሮባንድ ንግድ ለማንጓጓ ግመሎችን በማከራየትና የእንስሳት ሀብቶቹን በጥሩ ዋጋ በመሸጥ ኑሮውን ይደጉም የነበረው የኮንትሮባንድ ንግዱ በመታገዱ ለአስከፊ ድህነት የዳረገው መሆኑ
- የአርብቶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻል በመንግስት በኩል ተገቢውን ትኩረት ያልተሰጠው

2.4.2.በከተማ

- አብዛኛው የከተማው ሕዝብ መተዳደሪያ የሆነው የንግድ ዘርፍ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ እየተዳከመ መሄድ
- በኮትሮባንድ ንግድ ላይ ሕጋዊ እርምጃ ሲወሰድ በምትኩ ሕጋዊ ንግድን እና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ተገቢው ጥረት አለመደረጉ
- ለጥቃቅን ንግድ የሥራ ዘርፍ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ አስፈላጊ ድጋፎች አለመደረጉ
- የከተማው ነባር ፋብሪካዎች በከፍተኛ ደረጃ እየተዳከሙ መሄድ
- ካሉት ጥቂት ፋብሪካዎችም ከሥራ የተቀነሰው ወዛደር ቁጥሩ እጅግ በርካታ ሲሆን በሴፍቲኔትና በሌሎች ፕሮጀክቶችም ለማቋቋም የተደረገ ጥረት አለመኖር
- የከተማው ሥራ አጥ ቁጥር እየተበራከተ መሄድ በተለይ 12ኛ ክፍልን አጠናቀው በሥራ አጥነት በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚኖሩ ወጣቶች ከዓመት ዓመት እየጨመረ መምጣት
- በአጠቃላይ የአብዛኛው የከተማው ኗሪ ገቢ እያሽቆለቆለ ሲሄድ በሌላ በኩል የመሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ እየናረ መሄዱ

CCRDA

- በከተማው የተለያዩ የማሕበራዊ ጠንቅ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መምጣት

2.5. ከድህነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የማሕበራዊ አገልግሎቶችና የመንግስት አስተዳደራዊ መዋቅሮች ገፅታና ችግሮቻቸው

2.5.1. የትምህርት አገልግሎት

ሀ. በገጠር

- በጠለፋና በሌሎች ማሕበራዊ ችግሮች ሳቢያ የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆን
- በተለይ በርካታ ልጆች ያሏቸውና ደሀ ገበሬዎች ልጆቻቸውን ለማስተማር የአቅም ውስንነት
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ የትምህርት አገልግሎት አለመስፋፋትና ተንቀሳቃሽም ሆነ የአዳሪ ት/ቤት በመክፈት ልጆቹ እንዲማሩ በሚመለከተው ክፍል አንዳችም ጥረት አለመደረጉ

ለ. በከተማ

- በከተማ የሚገኙ ት/ቤቶች ከአቅማቸው በላይ ተማሪዎችን ተቀብለው በማስተማራቸው የመማሪያ ቦታ ጥበትና ለትምህርት አሰጣጡ ምቹ አለመሆን
- የመምህራን እጥረትና በሰለጠኑበትና የትምህርት ዓይነት ያለመመደብ ችግር
- ከ10ኛ/ክፍል በኃላ ለትምህርት አገልግሎት የሚጠየቀው ዓመታዊ ክፍያ ከደሀው ቤተሰብ አቅም ጋር አለመጣጣሙ

2.5.2. የጤና አገልግሎት

ሀ. በገጠር

- በአቅም ማነስና በግንዛቤ እጦት የባህላዊ የሕክምና ተጠቃሚ ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ መሆን
- በገጠር ያሉ አብዛኞቹ የጤና ባለሙያዎች ለገጠሩ ሕብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት የማይሰጧቸው መሆኑ
- ገበሬው ለመድኃኒት አገልግሎት ክፍያ ከአግባብ በላይ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ መሆኑ

CCRDA

ለ. በከተማ

- የከተማው ሕዝብ በየጊዜው በከፍተኛ መጠን እያደገና እየጨመረ የመጣ ሆኖ ሳለ ለረዥም ዓመታት ተጨማሪ ምንም ዓይነት የጤና ተቋማት እንዲሰራ ያልተደረገ መሆኑ
- የመድኃኒት ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ በመምጣቱ ከደሀው ሕብረተሰብ የመግዛት አቅም በላይ መሆኑ
- ከቀበሌ የነፃ ሕክምና ፍቃድ ላወጡ ተረጂዎች አስፈላጊው ደጋፍ አለመስጠቱና መድኃኒት ከውጭ እንዲገዙ መገደዳቸው.
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ በከፍተኛ ፍጥነት መዛመት
- የአብዛኞቹ የጤና ባለሙያዎች በአገልግሎት አሰጣጥ ከፍተኛ የስነ ምግባር ችግር መኖሩ
- የከተማው የጽዳት አገልግሎት በየጊዜው እያሽቆለቆለ መሄድ

2.5.3. **የመሰረተ ልማት አገልግሎት አቅርቦትና ችግሮቻቸው.**

- በተለይ በድሬዳዋ ከተማ የመኖሪያ ቤት አዋረት ችግር ከዓመት ወደ ዓመት በእጅጉ እየተባባሰ እንደመጣ
- ለመኖሪያ ቤት መስሪያ የሚውል ቦታ ያለማግኘት የጎላ ችግር በመኖሩ ሳቢያ የጨረቃ ቤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መሄድ
- ነባር የቀበሌ ቤቶች በጥገና እጦት እያፈራረሱ እንደሚገኙ
- የገበያ ሥፍራዎች ባለመሰራታቸው ከፍተኛ ቁጥር ያለው በጥቃቅን ንግድ ላይ ተሰማርቶ የሚተዳደረው ድሀው ሕብረተሰብ በተለይ ሴቶች ለፀሀይ፤ ለአቧራና ለዝናብ ችግር የተዳረጉ መሆናቸው
- በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙና በጨረቃ ቤቶች የሚኖሩ በርካታ የከተማው ኗሪዎች ለመኖር በጣም አስፈላጊና መሰረታዊ የሆነውን የውሀና የመብራት አገልግሎት የማግኘት መብታቸው መነፈጉ
- የድሬዳዋ ከተማ የአገሪቱ 2ኛ ትልቅ ከተማ ሆና ሳለች እስከ አሁን የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት እንዲኖራት አለመደረጉና የታክስ ክፍያ ከደሀው ሕብረተሰብ አቅም በላይ መሆኑ

2.5.4. **የመንግስት አስተዳደር መዋቅሮች ገጽታና ችግሮቻቸው.**

2.5.4.1. የቀበሌ መስተዳድርና የቀበሌ ገበሬ ማህበራት

- የቀበሌ መስተዳድር አሰራር በሕገወጥ ጥቅማ ጥቅም ላይ የተመሰረተ መሆኑና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ችግር መፈጠሩ

CCRDA

- የቀበሌ አመራር አካላት ምርጫ አግባብ ባለው መመዘኛ እና ሕዝባዊ ወገናዊነት የተመረኮዘ ባለመሆኑ እንዲሁም የደመወዝ ክፍያ ስለማያገኙ ለሙስና አመቺ ሁኔታን መፍጠሩ
- የገጠር የቀበሌ የገበሬ ማህበራት አመራር አካላት ስለተግባርና ኃላፊነታቸው ምንም አይነት ስልጠና ያላገኙና ክፍያ የሌላቸው ስለሆነ ወደ ግል ሥራቸው የማድላት ችግር መኖሩ
- አብዛኞቹ ተመራጮች የአመራር ብቃት ስለሌላቸው ሕዝብን ያሳተፈ የልማት እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አለመሆናቸው

2.5.4.2. የአስተዳደር ካውንስል ጽ/ቤት

- የድሬዳዋ አስ ካውንስል ነፃ ክልል ሆኖ በምክር ቤት መተዳደር ሲገባው እስከ አሁን ሕዝቡ የዲሞክራሲያዊ መብቱን በመጠቀም ተጠያቂነታቸውና ተጠሪነታቸው ለሕዝቡ የሆኑ የራሱን የመስተዳደር አመራሮች ለመምረጥ አለመቻሉ
- የልማት ዕቅዶችን በጋራ አለማቀድ፤ የአፈፃፀም ውጤታቸውንና ችግሮቻቸውን ለሕብረተሰበሀ አለማሳወቅ፤ ሕዝባዊ ቁጥጥርና ክትትል በየደረጃው ለማስፈን አለመቻል፤
- ሕዝቡን በልማት ችግሮች ዙሪያ ለማወያየት እና ችግሮቹን ለማዳመጥ ጥረት አለማድረግ

2.6. ባህላዊ ተጽእኖዎች

ሀ. በገጠር

- ጠለፋ፤ አቅም ሳይኖር መጋባት፤ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሕፃናትን መዳር፤ ለጥሎሽና ለጋብቻ ከፍተኛ ወጪ ማውጣት
- የሴት ልጅ ግርዛት፤ ብልት መስፋት፤ እንጥል መቁረጥ፤ እርጉዝ ሴትን ማሸት

ለ. ከተማ

- ሥራን መናቅና የሥራ ክቡርነትን አለመገንዘብ
- ከማን አንሼ በሚል ለተስካር፤ ለሰርግ ለመሳሰሉት ከፍተኛ ወጪ ማውጣት

2.7 ድህነትን ለመቀነስ መውሰድ ያለባቸው ቀጣይ እርምጃዎችና ዋና ዋና የሕብረተሰቡ የልማት ፍላጎቶች

2.7.1 በገጠር

- የዝናብ አጥረትንና ድርቅን ለመቋቋም እንዲቻል የጎርፍ ውሀን በመገደብም ሆነ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የመስኖ ልማትን ማስፋፋት

CCRDA

- የእርሻ በሬ፤ የእጅ መሳሪያዎችና የምርጥ ዘር አቅርቦትን ማሻሻል
- የብድር አገልግሎትን በማጠናከር ገበሬው ለተሻለ ኢኮኖሚያዊ የስራ ዕድል መፍጠር
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ የመሰረተ ልማት አውታሮችንና መንገዶችን በመስራት በእንስሳት ሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል
- የእንስሳት በሽታን የመከላከል ስራ ማጠናከር
- ለሰውም ሆነ ለእንስሳት የንጽህ መጠጥ ውሀ አቅርቦትን በቅርብ ርቀት እንዲያገኙ ማስቻል
- ለውሀ አገልግሎት የሚገጠሙ ቁሳቁሶች ዘላቂነትና አስተማማኝ ማድረግ
- በጤና ኬላዎች የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ ቁሳቁሶች አቅርቦትን ማሻሻል
- የወባ በሽታን በተጠናከረ ሁኔታ መከላከልና ለእናቶችና ሕፃናት ሕክምና ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ
- የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ የሚያድግበትን ሁኔታ ማመቻት
- ለት/ቤቶች በቂ መምህራንን መመደብ፤ ለመምህራን የመኖሪያ ቤት እንዲሁም ለት/ቤቶቹ የውስጥ ድርጅታቸው እንዲሟሉላቸው ማድረግ
- በምሽት ትምህርት የጎልማሶችን ትምህርት ማጠናከር
- ለሕብረተሰቡ ተቆርቋሪና ሐቀኛ የሆኑ የመንግስት ሰራተኞችን በገጠር በመመደብ ሕብረተሰቡን በቅንነት እንዲያገለግሉ ማድረግ
- ባህላዊ ተጽእኖዎችና ጎጂ ልምዶችን ደረጃ በደረጃ መቀነስ

2.7.2 በከተማ

- በየአመቱ 12ኛ ክፍል እያጠናቀቀ የቤተሰብና የአገር ሸክም የሚሆነውን ወጣት ተጨማሪ ስልጠና ሰጥቶ ወደ ስራ ለማሰማራት የሚያስችል የስልጠና ተቋም መፍጠር
- በድንገት በስራቸው የሚፈናቀሉ የበርካታ ቤተሰብ አስተዳዳሪ የሆኑ የፋብሪካ ሠራተኞች አማራጭ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት ሁኔታ መፍጠር ወይም የሥራ ዋስትና.ውና መብታቸው እንዲጠበቁላቸው ማድረግ
- ነባር የከተማው ፋብሪካዎች ለግል ባለሀብቶች ቢሸጡም በአፈፃፀም መንግስት በቅርብ እንዲከታተልና እንደገና የሚያንሰራሩበትና ትርፋማ የሚሆኑበት ሁኔታ ትኩረት ቢሰጠው
- ድህነትን ለመቀነስ በኢንቨስትመንት ላይ ትኩረት ይደረግ
- ዕውቀትም ሆነ የጉልበት ብቃት እያላቸው በመንቀሳቀሻ ካፒታል እጦት ስራ መስራት ላልቻሉት የሕብረተሰብ ክፍሎች የብድር ተጠቃሚ ማድረግ
- ለከተማው ዕድሮች የሙያ ስልጠና በመስጠት በድህነት ቅነሳ እንዲሳተፉ ማስቻል
- በተበታተነ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ አነስተኛ ኑጋዴዎችን ማደራጀትና ሕጋዊ የንግድ አመራር መስጠት

CCRDA

- የድሬዳዋ ልማት ማህበር /ድልማ/ በማቋቋምና በማደራጀት ሕብረተሰቡ የልማት አጋር የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- ሕዝቡ የዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ አስተዳደር ካውንስሉ ሕዝባዊ አመኔታ ያላ.ው ብቁና ታታሪ የሕዝብ ተወካዬች የሚመረጡበት ሁኔታ ቢመቻች
- የክልሉ መንግስታዊ አስተዳደር መዋቅሮች የሥራ አፈፃፀምና እንቅስቃሴ በየ6ወሩ በይፋ በህዝብ የሚገመገምበት ሁኔታ ቢመቻች
- ለኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ ተጠቂዎች ተገቢው ድጋፍና ትኩረት ይሰጥ እንዲሁም የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው ውጤታማ እንቅስቃሴ ማድረግ
- የመኖሪያ ቤት እጥረትን ለማቃለል የሚያስችሉ ተጨባጭ እርምጃዎች መወሰድ፤ የከተማ ቦታ አሰጣጥን ማሻሻልና ከኗሪው አቅም ጋር የተገናዘበ እንዲሆን ማድረግ

3. የክልል ምክክር ግኝት

የክልል ምክክር ስብሰባው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናቶች ሕብረተሰቡ በወረዳዎች ምክክር ወቅት ባነሳ.ው ጉዳዬች ላይ ተመስርቶ በዝርዝርና በጥልቀት በመወያየት ተጨማሪ መካተት የሚገባቸውን ሀሳቦች በማከል የበለጠ የወረዳ ምክክር ዶክመንቱን እንዲዳብር አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ በሶስተኛው ቀን የክልል ምክክር ተሳታፊዎች በቡድን ተከፋፍለው ባደረጓ.ው ውይይቶች እጅግ በርካታ ጠቃሚ አስተያየቶችና ሀሳቦች የቀረቡ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም ከዚህ በታች በየውይይት ርዕሱ ቀርቦ ይገኛል።

3.1 በመንግስት የተዘጋጀው ሰነድ በክልሉ ሕዝብ ተጨባጭ የድህነት ሁኔታ ጋር ሲታይ የሚያሳየው ክፍተት በተመለከተ፣

- አርብቶ አደረነት በኑሮ መተዳደሪያነት /mode of life/ ታይቶ ሕብረተሰቡን በተቀናጀ የልማት ሥራዎች ተጠቃሚ ለማድረግ በአርብቶ አደሩ የአኗኗር ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ልማት ለማካሄድ ልዩ ትኩረት አለመስጠት
- በአገሪቱ ባሉት ትላልቅ ከተሞች ያለው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች፤ ጎዳና ተዳዳሪነት፤ ሥራ አጥነት፤ ወዘተ ውስብስብ እንደመሆኑ መጠን በሰነዱ ውስጥ በበቂ አለመካተት
- ጎጂ ባህሎችን በማስወገድና ጠቃሚ ባህላዊ ልምዶችን ወደ ዘመናዊነት በማሸጋገር ለመጠቀም እንዲቻል ባህል ራሱን ችሎ እንደ አንድ ኮምፖነንት አለመካተት
- የሕብረተሰቡ ግማሽ ክፍል የሆኑት ሴቶች በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ካላቸው ጉልህ ሚና እንዲሁም የሕዝብ ዕድገት ሁኔታ በበቂ አለመካተት

CCRDA

- የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ያለውን ሥራ አጥነት ለመቀነስ ሕብረተሰቡ የአገር ውስጥ ምርትን እንዲጠቀም የማበረታታትና በአገር ውስጥ ያሉ ፋብሪካዎች በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል አካሄድ ትኩረት አለማግኘት

3.2 ድህነትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቀነስ መንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች NGO's ፤ የግል ባለሀብቱና ሕብረተሰቡ በቀጣይ በተናጠልም ሆነ በጋራ ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸው ሰልት እና የሚኖራቸው ሚና በተመለከተ፣

3.2.1 የመንግስት ሚና

- የልማት ችግሮች ሕብረተሰቡ በተናጠል የሚያደረጋቸው እንቅስቃሴ ይበልጥ በህብረት ተደራጅቶ መስራት በችግር ፈቺነት ውጤታማ ስለሚሆን የሕብረት ሥራ ማህበራትን እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ማድረግ
- መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሕብረተሰቡ ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በጋራ ማዘጋጀትና አፈፃፀሙን መከታተል
- በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ላይ ከሕብረተሰቡ የሚመጡ የልማት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ
- የልማት ችግሮቻችን በርካታ በመሆናቸውና የማስፈፀሚያ ሀብትና አቅም ውስን በመሆኑ የልማት ክፍተቶችን መለየትና በቅደም ተከተል ማስቀመጥና በአንገብጋቢነታቸው ቅድሚያ የተሰጣቸውን መተግበር
- የተሻሻሉ አሰራርና ቴክኖሎጂ ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ የሚቀርብበትን መንገድ መቀየስ
- ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የወጡ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችን በመገምገም እንዲሁም አለም አቀፋዊና አገራዊ ሁኔታች ላይ በመመስረት ማሻሻያዎችን ማድረግ
- የኢንቨስትመንት አማራጮችና ዕድሎችን ማስጠናትና ማዘጋጀት እንዲሁም የኢንቨስተሮችን አቅም በስልጠናና በልምድ ልውውጥ መገንባት
- የአገር ውስጥ አምራቾችንና ኤክስፖርተሮችን ሊያበረታታ የሚችል አገራዊ ጠቀሜታ ያለው የታክስ ስርዓት ማውጣት
- የልማት አንቀሳቃሽ የሆነውን የሰው ኃይል ልማት ስልጠና ትኩረት በመስጠት ማጠናከርና የሚሰጡ ስልጠናዎች ችግር ፈቺነታቸውን ማረጋገጥ
- መንግስት በሚያደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴ አርአያዊ አመራር መስጠት
- የመንግስት አካላትን ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን የሚያስፍን የአሰራር ዘዴ መቀየስ

3.2.2 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGO's)ሚና

- በክልሉ የገጠር ክፍል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባደረጉት የልማት ስራ ያፕዙትን ልምድ በመጠቀም ለከተማው ክፍልም ትኩረት መስጠት
- ሕብረተሰቡን በስፋት ያሳተፈ የልማት ፕሮጀክቶች ቀረፃ፣ ትግበራና ቁጥጥር ማስፈንና የሚሰራውን ስራ ለሕብረተሰቡ ግልፅ ማድረግ

CCRDA

- በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መ.ያ.ድ የሚተዳደሩበት መመሪያ (code of conduct)በክልል ደረጃ እንዲኖራቸውና በሰው ኃይል አቅም ግንባታ ሥራም ቢሳተፉ
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድግግሞሽን ያስወገደ ቅንጅታዊ አሰራር ከመንግስት ጋር በመተባበር እንዲንቀሳቀሱ
- ዘላቂነት ያለው የልማት ሥራ ላይ ማተኮር፣ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ በህብረተሰቡ በሚያስፈን፣ የልማት ሀብትን በመሳብና በሥራ ግምገማ ሂደት ሕብረተሰቡን በማሳተፍ የልማት አጋርነት ሚናን ማጠናከር

3.2.3 የሕብረተሰቡ ሚና

- ሥራን ባህል በማድረግ ሕገወጥነትን መቃወምና የልማት ችግር ፈቺነት ባህልን ማዳበር
- በተለያዩ የልማት ኃይላት በሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ በመመስረት የተረጂነት ስሜትን ማስወገድና በራስ ተነሳሽነት የልማት ሥራዎችን ማካሄድ
- ሕብረተሰቡ እንዲመሩት የመረጣቸውን የአመራር ወኪሎች የመከታተልና ከየመቆጣጠር ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት
- የጎሰኝነት ስሜትን በማጥፋት ወገናዊነትና ወንድማማችነትን ማበረታታት

3.3. በክልሉ ቀጣይነት ያለው ልማት በማካሄድ ድህነትን በአስተማማኝ ለመቀነስ በረዥም ጊዜ መወሰድ ያለበት የልማት ስልት በተመለከተ

3.3.1 በአጭር ጊዜ /በመጪው 5 ዓመት/

ሀ. በገጠር አርሶ አደር

- ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድግ የሚችል የመሬት አጠቃቀም ዘይን መፍጠርና የአካባቢ እንክብካቤ ትምህርት ማጠናከር
- በክልሉ ካለው የዝናብ አጠርነት የአየር ፀባይ አንፃር ጉዳቱን ለመቀነስ የሰብል ስብጥርን ማስፋት
- አርሶ አደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ የተሻሻለ የምርምርና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር
- ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑና በሽታን የመቋቋም ብቃት ያላቸው የሰብልና የእንስሳት ዝርያ አያያዝና አጠባበቅን ማጠናከር
- የመሬት ባለቤትነት ስሜት ለአርሶ አደሩ ለማጠናከር የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መፍጠር

ለ. በአርብቶ አደር

- የአርብቶ አደሩን አኗኗር መሰረት ያደረገ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መመስረት
- በሕብረተሰቡ ተሳትፎና ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ የተሻሻለ የአሰፋፈር ሂደት መመስረት
- ነባራዊ ልምዶችን ያካተተ የተሻሻለ የእንስሳት እርባታን ማስፋፋት

GCRDA

- አርብቶ አደሩ ከእንስሳቱ እርባታና ውጤቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆን የገበያ መሰረተ ልማትን ማጠናከር
- የተሻሻሉ የመኖ ዝርያዎችን ማስተዋወቅና ማስፋፋት እንዲሁም የእንስሳት ህክምና አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር

ሐ. በከተማ

- ኢንቨስትመንትን በማጠናከርና በማስፋፋት ስራ አጥነትን መቀነስ
- በክልሉ ያለውን የተማረ የሰው ኃይል በመጠቀም ውጤታማ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን መፍጠር
- ከፋብሪካዎች በተለያዩ ምክንያት የሚቀነሱ ሰራተኞችን በሴፍቲኔት ፕሮግራም ማደራጀት
- በአነስተኛ ንግድ ለሚተዳደሩ የምክር አገልግሎት ለመስጠት የአነስተኛ ንግድ አንተርፕራይዝ ኤጀንሲ ማቋቋም
- 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁም ሆነ ሌሎች ስራ አጦችን እንደዝንባሌያቸው ገቢ ሊያስገኙ በሚችሉ የሰራ መስኮች ማሰልጠንና የመንቀሳቀሻ ገንዘብ የሚገኝበትን መንገድ ማፈላለግ
- እየተዳከሙ ያሉትን ፋብሪካዎችን ለማጠናከርም ሆነ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በአጎራባች ክልል ያለውን የኮንትሮባንድ ንግድ መንግስት ከህብረተሰቡ ጋር ተቀናጅቶ መከላከል
- በኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ መቆጣጠርና መከላከል እንቅስቃሴ ዝምታውው ሰብረው ለወጡ የቫይረሱ ተጠቂዎች ድጋፍ ማድረግና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ጠንክሮ መንቀሳቀስ
- በተለያዩ የመንግስትና የህብረተሰቡ መነሻ ችግሮች ለተሰሩ ሕገወጥ የጨረቃ ቤቶች ሕብረተሰቡን ያሳተፈ መፍትሄ ማፈላለግ
- ፍትሀዊ የልማት አመራር ለመገንባት ከታችኛው እስከ ላይኛው ክፍል ሕዝባዊ አደረጃጀት ማጠናከርና አፈፃፀሙንም መከታተያ ስርዓት መመስረት
- የድሬዳዋ ከተማን ምክር ቤት መመስረት

3.2. በረዥም ጊዜ /በመጪው 20 ዓመት/

ሀ. በገጠር

- አነስተኛና ትላልቅ የውሀ ግድቦችን መገንባትና ዘላቂ የመስኖ ውሀ አጠቃቀም ዘዴ መቀየስ
- በክልሉ ሊኖር የሚችለውን የማዕድን ሀብት አዋጭቶ ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታን መፍጠር
- የገጠር ገበያና መጋቢ መንገዶችን በማስፋፋት ለሕብረተሰቡ የተሻለ አቅም መፍጠር
- ባህላዊ ተጽእኖዎችና ጎጂ ልምዶችን በሂደት መቀየር

CCRDA

ሰ. በከተማ

- የሕብረተሰቡን የአሰፋፈርና የሕዝብ ዕድገት ከግንዛቤ ያስገባ የመሰረተ ልማት አውታር መዘርጋት
- የሥራ አጥነት ምጥነትን መቀነስ
- የመኖሪያ ቤት ስራን ከሕዝብ ዕድገት ጋር በማገናዘብ ማስፋፋት
- የትምህርት ተሳትፎን በተለይ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎን ማሳደግ እንዲሁም የትምህርት ጥራትን ማሻሻል
- ሕጋዊነትንና ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን ማጠናከር
- በአገር አቀፍና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ክስተቶችን ለሕብረተሰቡ ለማዳረስ ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት

CCRDA

Final

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልላዊ መንግሥት
የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት
ክልላዊ ምክክር ሪፖርት

CCRDA

የሩይናንስና ኢኮኖሚ ልማት
ማስተባበሪያ ቢሮ
የካቲት 1994
አዋሳ

ማውጫ

ዝርዝር ገጽ

መቅድም

1. መግቢያ ---------- 1

1.1 አጠቃላይ ገፅታ ---------- 1

1.2 ኢኮኖሚና ማህበራዊ ገፅታ ---------- 2

2. የሰነድ ዝግጅትና ሂደት ---------- 3

3. ቅድመ የወረዳ ምክክር ዝግጅት ---------- 4

4. የወረዳዎች ምክክር ---------- 5

5. የክልል ምክክር ሂደት ---------- 12

6. የድህነት ሁኔታ በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ---------- 14

7. የሕዝቡ የኑሮ መሠረትና የሀብት አጠቃቀም ---------- 15

8. ድህነትና የድህነት መገለጫዎች ---------- 16

9. የድህነት መሠረታዊ መንስኤዎችና ተፅዕኖዎች ---------- 17

10. ድህነትን የሚያባብስ የልማዳዊ ባህላዊ ተፅዕኖዎች ---------- 19

11. ድህነትን ለመቅረፍ ባለፉት 5ዓአመታት የተወሰዱ እርምጃዎች ---------- 18

12. አስተዳደራዊ መዋቅሮችና የልማት መ/ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎትና ያሉ ችግሮች- 22

13. ድህነትን ለመቀነስ ወደፊት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችና በየደረጃው ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ---------- 28

14. የመረጃ ግኝቶች ---------- 39

ዕዝሎች

CGRDA

መቅድም

የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሠነድ/PRSP/ የአንድ ሀገር ብሔራዊ ፕሮግራም ነው ፕሮግራሙም ድህነት ለመቀነስ የሚነደፍ ነው የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሠነድን ማዘጋጀት ያስፈለገው ዓለም ዐቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) እና የአለም ባንክ (World Bank) ለአንድ ሀገር ለልማት ተግባር የሚውል ብድር የሚሰጡት በዛ ላይ ተመሥርተው በመሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በእነዚህ ተቋማት አስተባባሪነት ከፍተኛ የውጭ ዕዳ ላለባቸው አገሮችም የዕዳ ቅነሣ ውሳኔ የሚደረገው በዚሁ ሰነድ ይዘት፣ ጥራትና ብቃት መሠረት በመሆኑ ነው።

የክልላችን የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሰነድን ባካተተ መልኩ ሀገራችንም ከ1994-1997 ላሉት ሦስት ተከታታይ አመታት የሚያገለግል የድህነት ማቃለያ ስትራቴጂ በመቅረፅ ላይ ትገኛለች የስትራቴጂው ሠነድ በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ነው። እነርሱም ድህነት ቅነሣ ላይ ማተኮሩና የዝግጅቱ ሂደት ሰፊ የሕዝብ ተሣትፎ የሚያንፀባረቅ መሆኑ ናቸው። እንደሚታወቀው በብሔራዊ ደረጃም ሆነ በክልላችን ባለፉት ዘጠኝ አመታት ተነድፈው በመተግበር ላይ ያሉ የልማት ስትራቴጂዎች ፖሊሲና ፕሮግራሞች ድህነትን በመቅረፍ ላይ ያተኮሩ የነበሩ በመሆናቸው አሁን የሚቀረፀው ስትራቴጂ ደግሞ ሰፋ ያለና የነበረውን ጅምር ጥረት አጠናክሮ የሚቀጥል እንደሚሆን ይታመናል።

በድህነት ማቃለያ ስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት በሕዝቡ ተሳትፎ የመነጨውን የወረዳ ምክክርን ፍሬ ሀሳብ ውጤታማ እንዲሆን የ18ወረዳዎችን መረጃ መሠረት በማድረግ የክልሉ የድህነት ሁኔታን፣ መንስኤዎችን የልማት ፍላጐት ቅደም ተከተልና ወደፊት መወሰድ ስላለባቸው መፍትሄዎች በተመለከተ የተለያዩ የህብረተሰብ ተወካዮችን ባሳተፈ ሁኔታ በክልል ምክክር ዐውደ ጥናት ዳብሮ ቀርቧል። ስለዚህም በወረዳ ዳረጃና በአማሮ ኢኮሎጂ ክፍፍል መሠረት የተዘጋጁት ሪፖርቶች በገጠርዝር ለሚቀረፀው የድህነት ማቃሊያ ስትራቴጂ መነሻ መረጃ እንደሚሆኑ ይታመንበታል። በተጨማሪ ይህ በወረዳና በክልል ደረጃ የተዘጋጀ ማጠቃለያ ሪፖርትም ድህነትን ለማቃለል የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታን መሠረት በማድረግ ሕዝብን በሳተፈ መልኩ ወደፊት መወሰድ ስላለባቸው መፍትሄዎችና የልማት አቅጣጫዎች ይጠቁማል።

CCRDA

1. መግቢያ

1.1 አጠቃላይ ገጽታ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በአገሪቱ ከሚገኙ ዘጠኝ የክልል መንግሥታት አንዱ ነው። ክልሉ በደቡብ ከኬንያ በደቡብ ምዕራብ ከሱዳን ሪፐብሊክ ሲዋሰን በሀገር ውስጥ በምሥራቅ፣ በሰሜንና ሰሜን ምዕራብ የኦሮሚያ በምዕራብ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ያዋስኑታል። የክልሉ የቆዳ ስፋት 113539 ካሬ ኪ.ሜትር ሲሆን ይህም የአገሪቱን 10 በመቶ ይሸፋናል። በአየር ንብረት ቀጣና ሲከፋፈልም 8.4 በመቶ ደጋ 33. 9 በመቶ ወይናደጋና 57.5 በመቶ ቆላማ ነው። በአስተዳደራዊ ክፍፍሉም በ13 ዞኖችና በ8ልዩ ወረዳዎች ተከፋፍሏል። በአጠቃላይም 96 ወረዳዎችና 8ልዩ ወረዳዎች አሉት። ክልሉ ከሌሎች የሚለይበትም የራሳቸው ባህልና ቋንቋ ያላቸው ከ56 በላይ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በህብረት የሚኖሩበት በመሆኑ ነው። የክልሉ አጠቃላይ ሕዝብ ብዛት እ.አ.አ.በ2000 12.9 ሚሊዮን እንደ ነበር ሲገመት ከሀገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ 21 በመቶ ድርሻ አለው ። ካለው ሕዝብም 92.2 በመቶው የገጠርና ቀሪው 7.8 በመቶው የከተማ ነዋሪ ነው። በአሠፋፈርም 70 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ሕዝብ 42 በመቶ በሚሆነው የክልሉ (Highland areas) ደጋና ወይናደጋማው አየር ንብረት ቀጠና ሲኖር ቀሪውን 30 በመቶ የሚሆነውን የክልሉን የቆዳ ስፋት የሚሸፍነው ሕዝብ 58 በመቶ በሚሆነው በቆላማው (Low land areas) ክልል የሚኖር ነው።

የክልሉ ሕዝብ ኑሮ የተመሠረተው በእርሻና በጥምር ግብርና ነው የተለያየ የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት በመኖሩ ልዩ ልዩ ጥራጥሬ እህል፣ እንሰት፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የቅባት እህልና ቡና ይመረታል። በተለይም የቡና መገኛ ክልልም በመሆኑ 40 በመቶ የሚሆነው የኤክስፖርት ቡና ወደ ውጭ ገበያ የሚቀርበው ከዚሁ ክልል ነው። ክልሉ በተፈጥሮ ሀብት የታደለ በመሆኑ በገፀምድርና በከርሰምድር የውሃ ሀብት (ወንዞችና ሃይቆች)፣ የተፈጥሮደን የተለያዩ የዱር እንስሳትና ድንቅ አዕዋፋት መገኛ ነው። ከሕዝቡ ኢኖኗርና ባህል በተጨማሪ የማጐ፣ የኦሞና የነጭ ሣር ብሔራዊ ፖርኮች ዋነኛ የቱሪስት መስህብ ናቸው። ምንም እንኳን ክልሉ በተፈጥሮ የታደለና እምቅ ሀብት ቢኖረውም በበርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ምክንያት የተነሳ የተጠበቀውን ያህል የተፋጠነ ልማት ማምጣት አልተቻለም።

CCRDA

1.2 ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገፅታዎች

ከክልሉ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 54.9 በመቶ የሚሆነው የእርሻ መሬት (የታረሰና ሊታረስ የሚችል) ቢሆንም ክልሉ በምግብ ራሱን ለመቻል በገጠር ልማት ዘርፍ ገና ብዙ መስራት ይጠበቅበታል አብዛኛው የገጠሩ ነዋሪ ሕዝብ በደጋና በወይናደጋማው ከፍታማ አካባቢዎች የሚኖር በመሆኑም ከፍተኛ የመሬት ጥበት ይታያል:: ከክልሉ አርሶ አደሮችም 62.9 በመቶው ከአንድ ሄ/ር በታች የእርሻ መሬት ሲኖራቸው ቀሪዎቹ 37.1 በመቶ የሚሆኑት ከ1.1-2. ሄክታር መሬት ብቻ ያላቸው ናቸው:: በተጨማሪ 54.7 በመቶ አርሶ አደሮች ምንም በሬ የሌላቸው ሲሆኑ 31.2 በመቶው አርሶ አደሮች አንድ በሬ ብቻ ያላቸው ናቸው::

ስለዚህም አብዛኛው ሕዝብ ኑሮውን በድህነት የሚገፋ ነው:: በምርትና ምርታማነት ዝቅተኝነት፣ በተደጋጋሚ በሚከሰተው ድርቅና በሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ በተፈጥሮ ሀብት ላይ በሚደርሰው መመናመንና የበረሃማነት መስፋፋት ምክንያት ሕዝቡ ለምግብ ዕጥረት የተጋለጠ ሆኗል:: በመሬት ጥበትም ምክንያት ሕዝቡ ወደ ከተሞች በመፍለስ የሥራ አጥነት ችግር እየተባባሰ መጥቷል:: በአየር መዛባት ሳቢያ በተከሰተው ተደጋጋሚ ድርቅ በ1992ዓ/ም ብቻ በክልሉ ለምግብ ዕጥረት ተጋላጭ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ከአጠቃላዩ ነዋሪ ሕዝብ 11በመቶ ያህል ደርሶ ነበር ::

የችግሩ ምክንያትና ስፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በድህነት የሚኖረው ሕዝብም በየጊዜው እየጨመረ ሊመጣ ግድ ሆኗል:: በክልላችን ከሚኖረው አጠቃላይ ሕዝብ መካከል 56.5 በመቶ ያህሉ ከድህነት ወለል (Poverty line) በታች ኑሮውን በመምራት ላይ እንደሚገኝ አንዳንድ የጥናት ውጤቶች ያመለክታሉ:: ባለፉት አመታት የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመፍታት በተደረገው ጥረት የግብርና ልማትን ለማስፋፋት 30 በመቶ የሚሆነው አርሶአደር በኤክስቴንሽን ፖኬጅ እንዲሣተፍ ተደርጓል፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ 60.3 በመቶ፣ የጤና ሽፋን 50 በመቶና የመጠጥ ውሃ ሽፋን 28በመቶ ሊደርስ ችሏል:: ምንም እንኳን በመንግስት፣ በለጋሽ ድርጅቶች፣ በግሉ ኢንቨስትመንትና በመያድ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የልማት እንቅስቃሴ ቢደረግም የተፋጠነ ዕድገት ለማምጣት፣ ግን አልተቻለም:: ለዚህም ምክንያቱ 89 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ሕዝብ የሥራ ላይ ስምሪት ዘመናዊ ባልሆነ የእርሻ ሥራ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ነው::

CGRDA

ከዚህም ሌላ በሕዝብ ቁጥር መጨመርና በተለይም በገጠር በቂ የመሠረተ ልማት መቀቅር ባለመዘርጋቱና ተደጋጋሚ ድርቅ በመከሰቱ፣ ለከተሞችም ከህዝቡ ብዛት ጋር የተመጣጠነ አገልግሎት ካለመቅረቡ የተነሳ በተፈለገው መጠንና ፍጥነት የህብረተሰቡን ህይወት መለወጥ አልተቻለም::

እንደሚታወቀው በክልሉ የተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት መንግሥት ባለፉት አመታት ባወጣው የልማት መርሐ ግብር ህብረተሰቡን በማሣተፍ፣ የመያድ የልማት እገዛንና የግሉን ሴክተር በማሳተፍ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን የማካሄድ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል:: በክልሉ ሴክተር የሚቀጥለው የሁለተኛው የመካከለኛ ዘመን /1993-97/ የአምስት አመት የልማት መርሃ ግብር የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞች ተነድፈው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ናቸው:: መንግስትም ብሔራዊ ልማትን ለማፋጠን የኢትዩጵያ ጊዜያዊ የድህት ማቃለያ ስትራቴጂ /1993-95/ ሰነድ አዘጋጅቶ ለአለም ባንክና ለአለም የገንዘብ ድርጅት በማቅረብ ሀገሪቱ የዕዳ ስረዛ ዕድል እንድታገኝ በማድረግ ላይ ነው :: በዚሁ መሠረት ለዋናው የህገሪቱ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ብሔራዊ ሰነድ ዝግጅት መረጃ ሊሆን የሚችል ከክልላችን የሚጠበቀው የድህነት ማቃለያ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ተጀምሮ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል::

2. <u>የሰነዱ ዝግጅትና ሂደት</u>

2.1 የሰቲሪንግና የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲሁም የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ነሐሴ 1994ተቋቋመ::

2.1.1የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላት

ሀ/ የክልሉ ም/ቤት የኢኮኖሚ ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ-በአሁኑ ወቅት የገንዘብና ኢኮኖሚ ማስተባበሪያ ቢሮ ሃላፊ	ሰብሳቢ
ለ/ የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ	አባል
ሐ/ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ	አባል
መ/ የንግድ ኢንዱስትሪ ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ	አባል
ሠ/ የገጠር መንገዶች ባለስልጣን ሥራ አስኪያጅ	አባል
ረ/ የጤና ቢሮ ኃላፊ	አባል
ሰ/ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ	አባል
ሸ/ የሴቶችጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ	አባል
ቀ/ የግብርና ቢሮ ኃላፊ	አባል
በ/ የግብርና ምርምር ሥራ አስኪያጅ	አባል
ተ/ የኢማተልፊ ስራ አስኪያጅ	አባል

CCRDA

ሲሆን የስቲሪንግ ኮሚቴ ዋና ተግባር ሥራውን በበላይነት መቆጣጠርና ለቴክኒክ ኮሚቴው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ነው::

2.1.2 የቴክኒክ ኮሚቴና የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት

2.1.2.1 የቴክኒክ ኮሚቴው ሰብሳቢ የፕላንና ኢኮኖሚ ቢሮ ኃላፊ ሲሆኑ ሌሎች አባላት በስቲሪንግ ኮሚቴ ስር ከተዘረዘሩ መቤቶች አንዳንድ ባለሙያች የተውጣጡበተ ነው::

2.1.2.2 የቴክኒኮ ኮሚቴ የሥራ ድርሻ ውይይቱ የሚካሄድባቸውን ሂደቶች ማቀድ ማካሄድና ሪፖርትም ማድረግ አጠቃላይ የቴክኒክ ድጋፎችን መስጠት ነው::

2.1.2.3 የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት አንድ ዋናና ሶስት ረዳት አስተባባሪዎች ያሉት ሲሆን ሁሉም የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ባለሙያዎች ናቸው::

2.1.2.4 የሴክሬታሪያቱ የስራ ድርሻ የጽህፈት ስራዎች ጨምሮ የዕለት ተዕለት ስራዎችን ማከናወንና በጀትን ማስተዳደር የሚፈለገውን መረጃ ለፈጸራሉ ማስተላለፍ የመሳሰሉት ናቸው::

3 . ቅድመ የወረዳ ምክክር ዝግጅት

3.1 የቴክኒክ ኮሚቴው በደብረዘይት ማኔጅመንት ተቋም በተካሄደው አገረ አቀፍ አውደጥናት ተካፍሏል:: በዚህ ሴሚናር ላይ ድህነትን አስመልክቶ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች የቀረቡ ሲሆን ከዚህም ሌላ ውይይቶች ስለሚካሄዱባቸው አጠቃላይ ሁኔታዎች ስምምነት ተደርሷል:: ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የወረዳዎች ቁጥርና የሚመረጡበት መስፈርት፣ የተሳታፊዎች ቁጥርና ምን ያህል ከየተኛው ህብረተሰብ አካል ይሁን? ውይይቱ የት ቦታ ይካሄድ? እና ለስንት ቀናት ወዘተ የሚሉ ናቸው:: ከዚህ ቀጥሎ ሶስት ሶስት ባለመያዎችን ያቀፈ አራት ቡድን በነሐሴ መጨረሻ የመሰክ ስምሪት አድርጓል:: የዚህ ስምሪት ዋና ዋና ተግባራት

3.1.1 በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት አስቀድሞ በቴክኒክ ኮሚቴው የተደረገውን የወረዳ ምርጫ ከዞን ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ማጽደቅና ስለ ሰነዱ ለሚመለከታቸው አካላት ገለጻ ማድረግ

3.1.2 ከትምህርት ከጤናና ከግብርና ሆኖ በየወረዳው አንድ አወያይና ሁለት ራፖርተሮች ማስመረጥ

3.1.3 የውይይት ሰነድ አንድንና ሰነድ ሁለትን ማሰራጨትና ቀጥሎ በክልሉ የአወያዩችና የራፖርተሮች ስልጠና እንደሚደረግ አሳውቆ ዝግጅት እንዲያደርጉ በመግለጽ መመለስ ነበር::

CCRDA

3.2 በቡድኑ ሪፖርት መሠረት የተመረጡት ወረዳዎች 18 ሲሆኑ 6 ክፍፍል አላቸው

ሀ/ የወጪ ምርት የሚያመርቱ /አለታወንዶ አማሮ ወናጎና የኪ/

ለ/ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለባቸው /ሸበዲኖ ዳሞት ጋሌ አንጋጫና የም/

ሐ/ በቂ ዝናብ የሚያገኙና እህል አምራች /ሊሞ ጨንቻና ገዋታ/

መ/ ዝናብ አጠር እህል አምራች /ዳሎቻ ቸሃና ሎማ/

ሠ/ በተደጋጋሚ በድርቅ የሚጠቁ /ኮንሶና ሁምቦ/

ረ/ አርብቶ አደር አካባቢዎች /የሐመርና ሱርማ /ወረዳዎች ናቸው::

3.3 መስከረም 25-27 ላይ የአወያዮችና ራፖርተሮች ስልጠና ለሶስት ተከታታይ ቀናት ከየወረዳው ሶስት ሶስት በአጠቃላይ 54 ሠልጣኞች ተካፍለዋል:: ሥልጠናው የተሰጠው ከፌደራልና ከክልል ቴክኒክና ሴክሬታሪያት በጋራ ነው ::

የዚህ ስልጠና ይዘት የሚሆነው:-

ሀ/ የድህነት አጠቃላይ ጽንስ ሃሳብን በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጥና እንዲሁም ጎላባሉ የትምህርት የጤና የግብርና የመንገድ የሴቶች ጉዳይን በመሳሰሉት ጥናታዊ ጽሁፎች በማቅረብ መወያየት

ለ/ ለእያንዳንዱ ወረዳ ምክክር የመወያያ አጀንዳዎችን በየራሱ አወያዩችና ራፖርተሮች አስቀርጾ በቡድን ውይይት ማዳበር

ሐ/ ከተለያየ የህብረተሰብ ክፍል የመጡትን ከማወያየት አንጻር ከአወያዩች የሚጠበቁ ሁኔታዎችን ወደ አንድ ሃሳብ ማምጣት የሁሉን ተሳትፎ ማረጋገጥ በጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማወያየት ወዘተ? ማስገንዘብን ያካተተ ነበር::

3.4 ከስልጠናው በኃላ ስለተሳታፊዎች አመራረጥ በየተመረጡት ወረዳዎች በአወያዩችና ራፖርተሮች እንዲሁም በምክር ቤት ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት በሌላ በኩል በሴክሬታሪያቱና በክልል ቴክኒክ ኮሚቴው በኩል ለወረዳው ምክክር የቅድመ ዝግጅት ሲከናወን ነበር::

ከዚህ ቀጥሎ እንደተለመደው ሶስት ባለሙያዎችን ያቀፈ አራት ቡድን በአራት ማዕከሎች ለቅስቀሳ ስራ (Senstization) እና ሃምሳ ተወያዮች መረጣን ሂደት ለመከታተል እንዲሁም የአወያዮች ወደየማዕከላቱ የሚጓጓዙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው ::

የአወያዮችን ስብጥር ስንመለከት ዕድሜን ጾታን የስራን ዓይነት (Occupation) ከግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ እናገኘዋለን:: ከአንድ ወረዳ ከ50ው ቢያንስ 30 ከመቶው ሴቶች እንደገና ከ50ው ከ30 እስከ 35 የሚሆኑት ከህብረተሰቡ ማለትም ገበሬዎች ነጋዴዎች አሣውንቶች የቤት እመቤቶች ሥራ አጥ ወይም ተማሪ ወጣቶች የተመረጡ ሲሆን ቀሪው

CCRDA

ከ10 እስከ 15 የተመረጠው ከመንግስት መስሪያቤቶች የሃይማኖት ድርጅቶችና መንግስታዊ ካልሆኑ አገር በቀልና ውጭ ድርጅቶች የተውጣጡ ናቸው::

ጋህ ተግባር በሶስት ቡድኖች የአንድ ሳምንት ተግባር ሲሆን ወደ ጂንካና ወላይታ አካባቢ ለተሰማራው ቡድን ሁለት ማዕከልና ስድስት ወረዳዎች ስለነበር እጥፍ ጊዜ ወስዶበታል::

4. የወረዳዎች ምክክር

4.1 የወረዳ ምክክር ከጥቅምት 12 እስከ 14 በዲላ የአለታወንዶ ሸበዲኖ አማሮና ወናጎ ወረዳዎች፣ በሆሳእና የአንጋጫ ሊሞ ዳሎቻ ቸሃና የም ወረዳዎች በሚዛን የሱርማ የኪና ገዋታ ወረዳዎች በጂንካ የሀመር ወረዳ ከጥቅምት 19 እስከ 21 በሶዶ የኮንሶ ጨንቻ ሎማ ሁምቦና ዳሞት ጋሌ ወረዳዎች በተናጠል ተካሂዷል:: የምክክሩ ሂደት ሙሉ በሙሉ የተሳካ አንደነበር ታዛቢዎች ጭምር የመሰከሩት ነው :: በተለይም ሴቶች ተሳተፎአቸው ከባህል ተጽዕኖው የተነሳ ያንሳል ተብሎ የታሰበው ሳይሆን የጎላ ተሳትፎ ሲያደርጉ ተስተውሏል::

የምክክሩ ሒደት በቪዲዮ ካሴትና በቴፕ ካሴትና በጽሁፍ ተቀድቷል :: በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች ውይይቱ በየብሄረሰቡ ቋንቋ የተካሂደ ነው ::

4.2 የወረዳ የምክክር አጀንዳዎች

ሀ/ የድህነት ምንነት ከወረዳው ተጨባጭ ሁኔታና ከህዝቡ የህይወት ልምድ አንጻር በህብረተሰቡ አንዴት ይገለጻል መለኪያዎቹስ ምንድናቸው::

ለ/ ህብረተሰቡ በአጀንዳ አንድ ላይ ድህነትን ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን መለኪያዎች መሰረት በማድረግ ድህነት ባለፉት ዓመታት ምን ይመስላል?

ሐ/ ለድህነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ምክንያቶች በቅደም ተከተል ቢገለጽ

መ/ የህዝቡ ኑሮ /livelihood/ የተመሰረተው በምን ላይ ነው ከዚህ አንጻር ያሉት መስረታዊ ችግሮችና ይህንን ለመቅረፍ በህብረተሰቡ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተወሰዱና ወደፊት ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድናቸው?

ሠ/ ድህነትን በመቀነስ የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በማህበራትና በህብረተሰቡ የተወሰዱ እርምጃዎች ምን ይመስሉ ነበር?

ረ/ በወረዳው የሚገኙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋሞች ለህብረተሰቡ እየሰጡ ያሉት አገልግሎተ ምን ይመስላል ችግሮች ካሉ ቢገለጽ

CGRDA

ቀ/ ድህነትን የሚጋበዙ ባህላዊ፣ ሃማኖታዊና የግል ባህሪያት ምንድናቸው?

በ/ በተለያየ ደረጃ ያሉ አስተዳደራዊ መዋቅሮች ለህብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምን ይመስላል? ምን ችግር አለ?

ተ/ የኤች አይቪ ኤይድስ እያስከተለ ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ምን ይመስላል? ለድህነት የሚዳርገው አስተዋጽኦስ ምን ያህል ነው? የሚሉ ናቸው::

በክልሉ ምክክር በተካሄደባቸው 18 ወረዳዎች ከእያንዳንዳቸው አምሣ አምሣ በአጠ ቃላይ 900 ተሳታፊዎች በ5ዞን ማዕከላት (በአርባምንጭ፣ በዲላ ፣በጂንካ፣ በሆሣዕናና በሚዛን ተፈሪ) እንዲሠባሰቡ ታቀዶ በምክክር ስብሰባው ላይ ግን በአጠ ቃላይ 935 ሰዎች ሊሳተፉ ችለዋል:: በዚህም ከመንግስት ሠራተኛ 280፣ ከህብረተሰብ 609፣ ከመያድና ከግል ድርጅቶች 46 ተሳትፈዋል:: በዚህም ከአጠ ቃላዩ ተሰብሳቢ 65 በመቶ የሚሆኑት የገጠርና የከተማ የድህነት ተጠቂ ህብረተሰብ ተወካዮችን ቁጥር ለማብዛት ተሞክሯል::

በሌላ በኩል በሰነድ ዝግጅቱ ተሳትፎአቸውን ለማሣደግ በተደረገው ጥረት ሴቶች 25.2 በመቶ ድርሻ እንዲኖራቸው ተደርጓል:: ምክክር በተካሄድባቸው ወረዳዎች ስብሰባውን በታቀደው ሁኔታ ለመምራት የሚችሉ ከመንግስት መሥሪያ ቤቶች 54 ባለሙያዎች (18 አወያዩችና 36 ራፖርተሮች) ተመርጠው የነበረ ሲሆን በስብጥራቸውም 30 የግብርና 8ቱ የትም/ት እና ስድስቱ የጤና ባለሙያ ናቸው:: በየታም ረገድ ከአጠቃላዩ 46 ወንዶችና 8 ሴቶች ነበሩ::

በክልሉ የደህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ሂደት ከወረዳ ጀምሮ ሕዝቡን፣ በተለይም ደሀውን ህብረተሰብ ተሣታፊ በማድረግ የህይወት ልምዱን መሠረት ያደረገና ከድህነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቁልፍ መረጃዎችን ለማስባሰብ ተችሏል:: በሰነዱ ዝግጅትም በክልሉ ያሉ የመንግስት፣ መያድ፣ ሲቪል ማህበራት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚና ለጋሾች ጥረታቸውን አቀናጅተው በድህነት ማቃለል ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ በመንደፍ ውጤታማ የልማት ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ ታቅዷል::

ከፌደራል የድህነት ቅነሳ ስት/ሴክ/ጽ/ቤት የመጣውን የወረዳዎችን የምክክር ፕሮግራምና ጊዜ ለመጠበቅ ከተደረገው ጥረትና ከዞኖችና ወረዳ መስተዳድሮች ጋር ከተደረገው ቅንጅታዊ ሥራ አኳያ አብዛኛው የሥራው ሂደት የተሣካ እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል::

CGRDA

ይሁን እንጂ ክልሉ ካለው የቆዳ ስፋት አንፃርና የተመረጡትም ወረዳዎች ከሁሉም ዞኖችና በከፊል ከተወሰኑ ልዩ ወረዳዎች ስለነበር በሥራ ሂደት ላይ መጠነኛ ችግሮች ነበሩ::

ከነዚህም:-

1. አንዳንድ ወረዳዎች የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሉት የማይሰጥባቸው ስለነበሩ ሕዝቡን በአይሱዙ የጭነት መኪና ለማጓጓዝ ሁኔታዎች ማስገደዳቸው፣
2. ለምክክሩ ተሳታፊዎች የተዘጋጁ የመወያያ ሰነዶች ዕጥረት መከሰቱ፣
3. ከመንግስት መሥሪያ ቤት ተወክለው በምክክሩ ለመሣተፍ የመጡ ተሰብሳቢዎች አበላቸውን ለመክፈል የሚያስችል መረጃና ከመጡበት መ/ቤት ደሞዛቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ ባለማቅረባቸው በአስተባበሪዎች ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደራቸው የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው::
4. የአዳራሽ ግኝት ችግር ነበር

4.3 ከምክክሩ ሂደት በኃላ ከተያዘው ቃለጉባኤና መረጃ በመነሣት ወጥ በሆነ ቅደም ተከተልና ቅጽ መሰረት አወያይና ሪፖርተሮች በቲክኒክ ኮሚቴዎቹ ሙሉ ድጋፍ የእያንዳንዱ ወረዳ ሪፖርት በተናጠል የተዘጋጀ ሲሆን ከነዚህ ሪፖርቶች በመነሳት እንደገና በቲክኒክ ኮሚቴ አባላት በአግሮኢኮሎጂ ክፍፍል መሰረት 6 ጥራዝ የምክክር ሪፖርት ተሠርቷል

እነዚህም:-

1. የወጪ ምርት አምራች ወረዳዎች
2. ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለባቸዉ ወረዳዎች
3. በቂ ዝናብ የሚያገኙ ወረዳዎች
4. ዝናብ አጠር ወረዳዎች
5. በተደጋጋሚ ድርቅ የሚያጠቃቸዉ ወረዳዎች
6. የአርብቶ አደር ወረዳዎች ናቸው

በመጨረሻም ለክልሉ ምክክር የሚቀርብ 22ገፅ ያለው የማጠቃለያ ሪፖርት /Executive Summary report/ ተዘጋጅቷል:: ይህም የወረዳው ግኝቶች በክልሉ ምክክር ዐውደ ጥናት እንዲዳብር ተደርጓል ::

CCRDA

5. የክልል ምክክር ሂደት

በክልል ምክክር ሂደት የተያዘዉ ፕሮግራም የሚሳተፉት መንግሥታዊ፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና እንዲሁም ማህበራዊ ተቋማትን የወከሉ ናቸዉ :: ከመንግስት አካላት የሚሳተፉት ከ13 ዞኖች የአስተዳደር፣ የሴቶች ጉዳይ፣ የልማት ማህበራት፣ የሩይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ሲሆኑ ከ8ልዩ ወረዳዎች ደግሞ የመስተዳድር፣የሴቶች ጉዳይና የልማት ማህበራት ተወካዮች ተጋብዘዋል:: ቀድሞ በወረዳ ምክክር ወቅት ከ18ወረዳዎች አወያይና ራፖርተር የነበሩ፣ ከክልል መስሪያ ቤቶች ደግሞ ሁሉም የማስተባበሪያ ቢሮዎች ሀላፊዎች ከአስፈጻሚ ሴክተር የቢሮዎችና የጽ/ቤቶች ተወካዮች ኃላፊዎች በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሀላፊዎች ሌሎች ከሲቪል ማህበራት፣ ከልማት ማህበራት፣ ከሃይማኖት ድርጅቶች ፣ ከኢንቨስተሮች ፣ ከጎጋዴዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች የተውጣጠ ናቸዉ::

በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ሁለት ቅናት በአጀንዳው በተመለከተው መሠረት ምክክር ከተካሄደ በኃላ ተሳታፊዎች በ4ቡድን ተከፍለው በተቀመጠው የመወያያ አጀንዳ ተወያይተው በ3ኛው ቀን ለአንድ ላይ በመሰብሰብ የደረሰብትን ነጥብ በሪፖርት በማዘጋጀት አቅርበው ሰፊ የሀሳብ መንሸራሸር ተደርጉ የወረዳውን የምክክር ግኝት በዳበረ መልኩ የምክክር ስብሰባው ተጠናቋል::

CGRDA

5.1 ለክልል ምክክር የወጣ የስብሰባ ፕሮግራም

በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልላዊ መንግስት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት (PRSP)

(የክልል ምክክር የጊዜ ሰሌዳ)

ቀን	ሰዓት	እርዕስት /ፕሮግራም ዓይነት/	አቅራቢ	አወያይ
30/5/94	2:30-3:00	ይተሳታፊዎች ምዝገባ	-	ክልል ሲክሬታሪያት
	3:00-3:05	ፕሮግራም ማስተዋወቅ	አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል	-
	3:05-3:15	ይመንሺያ ንግግር	አቶ ጌታቸው ሀሞሳ	አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል
	3:15-3:30	ይመክፈቻ ንግግር	አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ	አቶ ጌታቸው ሀሞሳ
	3:30-3:45	ይኢትዮጵያ የድቅስሰ ዝግጅት መሠረት ሀገብ	አቶ ሮማኮንን ማንያዘዋል	አቶ ያዕቆብ ዙላ አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል
	3:45-4:00	ይደ/ብ/ህ/ሕ/ክ/መ ድህነትና ድቅስሰ ዝግጅት ሂደት	ወ/ሮ ሮማን ጎንስፋዬ	ወ/ሮ ሮማን ተስፋዬ
	4:00-4:20	የሻይ እረፍት	-	መስተንግዶ ኮሚቴ
	4:20-4:40	ሀ/የወረዳ ምክክር ግኝቶች ማጠቃለያ	አቶ እበበ መንገሻ	አቶ ያዕቆብ ዙላ አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል
	4:40-6:30	ውይይት	-	በተሳታፊዎች
	6:30-8:00	ምሳ	-	በግል
	8:00-8:30	ይወረዳዎች ምክክር ቪዲዮ ማሳየት	-	ክልል ሲክሬታሪያት
	8:30-8:50	ለ/የወረዳ ምክክር ግኝቶች ማጠቃለያ	አቶ ግርማ በቀለ	አቶ ያዕቆብ ዙላ አቶ ተስፋዬ ወ/ሚ
	8:50-9:05	ሐ/ የሲቪል ማህበረሰብ የምክክር ግኝቶ	አቶ ግርማ ተጉ	አቶ ተስፋዬ ወ/ሚ ናአቶ ያዕቆብ ዙላ
	9:05-10:00	ውይይት	-	-
	10:-10:20	የሻይ እረፍት	-	-
	10:20-11:30	ውይይት	-	በተሳታፊዎች
1/6/94	2:30-3:00	ይወረዳዎች ምክክር ቪዲዮ ማሳየት	-	-
	3:00-4:00	ከድኅሶት ሁኔታ ጋር የተያያዙ ጥናታዊ ጽሑፎች	አቶ ተመልዴ	አቶ ያዕቆብ አቶ ተስፋዬ ወ/ሚ
	4:00-4:30	ውይይት	-	-
	4:30-4:50	የሻይ እረፍት	-	በመስተንግዶ ኮሚቴ
	4:50-6:30	ብክለል የተካሄዱ የልማት ሥራዎች፣ ሙሰቤቶች ችግርና ይመፍትሔ ርምጃዎች	አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል	አቶ ያዕቆብ ዙላ
	6:30-8:00	ምሳ	-	በግል
	8:00-8:30	ቪዲዮ	-	-
	8:30-10:00	ውይይት	-	-
	10:00-10:20	ሻይ እረፍት	-	በመስተንግዶ ኮሚቴ
	10:20-10:30	ዘ/ውይይት ለ/ የቡድን ምስረታ አካሄድ ሐ/ ሰብሳቢና ራፖርተሮች መረጣ	-	በተሳታፊዎች
2/6/94	2:30-5:30	የቡድን ውይይት	-	በየቡድኑ
	5:30-6:30	የቡድን ሪፖርት ይቀርባል	-	-
	6:30-8:00	ምሳ	-	በግል
	8:00-11:00	የቡድን ውይይት በጋራ	-	-
	11:00-11:30	ይመዝጊያ ሥነስርአት	-	-

CCRDA

5.2 የስብሰባው አጀንዳ

1. የኢትዮጵያ የድቅስሰ ዝግጅት መሰረተ ሀሳብ
2. የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ድህነትና ድቅስሰ ዝግጅት ሂደት
3. የወረዳ ምክክር ግኝቶች ማጠቃለያ
4. የሲቪል ማህበረሰብ የምክክር ግኝቶች
5. የቡድን ውይይት ድህነትን ለመቀነስ በቀጣይ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች
   5.1 በኢኮኖሚና በማህበራዊ ልማት ዘርፍ ወደፊት መሰራት ያለባቸው ሥራዎች
   5.2 ሠላም ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ለማስፈን ወደፊት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች
   5.3 የመያድ ግሎ ክፍለ ኢኮኖሚ ሲቪክ ማህበራት የልማት ማህበራት ድህነትን ለመቀነስ የሚያደርጉት አስተዋጽያ
   5.4 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሐይማኖት ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች በድህነት ቅነሳው የሚያደርጉት አስተዋጽያና የወደፊት ተሳትፎ እንዲሁም ልማዳዊና ባህላዊ ተጽዕኖዎች ማስወገድ የሚያበረክተው አስተዎጽያ

5.3 የክልል ምክክር ተሳታፊዎች ሁኔታ

በክልሉ ምክክር ጉባኤ የተጋበዙ ተሣታፊዎች በአጠቃላይ 250 ነበሩ ይሁን እንጂ በስብሰባው የተገኙት 197 ብቻ ናቸው ከነዚህ ውስጥም 45 ተሣታፊዎች ከዞኖችና ከልዩ ወረዳዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ከክልል ቢሮዎች፣ 49 ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ናቸው:: የተሣታፊዎችም ስብጥርም ከመንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች 130 ከመያድና ሲ/ማህበራት 26፣ ከልማት ማህበር10 ከኤምባሲዎችና ከታዛቢዎች7 ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት 8 ከግሉ ክ/ኢኮኖሚ 10ና ከሌሎች6 ናቸው:: በፆታ ስብጥርም ሲታይ 19 ሴቶችና 178 ወንዶች ናቸው::

5.4 አጠቃላይ የክልሉ የምክክሩ ሂደትና ያጋጠሙት ችግሮች

ሀ. ከስብሰባው ማዕከል የልዩ ወረዳዎች የቦታ እርቀት መኖሩ

ለ. የስብሰባው ፕሮግራም ከጊዜ አንጻር መጣበብና አንዳንድ አጀንዶዎች በበቂ አለመዳሰስ

ሐ. የተሣታፊ ሴቶች ቁጥር በስብሰባ ቦታ ከተጠበቀው በታች መሆን

መ. በበጀት እጥረት ምክንያት ከዞንና ከልዩ ወረዳዎች የሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች ተወካዮች አለመጋበዛቸው ጥሪ ቢደረግላቸውም የግል ባለሀብቶች በስብሰባው የተገኙት በቁጥር አነስተኛ ስለነበሩ ተሳትፎአቸውም የዛኑ ያህል ዝቅተኛ መሆን ናቸዉ::

CGRDA

6. የድህነት ሁኔታ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል

6.1 የድህነት ጽንስ ሃሳብ፣

ድህነት የሰው ልጅ ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን በዘለቄታዊነት ማሟላት አለመቻል ማለት ነው።

የድህነት ሁኔታ ከአገር አገር ከአካባቢ አካባቢ ሊለያይ ይችላል። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣

- የነፍስ ወከፍ ገቢ ወጪ፣
- የምግብ ግኝትና አጠቃቀም ሁኔታ፣

መሠረታዊ አገልግሎቶች ትምህርት ጤና፣ ንፁህ ውኃ... ወዘተ ሽፋን በመውሰድ ማየትይቻላል።

6.2 የነፍስ ወከፍ ገቢ፣

በአገር አቀፍ ደረጃ በ1988 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ሰርቬይ የተካሄደ ሲሆን በዚህ መሠረት፣

- የአገር አቀፍ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ብር 1087.8 ሲሆን፣
- የደቡብ ክልል ግን ብር 945.48 ብቻ ነው።
- ይህ በተለያዩ አካባቢዎች ሲታይ

  ሲዳማ፣ ጌድዎ፣ ቡርጂና አማሮ ብር1121.9

  ካፋ፣ ሸካ፡ ቤንች ማጅና ዮም ብር 1000.2

  ሃዲያ፣ ከአጠና ጉራጌ ብር 977.7

  ሰሜን አሞ፣ ደቡብ አሞ፣ ኮንሶና ደራሼ ብር 729.7 ልዩነት አላቸው።

6.3 የምግብ ግኝትና አጠቃቀም ሁኔታ

ለአንድ ሰው ለዕለት የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የምግብ ፍጆታ መለኪያ 2200 ኪ.ካሎሪ በሰው ቀን ነዉ

- የአገር አቀፍ ዕለታዊ የነፍስ ወከፍ የምግብ ፍጆታ 1954 ኪ.ካሎሪ ሲሆን
- የደቡብ ክልል ግን 1800 ኪ.ካሎሪ ብቻ ነው 15.4 ያንሳል
- ለምግብ እጥረት የተጋለጠ የክልሉ ሕዝብ ከጠቅላላው 11በመቶ ይደርሳል።

6.4 የድህነት ደረጃ

መሠረታዊ ፍላጎቶችን መሠረት በማድረግ የተሰላ የድህነት መስመር እንደሚጠቁመው በ1988 ከጠቅላላ

- የኢትዮጵያ ሕዝብ 45.5 በመቶ ከድህነት መስመር በታች ሲሆን፣

CGRDA

- የደቡብ ብ/ብ ሕዝብ 56.5 በመቶ ከድህነት መስመር በታች ነው ::
  ይህ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ሲታይ፣
- ሲዳማ፣ ጌድዎ፣ቡርጂና አማሮ 41.8 በመቶ
- ካፋ፣ሸካ፣ ቤንች ማጅና የም 49.6 በመቶ
- ሃዲያ፣ ከአጠና ጉራጌ 52.2 በመቶ
- ሰሜን አሞ፣ ደቡብ አሞ፣ ኮንሶና ደረሼ 77.4 በመቶ ሕዝብ
  በአስከፊ ድህነት ውስጥ ይኖራል::

6.5 የእርሻ መሬት ይዞታ

በገጠሩ የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ ከክልሉ አርሶ አደሮች

30.05 በመቶ ከ0 እስከ 0.5 ሄ/ር የመሬት ይዞታ ያላቸው፣

32.89 በመቶ ከ0.5 እስከ 1.0 ሄ/ር የመሬት ይዞታ ያላቸው

21.21 በመቶ ከ1.0 እስከ 1.5 ሄ/ር የመሬት ይዞታ ያላቸው

15.85 በመቶ ከ1.5 ሄ/ር በላይ የመሬት ይዞታ ያላቸው ናቸው::

62.94 በመቶ አርሶ አደሮች አንድ ሄ/ር እና ከዚያ በታች የመሬት ይዞታ አላቸዉ ::
ይህም የተበጣጠሰ የእርሻዎች በምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ
አላቸው

6.6 መሠረታዊ አገልግሎቶችና ሌሎች የድህነት አመልካቾች

ማህበራዊ አመልካች	ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ	ደቡብ ያለበት ደረጃ
ሀ. በኤክስ/የታቀፉ ገበሬዎች	42.2 በመቶ	30 በመቶ
ለ. የሕፃናት ክትባት አገል/	60.0 በመቶ	57 በመቶ
ሐ. የሕፃናት ሞት መጠን	97/1000	128/1000
መ. የእናቶች ሞት መጠን	705/100000	-
ሠ. የጤና አገል/ማግኘት ዕድል	51 በመቶ	50 በመቶ
ረ. የ1ኛ ደረጃ ት/ርት ተሳትፎ	45.8 በመቶ	58.7 በመቶ
ሰ. የሴት ተማሪዎች ብዛት ከወንዶች	37.5 በመቶ	-
ሸ. የንፁህ ውኃ አቅርቦት	30.0 በመቶ	28.75 በመቶ
ቀ.የአንድ ሰዉ አማካይ እድሜ	50.6 ዓመት	48 ዓመት

CGRDA

7. የሕዝቡ የኑሮ መሠረትና የሀብት አጠቃቀም

(ከወረዳ ምክክር የተገኘ)

- ሕዝቡ በአኗኗር ዘይቤውና በአግሮ ኢኮሎጂ የሚለያይ ቢሆንም በአጠቃላይ ግን በሚከተሉት ላይ የተመሠረተ ነው::
- በእርሻና ጥምር ግብርና ውጤቶች እና ከሽያጫቸው በሚገኙ ገቢ፣
- በሰብል ምርት
- በእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ምርት
- በማር ምርት (በንብ እርባታ)
- በቡና፣ ቅመማ ቅመም ዝንጅብል፣ ኮረሪማ በመሳሰሉት የወጪ ምርቶች በማምረት
- በአትክልት፣ በሥራሥርና በመሳሳሉት ምርት
- በዕጣን(ኮንሶ)
- በእንሰት(ቆጮ)
- በጫት ምርት
- በአነስተኛ ንግድ ሥራ ስምሪት
  - በጨቃ (ኮንሶ)
  - በጠላና ጠጅ መጠጦች ንግድ
  - በቅቤ ንግድ ገቢ
  - በእንጨት ሽያጭ ገቢ
  - በልብስ ስፌት ሥራ ገቢ
  - በባሕላዊ የወርቅ ቁፋሮ ሥራ ገቢ (ሡርማ)
- በጉልበት ኪራይና በቤት ሠራተኛነት (ዳሞትጋሌ፣ ሁምቦ)
- በአደን ተግባር ውጤት
  - የዱር እንስሳት ሥጋ በምግብነት በመጠቀም
  - የዱር እንስሳት ቆዳና ጥርስ ንግድ
- ከወንዞችና ሐይቆች ዓሣ በማጥመድ
- በሸክላ ሥራ ምርት ሽያጭ
- በጋብቻ ወቅት ከወንዱ ወገን በሚሰጥ ጥሎሽ(ሡርማና ሐመር)
- በትምባሆ ቅጠል ንግድ (ሐመር)
- በአነስተኛ የዕደጥበብ ሥራ ውጤት ሽያጭ(ኮንሶ)

CCRDA

8. ድህነትና የድህነት መገለጫዎች

(ከወረዳ ምክክር የተገኘ)

ድህነት ማለት ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ ቁሣዊና /ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ/ ቁሣዊ ያልሆኑ /ሠላም/ ፍላጐቶችን አለማግኘትና አለመቻል ነው:: በህብረተሰቡ አጠለፉ ግን የአርሻ መሬት፣ በሬ፣ የወተት ላም፣ መኖሪያ ቤት፣ የሌለውና አራቱንና ቤተሰቡን በቀን ሁለት ጊዜ መመገብ የማይችልና በአመት አንድ ጊዜ እንኳን ልብስ መልበስ የማይችል፣ በቂ የመኝታ ልብስ / ደሀና ምንጣፍ/ የሌለው፣ ወዘተ ማለት ነው::

መገለጫዎቹም:-

- የምግብ እህል እጥረት
- በቂ አልባሳት አለመኖር
- የመጠለያ ቤት አለመኖር
- የአርሻ በሬ አለመኖር
- የአርሻ መሬት ጥበትና እጠት
- ሥራ አጥነትና የሥራ መስክ ውስንነት
- የጤና ችግር ወይም የጤና ማጣት
- በቂ የቤት እንስሳት አለመኖር (በአራሹም በአርበቶ አደሩም)
- የሴት ልጅ አለመኖር (በአርብቶ አደር)
- የገንዘብ ዕጦት (እጥረት)፣
- የትምህርት፣ የጤናና የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት አለማግኘት፣
- የመንገድና የትራንስፖርት አገልግሎት አለማግኘት፣
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣
- የትምህርት፣ የጤናና የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ለማግኘት የገቢ ማነስ፣
- የማር ቀፎ አለመኖር (በአርብቶ አደሩ)፣
- በጥገኝነት መኖር (በአርብቶ አደሩ)፣
- መካንነት (በአርብቶ አደሩ)፣
- ወላጅና ዘመድ አልባነት፣
- የአርሻ መገልገያ መሣሪያዎች አለማግኘት፣

CCRDA

- የልመና መስፋፋትና የተመፅዋችነት ስሜት መኖር፣
- የሥራ ባህል አለመዳበርና የሥራ ተነሣሽነት አነስተኛ መሆን፣
- የቁጠባ ባህል አለመዳበር/አለመኖር/፣
- የህብት አጠቃቀም ዕውቀት ማነስ፣
- የገበያ አለመኖር፣
- የብድር ዕዳን ለመክፈል አለመቻል፣
- ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ ወ.ዘ.ተ.

በሴቶች:- ዕይታ በተለይ ከላይኛው መገለጫ ጋር ታክለው:-

- ገበያ፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃና የጤና አገልግሎት ለማግኘት፣ ረጅም መንገድ በእግር መጓዝ፣
- ወልዶ አለመታረስና ዕረፍት ማጣት፣
- የንብረት ባለቤትና የመብት እኩልነት ማጣት በዚህም ምክንያት የኢኮኖሚ ጥገኝነትና የልማት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣
- ለአቅመ አዳም የደረሱ በወቅቱ ትዳር አለመያዝ፣
- በሥራ አጥነት ምክንያት ከአካባቢ መፍለስ/ለቆ መሄድ/፣
- በሴቶች ላይ የሥራ ጫና መብዛት፣ ወ.ዘ.ተ. የድህነት መገለጫዎች ናቸው::

9. የድህነት መሠረታዊ መንስኤዎችና ተዕዕኖዎች

(ከወረዳው ከክር የተገኘ)

- የሕዝብ ቁጥር እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት፣
- የመሬት ጥበትና ለምነትም መቀነስ፣
- የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች አለመስፋፋት፣
- የአየር መዛበት፣ የድርቅ በተደጋጋሚ መከሰት፣
- የኢንዱስትሪ አለመስፋፋት፣ ሥራ አጥነት መብዛት፣
- የእርሻ ግብአት ዋጋ መናርና የሰብል ምርቶች መቀነስ፣
- የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና መራቆት፣ የአፈር መሸርሸር፣
- የደን ሀብት ቃጠሎ፣
- የሰብልና የእንስሳት በሽታ መከሰት፣
- የቁጠባ ባሕል አለመዳበር፣/አለመኖር/
- የመንገድ /ትራንስፖርት/ አለመስፋፋት፣/አለመኖር/
- የብድር አገልግሎት አለመስፋፋት፣/አለመኖር/

CCRDA

- የጐጂ ባሕልና የአምልኮዎች መስፋፋት፣
- የሰላም አለመኖርና አለመረጋጋት/ሀዲያ-ሌሞ/
- የሰብል ምርት ዋጋ መውደቅ/በተለይም-ቡና/
- የአጐራባች ብሔር ብሔረሰቦች ግጭት፣ዘረፋ፣ ወ.ዘ.ተ.
- የመሠረተ ልማት አውታሮች አለመዘርጋት፣
- የትራንስፖርት አገ/አለመኖርና አግባብ የገበያ ማዕከል በቅርበት አለመኖሩ

10.ድህነትን የሚያባብሱ ልማዳዊና ባሕላዊ ተፅዕኖዎች

(ከመረዳዎች ምክክር የተገኘ)

- ከአቅም በላይ ለሆነ ጥሎሽ ክፍያና ለሠርግ ዝግጅት ብዙ ገንዘብ ማውጣት ማባከን፣
- በሃይማኖታዊ ፕሮግራሞች ሰብሰባዎችና ኮንፈረንሶች ዘወትር በመሳተፍ በልማት ላይ መዋል የሚገባውን ጊዜ ከማባከንና ምርትና ምርታማነትን ከመቀነሱም በተጨማሪም የሥራ ተነሳሽነትንም መቀነሱ፣
- የቀብር፣ የሐዘንና የለቅሶ እንዲሁም የተስካር ሥርዓት መንዛዛትና ለዚሁ ብሎ ከፍተኛ ገንዘብ ማውጣት፣
- የቁጠባ ባሕል አለመዳበር፣ በሚያገኘው ገቢ መጠን የመተዳደርና የመጠቀም ልምድ አለመኖር፣
- ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት፣ ብዙ ልጆች መወለድን እንደሀብት መቁጠር፣ /አርብቶ አደር ወረዳዎች/
- በጐሳዎች መካከል አልፎ አልፎ የሚከሰት ግጭት፣
- የበሽታ /ኤች አይቪ/ ስርጭትና የሚያስከትለው ጉዳት፣
- የበዓልና የገበያ ቀናት መብዛት፣
- የልጅ የላይ ጥርሱ ቀድሞ ከበቀለ ገፌ /ሚንጊ/ ብሎ መጣል፣ ወይም ሰው እንዳያይ በመስጋት እንደልብ ተንቀሳቅሶ ለመሥራት መቸገር /ሐመር/
- የሴት ልጅ ጠለፋ፣ ያለዕድሚ ጋብቻ፣ በወር አበባና በወሊድ ጊዜ የሴቶች ከቤት መገለል፣ በሷ የሞተባት ሴት የባሏን ዘመድ እንድታገባ መገደድ /ዳሎቻ/
- ሴቶች የንብረት ባለቤት አለመሆን፣
- የሴቶች አምልኮኢዊ ስብሰባ ፣በለቅሶ ሥፋራ መውደቅ፣ አካል መብጣት፣ ሰውነት መተኮስና ፀጉር መንጨት እንዲሁም ወንዶች ለሥራ ወደሌላ ቦታ ሲሄዱ በሴቶች ላይ የሥራ ጫና መብዛት /ዳሎቻ፣ ቸሃ/
- ሴት ልጅን ት/ቤት አለመላክ፣ ያለአቻ ጋብቻ መፍቀድ ሥነልቦናዊ ቀውስ መፍጠር፣ የምርትና ምርታማነት አጋቾነቷን መገደብ፣
- በዱላ ምክቶሽ በርካታ የሥራ ጊዜ ማባከን/ሡርማ/ወ.ዘ.ተ.

CCRDA

11. ድህነትን ለመቅረፍ ባለፉት 5ዓመታት የተወሰዱ እርምጃዎች

(ከመረዳ ምክክር የተገኘ)

11.1 በህብረተሰቡና ህብረተሰቡ ባቋቋማቸው ድርጅቶች

- ዕድሮች በራሳቸው ተነሳሽነት በተለይ አደጋን ለመከላከል ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን በማቀናጀት መጋቢ መንገዶችን በመሥራት፣ የውሃ ምንጮችን በማጽዳትና በማጉልበት፣ እንዲሁም በኤክስቴንሽን መርሃ ግብር አፈጻጸም ረገድም ከመንግሥት ጋር በመሆን የጐላ እንቅስቃሴ አድርገዋል ::
- በወንፈል፣ በደቦ፣በጅጌ፣ተደራጅቶ በጋራ የማረስና ምርትን የመሰብሰብ ተግባር ተከናውኗል::
- በጉርብትና፣ በዕድርና፣ በሰንብቴ ተሰባስቦ ችግርን በጋራ የመቋቋም እንቅስቃሴ ተደርጓል::
- በዕቁብና በቁጠባ ማህበር በመሰባሰብ የገንዘብ አቅምን የማሣደግና የማጠናከር ሥራ ተካሂዷል::
- መረዳጃ ማህበር በማቋቋም፣ በድርቅ፣ በአደጋና በችግር ጊዜ የመተጋገዝና የመረዳዳት እንዲሁም ፈጥኖ የመድረስ ባህል ማዳበር ተችሏል ::
- የቀበሌ የልማት ማህበርን በማቋቋምና አባልና ተሳታፊ በመሆን የጋራ ችግርን በጋራ የመፍታት፣ በጋራ የልማት ሥራ የማከናወን፣ እንዲሁም ለአርሶ አደሩ የእርሻ ትራክተር የማቅረብና የብድር አገልግሎት የመስጠት ተግባር ተከናውናል::
- ለሥራ የሚያነሳሱ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን የመቀበልና የመተግበር ልምድ ተወስዷል::
- ጎጂ ባህሎችንና ባህላዊ ግጭቶችን በማስወገድ፣ በማስታረቅና በመዳኘት፣ ሠላም እንዲሠፍን፣ መተሳሰብ እንዲጎለብት በአጠቃላይ የባህርይ ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል::
- ለቅሶና ቀብር በበዓላትና ከሥራ ቀናት ውጪ እንዲሆኑና የህዘን ጊዜም እንዲያጥር ተደርጓል::
- ለሠርግና ለተዝካር የሚወጡ አቅምን ያልመጠኑ ወጪዎች እንዲቀነሱ የጋራ ግንዛቤና አቋም ተወስዷል::
- ት/ቤቶችን የመገንባትና የውስጥ ድርጅቶቻቸውን የማሟላት ጥረት ተደርጓል::
- በድርቅ ወቅት የሚነሳ ሰደድ እሳትን የመከላከልና ቃጠሎን የማጥፋትና የቤት ቃጠሎን የማዳን የህብረት ሥራ እንቅስቃሴ ተካሂዳል::

CGRDA

- በማህበርና ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት በገጠር ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ የመቆፈር፣ ምንጭ የማጉልበትና የመጥረግ፣ ባህላዊ የመስኖና የእርከን ሥራዎችን የመሥራት እንዲሁም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ላይ የመሠማራትና የእንጨት ድልድዮችን የመዘርጋት አበረታች ተግባር ተከናውኗል::
- በየቀበሌው ንዑስ መንደሮች ከ10-20 የሚደርሱ ሰዎች በቡድን ተደራጅተው ቅንጅታዊ የልማት ሥራዎችን እንዲሠሩ የማድረግ እንቅስቃሴ ተካሂዷል::
- ባህላዊ የሕክምና ዘዴዎችን በመጠቀም የሕ/ሰቡን አካባቢያዊ የጤና ችግሮች ለማቃለል ጥረት ተደርጓል::

2.2 <u>በመንግሥት</u>

- በግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ህብረተሰቡ በምግብ እህል ምርት ራሱን እንዲችልና የምግብ ዋስትናውን እንዲያረጋግጥ፣ የኤክስቴንሽን መርሃ ግብር ተነድፎ የተሻሻሉ የአሥራር ዘዴዎችን ከማስተዋወቅና ከማስተማር ጋር ለአርሶ አደሩ የግብአት አቅርቦት ሁኔታ እንዲሻሻል፣ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና የምርት ማሳደጊያ ግብአት ለገበሬው በብድር እንዲቀርብለት የማድረግ አበረታች ተግባር ተከናውኗል::
- ግብርናውን ዘርፍ አገልግሎት ለማስፋፋትና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣የሚያስችሉ:-
  - በተወሰነ ደረጃ የደንና የአፈር ጥበቃና ልማት ሥራዎች ተሠርተዋል፣
  - የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች ተቋቁመዋል፣
  - የልማት ጣቢያ ሠራተኞች መኖሪያና መጋዘኖች ተሠርተዋል፣
  - ለግብርና ልማት ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠና በብቃት ለመሰጠት ጥረት ተደርጓል::
  - ዘመናዊ የንብ እርባታና የእንስሳት መኖ ሠርቶ ማሳያ ጅምር ሥራዎች ተሞክረዋል::

ማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስርጭትና ሽፋን ከፍ እንዲልና አገልግሎቱም እንዲዳረስ አበረታች ጥረት ተደርጓል:: በዚህ አንጻር:-

ትምህርን፣ በማስተማሪያና መርጃ መሣሪያዎች እንዲሁም ዳርንቸር የተሟሉ ባይሆኑም በርካታ ት/ቤቶች ተገንብተዋል

ጤናሙያ፣ በህክምና መሣሪያዎችና በመድኃኒት አቅርቦት ረገድ በብቃት ዘደራጁም የማይናቅ ቁጥር ያላቸው ክሊኒኮች፣ ጤና ኬላዎችና ጤና ጣቢያዎች ሠርተዋል::

CCRDA

- የንጹህ የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ተቆፍረዋል ::
- በቂ ነው ሊባል ባይችልም የመሠረተ ልማት አውታሮችን ለመዘርጋትና የተጠቃሚውን ሕብረተሰብ ቁጥር ከፍ ለማድረግ አበረታች ጥረት ተደርጓል::

በዚህም በኩል:-

- አጫጭርና፣ ርዝመት ያላቸው መጋቢ መንገዶች ተሠርተዋል፣
- የመብራትና፣ የስልክ መስመሮችን የመዘርጋት ሥራ ተከናውናል፣
- የፖስታ አገልግሎትን ለማስፋትና ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል::
- በተለያዩ ቦታዎች የተከሰተውን የድርቅ አደጋ የመቋቋም ጥረት ተደርጓል::

3.3 <u>መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች</u>

እንደየአካባቢውና እንደሚሳተፉበት ፕሮግራም ዓይነት ውስን የሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድህነትን ለመቀነስ የሚያግዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን በማቋቋም ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆንና ችግሩ እንዲቀረፍ የማይናቅ ጥረት አድርገዋል:: በዚህም አኳያ:-

- በዝናብ ስርጭት መዛባት ምክንያት በሚከሰተው ድርቅ ህዝቡ የሚገጥመውን የምግብ እህል እጥረት ለመሸፈን የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በተጓዳኝ ሠርተዋል::
- ለሕፃናት፣ ለአረጋውያንና አቅመ ደካማ ለሆኑ የህ/ሰብ ክፍሎች ልዩልዩ መድኃኒቶችንና አልሚ ምግቦችን በመስጠት የሕይወት አድን ሥራ ሠርተዋል::
- ለምርትና ምርታማነት አስተዋፅዖ በሚያደርግ የአፈርና ውሃ ልማት ሥራ ተሠማርተው አበረታች ተግባር አከናውነዋል ::
- ለአርሶ አደሩ የእርሻ ሥራ እገዛ የሚያደርግ የትራክተር አገልግሎት የማቅረብ ጥረት አድርገዋል::

ከመንግሥት የልማት ፕሮግራሞች ጋር በመቀናጀት፣

- የትምህርትና የጤና ተቋማት ግንባታ አካሂደዋል፣ የውስጥ ድርጅታቸውን ለማሟላትም ጥረት አድርገዋል::
- የውስጥ ለውስጥ መጋቢ መንገዶችን ሠርተዋል::
- ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ምንጭ የመጥረግና የማጎልበት ተግባር አከናውነዋል ::

CCRDA

- የትምህርትና የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋትና ብቃቱን ከፍ ለማድረግ እንዲያስችል ለባለሙያዎች የአቀም ግንባታ ሥልጠና ለመስጠት ጥረት አድርገዋል::
- በቡና ልማት ሥራ በመሳተፍ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል::
- ለገበሬዎች ዘመናዊ የቡና አመራረትና አጠቃቀም ትምህርት ሰጥተዋል::
- ለአርሶ አደሮች የተሻሻሉ የእንስሳትና የአትክልት ዝርያዎችን አቅርበዋል::
- በግብርና ሥራ ጥናትና ምርምር ዙሪያ የገበሬዎችን ተሳትፎአዊ አንቅስቃሴ በማጎልበት ረገድ ድጋፍ አድርገዋል::

= የወጪ ምርት አምራች ወረዳዎችን በተለይ በሚመለከት ደግሞ በመንግሥትና በግል ደረጃ ቅንጅት በመፍጠር የቡናን ልማት ለማስፋፋት ብሎም የቡና አምራች ገበሬዎችን የኑሮ ደረጃና የገቢ መጠን ከፍ ለማድረግ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የቡና ችግኝ ተዘጋጅቶ ለገበሬው እንዲሠራጭ ተደርጓል::

⇒ በዚሁ አካባቢ በግል ባለሀብቶች በኩልም በርካታ የደረቅ ቡና ማበጠሪያዎችና የእሸት ቡና /የታጠበ ቡና/ መፈልፈያ ኢንዱስትሪዎች ተተክለውና ተቋቋመው በጥራትና በብዛት የተዘጋጀ የቡና ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ እንዲቀርብና በዚህም ምክንያት የውጪ ምንዛሪ እንዲገኝ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል::

CCRDA

ማጠቃለያ:-

ከላይ ከተጠቀሱት እንቅስቃሴዎች በሁሉም አንፃር ጥናት ከተካሄደባቸው አግሮ ኢኮሎጂያዊ አካባቢዎች በአርብቶ አደሩ አካባቢ የተደረገው እንቅስቃሴ፣ የተከናወነው ተግባርና ድህነትን ለመቀነስ ባለፉት 5ዓመታት የተወሰደው እርምጃ እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል::

12. አስተዳደራዊ መዋቅሮችና የልማት መ/ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎትና ያሉ ችግሮች

በመሠረቱ እንደሚፈለገውና እንደሚጠበቀው ያህል አይሁን እንጂ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና የልማት መ/ቤቶች በሁሉም መስኮች የልማት ሥራዎች እንዲካሄዱ ለማድረግ ጥረት ከማድረጋቸውም ባሻገር በተወሰኑ ዓመታትና አካባቢዎች እየተደጋገመ የሚከሰተውን የድርቅ አደጋና የበሽታ ወረርሽኞች ለመቋቋምና በቁጥጥር ሥርም ለማዋል የማይናቅ ተግባር አከናውነዋል። በተለይ በመንግሥት በኩል የልማት መ/ቤቶች ለህብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት መጠንና ጥራት አንጻራዊ መሻሻል እየታየበትና ትኩረት እየተቸረው የመጣ ጉዳይ ቢሆንም የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላትና በተወሰነ ደረጃ ሀገርካት ግን ገና ብዙ ሥራዎች መሠራትና በርካታ ሁኔታዎችም መስተካከልና መሟላት እንደሚገባቸው የሚካድ አይሆንም።

የልማት መ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥም በቂ ባለሙያ ካለመኖሩ፣ አደረጃጀቱ የተሟላ ባለመሆኑ፣ በጀት ከማነሱና በአንዳንድ ሁኔታዎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመቀነሱ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ እንዲሁም ከበርካታ መሰል ችግሮች መኖር የተነሳ ከህብረተሰቡ የሚጠበቅባቸውና እይታ አንጻር የተመጣጠነ እንዳልሆነ ቢታወቅም ዓይን ሊወጉ የሚችሉ ጉልህ ሥራዎቹ በመጠኑም ቢሆን እንደተሠሩ የማሸሸግ አይደለም። ስለዚህ ከዚህ ቀደም ሲል« ችግሮችን ለመቅረፍ ባለፉት5 ዓመታት የተወሰዱ እርምጃዎች» በሚለው ርዕስ ሥር በየክፍለተሰቡና ህብረተሰቡ ባቋቋማቸው ድርጅቶች፣ በመንግሥት እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተወሰዱ እርምጃዎች የሚለው መዘርዝር በሌላ መልኩ ሲታይ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና የልማት መ/ቤቶች ለህብረተሰቡ የሰጡትን አገልግሎት የሚገልጽ በመሆኑ ከዚህና የአቀራረብ ድግግሞሽን ከማስወገድ አንጻር በማየት በዚህ ዐቢይ ርዕሥ ሥር መዋቅሮቹና በልማት መ/ቤቶች ያሉ ችግሮችን ከምክክር ስብሰባዎቹ በተገኙት መሠረት ብቻ ለማሳየት የተሞከረ መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን ::

CCRDA

12.1 <u>በልማት መ/ቤቶች ያሉ ችግሮች</u> (በወረዳና በክልል ምክክር የጸበረ)

- የጤና ተቋማት በባለሙያ፣ በውስጥ ድርጅታቸው፣ በማቴሪያልና በመድኃኒት አቅርቦት ባለመሟላታቸው፣ ባለመደራጀታቸውና ባለመጠናከራቸው ምክንያት የተነሳ:-
  - የህብረተሰቡን ጤና በአግባቡ ለመጠበቅ አለመቻል፣
  - ህብረተሰቡ በውሃ ወለድና በልዩ ልዩ በሽታዎች ማለትም በወባ፣ በታይፎይድና በታይፈስ፣ በተቅማጥ፣ በሳምባ፣ በማጅራት ገትር፣ ወ.ዘ.ተ. እየተሰቃየ ያለ መሆኑና በቆላማ አካባቢዎች የሰውና የእንስሳት ወረርሽኝ መስፋፋትን ለመግታት ጥረቱ አናሳ መሆኑ፣ እንዲሁም የንጹሕ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ችግር በመኖሩም የውሃ ወለድ በሽታዎች ድግግሞሽ ከፍተኛ መሆኑ፣
- የክትባት አገልግሎት በአግባቡ ለመስጠትና ለማዳረስ አለመቻል፣
- የጤና ተቋማት /ክሊኒኮች፣ጤና ኬላዎች፣ የእንስሳት ጤና ክሊኒኮችና ጤና ጣቢያዎች/ ቁጥር አነስተኛ መሆንና በቂ አገልግሎት ሊሰጡ አለመቻላቸው፣
- ሴቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤና ትምህርትና የእናቶችና የሕፃናት ጤና ክብካቤ ትምህርትና አገልግሎት ማግኘት አለመቻላቸው፣ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ባለመቻላቸውም ለከፍተኛ የጤና ችግር መዳረጋቸውና ለሞት አደጋም የተጋለጡ መሆናቸው፣
- የንጹህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ሲዘረጋ የህብ/ሰቡን አሠፋፈር መሠረት ያላደረገ መሆንና ተሠርቶ ያለ አገልግሎት የሚቀመጥ መሆኑ፣ እንዲሁም ጥቂት አገልግሎት ሰጥተው በመበላሸት የሚቆሙትን የሚያስታውስና ለመጠገን የሚንቀሳቀስም ክፍል አለመኖሩ ::
- የኤድስን ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል በቂ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ አለመሠራቱ፣
- የት/ቤቶች ቁጥር አናሳ መሆን፣ የተሠሩትም የሕፃናትን ዕድሜ ግምት ውስጥ ባላስገባ ርቀት ላይ መገኘታቸው፣ ያሉትም ቢሆኑ በመምህራን፣ በማስተማሪያ መርጃና በመጻህፍት በተገቢ ማቴሪያሎች፣ ቁሳቁሶችና ፈርኒቸሮች ባለመሟላታቸው፣-
  - የመማር ማስተማር ሂደቱ አጥጋቢ አለመሆኑ፣
  - ት/ቤቶች ለተማሪዎች ሳቢና ምቹ ባለመሆናቸውና እንደ «እስር» ቤት የመቆጠር አዝማሚያ መታየቱ፣
  - የተማሪ ቁጥር እየቀነሰ መሄዱና አቋርጠ መውጣት መከሰቱ፣
  - ዕድሜያቸው ለትም/የደረሱ ሕፃናት ሊስተናገዱ አለመቻላቸው፣

CCRDA

- የመንገድ፣ የመብራት፣ የስልክና የፖስታ አገልግሎቶች (የመሠረተ ልማት አውታሮች) ሽፋን በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ መሆናቸው፣
- ለእንስት ተክል በሽታ መድኃኒት አፈላልጎ ማቅረብ አለመቻል፣
- የቡና ፍሬ በሽታ መከላከያ መድኃኒት ውድ ከመሆኑ ባሸገር የሚመለከተው ክፍል ሰገበሬው ማቅረብ አለመቻሉ::
- ለአርሶ አደሩ የእርሻና የልማት ማስፋፊያ ግብአት በብድር ለማቅረብ አለመቻል፣
- የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲቻል በባለሙያዎች ተገቢና ተከታታይነት ያለው የምክር አገልግሎት ሊሰጥ አለመቻሉ፣
- የኤክስቴንሽን ፖኬጆች አፈጻጸም የአካባቢውን አግሮ ኢኮሎጂ ያገናዘበ፣ ወቅቱን የጠበቀና ህብረተሰቡን ያሳተፈ እንዲሆን ባለመደረጉ ችግር ያለበት መሆኑና በዚህም አርሶ አደሩ የዕዳ ጫና ተሸካሚ እንዲሆን መደረጉ፣
- የልማት ተቋማት ስርጭት ፍትሐዊ አለመሆንና አገልግሎት አሰጣጡም የተዛባ መሆን፣
- ተፈላጊ የመንግሥት ሴክተር መ/ቤቶች ተሟልተው አለመቋቋማቸውና የተቋቋሙትም በተገቢ የሰው ኃይል፣ በቁሳቁስና በበጀት አለመሟላታቸው፣
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የአገልግሎት ሽፋን፣ ብቃት፣ ጥራትና ቀጣይነት አነስተኛ መሆን፣
- ባለሙያዎች ከሙያ ሥራቸው ይልቅ ለፖለቲካ ሥራ ቅድሚያ በመስጠት መንቀሳቀሳቸው፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች የሚያካሂዱት የልማት እንቅስቃሴና ሥርጭትም ፍትሐዊ አለመሆኑ፣
- የትም/ተሳትፎ በአጠቃላይና የሴቶች ደግሞ በተለይ በጣም አነስተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ፣
- በጥቅሉ የትም/ሽፋን፣ ብቃትና ጥራት ዝቅተኛ መሆን፣
- የትም/ተሳትፎና ሽፋን ከፍ እንዲል ህብረተሰቡን ስለትምህርት ተከታታይነትና ቀጣይነት ባለው መንገድ የመቀስቀስ ሥራ በአጥጋቢ ሁኔታ አለመሠራቱ፣
- መንግሥት የልማት ተቋማት ይልቅ የህብረተሰቡ የልማት ተሳትፎ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ የተሻለ መሆን የመንግሥት ልማት መ/ቤቶችን የአገ/አሰጣጥ ድክመት የሚያመለክት መሆኑ፣
- በተለይ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ህብረተሰቡ ለትምህርት ከሚሰጠው ትኩረት እናሳነትና በቂና ጠንካራ ቅስቀሳ ከማድረግ ጉድለት፣ ት/ቤቶች ለተጠቃሚው ሕ/ሰብ በአማካይ ቅርበት ካለመገኘታቸው፣ ከመምህራን፣ ከማስተማሪያና ከትም/መርጃ መሣሪያዎች እጥረት እንዲሁም ለአርብቶ አደሩ ልጆች ብተቋቋሙ

CCRDA

ሆስቴሎች ከሚታየው የምግብ እህል አቅርቦት እጥረትና ከመሰል ችግሮች መዳመር ጋር በአካባቢው የትም/ሽፋን እና ብቃት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣

- ሴቶችን ለልማት የማዳራጀት፣ የማንቀሳቀስና የማበረታታት እንቅስቃሴ በጣም ደካማ መሆንና እንዲያውም ሴቶች ራሳቸውን ለማደራጀት ያሰባሰቡትን ገንዘብና ቁሳቁስ ከምዝበራ ለማዳን ጥረት አለመደረጉ፣

12.2 <u>በአስተዳደራዊ መዋቅሮች ያሉ ችግሮች</u>

- በልማትም ሆነ በፀጥታ ችግሮች አፈታት ላይ ወቅታዊና ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት አለመቻል፣
- በብሔረሰብ ተዋፅዖ ሰበብ ብቃት የሌላቸውና ራስ ወዳድ የአመራር አካላት ተመድበው መገኘት፣
- ለፕሮጀክት ዕቅድ ማስፈፀሚያ የሚመደበውን በጀትና ማቴሪያል በወቅቱና በአግባቡ እንዲደርስ ጥረት ባለመደረጉ ምክንያት የተያዘ የልማት ዕቅድ ግብ ሊመታ አለመቻሉ።
- በዘመድ አዝማድና ከጥቅም ጋር በተሳሰሩ ግንኙነቶች መንስኤ ሥራና ሠራተኛ ላገናኙ አለመቻላቸውና ይህም ለሥራ መበደልና ለዕድገት መፋጠን እንቅፋት መሆኑ፣
- የእንስሳትና የሰው መድኃኒቶች እንዲሁም የፀረ-አረምና የፀረ-ተባይ መድኃኒቶችን ሕገ ወጥ ንግድ ለመቆጣጠር አለመቻልና የሚደረግ ጥረትም ቢኖር አነስተኛ መሆን፣
- [illegible]ን እስከ ቀበሌ ያሉት የመስተ/አካላት የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ ሰዓትን በአግባቡ እንዲያከብሩና እንዲጠቀሙ፣ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችም አሠራራቸውን ሕግና ሥርዓትን ተከትለው እንዲያስተካክሉ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለመቻል፣ እንዲሁም በአንዳንዱ ራሱንም ክፍል ለሥራ የማነሳሳትና የማላተፍ ብቃት አናሳ መሆንና የሥራ ተነሳሽነት ስሜትን የመቀስቀስ አቅምም አለመኖር፣
- ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ፣ አካባቢን ከመንከባከብና በአግባቡ ከመጠቀም አንፃሩም የባለቤትነት ስሜትን ከማሳልበት አኳያ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ፖሊሲን ተግባራዊ ለማድረግ አለመቻል፣
- [illegible]ትሕ አካላት ቀጠሮ ማብዛት፣ የፍትሕ መዛባትና መጓተት፣ የመዝ/ቤት ሠራተኞች የሚያደርሱት ማጉላላት፣ የማህበራዊ ፍ/ቤቶች አቅም አናሳ መሆንና ምን ጥቅም አገኛለሁ? ከሚል ግለኛ ሰሜት ሥራዎችን መወዘፍ፣ በዚህም የተኦላ [illegible]ረተሰቡ ጊዜውን፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን ያለአግባብ እንዲያባክን መገደዱ፣
- [illegible]ሕግ አስከባሪ አካላት /ፖሊሶች/ ወንጀል ሲከሰት እያዩ እንዳላዩ ዞር ማለትና [illegible]ንድን ግለሰብ ለመጉዳት ዓርብ ቀንና በበዓላት ዋዜማ በማሠርና የሰውን ሰብአዊና [illegible]መንግሥታዊ መብት በመጣስ ከ24 ሰዓት በላይ እስከፈለጉበት ጊዜ ድረስ [illegible]ር ቤት የማቆየት ኢ-ፍትሐዊ አሠራር መኖር፣
- [illegible]ረዳ እስከ ቀበሌ ድረስ ባለው አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ የተቀመጡ የአመራር

CCRDA

አካላት የትም/ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑና የተሰጣቸውን ኃላፊነት የመወጣት ብቃታቸውም አናሳ መሆኑ፣ የአመራር ብቃታቸውንና ትምህርታቸውን ከፍ ማድረግ እንዲችሉ ትምህርትና ተከታታይ ሥልጠና ስለማይሰጣቸውም

የሚያበረክቱት አገልግሎት፣ አመራራቸውና ውሳኔ አሰጣጣቸው ደካማ መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት ለህብረተሰቡ ችግሮችና ጥያቄዎች ወቅታዊና አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት አለመቻላቸው፣

- አብዛኛው የአመራር አካላት ለሚፈጽሙት ሕገ-ወጥ ተግባር ተገቢና ተመጣጣኝ ቅጣት ስለማይሠነዘርባቸውና ሕጋዊ የእርምት እርምጃ ስለማይወሰድባቸው የባሰ እንጂ የተሻለ አሠራርና አመራር ሊታይ አለመቻሉ፣
- የቀበሌ አመራሮች ለመንግሥት ግብርና ለተለያዩ የልማት ማስፋፊያ ግብአቶች ክፍያ ከአርሶ አደሩ ያለ ሕጋዊ ደረሰኝ የሚሰበሰቡትን ገንዘብ ያለ አግባብ ማባከናቸውና ለግል ጥቅም ማዋላቸው፣ በዚህም ሳቢያ ራሳቸውን ለዕዳ፣ ቤተሰባቸውን ለችግርና ህብረተሰቡንም ለዳግመኛ የመንግሥት ግብር፣ የግብአት ዕዳ ክፍያና የሥራ ጊዜን ለሚያባክን ውዝግብ መዳረጋቸው፣
- ከአመራር አካላት የብቃት ማነስ፣ ከተጠያቂነትና ከግልጽ የሥራ ግንኙነት አለመኖር የተነሳ እርስ በርስ ተቀናጅቶ ለመሥራት አለመቻልና ባለጉዳዮችን በመጠጥ ቤት የማስተናገድ አካሄድ ቁምር የሚታይ መሆኑ፣
- ሕብ/ሰቡን ለሚመለከት ወይም መንግሥታዊ ለሆነ ጉዳይ ሳይሆን ሕጋዊ ማህተምን ለግል ጉዳይ መጠቀሚያነት የማዋል አሠራር መኖሩ፣
- በአብዛኛው ፕሮጀክት ውስጥ ከዕቅድ እስከ አፈጻጸም ባለው ሂደት አመራሮች ያልተሳተፉበት በሚሆን ጊዜ በባለቤትነት ስሜት ክትትልና ቁጥጥር ስለመማያደርጉ በሚፈጠረው የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ጉድለት አብዛኛዎቹ ጥያቄ ውስጥ ሲገቡ መታየታቸው::
- በተደጋጋሚ በመንግሥት የተደረገው አንድን ወረዳ አንዱ የመጨፍለቅና በሌላ ጊዜ ደግሞ ራሱን እንዲችል የማድረግ ሂደት የወረዳውን ዕድገት እንዲጎተት ያደረገው መሆን፣
- ዞን በሥሩ የተደራጁትን ወረዳዎች በእኩል ዓይን በማየት አለማስተናገዱና አድሎአዊ አሠራር የሚፈፅም መሆኑ፣
- የስልጠና የሰው ኃይልን በአግባቡ ለመጠቀም ባለመቻል የተነሳ የባለሙያ ፍልሰት ማስከተሉ /ማባባሱ/፣
- የፖለቲካ ሥራን ከመንግሥት ሥራ ጋር የማቀላቀል፣ የማደባለቅና የማጋጨት እንቅስቃሴ መታየት፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዕቅድ አወጣጥ ወቅትም ሆነ በትግበራ ጊዜ ሕብረተሰቡን የማሳተፍ ትኩረታቸው አናሳ መሆኑና እንቅስቃሴያቸውም ሙሉ

CCRDA

በሙሉ በራሳቸው ፍላጎት ላይ /በአብዛኛው/ ያነጣጠረ መሆኑ ታውቆ በመንግሥት በኩል እነሱን የመቆጣጠር የመገምገም፣ የሚያካሂዱት የልማት ስርጭት ፍትሐዊ እንዲሆንና የተሻለ የአሠራር ስልት እንዲቀይሱ የማድረግ ሙከራ አለመታየቱ፣

- የአንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ከህገ መንግሥቱ ውጪ መንቀሳቀስ የሚታይ መሆኑ፣
- የአስተዳደር መዋቅሮች ከመንግሥት የሚተላለፉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወደህብረተሰቡ እንዲወርድ አለማድረጋቸውና ራሳቸውም ተግባራዊ አለማድረጋቸው መታየት፣
- የክልልና የዞን አስተ/እርከን አመራሮችም የወረዳ መስተ/አካላትን እየጠሩና እየሰበሰቡ ከማወያየት በስተቀር በአወያዩአቸው ጉዳዮች ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት፣ የተሠሩ ሥራዎችና የተገኙ ለውጠች ምን እንደሆኑ መከታተል አለመቻላቸው፣
- እስከዛሬ ድረስ ላለውና ለሚታየው አስተዳደራዊ ችግር ምክንያቱ ለህብረተሰቡ ተገቢ ግልጋሎት መስጠት የማይቻሉ አካላት ናቸው እየተባለና መሆናቸውም እየታወቀ በሥልጣን ላይ እንዲቆዩ የሚደረገው አሠራር መሆኑን፣
- በሕገ ወጥ ነጋዴዎችና ንግድ ላይ አስተዳዳራዊ ቁጥጥር ለማድረግ አለመቻልና በማዕከላዊ የቡና ጨረታ ማዕከል የሚታየውን የሙስና አሠራር ለማጽዳት አለመሞከር፣
- የአርብቶ አደሩን አካባቢ ለማልማት የተነደፈውን የተቀናጀ የልማት ፕሮግራም ለመተግበር የጎላ እንቅስቃሴ አለማድረግና ተጨባጭ ውጤት ለማሳየትም አለመሞከር፣
- የመንግሥት የልማት ፕሮግራም አፈጻጸም ሲታይ ህብረተሰቡን ከዕቅድ ዝግጅት እስከ አፈጻጸም ድረስ ያለሳተፈ መሆኑ፣
- ከአጐራባች አገሮች ጠረፍ አካባቢ ጋር በሚያደርጉት ሕገወጥ የመሣሪያ ንግድና ዝውውር ተግባር ላይ በመሠማራት በሚያገኙት በርካታና ልዩ ልዩ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በማስገደድ የህብትና የንብረት ዘረፋ እንደቋሚ ሥራ ቆጥረው የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ኅሣዎችንና ጥቂት ሕገ-ወጦችን ለመቆጣጠርና ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ ለማድረግ ጠንካራ የሆነ የመንግሥት ሕግ-አስከባሪ አካልና ሥርዓት አለመኖሩና አለመዘርጋቱ፣
- መንግሥት በየእርከኑ ያሉትን አስተዳደራዊ መዋቅሮችን አሠራር መቆጣጠርና ማስተካከል አለመቻሉና ትኩረቱም አናሳ ሆኖ መታየቱ፣
- የቀበሌ ገ/ማህበራት አመራር አካላት በነፃ ሕዝብን የሚያገለግሉና በሕዝብና በመንግሥት መካከል ድልድይ በመሆን የሚያገለግሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለኑሯቸው ገቢ ለማግኘት የሚያስችላቸውን ሥራ መሥራትና ሁኔታዎችን መፍጠርና ማመቻቸት ግድ የሚሆንባቸው በመሆኑ ሳቢያ ሁለቱን ኃላፊነቶች ጤናማ በሆነ አካሄድ ጐን ለጐን ማካሄድ የመቻላቸው ጉዳይ የአሠራር ችግር ያለበት መሆኑ፣
- የቀበሌ ገበሬ ማህበርና የከነማ ም/ቤቶች ተመራጮች የሥራ ዘመን ረዥም መሆን አሠራር ላይ ችግር ያለበት መሆኑ፣

CCRDA

13. ድህነትን ለመቀነስ ወደፊት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችና በየደረጃው ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች

(ከመረዳና ከክልል ምክክር የተገኘ)

13.1 በጎ/ሰቡ

- ከጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ባሕሎች በመላቀቅ፣ በማስወገድና የሥራ ተነሳሽነትን ማዳበር፣
- የቁጠባ ባሕልን ማዳበር፣ ከተረጂነት ለመላቀቅ መጣር፣ በራስ መተማመንን ማዳበር፣
- ቋሚ የሆኑ ማህበራዊ ዕሴቶችን አደራጅቶ፣ አዳብሮና አጠናክሮ መጠቀም፣
- ቋሚ የገቢ ማስገኛ ምንጮችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣
- በማህበር በመደራጀትና በመጠናከር መሥራት፣ ዘወትር የመንግሥትን እጅ አለመጠበቅ፣ ከመንግሥት ጐን በመቆም ለልማት ዕገዛ ማድረግ፣
- መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር አብሮ በቅንጅት የመሥራትን ባሕልና ልምድ ማዳበር፣ ጠቃሚ የልማት ሀሳቦችን ማፍለቅ፣
- ሰላም የልማት መሠረት እንደመሆኑ በጐሳዎች መካከል መተማመን፣ መተሳሰብና አብሮ የመሥራት ባሕል እንዲጐለብት መጣር፣ በጋራ በሚገኙ ጥቅሞችና አገልግሎቶች ላይ የባለቤትነትና የተጠቃሚነት እኩልነትና ፍትሐዊነት እንዲሰፍን ማድረግ፣
- አካባቢን መጠበቅ፣ መንከባከብና፣ ማልማት፣
- በብድር አገልግሎት በሥርዓት መጠቀም፣
- ከአጐራባች ብሔርና ብሔረሰብ ሽማግሌዎች ጋር በቅርብ ተገናኝቶ በመነጋገርና በመመካከር የርስበርስ ግጭቶችን መግታት፣ በአካባቢው ዘላቂ ሰላም ማስፈን
- የደን ቃጠሎን ማስቀረትና፣ ማውገዝ፣
- በዕድሮች ያለው ገንዘብ ለአካባቢው የተቀናጀ ልማት እንዲውል ማድረግ::
- በመንግስትና በመያድ የሚሰሩ የልማት ፕሮጀክቶችን ህብረተሰቡ ለይቶ እንዲ.ያውቅና አፈፃፀሙን እንዲከታተል ማድረግ

CGRDA

13.2 <u>በመንግሥት</u>

- የኤች አይቪ በሽታን ለመቀነስ ህብረተሰቡን ያሳተፈ የማስተማር የመከላከል አመራር ተግባራዊ ማድረግ
- የወባ የታይፎይድ የማጅራት ገትር ወረርሽኝ በሽታዎችን ለመከላከል የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎች መከናወን
- የምርምር ተቋማት የክልሉን የልማት ችግሮችን አቅጣጫዎችን በማመልከት ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ
- በክልሉ ባሉ ሐይቆች የአጠቃቀምና አስተዳደርን ባለቤት በመወሰን ገደብና ሥርዓት የለሽ የአሣ ማጥመድ ሥራ ቁጥጥር እንዲደረግበት ማድረግ ደንብ ማውጣት
- ከተቀረፁ ፖሊሲዎች ውስጥ የአካበቢ ፖሊሲ በክልሉ መንግስት ፀድቆ በመመናመንና በመውደም ላይ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ህዝብን ባሳተፈ ሁኔታ ለመጠበቅ በአግባቡ መጠቀም እንዲችል ፖሊሲው ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ማድረግ
- ከውጭ ሀገር ለደሀው ህብረተሰብ በቀጥታ የሚላኩ የትምህርት/መሣሪያዎች እንዲሁም መድሀኒቶች ከቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡበት ሁኔታ መፍጠር
- የውጭ ምንዛሪን ከማሣደግ አንፃር ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ መስፋፋት ምክንያት የሚሆኑ የውሃ፣ የደን፣ የዱር እንስሳት ሀብትን በመጠበቅ የመሠረተ ልማት መዋቅር በአካባቢው ማልማት
- በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታየው የባልና ሚስት ክርክር ጊዜ የሚፈጅ ስለሆነ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የተገናዘበ የቤተሰብ ሕግ በየአካባቢው /ዞን/ ተረቆ ተግባራዊ የሚሆንበት ሁኔታ ማመቻቸት
- የልማት በጀት በየደረጃው በህዝቡ እንዲታወቅና ቁጥጥር እንዲደረግበት ሁኔታዎች ማመቻቸት
- የሀገር ልማት ፀር ነው ከሚባለው የሙስና አሠራር በብቃት የምንከላከልበትን ዘዴ በመሻትና ፀረ-ልማት መሆኑን ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- የውሃ ሀብት አጠቃቀምን በማሻሻል በዝናብ አጠር አካባቢዎች በአመት ሁለትና ሦስት ጊዜ በማምረት ምርትን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ
- በመንግስትና በመያድ የተገበሩ እንዳንድ ልማቶች ብዙ በጀት ፈሰባቸው ከፍተሜ ሳይደርሱ መቅረታቸው /እንደ ሀሬ መስኖልማት/ አሳሳቢ ስለሆነ ልማቱ ሲጀመር ህብረተሰቡን ያሳተፉ በቂ ጥናት ላይ መሠረት አድርጉ መነሳትና መተግበር
- የአካባቢው ኢኮሎጂና የአርሶ አደሩን ፍላጐት ያገናዘበ የኤክስቴንሽን መርሀግብር በጥራትና በብቃት ማስፋፋት
- ለየአካባቢው አፈር የሚስማማ ግብአትና ምርጥ ዘር ማቅረብ

CCRDA

- ከማዳበሪያ ጐን ለጐን Organic ማዳበሪያና Fertileser እንዲለምድ ማድረግ
- የአርብቶ አደሩን የኢኮኖሚ ማህበራዊ ፍላጐትና ጥያቄን መሠረት ያደረገ ስትራቴጂ /ፖሊሲ/ ማውጣትና መተግበር
- የዘር ማባዣ ድርጅቶችና ምርምር ተቋማት በአጭር ጊዜ ሊደርሱ የሚችሉ ዝርያዎችን በሁሉም ዐይነት ለገበሬው በብድር አገልግሎት ሊያቀርቡ የሚችሉበት ሁኔታ ማመቻቸት
- ከቡና ምርት በተጨማሪ በሌሎች ሰብሎች ላይ/እንደቅባት ሰብሎች ለወጪ ምርት ገበያ የሚመረትበት አማራጭ መፍጠር /Moncorop-Diversification/
- የባንኮች የብድር አሠጣጥ የቤት ችግር ላለበት የሚጠየቀው የወለድ መጠን ከፍተኛ ስለሆነ ደንበኞችን ሊያስተናግድ የሚችል የአሠራር ፖሊሲ ለወጥ ማድረግ
- የሚተገበሩ ፖሊሲዎች አፈፃፀማቸው እየታየ ውጤታማ ሳይሁኑ ሲቀሩ በወቅቱ የሚሻሻልበት ሁኔታ ማመቻቸት
- ከገጠር ወደ ከተማ ያለው ከፍተኛ ፍልሰት መንስኤውን በማጥናት መሠረታዊ መፍተሄ መፈለግ
- የትምህርት ፖሊሲ አፈፃፀምን ከየወረዳዎች የት/ቤት ስርጭት የሕዝብ አሰፋፈርና የኑሮ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ማድረግ
- በሕዝብ ብዛት ዕድገት ምክንያት የሚከሰተውን የመሬት ጥበትና ጫና ለመቀነስ የሴቶችን ትምህርት ተሳትፎ በማሳደግ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ማሰፋፋትና እንዲሁም በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሠፈራ ፕሮግራም ማካሄድ ሌሎች ከአርሻ ሥራ ዉጭ የሆኑ ሥራዎች ማስፋፋት
- ግልፅነትና፣ መተማመንን በመርሆነት መከተል፣ ከጎ/ሰቡ የሚፈልቁ ሀሳቦችን መቀበል፣ ዘመናዊ የአርሻ ዘዴን ማስፋፋት፣ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማስረጽ፣
- የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብና ግልግት::
- ለወጪ ምርቶች ትኩረት መስጠት፣ በብዛትና በጥራት ለገበያ እንዲቀርቡ ማድረግ፣
- እርሶ አደሩ ላመረታቸው የግብርና ምርቶች ገበያ ማፈላለግ፣ መፍጠር፣
- የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ማውጣት፣
- ዙሪያት ላይ የተመሠረተ የጎ/ሰቡን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና ያሳመነ የሰፈራ ፕሮግራሞች ማካሄድ::
- የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮችን ለማቃለልና ለመቆጣጠር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ ማደራጀት፣ የምግብና የመድሃኒት መጠባበቂያ ክምችት መፍጠር፣

GCRDA

- ጠቃሚ የልማት ሀሳቦችን መቀበልና በሥራ መተርጐም፣
- የኅ/ሰቡን የገቢ ምንጭ ለማሳደግ የኑሮ መሠረቱን የተመረኮዘ የልማት ስትራቴጂ መቀየስ፣
- የመገናኛ አውታሮችን በተለይም መንገድን ማስፋፋት፣
- በፕሮጀክቶች ሂደት ከቀረጻ እስከ ትግበራ የኅ/ሰብ ተሳትፎ እንዲጐለብት ማድረግ፣
- ኢንዱስትሪዎችን በተቻለ መጠን በማስፋፋት የሥራ አጦችን ቁጥር መቀነስ፣
- የኅ/ሥራ ማህበራትንና ዩኒየኖችን ማደራጀት፣
- የቀ/ገ/ማህበራት አመራር አባላት በመንግሥትና በኅ/ሰቡ መካከል ሆነው እንደድልድይ የሚያገለግሉ ናቸው እነዚህ አካላት ገበሬዎች እንደመሆናቸው የራሳቸውንም የግብርና ሥራ ያከናውናሉ :: ሁለቱን ጐን ለጐን ማካሄድ ደግሞ አስቸጋሪ ነው :: በመሆኑም የአፈጻጸም ችግር ይታይል፣ የሚፈለገው ሥራ አይከናወንም:: ስለዚህ ክፍያ የሚያገኙበት መንገድ መፈለግ/ መተግበር፣
- በብሔረሰብ ተዋጽኦ ሰበብ ብቃት የሌላቸውን ሰዎች በአመራርና ወሳኝ ቦታ አለመመደብ፣
- ሙስናን ለመቆጣጠር ስልት መቀየስ፣ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ፣
- ለመያድ አመቺ የሥራ ሁኔታ መፍጠር /በፍቃድ አሰጣጥ በምዝገባ
- መያድና የሲቪል ማህብረተሰብ ተቋሞች አንዲሰፋፉና እንዲጠናከሩ ድጋፍ መስጠት
- በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የሲቪል ማህበረሰብና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ቀጥተኛ ተሳትፎ መኖሩን ማረጋገጥ
- በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን ሥርጭት ሚዛዊ እንዲሆን ማድረግ
- በልማት ሀይሎች ድግግሞሽ የሌለበት የተቀናጀ የልማት ሥራ እንዲኖር ጥረት ማድረግ
- ከመያዶች አሠራር ለመማር /ልምድ ለመለዋወጥ/ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ለምሳሌ/ተሳትፎአዊ አሠራሮች አማራጭ የአሠራር ሞዴሎች/
- ትልልቅ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ለአነስተኛ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ትኩረትና ድጋፍ መስጠት የብድር አገልግሎተ መስጠት
- ባንኮች የብድር አገልግሎት ሲሰጡ በጥናት ላይ የተመሠረተ ቢሆን
- የባንክ የብድር ወለድ (Interstrate) ቢቀነስ
- የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በግብአቶች አቅርቦት የሚሰታፉበት ሁኔታ ቢጠናከር

<u>ወጣቶችንና ሴቶችን በተመለከተ</u>

- በክልላችን የሴቶች የመሬት ባለ ይዞታነት መብት ጉዳይ በህግ እንዲረጋገጥ ማድረግ
- ሴቶች በልማት አስተዋፅአ እንዲያበረክቱ በሙያና በዕቃ ማህበራት ማደራጀት
- የስነ ጤና ተዋልዶ አገልግሎት ለሁሉም ሴቶች ማዳረስ

CCRDA

- ሥራአጥ ወጣቶች በራሳቸው ጥረትና በመንግሥትናበበመያድ ድጋፍ በአነስተኛ ዕደ ጥበብ ሥራ የሚሠለጥኑበት ሁኔታ መፍጠር
- ከቴክኒክ ሙያ ማሠልጠኛ የተመረቁ በማህበር እየተደራጁ የገንዘብ ብድር አግኝተው ቢሠሩ የሥራ ቦታም ከሊዝ ነፃ ቦታ እንዲያገኙ ማድረግ

<u>ከሲቪክ ማህበረሰብና ግል ክ/ኢኮኖሚ ምክክር የተገኘ</u>

- ምንም እንኳ አብዛኛው ህብረተሰብ የሚገኘው በገጠር ቢሆንም በዘላቂነት ችግሮች ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በከተሞች ልማት ላይም ትኩረት መስጠት
- ድህነትን በማቃለሉ ሂደት ከማህበረሰቡ ለተገሉ እንደጎዳና ተዳዳሪዎች ሴትኛ አዳሪዎችና ረዳት የሌላቸው አዛውንቶች የመልሶ ማቋቋሚያና ስልት በመንጫት እንዲዘጋጁ ማድረግ
- የኤች አይቪ ኤይድስና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ተዕዕኖዎች ድህነትን ለማቃለል ብሎም ዘላቂ ልማትን ለማምጣት እንቅፋት በመሆናቸው መንግስት የሲቪል ማህብረሰብ ድርጅቶችን በማስተባበር ለችግሮች መፍትሄ መስጠት
- የግሉ ኢንቨስትመንት ስራ አጥነትን በማቃለልና ድህነትን በማስወገድ ሂደት ጉልህ ሚና ስላለው የሚታዩትን የፖሊሲና የአሠራር ማነቆዎችን መንግስት እንዲያስወግድ

13.3 <u>መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፡-</u>

- የጎ/ሰቡን ተሳትፎ በየደረጃው ማጐልበት፣ ከጎ/ሰቡ ጋር መሥራት፣
- መንግሥት ባልደረሰባቸውና ሊደርስ በማይችልባቸው መስኮችና ሴክተሮች በመመካከር መሳተፍ፣ ከመንግሥታዊ የሥራ ዕቅድና ፕሮግራም ጋራ መቀናጀት፣
- ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ባሕሎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ ሥልቶችን መቀየስና ጎ/ሰቡን ማስተማር::
- የሥራ አጥነትን ችግር ለመቅረፍ ገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችን መቅረጽ::
- ተሳትፎአዊ የልማት አሠራር ትኩረት መስጠት
- ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ማዳበር
- ዕረዳታንና ልማትን ማገናኘት (Link Relief with Development)
- ለሴቶችና ለህፃናት ትኩረት መስጠት
- የሚካሄዱት የልማት ሥራዎች በሕብረተሰቡ ሕይወት ለውጥ ማምጣቱንና አለማምጣቱን በቅርብ መከታተል (I mpact assesment)
- በበጀት አጠቃቀም በኩል የሚታዩ ችግሮችን ማሻሻል

CCRDA

- ለመንግስት ተቋማት የአቅም ግንባታ መስጠት የሙያና የፋይናንስ ድጋፍ መስጠት
- ሀገር በቀል መያዶች የሲቪክ ማህበረሰብ ተቋሞች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ማድረግ
- በሰብአዊ መብትና ዲሞክራሲያዊ ሂደት የህብረተሰቡ ተሳትፎን ማጠናከር
- የሕብረት ሥራ ማህበራትና ባህላዊ ተቋሞችን /ዕቁብ/ የመሣሠሉ ተቋማት በመጠቀም በገጠርና በከተማ የቁጠባና የብድር አገልግሎት ማስፋፋት
- የመንግሥት አቅም ውሱን በሆነባቸው አካባቢዎች አገልግሎት መስጠት
- የገቢ ምንጭን ሊያሳዱጉ የሚችሉ Off farm ሥራዎችን ማስፋፋት
- በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት ሥራዎች በቂ ትኩረት ማድረግ
- የሥራ ተነሣሽነት እንዲኖር የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ማስተማር
- በእርሻ ምርምርና በኤክስቴንሽን መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር
- Origanic Fertilizer አጠቃቀም ማስፋፋት
- በአነስተኛ ኢንዱስትራዎችና የንግድና ኢንዱስትሪ ሴክተር ድጋፍ በመስጠት ማጠናከር
- የሴቶች መብት እንዲከበር ድጋፍ መስጠት ምሣሌ የመሬት ባለቤትነትና ጐጂ ባህላዊ አሠራሮችን እንዲለወጡ ማድረግ
- ባህላዊ የሆኑ ተቋሞች /ዕድር፣ ደቦ፣ ጅጌ እቁብ/ የመሣሠሉትን ማጠናከር በልማት ሥራ እዲሰፉፉ ማድረግ
- የህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር በመንግስትና ደኢሕልማ መካከል የልምድ ልውውጥ በማድረግ አሠራሩን ማሻሻል

13.4 በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

- ከፍተኛ ትም/ተቋማት ድህነት ለመቀነስና ልማትን ለማስመዝገብ አለማቸው አድርገው መነሣት ይኖርባቸዋል
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ካረኩለም ሕብረተሰቡን በተለይም ገጠር ነዋሪ የሆኑውን ማዕከል ባደረገ ሁኔታ መቅረፅና መተግበር
- የትምህርቱ አሰጣጥና የተመራቂው ትም/ዝግጅት ለድህነት ቅነሣና ለሀገር ዕድገት አስተዋፅኦ እንዲሰጥ የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ
- የከፍተኛ ትም/ተቋማት መምህራንም ሆነ ተማሪው የህብረተሰቡ አካል እንደመሆናቸው መጠን ይህንንም ተረድተው የህብረተሰቡን ኑሮ ለመለወጥ ዝግጁ ሆነዉ ችግሩን ቢጋሩ መወጣት
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማይገናኝ የሀሳብ መስመር የተሰማሩ ወይም በማንብ የታጠሩ « Ivory Towers » ሳይሆኑ ከህብረተሰቡ ጋር ተቆራኝተው የሚሠሩ የለውጥ ማዕከላት መሆን ይኖርባቸዋል

CCRDA

- የከፍተኛ ትም/ተቋማት ካሪኩለም ለልማትና ለዕድገት እንቅፋት የሆኑትን ጐጂ ባህሎች ልማዶች አስተሳሰቦችና አመለካከቶች እንዲወገዱ የሚያስችል መሆን ይገባዋል
- የከፍተኛ ትም/ተቋማት ካሪኩለም በየጊዜው እየተፈተሸ ድህነትን ለመቀነስ ተኽኒነት እና ዝግጁነት ያላቸው የሥራ ክቡርነትን የሚያምኑ ባለሙያዎችን የሚያፈራ መሆን ይኖርበታል
- ከፍተኛ ትም/ተቋማት የሚያከናውኑት ምርምር በህብረተሰቡ ችግር ላይ ያነጣጠረ ዘለቂታዊ መፍትሄ እንዲሰጥ ፋይዳ ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ከመንግስት ከመያድና ከህብረተሰቡ እና ከግሉ /Stake Holders/ ጋር በቁርኝት መሥራት ይኖርባቸዋል የምርምር ውጤቶችም ወደ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ፪ልቆ መግባት ያኖርበታል
- በከፍተኛ ትም/ተቋሞት አንዴ ገብቶ ሠልጥኖ መውጣት ብቻውን በቂ እንደማይሆንና ተከታታይነት ያለው ሥልጠና /Continuing Education/ ካልተሰጠ Continued ingnorance ስለሚፈጠር ለሥራ ላይ ሥልጠና ትኩረት ማድረግ
- ከፍተኛ ትም/ተቋማት የህብረተሰብ ኑሮ በዘለቂታዊነት እንዲለወጥ Research Consultancy ማድረግ አለባቸው
- ከፍተኛ ትም/ተቋማት ስለ ድህነት ምንነት፣ መገለጫዎች ግዝፈትና Intervention Strategies በተመለከተ ቀጣይነት ባለውና ሲስተማቲክ በሆነ ሁኔታ የተሰያዩ አማራጮችን፣ ማለትም ፓናል ውይይቶችን፣ ሲሚናሮች ሲምፖዚይሞች፣ ፅሑፎች ቅስቀሣዎችና የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ግንዛቤ ማስጨበጥ ይኖርባቸዋል
- ድህነትን ለመቀነስ ፖሊሢ ሲቀረፅ ስትራቴጂ ስነዶች ሲዘጋጁ ከፍተኛ ትም/ተቋማት ከማቀድ ጀምሮ ከመንግስት ከመያድ ጋር በአጋርነት መሥራት ይኖርባቸዋል

13.5 በሃይማኖት ድርጅቶች

- የሃይማኖት ተቋማት በአደገኛ ሁኔታ በመጨመር ላይ ስላለውና በአጭር ጊዜ በመስፋፋት ላይ ስላለው HIV AIDS በሽታ መከላከል የማስተማር ሥራ መጠናከር
- የአምልኮ ነፃነት ሕገመንግስታዊ መብት እንደመሆኑ መጠን በጥንቃቄ እስከተያዘ ድህነትን ለመቀነስና መልካም ዜጋ ለመፍጠር ጠቃሚ ነው
- ትክክለኛ ስብዕና ያላቸው ወጣቶችን ለመፍጠር ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረውን Moral Education /ግብረገብነት/ እንደገና አደራጅቶ መስጠት

- የሃይማኖት ተቋማት ከሚኖራቸው Spritual values and roles በተጨማሪ ልማትን በማስመዝገብ፣ መልካም ዜጋ በማፍራት ጐጂ ባህሎችን በማስወገድ ብሎም ድህነትን ለመቀነስ እንደ አላማ በማድረግ በተጠናከረ ሁኔታ መንቀሳቀስ

CCRDA

- የሃይማኖት Denominations በየሠፈሩ ማበርከት ይህም በሥራ አገርን ለመለወጥ የሚችሉትን በተለይም ወጣቶች በአብዛኛው ጊዜ በሃይማኖት ትምህርትና ሌሎች ፕሮግራሞች እንዲያስልፉ የሚያደርገውን ሥርዐት መለወጥና ብዙ ጊዜያቸውን ለሥራ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ

13.6 በታዋቂ ግለሰቦች

- ታዋቂ ግለሰቦች ማለት ታዋቂ ምሁራንን የአገር ሽማግሌዎች ሙዚቀኞች የጦር መሪዎች

ገበሬዎች ኮከብ ላብ አደሮች ሲሆኑ በተሰማሩበት የሥራ ድርሻ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ወገኖች ናቸው ስለዚህም

- ታዋቂ ግለሰቦች ድህነትን ለመቀነስ ጐጂ ባህሎችን ለማስወገድ በሚነደፈው ስልታዊ ዕቅድ እና ስትራቴጂ ከመንግስትና መያድ ጋር በቁርኝት ከጥንስሱ ጀምሮ በአተገባበር እና በአገማገም (Monitoring an Evaluation) ሥራ የሚሰሩበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል
- ታዋቂ ገለሰቦች በፖለሚ አቀራረፅ እና የተቀረፁትን በመፈተሽ ረገድ የተሻለ ድርሻ እንዲያበረክቱ ይጠበቃል
- ታዋቂ ግለሰቦች ድህነትን ለመቀነስ ሕብረተሰቡን በሰፊው ማስተማርና ማስተባበር አለባቸው መንግስትም በዚህ በጐ ሥራ ላይ ከሚሳተፉ ታዋቂ ግለሰቦች ጋር እንደ አጋር ቆጥሮ መሥራት አለበት

13.7ሠላም ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ማስፈን

ባለፈው የአምስት አመት የልማት የሠላምና የዲሞክራሲ መርሃ ግብር አፈፃፀም ግምገማ መሠረት እንደተመለከተው ድህነትን ለማቃለል ሕዝብ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ኢኮኖሚያ እድገት ለማረጋገጥ ዘላቂነቱ የሚያስተማምን ሠላምና መረጋጋትን መፍጠር አብይ ተግባር ነበር:: ይህም በሕዝቡ ዙሪያ መለስ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲ ስርዓት መመስረትና ሠላምን ማረጋጋት በጥብቅ የተሣሠሩ ናቸው :: ክንዋኔዎቹም:-

- የሕዝቦችን እኩልነትና አንድነትን የማረጋጋጥ ተጋባራት
- ሕዝቦች ራሳቸውን ለማስተዳደር ያላቸውን አቅም ለማጉልበት የተሰሩ ስራዎች
- በክልሎች መካካል የተመጣጠነ እድገት እንዲኖር የተከናወነ ሥራ
- በሕዝቦች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዲኖር የተከዚደ ትግል
- ዲሞክራሲያዊ መንግስታዊ መዋቅሮችን የማጉልበት ሥራ
- የዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲስፋፋ የተደረገ ጥረት

CCRDA

- በሕዝብ ተሳተፎ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲን የመገንባት ስራ ናቸው እነዚህ ዲሞክራሲና አስተዳደራዊ ተግባራት ከሙላ ጉደል አጥጋቢ ሊባል የሚችል ውጤት እንደተገኘ በሠነዱ ተመልክቷል::

ይሁን እንጂ በአለፉት አመታት ተገቢ ጥረት ቢደረግም ፍፁም ዲሞክራሲ ሰፍኗል አስተዳደራዊ በደል የለም ከሙስና የፀዳ አስተዳደር ነበር ማለት ያዳግታል፣ ስለዚህም ፀያቃ አድልዎ (Gender inequltiy) በሰብአዊ መብት ችግር (Poroblems of human Right) አስተዳደራዊ ችግሮችና ሙስና (Administrative Problems and Corruption) የመስራያ ቤት የቡሮክራሲ ችግሮች (Institutional Injustice) ነበሩ:: በእነዚህ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ፀር ከሆኑ ክስተቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የለውጡን ሂደት ባይገቱትም በልማቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል :: ስለዚህም መስተካከልና ወይም መደረግ ያለበት:-

<u>ዲሞክራሲን በተመለከተ</u>

- በሕዝባዊ ስልጣን ስም በአንዳንድ አካባቢዎች አልፎ አልፎ ሥልጣን የሚይዙት ለሕዝብ አገልግሎት ከመሰጠት ይልቅ በብሔረሰብ መብት ስም በዘመድና በጐሣ ጥበቅ መገኘትን ማስተካከል
- ለድህነት ቅነሣ ሠላም ዲሞክራሲና ፍትህ አስፍላጊ በመሆናቸው መንግስት ጥበቃ እንዲያደርግላቸው
- ለህዝቡ ህገ መንግስታዊ መብቱንና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ማሣወቅ እንደሚገባ
- የመንግስትን ሥራ ለሕዝቡ ማሣወቅ አስፈላጊ እንዲሆነ
- በዲሞክራሲ ስም በአግባቡ ባለመጠቀም የተሳሰተ ግንዛቤ በመተርጐም የእኩልነትን መብት መፈታተኑን ወደፊት ተከታትሎ ማስተካከል
- ሕብረተሰብ በራሱ ጉዳይ እንዲወሰን ማድረግን ማጠናከር
- በሴቶች ጠለፋ ላይ ወንጀሉ ሳይጣራ ለረጅም ጊዜ መታሰር እና ዋስ ከከተማ እንጂ ከገጠር ነዋሪ ቢያቀርብ ተቀባያነት ማጣት የፍትሕ መዛባት ስለሚያስከትል ተገቢ መፍትሄ መስጠት::

<u>ሠላምን በተመለከተ</u>

- የአርብቶ አደር ህብረተሰብ ውሃና ግጦሽ ለመፈለግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚፈጠረው ግጭትና በሀገር ሽማግሌዎች ወቅታዊ መፍትሄ መፈለግ

- የጐሣ ግጭቶች ንብረትን በማውደም ለድህነት መንስኤ በመሆናቸው ተከታትሎ በጥንቃቄ አስቀድሞ መፍትሄ መሻት

CCRDA

- የጐሣ ግጭቶች አልፎ አልፎ በአስተዳደር ላይ የተመደቡት በሚፈጥሩት ጠቅላላ የተመሠረተ በመሆኑ በበላይ አካል የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ

<u>መልካም አስተዳደር በተመለከተ</u>

ሕዝብ የተሰጠውን ዲሞክራሲያዊ መብት አስፈፃሚ

- በመንግስት የሚወጡ ሕጐችን ፖሊሲዎችን መመሪያዎችን በአግባቡ አስተዳደራዊ አስፈፃሚ
- ለዘጐች የተሰጠትን ሰብአዊ መብቶች አስከባሪ
- ሕዝብን በእኩልነት ማያት የሚችል
- ሕዝብን የማልማት እንዲሁም በአንፃሩ
- የሕዝብን ሀብት የሚጠብቅና የሚያስጠብቅ ነው

<u>መወሰድ ያለበት መፍትሄ</u>

- በደሀ ሕዝብ ስም በፕሮጀክት የሚመጠን ገንዘብ በቢሮ አካባቢ በሚገኙ White Collaat Criminals የሚበላበትን ሁኔታ በመልካም አስተዳደር ማስወገድ
- መልካም አስተዳደር ሥራና ሠራተኛን የሚያገናኝ መሆን እንዳለበት
- ለመ·ያዊ ዕውቀት ቅድሚያ በመስጠት ጠባብነት በማስወገድ ኢትዮጵያዊነት ማዳበር
- ሀገርን ከድህነት ለማላቀቅ በሁሉም ዘርፍ ተነሣሽነትን የሚያዳብሩ ስልቶችን መጠቀም
- ሠላም ዲሞክራሲዊ መልካም አስተዳደር የመንግስት መገለጫዎች ናቸው ስለሆነም መንግስት ሊያተኩርባቸውና ሊከታተላቸው ሊቆጣጠራቸው ይገባል
- የሠላም ዲሞክራሲ መልካም አስተዳደር ቀውስ ለድህነት ዋና መንስኤ ይሆናሉ በአግባቡ ከተያዙ ለድህነት ቅነሣ ዋና መድህኒት እንደሆኑ በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ::
- በመልካም አስተዳደር የሚመደቡ
- በጥሩ ሥነ ምግባር የታነፁ
- ከሙስና የፀዱ
- መመሪያ ተረድተው የሚተግብሩ
- ግልፅነትንና ተጠያቂነት የሚሰማቸው መሆን እንደሚገባቸውና መንግስትም በቂ ክትትል እንዲያደርግ

CCRDA

- በሰው ሃይል አጠቃቀም የጐላ ችግር እንዳለ ስለሚታወቅ እያንዳንዱ ዞን የራሱን የሰለጠ ነ የሰው ሃይል ብቻ መጠቀም አለመቻሉ ታውቆ ወደፊት የአሠራር ለውጥ በማድረግ መፍትሄ መሻት
- ሴቶች በዓታ ብቻ ሳይሆን በሥርዓተ ዓታ መሠረት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ላይ እንዲሳተፉ ድጋፍ ቢሰጣቸው
- አንዳንድ ባለሥልጣኖች በርካታ ጉድለት ፈፅመው ሳይነኩ መቀመጣቸውም መንግስቱ አውቆ ወደፊት በተመሳሳይ እንዳይደገም ማድረግ
- በክልሉ ባሉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ በተመጣጠነ ዕድገት የሚካሄድበት ሁኔታ ለመፍጠር የክልሉ መንግስት አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርግ
- ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው የክልላችን 57 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ቀጣይ ልማት ለማምጣት እንዲችል ከሕዝብ ብዛቱና ከልማት ደረጃው አንፃር የተገናዘበ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ከማዕከላዊ መንግስት እንዲያገኝ የተለያየ ጥረት ማድረግ የክልል መንግሥትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች ጥረት ቢያደርጉ
- በመንግስትና በሕዝብ መካከል እንደድልድይ ሆነው የደረጃው የአስተዳደርና የልማቱን ሥራ በማስተባበር ደረጃ ላይ ያሉት አካላት የተጣለባቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲወጡ ተከታታይ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የተጠያቂነት አሠራር እንዲሰፍን ማድረግ
- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በማንኛውም አካባቢ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖርና የመሥራች ሕገመንግሥታዊ መብቱን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶችን ይበልጥ ማጠናከር
- ሕዝብን በአግባቡ ለማስተዳደርና የልማት ተቋዳሽ ለማድረግ የወጡት ሕገመንግስታዊ ደንቦች አዋጆች መመሪያዎች እየተከታተሉ ይበልጥ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- የትምህርት ችሎታና የስራ መደብ ላይ ሲሰራበት የነበረው የብሔረሰብ ገደብ አሠራር የባለሙያ ፍልሰትን /attrition rate በማባባስ በልማቱ ጥረት ላይ አሉታዊ መፅዕኖ እንዲያሳድር አሠራሩን ማሻሻል::

GCRDA

14. የመረጃ ግኝቶች

በናሙና በተመረጡ ወረዳዎች ከድህው ህብረተሰብ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚጠቁመው የልማት ሀይሎች /ህብረተሰቡ ራሱ፣ መንግስት፣ መያድ፣ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ለጋሾች፣ ወዘተ/ ሕብረተሰቡ በቅደም ተከተል ባስቀመጠው ችግሮች አሳሳቢነት መሠረት ያሉትን ፖሊሣዊች በመተግበር ፖሊሣዎችን በማሻሻል ወይም አዲስ ፖሊሢ በመቅረፅና የድህነት ማቃለያ ስትራቴጂ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መግባት ዐቢይ ተግባር ነው። ለድህነት መንስኤ የሆኑ ዐቢይ ችግሮች በየወረዳዎቹ የተቀመጡ ሲሆን የልማት ቅደም ተከተል አንደወረዳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ለማመልከት ጥረት ተደርጓል ይህን መሠረት በማድረግም የአብዛኛዎቹን ወረዳዎች መሠረታዊ የድህነት ችግር መንስኤና የልማት ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ከመረጃው ማጠቃለል ተችሏል

- ለአብዛኛዎቹ ወረዳዎች አሳሳቢ ችግር የእርሻ መሬት ጥበት ነው ይህም ከህዝብ ብዛት መጨመር ጋር የተያያዘ ሲሆን በገጠሩ ችግሩ በመባባሱ አብዛኛው ሕዝብ በቂ የምግብ ዋስትና አያገኝም የምግብ ዕጥረቱ፣ በከተማ የሥራ አጥነት ችግር እየተባባሰ መጥቷል ችግሩን ለመቅረፍ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሢ፣ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሢና የሰነ ሕዝብ ፖሊሢ ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅ ተግባር ነው ከዚሁ ጋር በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሠፈራ ፕሮግራም ማካሄድ ሌላው አማራጭ መፍትሄ ነው፡
- ከመሠረታዊ ፍጆታ ግኝት አንፃር በምግብ፣ በንፁህ ውሃና በጤና አገልግሎት በአብዛኛዎች ወረዳዎች ዕጥረት ስለአለ ፍጆታቸው እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ በመባባስም ላይ መሆኑ መረጃው ይጠቁማል በዚህም ስትራቴጂው ለነዚህ ችግሮች መፍትሄ ትኩረት መስጠት አለበት
- የመሠረታዊ ፍጆታ ወቅታዊነት በተመለከተ በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች የምግብ ዕጥረቱ ከሚያዝያ ወር ጀምሮ በክረምት ጭምር የሚከሰት ሲሆን የበሽታ መብዛትና የንፁህ ውሃ ዕጥረት በብዙዎቹ ወረዳዎች በበጋ ወራት የበዛ ነው ፡
- የወረዳዎች የህብት ይዞታና አጠቃቀም በተመለከተ በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች እጅግ አነስተኛ ሲሆን የአንድ ገበሬ የመሬት ይዞታ ከፍተኛ 1.5-2.0 ሄ/ር ሲሆን ዝቅተኛው 0-0.5 ሄ/ር ነው
- የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ለአብዛኛዎቹ ወረዳዎች የግብርና ምርትና ምርታማነት ማነስ ዐቢይ ምክንያቶች የእርሻ መሬት ጥበት፣ አፈር ለምነትና

CCRDA

የዕውቀት ማነስ ማጣትና፣ የገናብ ዕጥረት ናቸው:: በምግብ ሰብል ምርት ራስን ለመቻል ለነዚህ ችግሮች መሠረታዊ መፍትሄ በስትራቴጂው ውስጥ መንደፍ አስፈላጊ ይሆናል::

- ምንም እንኳን የባህል ልዩነቱ የበዛ ቢሆንም በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች በሴቶች ላይ የሚደርሰው የሥራ ጫና ዋነኛው ባህላዊ /ልማዳዊ ተዕዕኖ ነው ከዚህ ውጭ የተንዛዛ የለቅሶና፣ የሠርግ፣ ድግስ፣ ጥሎሽና፣ ጠለፋ መሆናቸውን ወረዳዎቹን የሚያመላክሉና ለድህነት መባባስ ምክንያት የሚሆኑ ልማዳዊ ችግሮች ናቸው
- በመረጃው መሠረት በተፈጥሮና ሠው ሠራሽ ችግሮች አንፃር ካሉት ወረዳዎች አብዛኛዎቹ የድርቅን ችግር ቅድሚያ ሲሰጡት የአፈር መሸርሸር የኤች አይቪ ኤድስ በተከታታይ ከፍተኛ የድህነት መንስኤ እንደሆኑ ተመልክቷል
- በወረዳዎች የልማት ቅደም ተከተል ምርጫ አብዛኛዎቹ ወረዳዎች ለትምህርትና ለጤና ቅድሚያ ሲሰጡ ለግብርና ልማትም እንደዚሁ ትኩረት ሰጥተዋል
- መረጃ በተሰበሰበባቸው ወረዳዎች እንደተመለከተው በከተሞች የሚታየው ቤቅደም ተከተል የገንዘብ ብድር ማግኘት፣ የምግብ፣ የሥራ አጥነትና የመጠለያ ችግር የጐላ ነው::

በአጠቃላይ የወረዳ ምክክር ግኝቱ በእነዚህ ዙሪያ ስትራቴጂውን በመንደፍ ከሁለተኛው አምስት አመቱ የልማት መርሐ ግብር ጋር በማጣጣም በድህነት ላይ ተከታታይ ዘገባውን ለማቃለ የማቃለያ የልማት ማካሄድ ዋነኛው ተግባር ይሆናል::

CCRDA

1. በናሙናነት ከተጠኑ

የወረዳዎች የኑሮ ሁኔታና የችግሮች ቅደም ተከተል ዉጤት

ተ.ቁ	ወረዳ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ
1	ዳሎቻ	የእርሻ በሬ	ገንዘብ	ትዳር	ቋሚ ተክል	ምግብ
2	የኪ	ሠላም	መሬት	ገንዘብ	-	-
3	የም	መሬት	የእንስት ማሳ	የእርሻ በሬ	የወተት ላም	-
4	ወናሳ	መሬት	ምግብ	መጠለያ	-	-
5	ሉማ	በቂ ምግብ	ንፁህ ውሃ	መሬት	የእርሻ በሬ	-
6	ሁምቦ	መሬት	ምግብ	የቤት እንስሳት	ገንዘብ	-
7	ጨንቻ	መሬት	ምግብ	መጠለያ	ገቢ ምንጭ	-
8	አንጋጫ	ህዝብ ብዛት	መሬት ጥበት	ሠላም	ሥራ አጥነት	-
9	ቾሃ	መሬት	እንስት	ከብቶች	በሩና ጫት	-
10	ኮንሶ	ድርቅ	ገንዘብ	መሬት	ህዝብ ብዛት	ሥራ አጥነት
11	አለታወንዶ	የህዝብ ብዛት	መሬት ጥበት	ሥራ አጥነት	በሽታ ድርቅ	ርሃብ

CCRDA

2. የኑሮ ሁኔታ መገለጫዎች ችግሮች በገጠርና በከተማ ቅደም ተከተል

ተ.	ወረዳ	በገጠር	በከተማ
1	ሎማ	በቂ ምግብ ንፁህ ውሃ መሬት	-
2	አንጋጫ	የህዝብ ብዛት መሬት ጥበት ገቢ ማነስ	ገቢ ማነስ፣ መሬት ጥበት ሥራ አጥነት
3	ወናጐ	አልባሳት	-
4	የም	የምግብ ዕጥረት የእንስት ማሣ ልብስ	-
5	የኪ	ሠላም በቂ ገንዘብ መሬት	-
6	ሁምቦ	የምግብ ዕጥረት መሬት ጥበት የቤት እንስሳት እጥረት	በቂ ገንዘብ መጠለያ ምግብ ዕጥረት
7	ዳሎቻ	ቋሚ ተክል፣ የምረቢ ዕጥረት፣ ሥራ አጥነት	-
8	ጨንቻ	ምግብ ዕጥረት ጤና ገንዘብ	ምግብ ሥራ አጥነት ልብስ
9	ቾሃ	መሬት እንስት በቂ ገንዘብ ጤና	-
10	ኮንሶ	ድርቅ በቂ ገንዘብ፣ መሬት	በቂ ገንዘብ ድርቅ
11	አለታወንዶ	ሥራ አጥነት ጤና ድርቅ	-

CORDA

3. በወረዳዎቹ የመሠረታዊ ፍጆታ ግኝት ቅደም ተከተል

ተ.ቁ	ወረዳ	1	2	3	4	5	6
		የምግብ ግኝት	ንፁህ ውሃ	ጤና	መሠረ/ልማት	ትምህርት	መጠለያ
1	የኪ	አነስተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	-	-	-
2	የም	አነስተኛ	ዝቅተኛ	አነስተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	በቂ	
3	ወናጐ	እጅ/ዝቅተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	-	-	እጅግ/ዝቅ
4	ሎማ	እጅ/ዝቅተኛ	እጀ/ዝቅተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	-	-	-
5	ሁምቦ	እጅ/ዝቅተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	በቂ	-
6	ዳሎቻ	አነስተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	-	-	-
7	ጨንቻ	አነስተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	-
8	አንጋጫ	አነስተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	-	-	አነስተኛ
9	ቸሃ	እጅ/ዝቅተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	-	-
10	አለታወንዶ	አነስተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	-	-	-
11	ኮንሶ	አነስተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	-	-
12	ሐመር	እጅ/ዝቅተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	እጅ/ዝቅተኛ	-	-	-

CORDA

ተ.ቁ	ወረዳ	የምግብ ዕጥረት	የንፁህ ውሃ ዕጥረት	ይሰው በሽታ	ይእንስሳት በሽታ	ይሰብል በሽታ	ገንዘብ	ሥራ አጥነት
1	የኪ	ግንቦት - ሰኔ	ጥር - ሰኔ	ሰኔ - ህዳር	መጋቢ -ጥቅምት	ግንቦት-ህዳር	ግንቦት-ነሐሴ	የካቲት
2	አለታወንዶ	ታህሣስ - ነሐሴ	ታህሣስ - መጋቢት	ነሐሴ - ታህሣ	ታህሣ-መጋቢት	-	የብዙ ግምት	አመቱን ሙሉ
3	ኮንሶ	መጋቢት - ግንቦት	ታህሣስ - የካቲት	ሚያዝያ - ነሐሴ	ታህሣስ-የካቲት	ሚያዝ-ሰኔ	-	የብዙ -ግንቦት
4	ሐመር	ታህሣስ - መጋቢት	ታህሣስ - መጋቢት /የግሪሽ ቢታም/	በበጋ	በክረምት	-	-	-
5	ቾሃ	ሚያዝያ - ነሐሴ	-	ጥር - ሰኔ	-	-	ግንቦት-ጥቅምት	ህዳር ሰኔ
6	አንጋጫ	ሚያዝያ - ግንቦት ነሐሴ-መስከረም	ጥር - መጋቢት	ጥቅምት - ግንቦት	መጋቢት-ግንቦት ጥቅምት-ህዳር	-	ሚያዝያ- ህዳር	አመቱን ሙሉ
7	ጨንቻ	ጥቅምት - ህዳር ግንቦት-ሚያዝያ	ታህሣ - መጋቢት	ጥቅምት - የካቲት	የብዙ ግንቦት	-	ሰኔ-ህዳር	አመቱን ሙሉ በከተማዋ-ህ-ገጠ
8	ዳሎቻ	ግንቦት - ነሐሴ	የካቲት - ግንቦት	ሚያዝያ - ግንቦት	መስከረም ሚያዝያ ግንቦት	-	ነሐሴ-ጥቅምት	ዓመቱን ሙሉ
9	ሁምቦ	ሚያዝያ - ሐምሌ	የካቲት - ሰኔ	ሰኔ -ጥቅምት /መጋቢት - ሰኔ/	ጥር -ሚያዝያ /ገንዳ	-	ሚያዝያ-ጥቅምት	ግንቦት- ነሐሴ
10	ሉማ	የካቲት - ግንቦት	ጥር - መጋቢት	መጋቢት - ነሐሴ	ጥር-ግንቦት	-	ግንቦት -ህዳር	ሙሉ አመት
11	ውናጐ	ግንቦት - ጥቅምት	-	ሰኔ - ሐምሌ /ነሐሴ - ጥቅምት/	-	-	-	-
12	የም	ግንቦት - ጥቅምት	ታህሣስ - መጋቢት	ጥቅምት - ታህሣሥ /ሚያዝያ - ግንቦት/	ጥቅምት- ግንቦት	-	ክረምትና መስከረም-ህዳር	ክረምት መስከ-ጥር

CGRDA

5 የወረዳዎች የህብት ይዞታና አጠቃቀም

	ወረዳ	የመሬት ይዞታ በሄ/ር ከፍተኛ - ዝቅተኛ	እህል በኩንታል	የቤት እንስሳት በቁጥር	የሚፋቅ እንስት	ማር ቀፎ	አመታዊ ገቢ
1	ቸሃ	1.5 - <1	-	>6 - <2	ከ70 - <30	-	
2	ሌሙ	1.5 - <.25	-	12 - 1	-	-	
3	የም	2.0 - 0	15 - 2	10 - 1	-	-	120 -855 ብር
4	አንጋጫ	1.5 - 0.5		-	-	-	
5	ኮንሶ	2 - <0.25		-	-	✓	
6	ሐመር	-	8 - 1	2.00 - 30 100 - 20 300 - 40	-	12 - 2	
7	ጨንቻ	2 - 0.062	12 - 5	10 - 1	.25 - 0.001	-	
8	ዳሎቻ	1.5 - 0.5	30 - 6	5 - 1	0.25 - 0.12 ሄ/ክ	-	
9	ሁምቦ	3.75 - 1.5 ቆላ 1.5 - 0.25 ደጋ		✓		-	
10	ሎማ	2.0 - 1.0	-	6 - 1	-	-	
11	ወናጐ	2.0 - 0.25	-	-	-	-	
12	የኪ	2. - 0.5	-	3 - 1	-	-	
13	አለታወንዶ	2.0 - 0.125	-	-	-	-	

CORDA

6. የግብርና ምርታማነት ማነስ ምክንያቶች በቅደም ተከተል

ተ.ቁ	ወረዳ	1	2	3	4	5
1	ዳሎቻ	ዝቡሬ ዕውቀት ማነስ	እርሻ መሬት ዕጥረት	የእርሻ በሬ ዕጥረት	ብድር አገ/የለም	ተባብሷል
2	ሁምቦ	መሬት ጥበት	እርሻ በሬ ዕጥረት	የመሬት ለምነት መቀነስ	የዝናብ ዕጥረት	
3	አንጋጫ	መሬት ለምነት	አፈር መሸርሸር	ኃላቀር አሰተራረስ	የግብአት ዕጥረት	
4	አለታ ወንዶ	የእርሻ መሬት ጥበት	የአፈር ለምነት መቀነስ	የገበሬ ዕውቀት ማነስ	የብድር አገልግሎት አለመኖር	
5	የም	አፈር ለም መቀነስ	መሬት ጥበት	ህዝባዊ ግብአት መውደድ	-	
6	ቸሃ	ቴክኖሎጂ አለመጠቀም አመታዊ ሰብል አለማምረት	የእርሻ በሬ ዕጥረት	በሽታ	የአፈር ለምነት ማጣት	
7	ሐመር	የዝናብ ዕጥረት	ባህላዊ ተዕዕኖዎች	ሥራ አለመኖር	ዘመናዊ የእንስሳት ህብት የለም	
8	ኮንሶ	የዝናብ ዕጥረት	የመሬት ጥበት	የመሬት ለምነት ማጣት	የመሬት ድንጋያማነት ወጣገባነት	
9	ሌሙ	አፈር ለምነት ማጣት	የእርሻ ግብአት ማጣት	የብድር አቅርቦት መጓደል	የሰብል በሽታና አረም	
10	ጨንቻ	የመሬት ጥበት	የአፈር ለምነት	ዕውቀት ማነስ	ግብአት ማነስ	
11	የኪ	የዝቡሬ ዕውቀት ማነስ	የሰብል በሽታ	የብድር አገልግሎት አለመኖር	የመሬት ጥበት	
12	ወናጐ	የገበሬ ዕውቀት ማነስ	የቴክኖሎጂ ተጠ/አለመሆን	የብድር አገልግሎት አለመኖር	መሬት ጥበት	
13	ሎማ	የብድር አገ/ችግር	የመሬት ለም አለመሆን	የግብአት አቅርቦት ችግር		

CCRDA

7.የወረዳዎች ባህላዊና ልማዳዊ ተዕዕኖዎች ቅደም ተከተል

ተ.ቁ	ወረዳ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ
1	እንጋጫ	ለቅሶ	የተንዛዛ ሠርግ	የሴቶች ሥራ ጫና	የቁጠባ ባህል አለመዳበር	
2	ሌሙ	ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች	የለቅሶ ድግስ መንዛዛት	ቀብር መዘግየት	ለበአል የሚወጣ ከአቅም በላይ ወጪ	
3	ኮንሶ	ሴቶች የንብረት ውርስ መብት ማጣት	የተፈታችን ሴት ማግባት	የሠርግ ወጪዎች	መስቀል	
4	ሐመር	ልጅን ገፊ ሚንጊ ብሎ ጫካ መጣል መግደል	ህገወጥ ውርጃ	የሴት ልጅ ጥሎሽ	-	
5	ቸሃ	ፍልሰት ሱሰኝነት	ለመስቀልና አረፋ በአላት ከአቅም በላይ ወጪ	የሴቶች ሥራ ጫና መብዛት	-	
6	ጨንቻ	የቤተሰብ ሠላም ማጣት	የአለቃ ድግስ	በሃይማኖት በአል ሰበብ አለመሥራት	የለቅሶ ቀናት መንዛዛት ድርብ ጋብቻ	
7	ወናጐ	የሠርግ ሥርዓት መንዛዛት የቀብር፡ም " "	ቁጠባ ባህል አለመዳበር	የበአል መብዛት	-	
8	ዳሎቻ	የሴት ልጅ ግርዘት	ያለዕድሚ ጋብቻ ጠለፋ	ውርስ/ሚስቶች	-	
9	ሁምቦ	በአላት መስቀል፣ወጪ የሚያበዛ	ቁጠባ አለመዳበር	የተንዛዛ ለቅሶ ሠርግ	ከትም በላይ ድግስ	
10	የም	የባዕድ አምልኮ መስፋፋት	የሴቶች ጉዳት በጠለፋ ውርጃ	ባህላዊ ድግስ		
11	የኪ	ሴት ልጅ ት/ቤት አለመላክ	የተንዛዛ በአላት መብዛትና	እትምን ያላገናዘበ ድግስ		
12	አለታወንዶ	የተንዛዛ ሠርግ	ጥሎሽ	ጠለፋ	ሴት ልጅ ት/ቤት አለመላክ	
13	ሎማ	የተንዛዛ ለቅሶ ወጪ	የሠርግ ድግስ	የሴቶች ግርዘት ጠለፋ		

CCRDA

8.ተፈጥሮአዊና ሠው ሰራሽ ችግሮች በትደም ተከተል

ተ.ቁ	ወረዳ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ
1	ሎማ	ድርቅ	ኤች አይቪ ኤድስ	የወባ በሽታ	ደን መራቆት	የአፈር መሸርሸር
2	አንጋጫ	ድርቅ	ንፋስአዊ ጉርፍ	የአየር መዛባት	የቤት ቁጠራ	
3	አለታወንዶ	ድርቅ	ወረርሽኝ	ኤች አይቪ ኤድስ	ዘረፋና ሌብነት	
4	የም	ይድንበር ግጭት	ይአፈር መሸርሸር	ይመሬት መንሸራተት	የአየር ሚዛን መዛባት	
5	የኪ	ወባ በሽታ	የ ሰብል ተባይ	ኤች አይቪ ኤድስ	የብሔረሰቦች ግጭት	ድርቅ
6	ወናጐ	ድርቅ	ያለመረጋጋት	ኤች አይቪ ኤድስ	የደን ጭፍጨፋ	ገንዘብን በቁጠባ ያለመጠቀም
7	ሁምቦ	ድርቅ	በሽታ	የሕዝብ ቁጥር መጨመር	የአየር መዛባት	የተፈጥሮ ሀብት መመናመን የደን መራቆት
8	ዳሎቻ	የዝናብ ዕጥረት	አፈር መሸርሸር	ኤች አይቪ ኤድስ	የእንስሳት በሽታ	ደን መጨፍጨፍ
9	ሌሙ	ኤችአይቪ ኤድስ	የፖለቲካ አለመረጋጋት	ድርቅ	የአየር መዛባት /ዝናብ ዕጥረት/	ደን ምንጣሮ
10	ሐመር	ድርቅ	ወረርሽኝ	ይርስበርስ ግጭት		
11	ችሃ	ድርቅ	የእንስሳትና ሰብል በሽታ	ወባ ወረርሽኝ	የቤት ቃጠሎ	
12	ኮንሶ	ድርቅ	የዝናብ ዕጥረት	የእርሻ መሬት ጥበት	የመሬት መከላት	በሽታ

CCRDA

9.የወረዳዎች የልማት ቅደም ተከተል ምርጫ

ተ.ቁ	ወረዳ	ገጠር ወፍጮ	ግብርና	ምንገድ መ/ልማት	ጤና	ትምህርት	መጠጥ ውሃ	ተፈጥሮ ሀብት ጥ/ልማት
1	የኪ		1	-	2	3	-	4
2	የም	4	-	-	2	1	3	5
3	አለታ ወንዶ	-	-	4	2	1	-	3
4	ቸሃ	-	-	3	2	1	4	5
5	አንጋጫ	-	-	-	1	2	-	3
6	ዳሎቻ	-	3	5	2	1	4	3
7	ሎማ	-	1	4	3	2	6	5
8	ሌሙ	-				1		
9	ጪንቻ	-	2	4	3	1	-	-
10	ሁምቦ	-	3	5	2	1	2	4
11	ኮንሶ	-	3	4	2	1	6	5
12	ወናጉ	-	-	3	2	1	4	-

CCRDA

10. የወረዳዎች የከተማ ችግር ቅደም ተከተል

ተ.ቁ	ወረዳ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ
1	አንጋጫ	ሥራ አጥነት	የገቢ ማነስ	ሠላም	የሕዝብ ብዛት	ይመሬት ጥበቻ
2	ወናጐ	ምግብ	መጠለያ	እልባሳት		
3	የም	ምግብ	ቤት	ሱቅ	ልብስ መሬት	እንሰት
4	ሮቢ	ሠላም	ገንዘብ	ምሬት		
5	ሁምቦ	ገንዘብ	ቤት	ሥራ አጥነት	የቤተሰብ ብዛት	ብድር አለማግኘት /ምግብ
6	ዳሎቻ	ትዳር?	ልጆች?	ሠላም	ሥራ አጥነት	ገንዘብ ፍትህ
7	ጨንቻ	መጠለያ	ሥራ አጥነት	ግንዘብ	መሬት	ገቢ ምንጭ
8	ቾሃ	ገንዘብ	ጤና	ት/ቤት	ንፁህ ውሃ	
9	ኮንሶ	ገንዘብ	ድርቅ	ምሬት	ሥራ አጥነት	
10	አለታ ወንዶ	ምሬት ጥበት	ሥራ አጥነት	መጠለያ ችግር		

CCRDA

11 የልማት ሀይሎች ትድግፊ ትኩረት

ወረዳ	በመንግስት	በመያድ	ህዝባዊ ተቋማት	በህብረተሰብ	የሃይማኖት ድርጅት
1.ወናጐ	የመሬት ጥበት ትምህርት ጤና መንገድ /መሠረተ ልማት	ትምህሕርት ጤና መሠረተ ልማት	ትምህርት ጤና መሠረተ ልማት	ቁጠባ ቡና ጥራት መጠበቅ ጋብቻ ላይ ጋብቻ ማገድ ያለዕድሚ ጋብቻ ማገድ	ትምህርት ጤና መሠረተ ልማት ማስፋፋት ኤች አይቪ መከላከል
2.ሁምቦ	ግብርና ትምህርት ጤና አደጋ መከላከል	ግብርና ትምህርት ጤና አደጋ መከላከል	-	-	-
3.ዳሎቻ	ግብርና ትምህርት ጤና መንገድ	ግብርና ትምህርት ጤና መንገድ	ግብርና ትምህርት ጤና መንገድ ውሃ	ግብርና ትምህርት ጤና መንገድ ውሃ	-
4.ሌሙ	ምግብ ዋስትና ውሃ ትምህርት ጤና መንገድ	ምግብ ዋስትና ውሃ ትምህርት ጤና መንገድ	መንገድ ብድርና ቁጠባ ማህበራዊ አገልግሎት		የግብረገብ ትም/መስጠት ስለኤች አይቪ ማስተማር መድሀኒት አልባሳትና ምግብ ማቅረብ
5.የም	የድንበር ግጭት ማስወገድ መሠረተ ልማት ማስፋፋት ተፈጥሮ ሀብት መጠበቅ	ህፃናትና እናቶችን መንከባከብ መዋዕለ ህፃናት ግንባታ የትምህርት መሣሪያ ማቅረብ	ብድር አገ/መስጠት የምርት ግብይት ማቅረብ ማህበራትን ማጠናከር	ግብርና ትምህርት ጤና መንገድ ውሃ	የባዕድ አምልኮና ጉጂ ባህልን ማስወገድ የምግብ ዕርዳታ ማቅረብ የደን ልማት ማካሂድ
6.ዳሞት ጋሌ	የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ገበሬዎችን በፍላጐት ማስፈር አፈር መሸርሸር መከላአት ለጤና አብሶ ትኩረት መስጠት ለትምህርት	-		-	በጤና ዘርፍ በጐደለ ማማላት ስለ ኤች አይቪ መከላከል በትምህርት ዘርፍ ላልደረሰ ማዳረስ ደረጃ ማሣደግ በአደጋ ጊዜ ድጋፍ መስጠት
7.አማሮ	ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት አጠ ባባቅ ጤና ትምህርት መንገድ ሥራ ንፁህ ውሃ	-	መንገድና ድልድይ መስኑ አገልግሎት የአገልግሎት	-	ብጤና ዘርፍ በጐደለ ማማላት ስለ ኤች አይቪ መከላከል በትምህርት ዘርፍ ስላልደረሰ ማዳረስ ደረጃ ማሣደግ በአደጋ ጊዜ ድጋፍ መስጠት

CORDA

8.አለታውንዶ	መንገድ መብራት ጠጠ ትምህርት ጤና ኤክስቴንሽን ማጠናከር ሥራ አጥነትን መቀነስ	በሁሉም ልማቶች ህብረተሰቡን ማሣተፍ	-	-	
9.ቾሃ	የተሻሸለ ቴክኖሎጂን ብድር አገልግሎት ማስፋፋት፣ የቡና የእንሰትና ፍሬፍሬ በሽታን መከላከል የመሬት ይዞታን ለማሻሻል የመሬት አጠቃቀም ፖሊሢ መተግበር የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ማስፋፋት የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጉጂ ባህልን ማስወገድ ሥነ ሕዝብ ኤድስ ፖሊሲ መተግበር	ብልማቱ ሥራ የቅንጅት ሥራ ከህብረተሰቡ ጋር ማሰልጠን	-	ህብረተሰቡን ያሳተፈ ልማት ማካሄድ የሥራን ቀን መቀነስየቁጠባ ባህል ማዳበር የዕድርን ገንዘብ በልማት ላይ ማዋል	ኤድስ ስርጭትን መከላከል
10.ኮንሶ	የመስኖ ልማት ማስፋፋት የሠፈራ ፕሮግራሞች ትምህርት ጤና ንፁህ ውሃ አቅም ግንባታ ማካሂድ	አደጋዎችን መከላከል ኤች አይቪ ኤድስን መከላከል	-	-	የኤድስ ስርጭትን መከላከል
11.ሐመር	ጎጂ ባህሎችን ማስወገድ ገቢ ምንጭ ማሣደግ መንገድ	ኤች አይ ቪን ለመከላከል ማስተማር ትምህርት ማዳረስ	-	-	ኤች አይቪ ኤድስን መከላከል ሌሎች ልማቶች ማካሄድ

CCRDA

የክልላዊ ምክክር ሂደትና ዋና ዋና ግኝቶች

CCRDA

በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ኤኮኖሚ ልማት ቢሮ የድቅስሰዝ ሴክሬተሪያት ጽ/ቤት

የካቲት/1994

ጋምቤላ

1. መግቢያ

በክልል ደረጃ የተካሄደው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የምክክር ስብሰባ ልዩ ልዩ ሴክተር ቢሮዎችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የሃይማኖት ድርጅቶችንና ልዩ ልዩ የህብረተሰቡ ክፍሎችን ያሳተፈ ነበር:: በስብሰባው ተሳታፊዎችም ሀሳባቸውን በነፃ ያንሸራሸሩበትንና በዋናነት የወረዳ ግኝቶችን መሠረት በማድረግ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን በወረዳው ግኝቶች ላይ ያልተካተቱ ነጥቦች እንዲካተቱ እንዲሁም ተጨማሪ የማዳበሪያ ሀሳቦችም እንዲጠቃለሉ ተደርጓል::

ስለምክክሩ ሁኔታ ቀደም ሲል በኢንተር አፍሪካ ግሩፕ አስተባባሪነት የአንድ ቀን የግንዛቤ ማዳበሪያ አውደጥናት የተካሄደ ሲሆን ይህም በሰነዱ ዝግጅት ላይ ብዙሀን ባለድርሻዎች (Multi-Stakeholders) ስለሚኖራቸው ሚናና በቀጣይነትም ለተደረገው የምክክር ስብሰባ የምክክሩን አስፈላጊነት ከማሳወቅ አኳያ ግንዛቤን አዳብሯል:: ለተሣታፊዎች እንደመነሻ የሚሆን ስለ ክልሉ አጠቃላይ የድህነት ሁኔታና ባለፉት አመታት በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድህነትን ለመቀነስ የተደረገውን ጥረት በተመለከተ ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን ይህም በምክክሩ ላይ የተገኙ ተሳታፊዎች ባለፉት አምስት ዓመታት የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ያስገኙትን ውጤትና ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ ሰፊ ውይይት እንዲያደርጉበት አስችሏል::

በአጠቃላይ ይህ ሪፖርት በ5 ክፍሎች ተከፋፍሏል:: በዚህም መሠረት በ2ኛው ክፍል ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልላዊ ምክክር ስብሰባ የነበረው ሂደትና ተሳትፎ፣ 3ኛው ክፍል ዋና ዋና የክልል ምክክር ግኝቶችን፣ በ4ኛው ክፍል የድቅስሰ ዝግጅትን በተመለከተ ከተካሄዱ የምክክር ሂደቶች ምን ተማርን፣ በመጨረሻም የማጠቃለያ ሀሣብን በማካተት ቀርቧል::

CGRDA

2. በጋምቤላ ብ/ክ/መንግሥት ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልላዊ ምክክር የነበረው ሒደትና የተሳትፎ ሁኔታ፣

ሀ. ቅድመ ምክክር የነበረው ሁኔታ፣

የክልሉ ቴክኒክ ኮሚቴና የሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤት የምክክር ሥራውን ለመስራት የመጀመሪያ እንቅስቃሴውን ያደረገው፦

- ለውይይት መነሻነት በተዘጋጀው ሰነድ /interim PRSP/ ላይ ክልሉን ወክለው የሚወያዩ 4 ወረዳዎችን መምረጥ ነበር። በዚህም መሠረት የወረዳዎች አመራረጥ መመዘኛዎች በዋናነት የእርሻና ሥነ ምህዳራዊ ቀጠናን (Agro-Ecological Nature) ፣ የግብርና ዘይቤን (Farming Practice) እንዲሁም የብሔር ብሔረሰብ ተዋጽኦን (Ethnic composition) መሠረት በማድረግ 1. የጎግ ወረዳ 2. የጎደሬ ወረዳ 3. የጅካዎ ወረዳና 4. የጋምቤላ ወረዳዎች ተመርጠዋል።

- በመቀጠል የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅትን ለማስፈጸም የሚያስችል መዋቅር በዞንና በወረዳ መዘርጋቱ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ከሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤትና ከቴክኒክ ኮሚቴ የተውጣጣ አራት አባላት ያሉት ቡድን ወደ መስክ ጉዞ በማድረግ በሁለቱ ዞኖችና በ4ቱ ወረዳዎች ም/ሊቀመናብርት የሚመራ አምስት አምስት አባላት ያሉት የአስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁሟል፦

- የወረዳ ምክክሩን የሚመሩ ሰብሳቢና ራፖርተሮችን በማስመረጥ ከፌደራሉ የድቅስስዝ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በክልላችን አስተባባሪነት ከቤንሻንጉልና ከጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ለተውጣጡ 24 የስብሰባ መሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል።

GCRDA

- ከዚህ በኋላ የነበረው ሥራ በክልላችን ከሚገኙት ፋቱ ወካይ ወረዳዎች ውስጥ በምክክሩ ላይ የሚሳተፉ ከእያንዳንዱ ወረዳ 50 ሰዋችን በቀጥተኛ የሕዝብ ተሳትፎ ተመረጠው የሚመጡበትን መንገድ ማመቻቸት ነበር።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ቅድመያምክክር ሥራዎች በተገቢው መንገድ ፌማካሄድ የዞን በተለይ የወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ከክልሉ ሴክሬተሪያትና የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ጋር በመሆን በማንባር ቀደምትነት ከፍተኛ ሚና በመጫወት ውጤታማ የሆነ የድቅስስ በተፈለገው ጊዜ ገደብ አዘጋጅቶ ለማውጣት አስችለዋል።

ሰ. በምክክር ወቅት የነበረው የተሳትፎ ሁኔታ

ሂሚዘጋጀው የድቅስስ ለቀጣዩ የክልሉ የልማት ፕሮግራሞች መሰረት ከመሆኑም ባሻገር ህገሪቱም ለምታደርገው ዕዳ የመቀነስ ጥረት የጎላ ፋይዳ እንዲኖረው ለማድረግ ይቻል ዘንድ በተቻለ መጠን ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ጥረት ተደረጓል።

ዚህም መሠረት የወረዳ ምክክሩ በተለይ ክድህነት አረንቋ ውስጥ መውጫ አጥቶ ሂሚማስነው የየወረዳዎች የታችኛው የህብረተሰብ ክፍል በቀጥታ ድህነት ከሚያመጣቸው ችግሮች ጋር በዋነኝነት ተጠቃሽ በመሆኑ በዋነኝነት ከየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ በቀጥታ ተመርጠው በተወከሉ የጎ/ሰብ ክፍሎች (ገበሬዎች፣ሴቶች፣ወጣቶች፣ የሐይማኖት መሪዎች ወ.ዘ.ተ) እንዲሁም በወረዳዎቹ ውስጥ ከሚሰሩ የመንግሥት ሠራተኞች ፣ ግብረ-ሰናይ የልማት አጋር ኃይሎች(NGOs, CBOs) በተወጣጡ 137 ወንድና 66 ሴት አባላት ሙሉና ንቁ ተሳትፎ አንድ ሰንድ ለማውጣት ተችሏል / ዝርዝሩን ከሚቀጥለው ጠረጴዛ ይመልከቱ/።

ሥንጠረዥ 1. በጋምቤላ ክልል የወረዳ ምክክር ተሳታፊዎች አጠቃላይ ሁኔታ

ተ.ቁ	ውረዳ	ጠቅላላ		ገጠር		ከተማ		የመንግሥት ሠራተኛ		መያድ		የኃይማኖት መሪዎች		ሌሎች	
		ወ	ሴ	ወ	ሴ	ወ	ሴ	ወ	ሴ	ወ	ሴ	ወ	ሴ	ወ	ሴ
1	ጋምቤላ	36	17	22	9	14	8	5	6	2	1	2	-	6	-
2	ጅካዎ	34	16	20	10	14	6	7	1	1	-	2	-	4	15
3	ጎግ	33	17	20	10	13	7	8	6	2	-	2	-	2	1
4	ጎደሬ	34	16	20	9	14	7	11	5	-	-	1	-	2	2
ጠቅላላ ድምር		137	66	82	38	55	28	31	18	5	1	7	-	14	18

GCRDA

ክልላዊ ምክክሩም ከልዩ ልዩ ክፍሎች በተወከሉ 167 ወንዶችና 25 ሴቶች በድምሩ 192 ሰዎች የወረዳን ዋና ዋና ግኝቶች መሠረት በማድረግ ጥልቅ ውይይት (In-depth Consultation) በማድረግ ቀደም ሲል በወረዳ ደረጃ በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ያልተካተቱ ጉዳዮችን በማካተት፣ መዳበር የሚገባቸውን በማዳበር ክልላዊውን የድህነት ቅነሣ ስትራቴጅ ሰነድ ለማዘጋጀት ተችሏል።

በአጠቃላይ በክልሉም ሆነ በወረዳ ምክክር ወቅት የነበረው ተሳትፎ ለአብነት ያህል የሴቶችን ብናይ በወረዳ ደረጃ 32.5 በመቶ የነበረ ሲሆን በክልል ደግሞ ከወረዳው ከግማሽ በታች ሆኖ እናገኘዋለን። የብዙኃን ባለድርሻዎችን (Multi-Stakeholders Consultation) ተሣትፎ በተመለከተ ከመንግሥት ልዩ ልዩ የሴክተር መ/ቤቶች፣ በክልሉ ውስጥ ቀጥተኛ የሆነ የልማት ተሣትፎ ከነበራቸው ሰባት መንግሥታዊ ካልሆኑ የልማት አጋር ድርጅቶች፣ ከኃይማኖት መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ከነጋዴው ኅ/ሰብ የተወከሉ አባላት በምክክሩ ላይ በንቃት በመሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ሐ. ያጋጠሙ ችግሮች

- በቅድመና ድህረ የክልል ምክክር ዝግጅት ሂደት ውስጥ ይህ ነው የሚባል የጎላ ችግር ያላጋጠመን ቢሆንም እንደ አጠቃላይ ከፍተኛ የሆነ የጊዜ እጥረት የታየበትና በዚህ ሥራ ላይ በቀጥታ የተሣተፉ አካላትን ትርፍ ጊዜን ማለትም ማታ አምሽቶ ከመሥራት ጀምሮ እስከ ቅዳሜ እሁድን ሁሉ ሰውተው እንዲሠሩ ማስገደዱ /ይህን ችግር ከሌሎች ክልሎችና ከብሔራዊ ሴክሬተሩያት ጋር የምንጋራው ነዉ/፣
- ምንም እንኳን የሴንተሳይዜሽን /sentesaization/ ሥራዎች ከምክክሩ በፊት የተካሄዱ ቢሆንም ካለው የጊዜ እጥረት አኳያ በስፋት የተፈለገውን ያህል ያልተሄደበት በመሆኑ አልፎ አልፎ "የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ" የሚለውን ሀሳብ የተሣሣተ ትርጉም የመስጠትና የመመልከት ታይተው ነበር፣
- አንዳንድ የምክክር ተሣታፊዎች ካላቸው የፖለቲካ አመለካከትና የግል ፍላጎት አንፃር በተለይ በክልል ምክክር ወቅት የራስን ሀሳብ ኢምፖዝ ለማድረግ የመሞከር አዝማሚያ ማሣየታቸው፣
- በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ የመስተዳድር አካላት ያሳዩት ትብብር የተፈለገውን ያህል ያለመሆኑ ሊጠቀሱ የሚችሉ አነስተኛ ችግሮች ነበሩ።

CGRDA

3. ዋና ዋና የምክክር ግኝቶች

3.1 በጠቅላላ የጋምቤላ ክልል የድህንት ሁኔታ ምን ይመስላል?

የጋምቤላ ክልል በሁለት ዞኖችና በዘጠኝ ወረዳዎች የተከፋፈለ ሲሆን የቆዳ ስፋቱም የኢትዮጵያን መልክዓ ምድር 2.84 በመቶ የያዘና የአጠቃላይ የሕዝቡን 0.39 በመቶ የሚሸፍን ነው።

እንደ CSA(2000) ትንበያ የክልሉ ሕዝብ ቁጥር 246,756 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 85 በመቶው በገጠር ይኖራል ቀሪው 15 በመቶው የከተማ ነዋሪ ነው። የኑሮ መሠረቱንም ስናይ 27 በመቶ የሚሆነው ኑሮውን እጅግ ኋላቀር በሆነ እርሻ፣ አሣ በማስገር፣ የዱር እንስሳትን በማደንና ማር በመቁረጥ ላይ መሠረት ያደረገ ሲሆን 37 በመቶው ደግሞ አርብቶ አደር (Agro-Pastoralist) ነው /TESCULT(2000).Woody B.o-Mass/።

እንደ 1995/96 የኢትዮጵያ የድህነት ሁኔታ ግምገማ/Poverty Assessment/ ከሆነ 41.8 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ጎ/ሰብ ከድህነት ወለል በታች ይገኛል። አንድ ቤተሰብ በዓመት የሚያመርተው ምርት ቢበዛ ከሦስትና ከአራት ወር በላይ እራሱን ለመመገብ የሚያስችለው አይደለም። ለምሳሌ ያህል ባለፉት አራት አመታት አማካኝ የጥራጥሬ እህሎችን (በቆሎ ዘንጋዳና የመሳሰሉትን) ምርት ሥናይ በነፍስ ወከፍ 0.9 ኩንታል ሆኖ እናገኘዋለን።

በዓለም የጤና ድርጅት መመዘኛ መሠረት አንድ ጎልማሳ ቢያንስ በቀን 2100 ካሎሪ (2100 Cal /person /annum) እንደሚያስፈልገው ያስቀምጣል። በዚህ መመዘኛ መሠረት አንድ ሰው ቢያንስ በቀን 598 ግራም ጥራጥሬዎች ወይም በዓመት ቢያንስ 2.18 ኩንታል በነፍስ ወከፍ መመገብ ቢኖርበትም በኛ ክልል በኩል የሚገኘው ምርት ግን አንድን ሰው ማግኘት ከሚገባው የኢነርጅ ፍጆታ ውስጥ 41 በመቶ ብቻ የሚሸፍን ሆኖ እናገኘዋለን።

በሌሎችም መመዘኛዎች ስናይ በክልሉ ያለው የድህነት ሁኔታ እጅግ በከፋ ደረጃ ላይ ይገኛል።

ለአብነት ያህል:-

- እንደ DHS(2000) ውጤት በክልሉ ከሚወለዱ አንድ ሺህ ህፃናት ውስጥ 122.6 የሚሆኑት እድሜአቸው አንድ ዓመት ሳይሞላ ይሞታሉ።

GCRDA

- ከዚህ በተጨማሪ ከአንድ ሺህ ህፃናት ውስጥ 233ቱ የአምስተኛ ዓመት ልደታቸውን ሳያከብሩ ይህችን ዓለም ይሰናበታሉ።
- የምግብ እጥረትን በተመለከተ እንደዚሁ ባሉት መመዘኛዎች ማለትም:-
  - Height-for-Age (HA)
  - Weight-for-Height (WA) የክልሉ ሁኔታ ሲገመገም
    - ዕድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑት የክልላችን ሕፃናት ውስጥ 41.8 በመቶው Stunted (Chronically Malnourished) ሴሎች 10.2 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ Wasting (Acute Malnourished) እንደሆኑ አንዳንድ የጥናት ዶክመንቶች ይጠቁማሉ *(Example:- Health and Nutritional Survey, 1998)*። በከተማና በገጠር ሲተነተን ደግሞ :-

A. Stunting Urban 24.1%

Stunting Rural 45.5%

B. Wasting Urban 12.8%

Wasting Rural 9.6%

- በትምህርት ጥራት ተሳትፎ በኩልም ሲኬድ የሀገሪቱ የትምህት ስታትስቲክስ መረጃዎች በአንደኛ ደረጃ ክልሉ ከፍተኛ አጠቃላይ ተሳትፎ (GER) እንዳለው ቢያመለክቱም ቅሉ እድሜአቸው ለትምህርት ከደረሱ ሕፃናት ውስጥ የትምህርት እድል የገጠማቸውን ብናይ እጅግ ዝቅተኛ ሆኖ እናገኘዋለን /*ለበለጠ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ 2 ይመልከቱ*/።

ሠንጠረዥ 2 እድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ የክልሉ ሕፃናት የትምህርት ተሳትፎ ሁኔታ

ዓ/ም	አንደኛ ደረጃ			ሁለተኛ ደረጃ		
	ወ + ሴ	ሴት	ወንድ	ወ + ሴ	ሴት	ወንድ
1988	29.6	21.7	37.1	4.9	2.3	4.9
1989	39.1	29.3	49.7	5.8	2.9	5.8
1990	37.2	29.1	44.9	5.1	2.6	5.1
1991	42.3	34.1	50.2	7.0	3.7	7.0
1992	46.0	37.2	46.0	7.1	3.2	7.1

ምንጭ /ኩጋሜላ ትምህርት ቢሮ 1993 ከተሻሻ መረጃ በመነሳት የተቀመረ/

እንደዚሁ በንፁህ ውኃ አቅርቦትና ንፅህና አጠባበቅም ቢሆን በዝቅተኛ ሁኔታ ላይ ይገኛል (ሽፋኑ 16.89 በመቶ ብቻ ነው)። 85 በመቶ ከሚሆነው የክልሉ የገጠር ንዋሪ ውስጥ የንፁህ ውኃ ተጠቃሚው 8.7 በመቶው ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን።

CCRDA

እንደዚሁ የንፅህና አገልግሎቶች ሽፋንም ሲታይ 5.33 በመቶ ብቻ መሆኑን አነረዳለን ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች አጠቃላይ የክልሉን የድህንት ሁኔታን ገላጭ ሲሆኑ በክልል ምክክር ወቅት ተሳታፊዎች በገጠርና በከተማ ያለውን ሁኔታ ባቀረቡት መሠረት ዋና ዋና ነጥቦችን እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞክራል።

3.2 የድህነት ሁኔታ በጋምቤላ ገጠራማ አካባቢዎች፣

- የገጠሩ ህዝብ ለዓመት ፍጆታው የሚበቃ ምርት ሊያመርት አለመቻሉና የምግብ እጥረት መኖር /ባንድ የመኸር ወቅት የሚመረተው ምርት እጅግ ቢበዛ ከ3 እና ከ4 ወር በላይ ሊቀልብ አይችልም/፣

- ሰውና እንስሳት በወረርሽኝ መጠቃት፣ የውሃ ወለድ በሽታዎች መስፋፋትና የንፁህ ውሃ ህብረተሰቡ እንደተፈለገው አለማግኘቱ፣

- የትምህርት አቅርቦቱ የተሻሻለና የተማሪዎች ተሳትፎም በከፍተኛ ሁኔቴ ማደጉን ዓመታዊ የስታትስቲክስ መረጃዎች ቢያሳዩም በአንፃሩ ዕድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት እንደተፈለገው እየሄዱ አይደለም። ለምሣሌ እንደ Demographic and Socio-Economic Profile of the Region, Jan. 2001, በ1992 የት/ዘመን በአንደኛ ደረጃ የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ የክልሉ ህፃናት ውስጥ 54 በመቶዎቹ ወደ ት/ቤት የመሄድ እድል አልነበራቸውም */ለዝርዝሩ ሠንጠረዥ 2ን ይመልከቱ/*፣

- የጤናና የትምህርት አገልግሎት ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለገጠሩ ህዝብ አለመዳረስ፣

- የመንገድና ሌሎች የመገናኛ አገልግሎቶች በገጠሩ አለመስፋፋትና የትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖር፣

- የገቢ ማስገኛ የሥራ መስኮች በገጠር አለመኖርና በኋላ ቀር የአስተራረስ ዘይ ገበሬው ተወስኖ መቆየቱ፣

- አምራች ሃይል የሆነው ወጣት ወደ ከተማ መፍለስ በገጠር የግብርናው ሥራ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣ በዋና ዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

CCRDA

የድህነት መንስኤዎች በቅደም ተከተል

- የትምህርት ፣ የጤና፣ የግብርና፣ የመንገድ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎት አለመስፋፋት፣

- ህዝቡ ከጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦች አለመላቀቁ፣ የጋብቻና የጥሎሽ ሁኔታዎች አሉታዊ ገጽታ፣

- ኋላቀር የአስተራረስና የአመራረት ዘይ፣

- የህብረተሰቡ የተበታተነ አሰፋፈርና የአኗኗር ባህል፣

- ህዝቡ በማህበራት አለመደራጀት፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት አለመስፋፋት፣ የተሻሻሉ የግብርና መሣሪያዎች ለገበሬው አለመድረስና ትምህርት አለመሰጠት፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት አለመኖር፣

- ባለው ያመራር ብቃት ችግር ምክንያት ህዝቡን ለልማት ማነሣሣት አለመቻል፣

- ህብረተሰቡ በከብት ጉልበት የመጠቀም ልምድ አለማዳበሩ በዚህም ምክንያት ረጅም የስራ ጊዜን በሰው ጉልበት ብቻ መጠቀም፣

- ለአርሶ አደሩ ከብቶች የጤና አገልግሎት አለመሟላት፣

- በክልሉ የጤና አገልግሎት ዝቅተኝነትና እንደ ወባ ባሉ በሽታዎች የህዝቡ መጠቃት፣

- የፀጥታ በአንዳንድ ወረዳዎች አለመረጋጋት፣

- ልዩ ልዩ ገቢ የሚያስገኙ ምርቶችን በስፋትና በዓይነት የማምረት ልምድ አለመኖር (diversified products)፣

- የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ አለመጠቀም፣

- የውጭ አገር ስደተኞች በህዝቡ መሃል መስፈር፣ አንዳንድ የምግብ እህሎች ከስደተኛው በዕርዳታ በቀላሉ በሚገኙበት ወቅት ህብረተሰቡ በግብርናው የተሻለ ምርት ለማምረት ያለውን ተነሳሽነት መቀነስ፣

CCRDA

- በጥናት ላይ የተደገፈ መረጃ አለመኖር፣ የግንኙነትና የመርጃ ልውውጥ ችግር፣

3.2. የድህነት ሁኔታ በከተሞች አካባቢ፣

- የመኖሪያ ቤትና የምግብ እህል እጥረት እንዲሁም የቀጋ ጎረት፣
- የስራ አጥነት መስፋፋትና የተረጅነት መንፈስ መዳበር ፣
- በቂ ጤና አገልግሎትና የትምህርት መስጫ ተቋማት አለመኖር፣
- የመሠረተ ልማት አውታሮች /መብራት ፣ ስልክ ወዘተ / አለመስፋፋትና የንፁህ መጠጥ ውሃ ችግር፣
- ወጣቱ በተገቢው ሁኔታ ትምህርቱን አለመከታተልና ለተሻለ ውጤት አለመብቃት፣ የሌብነት መስፋፋትና የወጣቱ ስነምግባር ጉድለቶች፣
- ከአንድ በላይ ጋብቻና አንዳንድ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች
- የገቢ ምንጭ የሚፈጥሩ የስልጠና ፕሮግራሞችና የብድር አገልግሎት አለመኖር።
- የሃይል ምንጭና የመብራት አገልግሎት እጥረት፣
- የወባና የውሃ ወለድ በሽታዎች ማስፋፋት፣
- በከተሞች የመጸዳጃ ቤት ዕጥረትና አጠቃላይ የንፁህና ጉድለት።

የድህነት መንስኤዎች በቅደም ተከተል

- በመንግስትም ሆነ በግለሰቦች የመኖሪያ ቤቶች እንደተፈለገው ተገንብተው አገልግሎት ላይ አለመዋል፣
- በአካባቢው የእህል ሰብል እንደተፈለገው አለመመረት፣ ገበያን ለማረጋጋት የተወሰደ እርምጃ አለመኖር፣
- የቁጠባ ባህል አለመዳበርና የግል ሃብትን ለማፍራት የሚደረግ ውድድር አለመኖር፣

CCRDA

በከተማ

- የከተማው ነዋሪ በማህበራት እንዲደራጅና የብድር አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አለመኖር፣
- ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና ከአንድ በላይ ጋብቻ፣
- ሥራ አጥነትን ለመቀነስ የሚያስችል የገቢ ማስገኛ መስኮችን አለመፍጠር፣
- ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት፣ በአንድ ቤተሰብ ላይ ጥገኛ በመሆን በርካታ ዘመዳሞች መኖር። በጋራ የመኖር ባህል ምክንያት የግል ሃብት ለማፍራትና ስራ ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ውሱንነት፣
- የንፁህ ውሃ አቅርቦት መዳከምና የጤና ተቋማት ግንባታ ቁጥሩ እያደገ ካለው የከተማ ህዝብ ጋር አለመጣጣም፣
- ትምህርትን በጥራት ለህዝቡ አለማዳረስ፣ ወጣቱ በተነሳሽነት ስሜት ትምህርቱን ተከታትሎ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንደተፈለገው አለመብቃቱና ወላጆችም ልጆቻቸውን በአግባቡ አለመከታተልና አለመቆጣጠር፣
- የከተሞች ማስተር ፕላን አለመጠናቀቅና በማስተር ፕላኑ መሠረት ግንባታዎች እንዲካሄዱ ትኩረት አለመስጠቱ፣
- የመሠረተ ልማት አውታሮችን በከተሞች ለማስፋፋት ባለፉት ዓመታት የተወሰደው እርምጃ ዝቅተኛ መሆን፣
- በከተሞች አማራጭ የሃይል ምንጮች አለመለመድ፣

3.3 ወደፊት መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች በቅደም ተከተል።

በገጠር

- የሥራ ተነሳሽነት እንዲኖር፣ የቁጠባ ባህል እንዲለመድ በአጠቃላይም ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችንና አለመካከቶችን ለማስወገድ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የህዝብ ተመራጮች፣ የአገር ሽማግሌዎች ወዘተ በቅንጅት ህዝቡን መቀስቀስና ማስተማር፣
- የትምህርትን ፣ የጤናን ፣ የግብርና ፣ የመንገድ አገልግሎትን በተሻለና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለገጠሩ ህዝብ ማዳረስ አሁን ያሉትን ማህበራዊ ተቋማት በሰው ሃይልና በቁሳቁስ ማደራጀት። የስልክ ፣ የመብራትና የፖስታ አገልግሎት ማስፋፋት፣
- ህብረተሰቡን ከውሃ ወለድ በሽታ ለመታደግ የንፁህ ውሃን ለህዝቡ ማዳረስ፣
- ኤች አይ ቪ /ኤድስ/ እያደረሰ ያለውን አልቂት ለመከላከል ለህብረተሰቡ በአፍ መፍቻ ቋንቋው የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት እንዲሰጠው ጥረት ማድረግ፣
- የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማጠናከር፣

CCRDA

- የተሻሻሉ የግብርና መሣሪያዎችን ለገበሬው በስፋት ማዳረስና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን በተሻለ መልኩ ማስፋፋት ከክልሉ የአሳ ሀብት ገበሬው ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበትን ስልት መቀየስ፣

- የሴቶችን ትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ፣ የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅና የመማር ማስተማሩ ሂደት ስነምግባር እንዲሻሻል ማድረግ። ወላጆችና የትምህርት ባለሙያዎች ቅንጅት በመፍጠር ትምህርታቸውን በአግባቡ ለማይከታተሉ ተማሪዎች ምክር መስጠትና አስፈላጊ ክትትሎችና የመፍትሄ እርምጃዎች መውሰድ።

- የጎልማሶች ትምህርትን ማጠናከር ፣ የክህሎት መስጫ ተቋማትን ማስፋፋት፣

- የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበትና ገበሬው ልዩ ልዩ የግብርና ሙያ ስልጠና እንዲያገኝና አማራጭ የገቢ ምንጭ እንዲፈጥር የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን ማጠናከር፣

- የሀብረት ስራ ማህበራትን ፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎትን ማቋቋምና ማስፋፋት። አመቺ የገበያ ሁኔታ መፍጠር ፣

- በክልሉ ***ሰላምና ፀጥታን*** ለማስፈን ህዝቡን ላሳተፈ መልኩ የችግሩን መነሻ በጥልቀት ማጥናት ፣ ለችግሮች መሠረታዊ መፍትሄዎችን መፈለግ በገጠር አካባቢ ያሉ ህገወጥ ታጣቂዎችን ትጥቅ ማስፈታት፣ በተለይ በዚህ ችግር ተጠቂ የሆኑት የክልሉ አረብቶ አደር የሚገኝባቸው ሁለቱ ወረደዎች /ጅካምና አኮቦ/ ምንም እንኳን የክልሉን 18 በመቶ የቆዳ ስፋትና የክልሉን ሕዝብ 37 በመቶ የያዙ ቢሆንም ባለው የፀጥታ አለመረጋጋትና ወይም ዋስትና ማጣት (Insecurity) ምክንያት አርብቶ አደሩ በክልሉ በመሠራት ላይ ከሚገኘው የልማት እንቅስቃሴ በተፈለገው መለኩ ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም። ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በአብዛኛው ጊዜ የፀጥታ ችግሮች የሚከሰቱት በሀብት መመናመንና በፖለቲካዊና ማህበርዊ ጉዳዮች አራጋቢነት ነው። ስልዚህ ይህን ችግር ለመፍታት በክልሉ መልካም አስተዳደርን (Good Gornance) መገንባትና ጎ/ሰቡን ሙሉ የፖለቲካው ተሳታፊ ማድርግ እንዲሁም ከግጠሽ መሬትና ከመሬት ይዞታ ጋር በተየተያያዘ መልኩ ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በየጊዜው የሚከሰቱ ችግሮችን እልባት መስጠትና የእንስሳት ንግድና ገበያ የሚስፋፋበትን መንገድ ማፈላለግ ግጭትን እንዲቀንስ ሰለሚያስችል በዚህ በኩል ብዙ ሥራ መሠራት ያለበትና ተገቢውም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያስገነዝበናል፡

- የአርብቶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻል በእንስሳት ሃብት ልማት ዙሪያ የኤክስቴንሽን ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣

- ዘላቂነት ያለው የሰፈራ ፕሮግራም ማካሄድ፣

CCRDA

- አነስተኛ የመስኖ አገልግሎቶችን በስፋት ማካሄድ ፣ አሁን ግንባታው ተቋርጦ ያለውን የአልቄሮ መስኖ ሥራ ስራውን እንዲጀምር ማስቻል።

- አሁን ያለውን የመምህራንና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በሌሎች የሙያ ዘርፎችም ስልጠና እንዲሰጥ ማስቻል፣

- የአመራር አካላትን አቅም ማጎልበት፣

- በመንግስታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶች ፣ መካከል ያለውን የስራ ግንኙነት ማጠናከር፣

- በህብረተሰቡ የመኖሪያ አካባቢ ያለውን የስደተኞች ካንፕ ከህብረሰቡ ጋር ችግር በማይፈጥር አካባቢ እንዲሆን ማድረግ።

- የተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅና በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል ህብረተሰቡን ስለተፈጥሮ ሃብት ጠቀሜታ ማስተማር ፣ የደን ተከላ ፕሮራምን ማጠናከር ፣ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲን ማውጣት፣በተለይ በስደተኞች ምክንያት እየደረሰ ያለው የደንና ብርቅየ የዱር እንስሳት መጨፍጨፍ የሚገታበትን መንገድ መፈለግ፣

- በከተሞች አካባቢ ያለው የድህነት ሁኔታ እየተባባሰ በመሄድ ላይ እንዳለ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ገልጸዋል። አሁን ካለበት ሁኔታ እየተባባሰ ከመሄዱ በፊትም የመፍትሄ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው ምክክር ተደርጎበታል።

- የገጠሩ ህዝብ ወደ ከተማ የሚያደርገውን ፍልሰት ለመግታት በገጠር አካባቢ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የግብርና ልማትን ማጠናከር፣

- የምግብ እህል ሰብል በክልሉ እንዲመረት ጥረት ከማድረግ ጎን ለጎን አሁን ያለውን የዋጋ ንረት ለመቋቋም የሸማቾች ማህበር ማቋቋም ወይም የእህል ሰብል ድርጅት የእህል አቅርቦት ዋጋን እንዲያረጋጋ ማድረግ፣

- የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ ቤት ሠሪዎችን በማህበር በማደራጀት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ በመንግሥት ለሚሠሩ መኖሪያ ቤቶችም ትኩረት መስጠት፣

- የከተሞች ማስተር ፕላን እንዲዘጋጅና የመሠረተ ልማት አውታሮች በከተሞች እንዲስፋፉ ማድረግ፣

- ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የተጀመረውን ጥረት ማጠናከር፣

CCRDA

- የከተሞችን ውሃና ፍሳሾች አገልግሎት መስሪያ ቤቶችን ማጠናከርና ህብረተሰቡ ፍትሃዊ የሆነ የንጹህ ውሃ አቅርቦት እንዲያገኝ ማስቻል።

- የግል ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ማበረታታት

- በየቀበሌዎች የልማትና የጤና ኮሚቴዎችን ማጠናከር፣ የጤና ተቋማት አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ በተሻለ ማደራጀትና ተጨማሪ ግንባታ ማካሄድ፣

- የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅና ወጣቱ በስነምግባር የታነጸ ዜጋ እንዲሆን ትምህርት ቤቶች ወላጅና መንግስት የጋራ መድረክ በመፍጠር ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ። ያለውን የክፍል ጥበት ለመቅረፍ ተጨማሪ ግንባታ ማካሄድ፣

- ወጣቱን ከአጉል ድርጊቶች ለመታደግ የምክር አገልግሎትና የቤተ መጻሕፍትና የመዝናኛ ማዕከላትን ማስፋፋት፣

- የህብረት ስራ ማህበራትን ማደራጀትና የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ መፍጠር፣

- ወጣቱ ልዩ ልዩ የሙያ ስልጠናዎች እንዲያገኝና ሥራ ፈጣሪ እንዲሆን ማነሳሳት፣

CCRDA

3.4 በክልሉ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማካሄድና ድህነትን በአስተማማኝነት ለመቀነስ በአጭርና በረጅም ጊዜ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች፣

ሀ. በአጭር ጊዜ

- ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና በምግብ እህል ራስን ለመቻል የእርሻ መሣሪያዎችና ልዩ ልዩ ግብአቶች የመጠቀም ልምድ እንዲዳብር የተጠናከረ ጥረት ማድረግ፣ የእንስሳት ጤና አጠባበቅን ማጠናከር፣

- የአገልግሎት ሀብረት ሥራ ማህበራትን በማቋቋምና በማጠናከር ህብረተሰቡ የተሻለ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻልና የቁጠባ ባህልን ማዳበር፣

- ገበሬው የአነስተኛ መስኖ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን የመስኖ ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር፣ የኤክስቴንሽን መርሃ ግብሩ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ እንዲነድፍና ተግባራዊ እንዲሆን ማስቻል፣

- የአካባቢውን ሰላምና ፀጥታ በተጠናከረ መልኩ ማረጋጋት የግጭት መንስኤዎችን ማስወገድ፣

- የትምህርት ቤቶችን ስርጭት በተመለከተ ራቅ ባሉ ወረዳዎች በበቂ ሁኔታ እንዲዳረስ ማድረግ፣ የትምህርቱን ጥራት ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ፣ የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ፣

- የተፈጥሮ ሃብታችንን ከአደጋ ለመከላከል የሚያስችል ፖሊሲ ማውጣት፣ የደን ተከላ ፕሮግራሞችን ማጠናከር ለህዝቡ ስለተፈጥሮ ሃብት ጠቀሜታ ማስተማር። በከተሞች አማራጭ የሃይል ምንጮችን ማስተዋወቅ፣

- ከቀበሌ እስከ ክልል የልማት ማህበራትና ኮሚቴዎችን ማቋቋም ፣ ህዝቡን ለልማት ማነሳሳት። የአካባቢን ንጽህና ለመጠበቅ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ፣

- የመዋቅር ማስተካከያ ማድረግ፣ የወረዳና የቀበሌ አመራር አካላትን አቅም መገንባት ፣ ክትትልና ግምገማዎችን ማጠናከር፣

CGRDA

- የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት እንዲጠናከር ማድረግ፣
- የውጭ አገር ስደተኞች ከህብረተሰቡ ራቅ ወዳለ ቦታ እንዲሰፍሩ ማድረግ፣
- HIV/AIDS በተመለከተ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበርና ስርጭቱን ለመቀነስ የሚያስችል የመከላከል እርምጃዎች በተለይም በጎ/ሰቡ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በተጠናከረ መልኩ መስጠት።

ለ. <u>በረጅም ጊዜ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች</u>

- በፍቃደኝነትና በጥናት ላይ የተመሰረተ የሰፈራ ፕሮግራም ማካሄድ፣
- ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችንና አስተሳሰቦችን ለማስወገድ ህብረተሰቡ ማስተማር፣
- የህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር፣ ህብረተሰቡ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል፣ ህብረተሰቡ የቁጠባን ባህል እንዲለምድ ማስተማር፣ የስራ አጥነትን የሚቀርፍ እርምጃዎች መወሰድ፣
- የመንገድ፣ የመብራት፣ የውሃ፣ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች ልማትን በሚያፋጥንና ፍትሃዊ በሆነ ስርጭት እንዲስፋፋ ማድረግ፣
- ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ሁኔታዎች መፍጠር፣
- የመኖሪያ ቤቶችን ግንባታ ማጠናከር፣ የከተሞችን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ማሻሻል በአጠቃላይም የከተሞችን ማስተር ፕላን በዝርዝር ማዘጋጀት፣
- የተፈጥሮና አካባቢ ጥበቃን በተጠናከረ መልኩ ማካሄድ አካባቢን ከብክለት መከላከል፣
- የገበሬውን ምርታማነት ለማሳደግ የተጠናከረ የገጠር ልማት ማካሄድ፣ የመስኖ ሥራን ለገበሬው ማዳረስ፣
- አገር በቀል የልማት ማህበራትን ማጠናከርና ህብረተሰቡን ለልማት ማነሳሳት።

CCRDA

4. የድቅስሰ ዝግጅትን በተመለከተ ከነበረው የምክክር ሂደት ምን ተማርን?

በአጠቃላይ ከዚህ የምክክር ሂደት የተማርናቸውን ነገሮች በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:-

4.1 በክልሉ ተንሰራፍቶ ያለውን የድህነት ሁኔታ ለመቅረፍ ከመፈለግ አንፃር የተገኙ ልምዶች፣

4.2 በአጠቃላይ ልማትን ለማፋጠንና ለማስፋፋት ይቻል ዘንድ የሚያግዙ ስልቶችን ከመጠቆም አንፃር፣

4.1 በክልሉ ተንሰራፍቶ ያለውን የድህነት ሁኔታ ለመቅረፍ ከመፈለግ አንፃር የተገኙ ልምዶች፣

- በክልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ ልማትን ለማምጣትና ድህንነትን ለመቀነስ ጎ/ሰቡ የራሱ ድርሻ ያለው መሆኑና በአግባቡ ከቀረቡትና ካዳመጡት ስለራሱ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳቦች ካወያዩት ለድቅስሰ ተግባራዊነት የላቀ ውጤት የማምጣት እምቅ ኃይል (Potential) ያለው መሆኑን፣
- ባለፉት ዓመታት የነበሩ ሚዛናዊ ያለሆኑ የልማት እና የፖሊሲ አካሄድና አተገባበሮች ለህ/ሰቡ በፍፁም ድህነት መዳረግ አይነተኛውን ሚና ያበረከቱ መሆናቸውን፣
- ምንም እንኳን በክልሉ ያሉ የስሺል ማህበራት አነስተኛ ቢሆኑም የክልሉ መንግስት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦና በጎ አመለካከት ከግምት በማስገባት አብሮ እየሰራ መሆኑን፣
- ድቅስሰ ቀጣይነት ያለው የሥራ ሂደት በመሆኑ ከዝግጅቱ ባሻገር በቀጣዩ ሥራ አሁን በመንግሥትና በስሺል ማህበረሰቡ (Civil Communities) መካከል የታየው ትብብር (Integration) መቀጠል እንዳለበት፣

4.2 በአጠቃላይ ልማትን ለማፋጠንና ለማስፋፋት ይቻል ዘንድ የሚያግዙ ስልቶችን ከመጠቆም አንፃር፣

ሕዝብን የሁሉም ነገር መነሻ እና መድረሻ የማድረግ እና በልማት ሥራ ውስጥ ከጥንስስ እስከ ዝርዝር የመስክ ትግበራ ድረስ እሱ ዋነኛ ባለቤት እና መሪ እንዲሆን አድርጎ የመስራት ጉዳይ ከማንኛውም ነገር በላይ እጅግ ወሳኝ ነገር መሆኑን። ይህም ማለት:-

- ሕዝብን የዘነጉ ወይም ባግባቡ ከመነሻው ያላሳተፉ የልማት ፕሮጀክቶች የፈለገውን ያህል ገንዘብ እና የባለሙያ ጉልበት ቢፈስባቸው የኋላ ኋላ ችግር እንደሚገጥማቸው፣

CGRDA

- ሕዝብ ከመነሻው ፈቅዶ የተሳተፈባቸው ፕሮጀክቶች ስኬታማ እንደሚሆኑ፣
- የተሳትፎ ትርጉም እንጨት እና ድንጋይ ማቀበል ወይም ከላይ ታቅዶ የመጣን ነገር መተግበር አለመሆኑን፣
- እውነተኛ ተሳትፎ ሕዝቡ ራሱ በማንኛቸውም ዝርዝር ጉዳዮች ላይ በውሳኔ ሰጭነት ሲንቀሳቀስ ማለት እንደሆነና ይህም ለባለቤትነት ስሜት መፈጠር ወሳኝ መሆኑን፣
- ይህን ከመነሻው ለማመቻቸት የሚቻለው ደግሞ በተለመደው የትዕዛዝና የኔ አውቅልሀለሁ መንገድ በመሄድ ሣይሆን ወይም መንግስት ይህን ከላይ ወስኖልሃል እና ይህን አድርግ በማለት ሣይሆን ወደታች ወረድ ብለው ችግሩን በማዳመጥ ስሜት በምክክር መንፈስ ሲቀርቡት መሆኑን በሁሉም ደረጃ የተካሄደው ምክክር ጠቁሞን አልፏል።

CCRDA

ማዕከላትን መገንባት ለወጣቱ መደረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ እንደሆነ የክልላችን ህዝብ ያምናል።

የክልሉ የትምህርት ሽፋን አጥጋቢ ቢሆንም በመምህራን ሙያዊ ብቃት አና በመጻህፍት ስርጭት ማነስ ፣ በቅድመ መደበኛ ትምህርት አለመጠናከር ፣ በፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት ብቃት ማነስና በተማሪው ለትምህርት ያለው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆንና የስነምግባር ጉድለቶች ምክንያት ጥራቱ እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት አፋጣኝ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል።


የተፈጥሮ ሃብትንና የመሬት አጠቃቀምን በተመለከተ የአጠቃቀም ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣትና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግ በስፋት የሚወሳ ጉዳይ ነው። በከተሞች አካባቢም የከተሞችን ማስተር ፕላን ማጠናቀቅና የመሠረተ ልማት አውታሮችን መዘርጋት ትኩረት የሚያሻው የልማት አጀንዳ ነው። በተለይ በከተሞች አካባቢ ያለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ሌላው ከድህነት ቅነሳ ስትራቴጂው ጋር ተያይዞ የተነሳው ጉዳይ የሴቶች በሁለንተናዊ መልኩ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን ነው።

ድህነትን ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት ከግብ እንዲደርስ ሴቶችን በማህበራዊ ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዬች ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግና ለዚሁም ተግባራዊነት በትምህርቱ ዘርፍ የተሻለ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ሠፊ ሥራ መሥራት አለበት። ለሴቶች የገቢ ምንጭ የሚሆኑ ዘዴዎችን መፍጠርና የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የዕደ ጥበባት ውጤቶችን በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ ፈጠራን በማነልበት አምርቶ ለገበያ ማቅረብና የህዝቡንም ባህል ማስተዋወቅ ተገቢ ነው።

በአሁኑ ወቅት ህዝቡን እየተፈታተነ ያለው የHIV/AIDS በሽታ ነው። በሽታው በተለይ በከተሞች ከገጠሩ በባሰ ሁኔታ እየተስፋፋ ይገኛል። በዚህ ዙሪያ ሁለ አቀፍ እንቅስቃሴ ማድረግና ህዝቡ ከዚህ አስከፊ በሽታ እራሱን እንዲጠብቅ ማስተማርና የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከላይ በጥቅሉ የተነሱ ነጥቦች በክልል ምክክር ወቅት እንደ ዋና ዋና ነጥቦች ተደርገው የተነሱ ሲሆን በክልሉ ለሚታዩ አጠቃላይ የድህነት መንስኤዎች ይመለከተኛል የሚል ወገን ሁሉ አንድ ሆኖ መነሳትና ድህነትን ከክልሉ ለመቀነስ ሰፊ ርብርብ ማድረግ አስፈላጊ ስለመሆኑ ሠፊ የጋራና የቡድን ውይይት ተደርጎበታል።




የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሠነድ

CCRDA

መጋቢት /1994 ዓ.ም.
አይሣኢታ፣


AFAR NATIONAL REGIONAL STATE
N
Afar01.shp
Zone1
Zone2
Zone3
Zone4
Zone5
Bure Mudaytu
Dulecha
Scale 1:2,000,000
CCRDA

ማ ው ጫ

ተ.ቁ	አርዕስ	ገጽ
1	መግቢያ	1
2	የክልሉ አጠቃላይ ገፅታ	2
	2.1 የሕዝብ ብዛት እንቅስቃሴና አሰፋፈር	2
	2.2 የማህበራዊ ገፅታ	2
	2.3 የኢኮኖሚያዊ ገፅታ	5
	2.4 የምግብ ዋስትና	6
3	የተሣታፊዎች ቅንብር	7
4	ለምክክር የቀረቡ አጀንዳዎች	7
5	የምክክር ዋና ዋና ግኝቶች	9
	5.1 በክልሉ የድህነት ምንነት እና መገለጫዎች	9
	5.2 የክልሉ የኑሮ ድህነት ሁኔታ	11
	5.3 በክልሉ ለድህነት የሚዳርጉ ምክንያቶች	12
	5.4 በአለፉት 5 ዓመታት ድህነትን ለማስወገድ/ለመቀነስ የተደረጉ ጥረቶች	15
	5.5 ድህነትን ለመቀነስ መወሰድ ያለባቸው ቀጣይ እርምጃዎች	18
6	ያጋጠሙ ችግሮች	20
7	አባሪዎች	21

CCRDA

መግቢያ

እንደሚታወቀው በሀገራችን በአለፉት መንግስታት ሲታቀዱ እና ሲተገበሩ የነበሩ የልማት ፕሮግራሞች የሕብረተሰብን የኑሮ ሁኔታ ያገናዘቡ እና የተከተሉ ሣይሆን ጥቂት ግለሰቦች በሚፈልጉት አካሄድ የሚታቀድ እና የሚተገበር እንደነበር የማይካድ ሀቅ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ከድንቁርና እና ከረሀብ እንዳይላቀቅ አድርጎታል።

ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ባለፉት 10 ዓመታት ተነድፈው በመተግበር ላይ ያሉ የልማት ስትራቴጂዎች፣ፖሊሲና ፕሮግራሞች ሕዝቡን ከድህነት ማቅ ለማውጣት ታልመው እና ታስበው የሚተገበሩ ቢሆኑም የሕዝቡን ፍላጎት መሉ በመሉ አሟልተዋል ባይባልም አጥጋቢ ናቸው ማለት ይቻላል።

ይህንን ጅምር ጥረት አጠናክሮ ለመቀጠል የአገሪቱ መንግስት እንደ አዲስ የልማት ስትራቴጂ አድርጎ የያዘውን የድህነት ቅነሣ ስትራቴጁ ዝግጅት ከምንጊዜው በበለጠ ሁኔታ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ከጀመረ ጥቂት ወራትን አሣልፏል።

በመሆኑም የአገሪቱን የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ለመቅረፅ የክልላችን ተሣትፎ ወሣኝ እና ዋነኛ ተግባር በመሆኑ በዚሁ መሠረት የክልላችንን ስትራቴጂ ለመቅረፅ በተደረገው ከፍተኛ ርብርቦሽ ከመስከረም 1994 እስከ መጋቢት ወር አጋማሽ አጠናቅቆ ለመጨረስ ተሞክሯል።

ምንም እንኳ በአገር አቀፍ ደረጃ ቀደም ተብሎ የተጀመረ ቢሆንም በክልላችን በተለያዩ ምክንያት ዘግይቶ የጀመረ ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ በጠቅላላው ከተመረጡ ወረዳዎች ለክልላችን 6 ወረዳዎችን እንዲመረጥ እና የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂውን እንድናዘጋጅ በተነገረን መሠረት ክልሉን ይወክላሉ የተባሉ 6 ወረዳዎችን በመምረጥ ስትራቴጂውን ለመቅረፅ ተሞክሯል።

በዚህም መሠረት ክልሉ አርብቶ አደር እንደመሆኑ እና በተለይ ድህነት በስፋት ተንሰራፍቶ የሚታይበት በሆኑ ለጉዳዩ በይበልጥ ትኩረት በመስጠት ሕብረተሰቡን ወረዳ ድረስ ወርዶ በማወያየት እና ችግሩን ከራሱ አንደበት ለመስማት እንዲሁም ለአጭር ጊዜ የሚሆን የመፍትሔ ሀሳብ እንዲሰጥበት በማድረግ ስትራቴጂው ተቀርፃል።

በመጨረሻም በነዚህ በተመረጡ ወረዳዎች ተገኝቶ ከ300 የሚበልጡ የመንግስት፣መንግስታዊ ያልሆኑ እና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በማወያየት ስለድህነት ምንነት እና መገለጫ እንዲሁም ችግሮችን በመዋያየት በነዚህ ወረዳዎች ላይ የተነሱ ሀሣቦችን ለማዳበር እና የክልሉን የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ለመቅረፅ የክልል ምክክር በማድረግ ይህንን ስትራቴጁ ለመቅረፅ ተችሏል።

ክልሉ ከመቶ 90% አርብቶ አደር እንደመሆኑ መጠን በየወረዳዎች የተነሱ ሀሳቦች አንድ ዓይነት በመሆናቸው ግልፁና አጭር የሆነ ሰነድ ነው ተብሎ ይታመናል።

በአጠቃላይ በሰነዱ ውስጥ በወረዳ የተነሱ ዝርዝር ግንቶችን እንዲሁም መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል።

CGRDA

2. የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ

የአፋር ብሔራ ክልላ መንግስት ከመቋቋሙ በፊት ባለፉት መንግስታት የአፋር ሕዝብ በአካባቢው ከነበሩ አውራጃዎች ፣ ክፍለ ሀገራትና ራስ ገዝ መስተዳድር ጋር ያለፍላጎቱ በሥራቸው እንዲተዳደር ሲደረግ መቆየቱ ይታወሣል። በአሁኑ ጊዜ የአፋር ህዝብ በህገመንግስቱ በተረጋገጠለት መብቱ መሠረት የራሱን መንግስት በማቋቋም ለአስተዳደር በሚያመች መልኩ በአምስት ዞኖች ፣ በ28 ወረዳዎች ፣ በአንድ ልዩ ወረዳና በ358 ቀበሌዎች ተደራጅቶ ራሱን በራሱ በማስተዳደር ላይ ይገኛል።

የአፋር ብሔራ ክልል የምስራቅ አፍሪካ ሰምጥ ሸለቆ ክፍል በሆነው በሰሜን ሰምጥ ሸለቆ የሚገኝ ሆኖ ከአራት ብሔራ ክልሎችና ከሁለት ሀገሮች ጋር ይዋሰናል። እነዚህም በሰሜን ከትግራይ ክልልና ከኤርትራ መንግስት ፣ በደቡብ ከኦሮሚያ ክልል ፣ በምስራቅ ከሱማሌ ክልልና ከጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት ፣ በምዕራብ ከአማራ ክልል ሲሆን የክልሉ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 97,256 ስኬየር ኪሎ ሜትር እንደሚሆን ይገመታል።

የመሬት አቀማመጡ በአብዛኛው ሜዳማ ሆኖ ዝቅተኛ ቦታዎች ከባህር ወለል በታች እስከ 120 ሜትር እና ከፍተኛ ቦታዎች ከ1,000 - 1,500 ሜትር ከባሕር ወለል በላይ ከፍታ የያዘ ነው። በአጠቃላይ ግን 96 በመቶ የሚሆነው መሬት ከ1,000 ሜትር የባሕር ወለል ከፍታ በታች የሚገኝ ነው ። ባለው መረጃ መሠረት ከ500 - 1,000 ሜትር ከፍታ ያላቸው 49 በመቶ ፣ ከ0 - 700 ሜትር ከፍታ ያላቸው 38 በመቶ እና ከባህር ወለል በታች የሚገኙ ቦታዎች 8 በመቶ አካባቢ ናቸው።

የክልሉ የአየር ንብረት በአብዛኛው ደረቅና ከፊል ደረቅ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የሙቀት መጠንና ዝቅተኛ የዝናብ መጠን አለው። የዝናቡ መጠን ከ80 - 700 ሚ.ሜትር ሲሆን የሙቀቱ መጠን በከፍታ ቦታዎች በአማካይ 25 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እና በዝቅተኛ ቦታዎች ደግሞ በአማካኝ 40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይደርሳል።

2.1. የህዝብ ብዛት እንቅስቃሴና አሰፋፈር

በ1988 ዓ.ም. በተካሄድው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሠረት በ1992 ዓ.ም. በክልሉ ይኖራል ተብሎ የሚገመተው የክልሉ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 1,215,255 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 57 በመቶ ወንዶች ናቸው። ከጠቅላላው የህዝብ ብዛት 92 በመቶ በገጠር ሲኖር በከተማ የሚኖረው 8 በመቶ ነው። 90 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ህዝብ ኑሮው በእንሰሳት እርባት ላይ የተመሠረተና ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር ነው። የክልሉ የህዝብ እድገት መጠን በከተማ 4.11 በመቶ ሲሆን በገጠር 2.23 በመቶ ነው።

የአሰፋፈር ሁኔታ

ምንም እንኳን የህዝቡ አሰፋፈርና ስርጭት ከዞን ዞን የተለያየ ቢሆንም የክልሉ አማካኝ የህዝብ ስርጭት 13 ሰው በአንድ ስኩዬር ኪ.ሜትር እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ ።

የህዝብ መጠን በእድሜ ክፍፍል

የክልሉን አጠቃላይ የህዝብ ብዛት በእድሜ ክፍፍል ስንመለከት 46.1 በመቶ የሚሆኑት እድሚያቸው ከ15 ዓመት በታች ናቸው።

ከ15 - 64 ዓመት ወይም Economically active የሆነው ክፍል 52.1 በመቶ ሲሆን እድሚያቸው ከ64 ዓመት በላይ የሆኑት 1.8 በመቶ ናቸው።

CCRDA

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት 92 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ህዝብ ሌሎች ተጨማሪ የገቢ ማስገኛዎች ሣይኖሩት በእንሰሳት እርባታ ላይ የተሰማራ ሲሆን ቀሪው የህብረተሰብ ክፍል ሰብል በማምረት ፣ በንግድና ሁለቱን የግብርና ሥራዎች በማጣመር የሚተዳደር ነው።

ከዚህ አንፃር 91 በመቶ የሚሆነው አርብቶ አደር ህብረሰብ አማራጭ መተዳደሪያ የሌለው መሆኑን ያሳያል። ይህ የሁለተኛ ወይም የተጨማሪ ሥራ ያለመኖር የአርብቶ አደሩን የገቢ ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሚያደርገው መገመት ይቻላል።

የህዝቡ ከቦታ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴና አሰፋፈር ሁኔታ

የአፋር አርብቶ አደር የቦታ ቦታ እንቅስቃሴና አሰፋፈር ሁኔታ በአጠቃላይ ስንመለከተው በዘፈቀደ የሚደረግ ሣይሆን ሥርዓትን የተከተለ ነው ሁለት ዓይነት እንቅስቃሴዎች ያሉ ሲሆን አንደኛው ቋሚ ሌላው ጊዜያ ነው። ጊዜያ የቦታ ቦታ እንቅስቃሴ ብዙ ጊዜ የተለመደና በክልሉ ውስጥም ሆነ ውጭ ለግጦሽና ለውሃ ፍለጋ የሚደረግ ነው። ቋሚ የቦታ ቦታ እንቅስቃሴው በጎሣና በጎሣው ክልል የተወሰነ ነው።

2.2. የማህበራዊ ገጽታ

ትምህርት

የክልሉ የትምህርት ሁኔታ እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን የትምህርት አመልካቾች ያሳያሉ። በ1992 ዓ.ም. በተደረገ ግምገማ መሠረት ጥቅል የተጣቶፎ ምጣኔ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት 10 በመቶ ፣ የሁለተኛ ደረጃ 2.7 በመቶ መሆኑን ያመለክታል።

በዚሁ ዓ.ም. መጨረሻ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ስንመለከት በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት 8.48 በመቶ እና 2.56 በመቶ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መሆኑን ያሳያል።

የክልሉ መንግስት የትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚ ሣይሆን የቆየውን የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ በርካታ ጥረቶችን ያደረገ ሲሆን በፊት የነበሩትን ዝቅተኛ ት/ቤቶች ቁጥር በ1992 ዓ.ም. መጨረሻ 122 የ1ኛ ደረጃና 6 የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲኖሩ ማድረግ ተችሏል። ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳትም የአዳሪ ት/ቤቶች ግንባታ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በክልሉ ባሉ 5 ዞኖች ለእያንዳንዳቸው አንድ አዳሪ ት/ቤት እንዲኖር በታቀደው መሠረት በአሁኑ ጊዜ 5ቱም ተገንብተው የዞን 1 አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛለል።

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትን ለማስፋፋት በየደረጃው ትምህርት የጨረሱ ወጣቶችን ለማሰልጠን በያዝነው በ1994 ዓ.ም. አስፈላጊው ዝግጅት ተሟልቶ ያልቆየ ቢሆንም ስልጠናው ተጀምሯል።

የጤና አገልግሎት

የክልሉ የጤና አገልግሎት በሀገሪቱ ውስጥ እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ ከሚገኙት የሚመደብ ነው። በ1992 ዓ.ም. በክልሉ 2 ሆስፒታሎች ፣ 5 ጤና ጣቢያዎች ፣ 50 ክሊኒኮችና 26 ጤና ኬላዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የነበሩ ሲሆን አጠቃላይ የጤና ሽፋኑም 29 በመቶ መድረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

አንድ ቤተሰብ የጤና አገልግሎት ለማግኘት የሚጓዘውን ርቀት ስንመለከት የ1 ሰዓት ጉዞ በድረግ የሚያገኘው 8.36 በመቶ ፣ ከ1 እስከ 2 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 16.2 በመቶ ፣ ከ2 - 3 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 10.83 በመቶ ፣ ከ3 - 4 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 14.45 በመቶ ፣ ከ4 - 5 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 13.18 በመቶ እና ከ5 ሰዓት በላይ በመጓዝ የሚያገኘው ደግሞ 37 በመቶ የሚሆነው ቤተሰብ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። በአጠቃላይ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆነው ቤተሰብ ቢያንስ ከ2 - 3 ሰዓት ያህል የጤና አገልግሎት ለማግኘት መጓዙ የግድ ነው።

CCRDA

በክልሉ ያሉት የጤና ድርጅቶች ለህዝቡ አገልግሎት ለመስጠት የሚኖራቸው ድርሻ 1 ጤና ኬላ ለ16,740 ሰው ፣1 ክሊኒክ ለ24,305 ሰው ፣ 1 ጤና ጣቢያ ለ243,051 ሰው ፣ 1 የሆስፒታል አልጋ ለ14,297 ሰው እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ።

የመጠጥ ውሃ አቅርቦት

በክልሉ ያለውን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ስንመለከት ከፍተኛ ውስንነት የሚታይበት ነው። በ1989 ዓ.ም. በገጠር የሚኖረው ህዝብ የመጠጥ ውሃ የሚያገኝባቸውን መንገዶች ስንመለከት 3.2 በመቶ ቤተሰብ ብቻ ከቧንቧ የሚያገኝ ሲሆን የተቀረው 2 በመቶ ከጥብቅ ጉድጓድና ምንጭ ፣ 27.2 በመቶ ካልተጠበቀ ጉድጓድና ምንጭ ፣ 67.4 በመቶ ከወንዝ ፣ ከሃይቅና ከኩሬ የሚጠቀም ነው ። አርብቶ አደሩ ህብረተሰብ ያለበት የውሃ ችግር ከፍተኛ ሲሆን የችግሩ መጠንም ከወቅት ወቅት የተለያየ ነው። በዝናብ ወቅት ለሰውም ሆነ ለእንሳሰት ከደረቃማ ወራቶች በአንፃራኑት የተሻለ አቅርቦት ያገኛል። በዝናብ ወቅት ውሃን ለማግኘት የሚጓዘውን ርቀት ስንመለከት የ30 ደቂቃ ጉዞ በማድረግ የሚያገኘው ቤተሰብ 49.59 በመቶ ፣ ከግማሽ እስከ 1 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 22.6 በመቶ ከ1 - 2 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 16.49 በመቶ ፣ ከ2 - 3 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 6.14 በመቶ ፣ ከ3 - 4 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 3.63 በመቶ ከ4 -5 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 1.5 በመቶ የሚሆነው ቤተሰብ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። በአንፃሩ በደረቅ ወቅት ውሃን ለማግኘት የሚደረገውን ጉዞ ስንመለከት እስከ 30 ደቂቃ በመጓዝ የሚያገኘው ቤተሰብ 14 በመቶ ፣ ከግማሽ እስከ 1 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 14.69 በመቶ ፣ ከ1 - 2 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 18.48 በመቶ ፣ ከ2 - 3 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 14.88 በመቶ ፣ ከ3 - 4 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 15.95 በመቶ ፣ ከ4 - 5 ሰዓት በመጓዝ የሚያገኘው 11.28 በመቶ እና ከ5 ሰዓት በላይ በመጓዝ የሚያገኘው 10.72 በመቶ የሚሆነው ቤተሰብ እንደሚሆን ጥናቶች ያስረዳሉ።

ከዚህ የምንረዳው 87 በመቶ የሚሆነው አርብቶ አደር በክረምት ወራት እንኳ ውሃ ለማግኘት እስከ 2 ሰዓት ለመጓዝ መገድዱን ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋኑን ለማሣደግ በክልሉ መንግስት ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን እስከ 1992 ዓ.ም. መጨረሻ 79 ጥልቅና 42 ጥልቅ ያልሆኑ ጉድጓዶች ፣ 50 የእጅ ፓምፖች ፣ 3 ምንጮች አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደነበሩና የክልሉ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንም 16.45 በመቶ መድረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

እንሰሳት ጤና አገልግሎት

በሀገራችን በርካታ የእንሰሳት በሽታዎች ያሉ ሲሆን ክልሉም ከአየር ንብረቱ ጋር በአብዛኛው በተያያዘ የብዙ የእንሰሳት በሽታዎች በፍንዳታ መልክ የሚነሳበት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በ1991 ዓ.ም. በመታፊሪያ ኮንሰልቲንግ ጥናት መሠረት ከጠቅላላው ቤተሰብ /House hold / 78 በመቶ የሚሆነው እንሰሳቶቻቸውን አላስከተቡም። ለዚህም ምክንያቶቹ 53 በመቶ የሚሆነው በቦታ ርቀት ፣ 28 በመቶ የሚሆነው በወቅቱ ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ባለመቻል ፣ 16 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ስለአገልግሎቱ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ ነው። በ1992 ዓ.ም. መጨረሻ ያሉት ክሊኒኮች ብዛት 17 የደረሰ ሲሆን 1 ክልላ የእንሰሳት ጤና ላቦራቶሪም በመገንባት ላይ ነበር ። በወቅቱ በተደረገ ግምገማ የእንሰሳት ጤና አገልግሎት ሽፋን 9.06 በመቶ ብቻ ነው።

መንገድ

መንገድን በተመለከተ የክልሉን ገፅታ ስንመለከት ጠቅለል ባለ መልኩ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው። ያሉትም ውስን መንገዶች በአነስተኛ ደረጃ የተሰሩና የጥገና ችግር የሚታይባቸው ናቸው። በዚህ ሣቢያም በአሁኑ ጊዜ ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት አነስተኛ ሆኖ ይገኛል። ለክልሉ በአሁኑ ጊዜ ግልጋሎት እየሰጡ የሚገኙትን መንገዶች ስንመለከት በዋነኝነት የባቲ - ሚሌ መንገድ እና የአዋሽ - ቡሬ ሃይዌይ ናቸው። አገናኝ መንገዶችን በተመለከተ በአብዛኛው በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሆነው ዞንና ወረዳን ከዋና መንገዶች ጋር የሚያገኙ ናቸው። መጋቢ መንግዶችም

በመጠኑ በየዞኑ ይገኛሉ። በአጠቃላይ በክልሉ 605 ኪ.ሜትር ርዝመት ያለው የአስፋልት መንገድ ፣ 592 ኪ.ሜትር RR50 ደረጃ ያላቸውና ክረምት ከበጋ የሚያገለግሉ ፣ 793 ኪ.ሜ. RR 30 ደረጃ ያላቸውና በበጋ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ መንገዶች ይገኛሉ።

2.3. የኢኮኖሚያዊ ገጽታ

የፖስታ አገልግሎት

የፖስታ አገልግሎት መስፋፋት ለመንግስታ ሥራ ፣ ለማህበራ ግንኙነት ፣ ለንግድ አገልግሎት እና ለመሣሰሉት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል። እስከ ከ1992 ዓ.ም. መጨረሻ በክልሉ 8 ከተሞች ብቻ የፖስታ አገልግሎት ሲኖራቸው በብዙ የወረዳ ከተሞች የፖስታ አገልግሎት የለም። የአገልግሎቱ አለመኖር ለአስተዳደራ ጉዳዩችም ሆነ ለልማት ሥራዎች ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን መረዳት ይቻላል።

ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት

በክልሉ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ችግር የግንኙነት ችግር በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚያሻው ነው። የቴሌፎን አገልግሎትን በተመለከተ በክልሉ በጥቂት ከተሞች ብቻ የሚገኝ ሆኖ እናገኘዋለን። እስከ 1992 ዓ.ም. መጨረሻ 10 ከተሞች የቴሌፎን አገልገሎት ተጠቃሚ እንደሆኑ ሲታወቅ ከዚህ ውስጥ የአይሣኢታና የዱብቲ ከተሞች ያለአንሬተር እርዳታ የቀጥታ /አናሎጅ ማይክሮዌቭ ሲስተም/ ያላቸው ናቸው።

የኤሌክትሪክ አገልግሎት

በክልሉ ያለውን የኃይል አቅርቦት ስንመለከት በጣም በአስተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው። በክልሉ የሃድሮፖወር ኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቋሚ የሆኑ ከተሞች 5 ሲሆኑ 3 ከተሞች ደግሞ ከጀኔሬተር ሃይል የሚጠቀሙና በብልሽት ጊዜ ግን ተተኪ የሌላቸው ናቸው። በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የጂኦተርማል ኃይል የሚገኝ ሲሆን ይህን ኃይል በጥቅም ላይ ለማዋል አስፈላጊ ጥናቶች የተደረጉ ቢሆንም በጥቅም ላይ ግን እስካሁን ማዋል አልተቻለም።

የባንክ አገልግሎት

ብቃት ያለው የባንክ ሥርዓትና የብድር የአልግሎት መኖር ለልማት እጅግ አስፈላጊ ነው። በአሁኑ ጊዜ በክልሉ በ2 ዞኖች /ዞን1 እና 3 / አራት/ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች የሚገኙ ይሁንእንጂ የብድር አገልግሎቱ በአነስተኛ ደረጃና በከተማ የተወሰነ ነው ። ለዚህም ዋነኛው በክልሉ የመሠረተ ልማት አውታሮች በሰፊው ያለመዘርጋት ነው።

የአየር ትራንስፖርት

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለክልሉ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። እስከአሁን በክልሉ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ከተሞች የሌሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በሠመራ ከተማ በአስፋልት የአውሮፕላን ማረፊያ እየተሰራ ይገኛል።

CGRDA

አነስተኛ ኢንዲስትሪዎች / የጎጆ - ኢንዱስትሪ /

ከአንዳንድ ጥናቶች ለመረዳት እንደተቻለው በአብዛኛው በክልላችን የአነስተኛ ኢንደስትሪዎች የሚገኙት በከተሞች አካባቢ ነው። በአሁኑ ጊዜ በክልሉ የእህል ወፍጮዎች ፣ የቦሎኬት ማምረቻዎች ፣ ባሕላ የሸማ መሥሪያዎች እና የብረታ ብረት ማምረቻዎች በዋነኝነት የሚገኙ የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ናቸው።

እንሰሳት እርባታ

ከክልሉ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት ውስጥ 90 በመቶ የሚሆነው በእንሳስት እርባታ የሚተዳደር ነው።

በቅርብ ጊዜ የተደረገ ቆጠራ ባይኖርም አንዳንድ ጥናቶች የክልሉ የእንሰሳት ሀብት ብዛት 4 ሚሊዮን እንደሚደርስ ያሳያሉ። በቤተሰብ ደረጃ ያለውን የእንሰሳት ዓይነት ስንመለከት 42.4 በመቶ የቀንድ ከብት ፣ 21.6 በመቶ በግ ፣ 25.5 በመቶ ፍየል ፣ 8.9 በመቶ ግመል ፣ 1.6 በመቶ አህያ እንደሆነ ጥናቶቹ ይጠቁማሉ። የእንሰሳት እርባታው ዋነኛ ጠቀሜታ ለወተትና ከወተት ለሚገኙ ተዋፅኦዎች ነው። በዚህም ሣቢያ ወተት ለአርብቶ አዳሩ ዋነኛው የእለት ተዕለት ምግብ ነው። በአማካኝ አንድ ሰው በዓመት ሊያገኝ የሚችለው ወተት መጠንም 320 ሊትር ይደርሳል።

እንሳሰት ገበያ

በክልሉ በቁጥር በጣም አነስተኛ የሆኑ የእንሰሳት ገበያዎች ያሉ ሲሆን ከክልሉ ውጭ ያሉ ገበያዎችንም ህዝቡ ይጠቀማል። የገበያ ቦታዎቹ በአግባቡ ያልተካለሉና በአብዛኛው አጥር የሌላቸው ሲሆን ሁሉም ዓይነት እንሰሳት በአንድነት ለገበያ የሚቆሙባቸው ናቸው።

ፍጆታና የገቢ ሁኔታ

ዋነኛው የክልሉ ህዝብ የገቢ ማግኛ ከእንሰሳት እርባታ የሚገኝ ነው። አነስተኛ የሆኑት እንሰሳት /በግና ፍየል/ በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውሉት መሠረታ ፍላጎቶችን / ምግብና ልብስ / ለማሟላት ሲሆን ትልልቆቹን እንሰሳት / የቀንድ ከብትና ግመል / ደግሞ ድንገተኛ የሆኑ እንደድርቅና ለሌሎች ማህበራ ጉዳዬች ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት አማካኝ የአንድ ቤተሰብ ወርሃ ፍጆታ 344 ብር ፤ አማካኝ የአንድ ሰው ወርሃ ፍጆታ ደግሞ ብር 54.50 ነው። ከአጠቃላይ ፍጆታው ውስጥ 76 በመቶው ለምግብ ፣ ለመጠጥና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጉዳዮች የሚውል ነው። ገቢን ስንመለከት ደግሞ የአንድ ቤተሰብ አማካኝ ወርሃ ገቢ ብር 414 ሲሆን አማካኝ የአንድ ሰው ወርሃ ገቢ ደግሞ ብር 65.50 ነው። የገቢ ማግኛ መንገዶቹ ድርሻ ስናይ 85.4 በመቶ ከግብርና ውጤቶች / 71.5 በመቶ ከእንሰሳት እና 13.9 በመቶ ከሰብል/ ፣ 10.7 በመቶው ደግሞ ከደመወዝና ከጉልበት ሥራ የሚገኝ ነው።

2.4. የምግብ ዋስትና

በክልሉ አማካይነት የቤተሰብ ብዛት 6 ሲሆን ይህ ቤተሰብ ሁሉንም የቤተሰብ አባላት ለመመገብ በዓመት 15.4 ኩንታል ስንዴ ወይም ማሽላ ያስፈልገዋል። ይህንን 14.4 ኩንታል ስንዴ ወይም ማሽላ ለመግዛት አንድ ቤተሰብ ቢያንስ ብር 3,388 ያስፈልገዋል። / 220 ብር በኩንታል / ። ይህንን መጠን በዓመት ውስጥ ላሉት ወራት ስናካፍል አንድ ቤተሰብ ቢያንስ 1.128 ኩንታል ስንዴ ወይም ገብስ በወር ያስፈልገዋል። ይህንን የወር ፍላጎት ለማሟላት ደግሞ አንድ

CCRDA

ቤተሰብ ቢያንስ በወር ብር 283 ያስፈልገዋል። ስለዚህ ይህንን የጥራ ጥሬ እህል ወርሃና ዓመታ ፍላጎት አንድ ቤተሰብ ለማሟላት የሚያስችል አቅም አለው ወይ ?

አንድ ቤተሰብ ወርሃ የጥራ ጥሬ እህል ፍላጎቱን ለማሟላት ቢያንስ 7 ፍየሎችን ወይም 1 በሬውን መሸጥ ይኖርበታል። በተመሣሣይ አንድ ቤተሰብ ዓመታ የጥራ ጥሬ እህል ፍላጎቱን ለማሟላት 84 ፍየሎችን ወይም 12 በሬዎችን መሸጥ ይኖርበታል። ነገር ግን አንድ ቤተሰብ ምን ያህል እንሰሳት ይኖሩታል? ወይም አንድ ቤተሰብ ከላይ የተጠቀሰውን ያህል እንሰሳት ሊሸጥ ይችላል ወይ ?

ጥናቶች እንደሚያሳዩት አማካኝ የአንድ ቤተሰብ የእንሰሳት ብዛት 1.5 በሬ ፣ 7.5 ጥጃዎች ፣ 4.6 ጊደሮች ፣ 1 ወይፈን ፣ 11.5 ላሞች ፣ 13.4 በጎች ፣ 15.7 ፍየሎች ፣ 5.5 ግመሎች እና 1 አህያ ናቸው።

ከነዚህ እንሰሳት ውስጥ ከላይ የተጠቀሰውን ያህል መጠን የጥራ ጥሬ እህል ፍላጎቱን ለማሟላት የሚያስችል እንሰሳት ወደ ገበያ ይዞ የሚወጣ ከሆነ ወደየት እንደሚሄድና ለምን ያህል ጊዜ ማሟላት እንደሚችል መገመት ይቻላል።

3. የተሣታፊዎች ቅንብር

በዱብቲ ከተማ ከ29/06/94 - 01/07/94 በተደረገው የክልሉ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ዝግጅት የምክክር ጉባኤ ላይ ከ200 ያላነሱ ተሣታፊዎች የተገኙ ሲሆን እነዚህም ተሣታፊዎች ከመንግስት፣መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከህብርተሰቡ የተውጣጡ ሲሆን እነዚህም በዝርዝር ተገልፀዋል::

- ከክልሉ እና ከዞን ም/ቤት ስራ አስፈፃሚዎች
- ከክልሉ ሴክተር ቢሮዎች
- ከዞን መምሪያዎች
- ከማኒስቴር መ/ቤቶች
- ከህዝብ ተወካዮች ም/ቤት
- ከንግዱ ማህበረሰብ
- ከማህበራት ተቋሞች
- ከሴቶች ተወካዮች
- ከሀይማኖት መሪዎች
- በክልሉ የሚገኙ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች
- ኢንቨስተሮች
- ታዋቂ ምሁራኖች
- የወረዳ ሰብሳቢዎች እና ራፖርተሮች
- የክልሉ ቴክኒክ ኮሚቴዎች ናቸው::

4. ለምክክር የቀረቡ አጀንዳዎች

ለክልል ምክክር ወቅት የቀረቡት አጀንዳዎች በቅድሚያ የክልሉን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ የሚዳስስ ፅሁፍ የቀረበ ሲሆን እንዲሁም ወረዳዎች እያንዳንዳቸው ያዘጋጁትን ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ በእያንዳንዱ ላይ ውይይት የተካሄደበት እና አስተያየት

CCRDA

የተሰጠበት ሁኔታ ሲሆን በአብዛኛው የተነሱት አጀንዳዎች በወረዳው ላይ የተነሱትን ማለትም:-

1. የድህነት ምንነት ከወረዳው ተጨባጭ ሁኔታና ከህብረተሰቡ የህይወት ልምድ አንፃር እንዴት ይገለፃል? የድህነት መገለጫና መለኪያዎቹ ምንድን ናቸው? የድህነት መለኪያዎች ምንድን ናቸው?

2. ድህነት ባለፉት አምስት ዓመታት ምን ይመስላል?

3. ለድህነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ምክንያቶች በቅደም ተከተል ቢገለፁ?

4. የሕዝቡ ኑሮ የተመሰረተው በምን ላይ ነው? ከዚህ አንፃር ያሉት መሠረታዊ ችግሮችና ድህነትን ለመቅረፍ በህብረተሰቡ፣በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተወሰዱና ወደፊት ለወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

5. በወዳው የሚገኙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋሞች ለሕብረተሰቡ እየሰጡ ያሉት አገልግሎት ምን ይመስላል? ችግሮች ካሉ ቢገለፁ /የችግሮች መንስኤ ይገለፅ/ ችግሮቹን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች ካሉ ቢገለፁ /በመንግስት፣መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣በግል ባለሀብቶች፣በሕብረተሰቡ/

6. ከድህነት ጋር የሚያያዙ ማህበራዊና የግል ባህሪያት ምንድን ናቸው?

7. በተለያየ ደረጃ ያሉ አስተዳደራዊ መዋቅሮች

8. ግጭቶች በወረዳው ላይ ግጭቶች መንስኤው ምንድ ነው?

9. ድህነትን ከወረዳው ለመቀነስ ወይም ለመቅረፍ ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው ጉዳዮች በቅደም ተከተል ቢገለጽ?

ሲሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን አጀንዳዎች በክልል ደረጃ ቀጣይ ሁኔታና ምን መደረግ እንዳለበት በመወያየት እና ሀሳቦችን በማሰራሰር ጠቃሚ መረጃዎች ተገኝተዋል::

CCRDA

5. የምክክር ዋና ዋና ግኝቶች

በምክክር ስብሰባው ላይ የተለያዩ አጀንዳዎች ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን የክልሉ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ይገልፃሉ ተብለው የታመነባቸው ከዚህ እንደሚከተለው በየአጀንዳው ቅደም ተከተል ተቀምጧል::

5.1. በክልሉ የድህነት ምንነትና መገለጫዎቹ

የድህነት ትርጉም

በክልሉ የድህነት ቅነሣ ምክክር ላይ ድህነት የተለያየ ትርጓሜ በህብረተሰቡ ተሰጥቶታል ይኸውም፣

- ቤተሰብን ለመቀለብ፣ለማስተማርና ለማሳከም አቅም ማጣት ፣
- ሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ ሀብት ንብረቱንና ቤተሰቡን ማጣት፣
- የትምህርት የጤና አገልግሎት ሽፋን አለመስፋፋት፣
- በችግር በርሃብ መሰቃየት፣
- ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች አለመሟላት፣
- ብዙ ቤተሰብ ኖሮት ምንም ዓይነት የገቢ ምንጭ የሌለው፣
- በዘካና በድጎማ የሚኖር የድህነትን ትርጓሜዎች ናቸው::

የድህነት መገለጫዎች

የድህነት መገለጫዎችን በተመለከተ በተደረገው ምክክር ሕብረተሰቡ ከታች የተዘረዘሩት ነጥቦች የድህነት መገለጫዎች እንደሆኑ አስቀምጠዋል::

- የተፈጥሮ ችግር /ደረቅ፣የዝናብ እጥረት/
- የማህበራዊ አገልግሎቶች አለመስፋፋት፣
- የመሠረተ ልማት አውታሮች አለመስፋፋት፣
- ግጭት መበራከት፣
- የሕብረተሰቡ ግንዛቤ ዝቅተኛነት /መሀይምነት/
- የግጦሽ መሬት መመናመን፣
- የምግብ እጥረት፣
- የገቢ ማነስ ናቸው::

የድህነት መለኪያዎች

ድህነት አርብቶ አደር በሆነው የገጠሩ ክፍል በእንስሳት ሀብት ቁጥር ስርጭትና ዓይነት የሚለካ ሲሆን በጥምር ግብርና ባለባቸው አካባቢዎች በመሬት መጠን በእርሻ መሳሪያዎችና በሚያገኘው ምርት መጠን ይለካል በአጠቃላይ በአርብቶ አደሩና በጥምር ግብርና በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በእስልምና ሀይማኖት ድንጋጌ መሠረት ዘካ መስጠት እንደዋነኛ የድህነት መለኪያ ይታያል:

CCRDA

ጥሩ ሕይወት

ጥሩ ሕይወት በክልሉ የሚገለፀው

- በቂ ዝናብ እና ለከብቶች ግጦሽ ሲኖር፣
- የሚያጓጉዙበት ግመልና አህያ ያለው፣
- ለሥራ የደረሱ ልጆች ያሉት፣
- ከ80 በላይ ከየዓይነቱ እንስሳት ያሉት፣
- በጥምር ግብርና በሚካሄድባቸው አካባቢ ደግሞ የሚያርሱበት አንድ ጥንድ በሬ ያለው የጥሩ ሕይወት መገለጫዎች ናቸው::

መጥፎ ሕይወት

መጥፎ ሕይወት በህብረተሰቡ የሚገለፀው

- የዝናብና የግጦሽ እጥረት ሲከሰት፣
- ለጭነት የሚሆኑ ግመልና አህያ የሌለው፣
- የሚታለብና የሚሸጡ የቤት እንስሳት አለመኖር፣
- በጥምር ግብርና አካባቢ ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ የሚያርሱበት የእርሻ በሬዎች የሌሉትና ዝቅተኛ ምርት ሲመረት /5 ኩንታል/

በክልል ደረጃ የድህነት መገለጫዎች በቅደም ተከተል

1. የምግብ እጥረት፣
2. የመጠጥ ውሃ አለመኖር፣/ለሰው እና ለእንስሳት/
3. የጤና ችግር /የሰውና የእንስሳት/
4. ግጭት /በሰላም አለመኖርና አለመረጋጋት/
5. ትምህርት፣
6. መንገድ፣
7. ገቢ፣

የድህነት መገለጫዎች በቅደም ተከተል በሴቶች አገላለፅ

1. ጤና፣
2. የምግብ እጥረት፣
3. የመጠጥ ውሃ እጥረት፣
4. ግጭት
5. ትምህርት፣
6. ገቢ፣
7. መንገድ፣

CCRDA

5.2. የክልሉ የኑሮ ድህነት ሁኔታ

5.2.1. ወቅታዊ ሁኔታና የለፉት አምስት ዓመታት ግምገማ

ባለፉት አምስት ዓመታት በክልሉ የገጠሩ ክፍል ውስጥ የኑሮ ሁኔታ ድህነት እየተባባሰ መጥቷል፡ ለዚህ እንደምክንያት የተገለፁት፡-

- የዝናብ እጥረትና ድርቅ በተደጋጋሚ መከሰት፣
- የሰውና የእንስሳት ወረርሽኝ መበራከት፣
- የአዋሽ ወንዝ የተፈጥሮ አቅጣጫውን በመሳቱ በአንድ በኩል በእርሻ መሬቶች ላይ የመስኖ ውሃ እጥረት በማስከተል የምርት መቀነስ ሲያስከትል በሌላ መልኩ ደግሞ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የውሃ መጥለቅለቅ በማስከተል በግጦሽ መሬት ላይ መተኛትና በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት ማድረስ፣
- ክልል ተሻጋሪ ወንዞች ላይ ሚዛናዊ ያልሆነ አጠቃቀም ባስከተለው የውሃ እጥረት በእንስሳት ውሃና በግጦሽ መሬት ላይ ችግር ማስከተል፣
- የግጦሽና የእርሻ መሬቶች በProsopise, Pertinium እና በሌሎች አላስፈላጊ ቁጥቋጦዎች መሸፈንና መወረር፣
- ግጭቶች ከክልሉ አጎራባች ከሆኑ ክልል ወረዳዎች ጋር መበራከት ምክንያት የተረጋጋ ሕይወት መምራት አለመቻል፣
- የእንስሳትና ሌሎች መሠታዊ ፍጆታዎች የሚገበያዩበት ገበያ በአቅራቢያቸው አለመኖር፣
- የመሠረተ ልማት አውታሮች በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት ሲሆን፣

ከትምህርት አገልግሎትና ተሳትፎ በኩል ባለፉት አምስት ዓመታት በተወሰነ ደረጃ የመሻሻል ሁኔታ አሳይቷል።

5.2.2. የመሠረታዊ ፍላጎቶች ለፍተኛ ጉድለት የሚታይባቸው ወቅቶች

በአርብቶ አደሩ አካባቢ በግጦሽና በውሃ ችግር ምክንያት የምግብ እጥረት ከጥር እስከ ሰኔ ባለው ጊዜ ውስጥ ሲከሰት ጥምር ግብርና ለሚያካሂድ አካባቢዎች ደግሞ ከሀምሌ እስከ መስከረም ይከሰታል።

በክልሉ የገጠር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ /ከወንዝና ከወራጅ ውሃ/ ለሰውም ሆነ ለእንስሳቱ እጥረት የሚታይባቸው ወራቶች ከሕዳር እስከ ሰኔ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

ሰውም ሆነ በእንስሳት ላይ የሚከሰቱ ወረርሽኝ በሽታዎች በሰው ላይ የወባ በሽታ ከመስከረም ወር አንስቶ እስከ ጥር ባለው የጊዜ ውስጥ የማከሰት ሲሆን በእንስሳት ላይ የተለያዩ የእንስሳት ወረርሽኝ በሽታዎች በዓመት ሁለት ጊዜ ይከሰታሉ። እነዚህም አንደኛው በዝናብ የመጀመሪያ ወራት /በሐምሌ/ አካባቢ ሲሆን ሁተኛው ደግሞ የግጦሽና የውሃ እጥረት በሚበረታበት ከየካቲት እስከ ሰኔ ባሉት ወራቶች ውስጥ ነው።

CCRDA

በጥምር ግብርና በማተዳደሩ አካባቢዎች የሰብል ተባይ ወረርሽኝ የሚከሰተው ከመስከረም እስከ ጥቅምት ሲሆን በተለየ መልክ በመከሰት የሰብል ምርት በመቀነስ የሚታወቀው ጥቁር ጢንዚዛ /Pitles/ በመባል የሚታወቀው ነው::

5.2.3. ለድህነት በይበልጥ የተጋለጡ አካባቢዎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ገፅታ

በአፋር ክልል ያለው የድህነት ደረጃ በአብዛኛው በእኩል ሁኔታ ላይ የሚገኝ እና ይህም ቢሆን ግን የድህነት ደረጃው ከቦታ ቦታ የተለያዩ ሲሆን ለድህነት በይበልጥ የተጋለጡት አካባቢዎች በአብዛኛው ከዚህ የሚከተለት ናቸው::

- በአዋሽ ወንዝ አካባቢ የመንግስት እርሻና ፓርክ በመስፋፋቱ የተነሳ የግጦሽ መሬት መጣበብና ከወንዝ ውሃ መራቅ፣
- ከአጎራባች ክልል ወረዳዎች ጋር ኩታ ገጠም በሆኑ ወረዳዎች /በግጭት የተነሳ/፣
- ክልል ተሻጋሪ ወንዞች ላይ ፍትሀዊ አጠቃቀም ባለመኖሩ የውሃው መጠን በጣም በመቀነሱ በዚያ አካባቢ የሚኖሩ አርብቶ አደሮች የበጋ ግጦሽ ቦታዎችን ለመጠቀም አለመቻል፣
- ከመንገድ ርቀው የሚገኙ አካባቢዎች እና
- በአዋሽ ወንዝ አነስተኛ መስኖ የሚጠቀሙ ገበሬዎች ወንዙ አቅጣጫ በመቀየሩ በውሃ እጥረት የተነሳ ምርት ማምረት ያልቻሉ አካባቢዎች ውስጥ ለድህነት በይበልጥ የተጋለጡት ሲሆኑ ከህብረተሰብ ክፍሎች፣

1. ሴቶችና ሕፃናት
2. ወጣቶች
3. አረጋውያን

5.3. በክልሉ ለድህነት የሚዳርጉ ምክንያቶች

5.3.1. በክልሉ የሀብት መገለጫዎች

ክልሉ በአብዛኛው አርብቶ አደር በሆኑ ዋነኛው የሀብት መገለጫዎች በቤት እንስሳት ብዛት ሲሆን በተወሰነ ደረጃ ጥምር ግብርና በማያካሄዱ አካባቢዎች ደግሞ በሰብል ምርትና እንስሳት ሀብት ነው::

5.3.2. የሕብረተሰቡ ዋና ዋና የገቢ ምንጭ

በክልሉ በገቢ ምንጭነት በዋነኝነት የሚጠቀሰው ከእንስሳትና ከእንስሳት ተዋፅኦ የሚገኘው ገቢ ሲሆን በጥምር ግብርና በሚተዳደሩ አካባቢዎች ደግሞ ዋናው የገቢ ምንጫቸው ከሰብልና ከእንስሳቱ ነው:: ከዚህም ውጭ በክልሉ በተወሰኑ ወረዳዎች ከጨውና ከሰሌን ምንጣፍ ሥራዎች ከላይ ከተጠቀሱት የገቢ ምንጮች በተጨማሪ ገቢ ያስገኛሉ::

CCRDA

በከተማው አካባቢ ደግሞ በሆቴልና በአነስተኛ ሽቀጣ ሽቀጥ ንግድ እንዲሁም በመንግስት ሥራ በመቀጠር የተዳደራሉ::

5.3.3. የክልሉ የሥራ ስምሪት እና ምርታማነት ችግሮች

በክልሉ ዋነኛ የሥራ ስምሪት የሆኑት

- ወጣት ወንዶች ለግመሎች እና ለከብቶች ግጦሽና ውሃ ፍለጋ መሰማራት፣
- ወጣት ሴቶች ለበጎችና ፍየሎች በቅርብ አካባቢ የግጦሽና ውሃ ፍለጋ መሰማራት፣
- ሴቶች ደግሞ ለመጠጥ ውሃ ፍለጋ፣ለቤተሰብ እንክብካቤና ለገበያ ስምሪት ሲሆን በከተማው ያለው የሥራ ስምሪት በሆቴል ሥራ፣በተለያዩ ንግዶችና በመንግስት ሥራ ነው::

በሰው ኃይል ምርታማነት ላይ ያሉ ችግሮች

- በእንስሳቱ የግጦሽና ውሃ አቅርቦት ያለው ችግር
- በመጠጥ ውሃ ችግር
- የጤና አገልግሎት አለመስፋፋት እና
- የገበያ ችግር ናቸው::

5.3.4. *በክልሉ ልማዳዊና ባህላዊ ተፅዕኖዎች*

በክልሉ ልማዳዊና ባህላዊ ተፅዕኖዎች በቅደም ተከተል፣ በተጎጂ ሕብረተሰብ ክፍልና በአካባቢ ሕብረተሰብ ያደረሰው ተፅዕኖ::

1. በሴቶች ላይ የሚደርሰው የሥራ ጫና- ተጎጂ ሴቶች
2. ብዙ ሴት ማግባት - .. ሴቶች
3. ብዙ ልጅ መወለድ - ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት
4. ሠርግ - ተጎጂ ቤተሰብ
5. ሠደቃ - .. ቤተሰብ
6. ሱሰኝነት - ተጎጂ ሴቶችና ህፃናት

5.3.5. የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች

በክልሉ እንደሚታወቀው አርብቶ አደር እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ የተፈጥሮ እና የሰው ሰራሽ ችግሮች ሰለባ እየሆነ መምጣቱ የሚታወቅ ነው:: ምንም እንኳን የአርብቶ አደሩ ችግር ተዘርዝሮ ባያልቅም ከዚህ በታች ዋና ዋና የተባሉትን በቅደም ተከተል እና በዋና የተጎጂ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለማስቀመጥ ተሞክሯል::

CCRDA

1. ድርቅ

በአርብቶ አደሩ እንደ ዋነኛ እና ቀዳሚ ችግር ተብሎ የሚጠቀሰው የድርቅ ወይንም የግጦሽ የውሃ ችግር ሲሆን በዚህም ችግር ምክንያት መላው የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጎጂ ናቸው::

2. ግጭት

ለአርብቶ አደሩ ሕብረተሰብ ሌላው ችግሩ የግጭት መከሰት ሲሆን ይህም- የሚሆነው ለእንስሳቱ የግጦሽ መሬት እንዲሁም ውሃ ፍለጋ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የሚያጋጥመው ነው:: በዚህ አጋጣሚ ሣይጠቀስ የማይታለፈው በአብዛኛው ግጭቱ ተባብሶ የሚታየው በአፋር ምድር ላይ ተቀምጦ የአፋርን ህብረተሰብ ሰላም የሚነሣው የኢሣ ብሄረሰብ ሲሆን መንግስት ለዚህ ዓይነቱ ችግር አፋጣኝ ምላሽ ካልሰጠ ችግሩ እየተባባሰ እና የብዙ ዜጎች ሕይወት እየተቀጠፈ ሊቀጥል ይችላል:: በዚህም መሠረት በአብዛኛው የችግሩ ተጋፋጭ የሆኑ ወጣት ወንዶች ቢሆኑም የሚጎዱት ግን ሴቶችና ሕፃናት እንዲሁም ቀሪው የአፋር ሕዝብ ነው::

3. የማህበራዊ አገልግሎት ችግር

ሣይፈልግና ሣይወድ የክብትን ጭራ ተከትሎ ለሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል የማህበራዊ አገልግሎት አለመኖር እና ያሉትም የአገልግሎት መስኮች የሱን የኑሮ ሁኔታ ያልተከተሉ በመሆናቸው ትኩረት ሊሰጥባቸው ያሻል::

4. የአቅም ግንባታ ችግር

በክልሉ የተለያዩ የልማት አውታሮች በተለያዩ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል አለመኖራቸው የታቀዱት ሥራዎች በአግባቡ ተግባራዊ ሊሆኑ አልቻሉም::

5. የመንግስት ትኩረት ያለመኖር

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ሕብረተሰቡ ማለትም አርብቶ አደሩ ብቻውን ለፈታ እና ሊወጣው እንደማይችል እየታወቀ በተለያዩ ጊዜ የሚቀያየሩ መንግስታት ይህንን ሕብረተሰብ ወደ ጎን በመተው እንዲሁም የሚቀረፁ ስትራቴጂዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የእነሱን ችግር የማይፈቱና የማያንፀባርቁ መሆኑ እየታወቀ ለብዙ ዘመናት ቆይተዋል:: በዚህም ችግሮች እየተባባሱ የመጡ ስለሆነ መንግስት አስፈላጊውን ትኩረት ለአርብቶ አደሩ በመስጠት ሊንቀሳቀስ ይገባል::

6. የአዋሽ ወንዝ የተፈጥሮ አቅጣጫውን መሣቱ

የአዋሽ ወንዝ ድሮ የነበረውን የተፈጥሮ አቅጣጫውን ስቶ አዲስ መንገድ በቀየሱ በአርብቶ አደሩ ሕብረተሰብ ላይ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል::

CGRDA

ይኸውም:-

- ወንዙ በክረምት ወቅት በሚሞላበት ጊዜ በርካታ መሬቶችን ስለሚያጥለቀልቅ በርካታ ሕብረተሰቦችን አፈናቅሏል፣አላስፈላጊ የሆኑ እፅዋት እንዲራቡና እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮላቸዋል። ከዚህም በላይ ቀደም ሲል በአካባቢው የነበሩት ለግጦሽ አገልግሎት የሚውሉ ነባር የሣር ዝርያዎችን በደለል በመሸፈኑ ዝርያዎቹም እንዲጠፉና እንዲመናመኑ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

- ቀደም ሲል የነበረውን የተፈጥሮ አቅጣጫውን በመሣቱ በወንዝ ዳርቻ በመንግስት እርሻና በሕብረተሰቡ ሲለሙ የነበሩ መሬቶች በተፈጠረው የውሃ ችግር ምክንያት ከጥቅም ወጭ ሆነዋል።

7. የሰብል ተባይ እና አረም

ወቅትን ጠብቆ የሚመጡ የተባይ ዓይነቶች አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆን በጥቂት አርሶ አደሩ አካባቢ ችግሮችን አስከትሏል።

8. ኤች. አይ. ቪ. /ኤድስ/

በግንዛቤ እጥረትም ሆነ በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት የዚህ ዓይነቱ በሽታ እየተባባሰና ሌላ ሥም እየተሰጠ ስር እየሰደደ መጥቷል። በዚህም ወጣቶችና ሴቶች በተለይ በከተማው ሕብረተሰቡ በብዛት ተጎጂ ሆኗል።

5.4. ባለፉት 5 ዓመታት ድህነትን ለመቀነስ የተደረጉ ጥረቶች

5.4.1. ሕብረተሰቡና ሕብረተሰቡ ያቋቋማቸው ድርጅቶች

በክልሉ ምንም እንኳን በሕብረተሰቡ የተቋቋሙ ማህበራት ወይም ድርጅቶች ባይኖሩም ሕብረተሰቡ ልማትን ለማፋጠን፣ አደጋን ለመከላከል የራሱን ጥረት አድርጓል።

ልማትን በማፋጠኑ በኩል በተወሰኑ ወረዳዎች ከዞን ከወረዳና ከተለያዩ ቀበሌዎች የሚያገናኙ ጥርጊያ መንገዶች በመስራት ለልማት ሥራዎች እገዛ እንዲሰጡ ማድረግና ማህበራዊ ተሀድሶ ልማት ፈንድ በሚያካሂዳቸው የማህበራዊ ተቋማት ግንባታ ላይ በገንዘብ፣በጉልበትና በማቴሪያል ድርጅቱን በመደገፍ አካባቢያቸውን ለማልማት ጥረት አድርገዋል።

አደጋን በመከላከል በኩል ከላይ የተጠቀሰው የመንገድ ሥራ አደጋን ከመከላከል በኩል አስተዋፅኦ ሲያደርግ ከዚህ በተጨማሪ ጎርፍ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች የቦይ ጠረጋ በማካሄድ የጎርፍ አደጋን ለመከላከል ጥረት ሲያደርጉ በአንዳንድ ወረዳዎች የውሃ እጥረትን ለማቃለል ሕብረተሰቡ በራሱ ቢርካዎች /ዝናብ ውሃ ማጠራቀሚያ/ በመስራት የውሃ እጥረትን ለመከላከል ሲጥር በሌላ መልኩ በሕብረተሰቡ መካከል ያለው የመረዳዳት ባህል አደጋ በሚከሰትበት ወቅት ያላቸውን ሀብት ቢያጡም የተረፈውን በጣም ለተቸገረው በመስጠት ችግሩን በጋራ ለመወጣት ይጥራሉ።

CCRDA

ልማትን ለማፋጠንና አደጋን ለመከላከል በሕብረተሰቡ ትኩረት የሚሰጣቸውና መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች፡-

- የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ የመጠበቅና የመጠቀም ልምድን ማጎልበት፣
- ባህላዊ የደን አጠባበቅ ስርዓቶችን ማጠንከር፣
- ሕብረተሰቡ የተለያየ ማህበራትን በማቋቋም በጋራ ልማትን ለማፋጠንና አደጋን ለመከላከል ጥረት ማድረግ፣ በሕብረተሰቡ በኩል ትኩረት መስጠት የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው።

5.4.2. መንግስታዊ ተቋማት

ባለፉት ዓመታት በክልሉ መንግስት በጤና፣በትምህርት፣በእንስሳት ጤና ተቋማትና በመጠጥ ውሃ ሥራ ላይ ትኩረት ተሰጥቷቸው የተከናወኑ የልማት ፕ ሮግራሞች ሲሆኑ ከዚህም በተጨማሪ የወረዳ መበህለሎችን ለመመስረት የተለያዩ ፅሕፈት ቤቶች በማሠራት የወረዳ መዓከላትን በማጠናከር ልማትን ለማፋጠን ጥረት ተድርጓል።

ሆኖም ግን በሕብረተሰቡ ዕይታ በመንግስት የተወሰደው የልማት ፕሮግራም ከሕብረተሰቡ ፍላጎት አኳያ ውስን ሲሆን እነዚህን የልማት ፕሮግራሞች ሕብረተሰቡ በሚከተለው መልኩ ተመልክቷቸዋል።

1. የጤና ተቋማት ካለው ፍላጎት አኳያ አነስተኛ ከመሆናቸው በተጨማሪ ያሉትም በሆኑ የባለሙያ፣የህክምና መሣሪያና የመድኃኒት አቅርቦት በቂ አለመሆን፣
2. በእንስሳት እክምና በኩል የተሰሩት ተቋማት ሕብረተሰቡ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተጣጥመው ባለመሰራታቸው አገልግሎት መስጠት አለመቻልና ከዚህም ውጭ የባለሙያና የመድኃኒት እጥረት በመኖሩ ለሕብረተሰቡ ግልጋሎት መሰጠት አለመቻል፣
3. በመጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ በወረዳ መዓከላት የተሰሩ የመጠጥ ውሃ ግንባታዎች ግልጋሎት ለመስጠት አለመቻልና ሲበላሹ የሚጠግናቸው በማጣት ለረጅም ጊዜ ያለ አግልግሎት መቆየት እና ለእንስሳቱ የሚሆን ከግጦሽ ጋር የተያያዙ የውሃ ሥራ አለመኖር እና
4. በትምህርት መስክ የተከናወኑ ሥራዎች የሕብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ያላገናዘቡ በመሆናቸው ካለው ወስንነት ጋር ተዳምሮ በትምህርት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደራቸው ሕብረተሰቡ በመንግስት የልማት ተቋማት ላይ ያያቸው ጉድለቶች ናቸው።

ከአብዛኛው የመንግስት የልማት ፕሮግራሞች ላይ ሕብረተሰቡ ያለው ተሳትፎ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገመገም በጣም ውስንና ዝቅተኛ መሆኑን መረዳት ቢቻልም የተቀናጀ አሠራር እና ሕብረተሰብ ያሣተፈ የልማት ፕሮግራሞች ቢነደፉ የተሻለ ልማት ማስመዝገብም እንደማቻል ሕብረተሰቡ የራሱን አስተያየት ሰጥቶበታል።

በአስተዳደርና እርከኖች መካከል ያለው ግንኙነት ዝቅተኛ እንደሆነ፣ በሚሰሩ ሥራዎች ቅንጅት እንደሌለና ከታች ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ውሳኔ ለመስጠት አለመቻልና በራስ ተነሳሽነት ሥራን አለመጣር በአስተዳደር እርከኖች ላይ የሚታዩ ችግሮች ናቸው።

CCRDA

በመንግስት በኩል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

በጤና ዘርፍ

- የጤና ተቋማትን ከመስራት ጎን ለጎን ያሉትን በሰው ኃይል በማቴሪያልና በመድኃኒት ማሟላት፣
- ለሕብረተሰቡ በቅርብ ሕክምና ሊሰጡ የሚችሉ ግንባር ቀደም የጤና ባለሙያዎችንና የልምድ አዋላጆችን በማሰልጠን ለሕብረተሰቡ ግልጋሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣

በእንስሳት እርባታ

- የእንስሳት ሕክምናን ለማሻሻል የመድሃኒት አቅርቦትን በአካባቢው ካለው በሽታ ጋር ማጣጣም እና አቅርቦቱን ማሻሻል፣ ከሕብረተሰቡ የወጡ የእንስሳት ጤና ተጠሪዎችን ማሰልጠን፣የእንስሳት ጤና አገልግለት መስጫ ተቋማትን ለሕብረተሰቡ በሚጠቅም መልክ መሰራትና በሰለጠነ የሰው ኃይል ማደራጀት፣
- የእንስሳት ጥራትና ምርታማነትን ለማሻሻል ከግጦሽ መሬት ጋር በተያያዙ መልኩ የውሃ አቅርቦትን ማስፋፋትና የእንስሳት መኖ ፕሮግራምን ማስጀመር፣

በእርሻ ልማት

- የመስኖ እርሻ ሥራዎችን ለማስፋፋት አነስተኛ የወንዝ ጠለፋን፣ የግድብ ሥራ ማካሄድ፣ አነስተኛ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችንና የእርሻ መሣሪያዎችን ማሟላት እንዲቻል የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- አነስተኛ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችንና የእርሻ መሣሪያዎችን ማሟላት፣
- ለሕብረተሰብ የመስኖ ውሃ አጠቃቀምና የወንዝ ጠለፋ ማካሄድ እንዲቻል የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፣

በውሃ ልማት

- የውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣
- በግጦሽ ቦታዎች ላይ የውሃ ሥራ ማካሄድ፣
- በፀሐይና በነፋስ የሚሰሩ የውሃ መሣቢያዎችን ለክልሉ ምቹ መሆናቸውን በማጥናት በሚገኘው ውጤት ጥቅም ላይ ማዋል እና
- ከሕብረተሰቡ ለተውጣጡ የውሃ አጠቃቀምና ጥገና ስልጠና መስጠት

በትምህርት ዘርፍ

- ትምህርት ቤቶችን በሰው ኃይልና በማቴሪያል ማሟላት፣

CCRDA

- በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በአለም አቀፍ የምግብ ድርጅት የሚካሄደውን የምግብ ኘሮግራምን ማጠናከርን በተለይ ለሴቶች የሚደረገውን ማበረታቻ ማጠናከር፣
- የትምህርት ካላንደሩን ከሕብረተሰቡ አኗኗር ጋር ማጣጣም፣
- ከሕብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ጋር የተጣጣመ የትምህርት ኘሮግራም ማስጀመር፣
- የአዳሪ ትምህርት ቤቶችንና የጎልማሶች ትምህርት ማስፋፋት፣

በመሠረተ ልማት

- የመሠረተ ልማት አውታሮችን ማስፋፋት በመንግስት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ሥራዎች ቢሆኑም ከእነዚህ በተጨማሪ ሌላ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ የቁጠባና ብድር አገልግሎትን በክልል በማስጀመርና በማስፋፋት ሕብረተሰቡን በልማት እንዲሳተፍ ማድረግ ነው።

5.4.3. መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት

መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በክልሉ አደጋን በመከላከልና በልማት ዘርፉ በአለፉት ዓመታት የነበራቸው ተሳትፎ ከሌላው ጋር ሲነፃፀር በጣም አናሳ ሲሆን እነዚህ ድርጅቶች በጤና በውሃ ልማት፣ በእንስሳት ጤና አገልግሎት ላይ በመሳተፍ የክልሉን መንግስት በተወሰነ መልኩ በመደገፍ ላይ ይገኛሉ።

መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚያከናወኑት ሥራዎች ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አነስተኛ ሆነው የልማት ኘሮግራማቸው ግን የክልሉን ፍላጎት ትኩረት የሰጡ ናቸው። ነገር ግን ያላቸው እንቅስቃሴ ከተሀድሶ ልማት ፈንድ ውጭ በተወሰኑ አካባቢዎች በተለይ በዞን ሶስትና በዞን አንድ በመሆኑ በሌላ ዞኖች ያላቸወ ተሳትፎ የለም ለማለት ያስደፍራል።

የሥራ ክንውንና አፈፃፀምን በተመለከተ በተወሰኑ ድርጅቶች ላይ ችግር ሲኖር ሕብረተሰቡን በኘሮጀክት ኘሮግራማቸው ላይ በማሳተፍ ላይ ያላቸው እንቅስቃሴ በአብዛኛ ው አነስተኛ ሲሆን በአንዳንዶቹ ላይ ጭራሽ የለም ማለት ይቻላል።

በቀጣይነት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በክልሉ ያላቸው ተሳትፎ ውስን ስለሆነ ወደፊት በልማት ኘሮግራሙ ላይ የሚሳተፉበት መንገድ በክልሉ መንግስት ቢመቻች እና በእነሱም ጥረት ቢደረግ፣
- እንዲሁም በክልሉ ራቅ ብለው በሚገኙና የልማት እንቅስቃሴው አናሳ በሆነባቸው አካባቢዎች ገብተው ለመስራት ትኩረት መስጠት እና
- በሚሰሩት የልማት ኘሮግራሞች ሕብረተሰቡን በማሳተፉ የኘሮጀክቶቹን ዘለቄታነት አስተማማኝ ማድረግ ናቸው።

CCRDA

5.5. ድህነትን ከክልሉ ለመቅረፍ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

ምንም እንኳ ድህነትን ለመቅረፍ በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ሕብረተሰቦች ብዙ ቢጠበቅም እንደየችግሮቹ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ዋና ዋና መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች እንደሚከተሉት በጭሩ ተዘርዝረዋል::

I. የውሀ እና የግጦሽ ችግርን ለመቅረፍ

ሀ. በቋሚነት ለሚፈሱ ወንዞች ዳርቻ ያሉ ክፍሎችን በኢሪጌሽን /መስኖ/ ለመጠቀም ከከብት ማርባቱ ጎን ለጎን የእርሻ ሥራን እንዲያከናውኑ የመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ሕብረተሰቡን ለእንደዚህ ዓይነት ሥራ ዝግጁ እንደሆኑ ማድረግ፣

ለምሣሌ:- አመቱን በሙሉ በሚፈሱ ወንዞች ባሉበት አካባቢ ለሚኖሩ::

ለ. ደረቃማ አካባቢዎችን ደግሞ የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮን እና የዝናብ ውሃን በመገደብ ግልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣

ሐ. በክልሉ የመስኖ ግድብ እና ዳይክ ስራዎችን በማጠናከር የአዋሽ ወንዝ የተፈጥሮ አቅጣጫው የአዋሽን ወንዝ የተፈጥሮ አቅጣጫው እንዳይዝ ማድረግ፣

መ. በግጦሽ መሬት ላይ እየተስፋፋ ያለውን የProsopise /ወያኔ ዛፍ/ እና ፓርቲነየም ስርጭትን መግታት፣

II. ግጭትን በማስወገድ ረገድ

ለልማት ዋናው መሰረቱ ሠላም በመሆኑ የክልሉ መንግስትም ሆነ የፌዴራል መንግስት የግጭቶችን መንስኤ ከሕብረተሰቡ ጋር በመለየት አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት ይኖርበታል::

III. የማህበራዊ አገልግሎት ችግሮችን በመፍታት ረገድ፣

መንግስት በአለፉት ዓመታት የገነባቸው የማህበራዊ ሰጭ ተቋማት የአፈፃፀም ችግር በማጤን ሕብረተሰቡ አስፈላጊውን አገልግሎት ሊያገኝ በሚችል መልኩ እንዲጠናከር ማድረግ::

ወደፊት አርብቶ አደሩ ማህበራዊ አገልግሎት ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆን መንግስትም ሆነ ሌሎች የልማት ሀይሎች ከእሱ የአኗኗር ዘይቤ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ የኘሮጀክቶች ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ::

CCRDA

IV. የመሠረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት

ለአርብቶ አደሩ ሕብረተሰብ መሠረታዊ ከሆኑት የግጦሽ እና የውሃ እንዲሁም የማህበራዊ አገልግሎቶች በተጨማሪ ለኑሮው መሣካት እና እድገት ዋነኛው በተጨማሪ የመሠረተ ልማት አውታሮች መስፋፋት ሲሆን መንግስትም ሆነ ሌሎች የልማት ሀይሎች ይህንኑ አውቀው ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ስትራቴጁዎችን መቅረፅ አለባቸው::

V. የአርብቶ አደሩ የልማት ኘሮጀክቶችን በተመለከተ

በዘላቂነት የአርብቶ አደሩን ችግር ለመፍታት በቅርቡ በመንግስት የተሰጠው ትኩረት ተጠቃሚ ሕብረተሰቡን በቀጥታ ባሣተፈ መልኩ ጠንካራ የአስተዳደር ስርዓት በመገንባት የአርብቶ አደሩን ችግር ደረጃ በደረጃ ሊቀርፉ የሚችሉ የልማት አውታሮችን በመዘርጋት ድህነትን መቀነስና መዋጋት ይቻላል::

6. ያጋጠሙ ችግሮች

ይህን ሰነድ ለማዘጋጀት የክልሉ መንግስት የሚጠበቅበትን ሁሉ ያደረገ ቢሆንም ከፌዴራል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የድህነት ቅነሣ ስትራቴጁ ዝግጅት ፅ/ቤት የተመደበውን በጀት ክልሉ ባቀረው ኘሮፖዛል ወቅቱን ጠብቆ ባለመላኩ የስራ መጓተትን እና ጫናን ፈጥሯል::

CCRDA

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት በክልል ደረጃ ለሚካሄደው የምክክር ስብሰባ ፕሮግራም

ሠንጠረዥ -1


ቀን	ሰዓት	ድርጊት	አቅራቢ	አወያይ
የካቲት 29/1994 ዓ.ም	2:30-3:00	ምዝገባ	ኮሚቴ	ሰብሳቢ
	3:00-3:15	የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር	አቶ ጀማል አብዱ ቃድር	..
	3:15-3:30	የመክፈቻ በቁርዓን	በአገር ሽማግሌ	..
ዓርብ	3:30-3:45	የመክፈቻ ንግግር	በዕለቱ ክብር እንግዳ ም/ፕሬዚዳንት	..
ጠዋት	3:45-4:15	ሻሂ ቡና /ዕረፍት/	መስተንግዶ ኮሚቴ	
	4:15-5:00	ከምክር ቤት የሚቀርብ ፅሑፍ	በአቶ ጀማል ኑር	..
	5:00-6:00	ከተወካዮች ም/ቤት የሚቀርብ ፅሑፍ	..	..
	6:00-9:00	የምሣ ዕረፍት	በግል	
ከሠዓት በኋላ	9:00-10:00	በቀረቡ ፅሁፎች ላይ ውይይት	በተሳታፊዎች	..
	10:00-10:30	ሻሂ ቡና /ዕረፍት/	መስተንግዶ ኮሚቴ	
	10:30-10:50	የገዋኔ ወረዳ ሪፖርት ይቀርባል	በወረዳው ሰብሳቢ	..
	10:50-11:30	በቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይት	በተሳታፊዎች	..
የካቲት 30/1994 ዓ.ም	2:30-2:50	የበራሀሌ ወረዳ ሪፖርት ይቀርባል	በወረዳው ሰብሳቢ	..
	2:50-3:30	በቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይት	በተሳታፊዎች	..
	3:30-3:50	የፋርሲ ወረዳ ሪፖርት ይቀርባል	በወረዳው ሰብሳቢ	..
ቅዳሜ	3:50-4:20	ሻሂ ቡና /ዕረፍት/	መስተንግዶ ኮሚቴ	
ጠዋት	4:20-4:50	በቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይት	በተሳታፊዎች	..
	5:00-5:20	የዱብቲ ወረዳ ሪፖርት ይቀርባል	በወረዳው ሰብሳቢ	..
	5:20-6:00	በቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይት	በተሳታፊዎች	..

ከሠንጠረዥ -1 የቀጠለ ...

ቀን	ጊዜ	የፕሮግራሙ ዝርዝር	አቅራቢ	አወያይ
የካቲት 30/1994 ዓ.ም	6:00-9:00	የምሣ ዕረፍት	በግል	
ከሠዓት በኋላ	9:00-9:20	የአውራ ወረዳ ሪፖርት ይቀርባ	በወረዳው ሰብሳቢ	በሰብሳቢ
	9:20-10:00	በቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይት	በተሣታፊዎች	..
	10:00-10:30	ሻሂ ቡና /ዕረፍት/	መስተንግዶ ኮሚቴ	
	10:30-11:10	የአርጎባ ወረዳ ሪፖርት ይቀርባል	በወረዳው ሰብሳቢ	..
	11:10-12:00	በቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይት	በተሣታፊዎች	..
መጋቢት 01/1994	2:30-3:00	በቀረቡት በሁለት ቀን ሪፖርት ላይ አጭር ገለፃ	በሰብሳቢዎች	..
ጠዋት	3:00-4:00	ውይይት	በተሣታፊዎች	..
እሁድ				..
	4:00-4:30	ሻሂ ቡና /ዕረፍት/	መስተንግዶ ኮሚቴ	
	4:30-5:30	የማጠቃለያ ውይይት	በተሳታፊዎች	..
	5:30-6:00	የመዝጊያ ንግግር	ም/ፕሬዚዳንት	..

CRDA

በኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት የሐረሪ ክልል የምክክር ሰብሰባ ግኝት አጭር ሪፖርት



CRDA

በሐ/ህ/ብ/ክ/መንግሥት

በፕ/ኢ/ል/ቢሮ የተዘጋጀ

መጋቢት 1994 ዓ.ም

ሐ ረ ር

1 መግቢያ

ሀገራችን እጅግ የተንሰራፋውን ድህነት ለመቅረፍ እንዲያስችል ብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ለማዘጋጀት ከጀመረችው በርካታ ጥረቶች አንዱ በወረዳ፣ በክልልና በፌደራል ደረጃ የሲቪክስ-ማህበረሰብና የሚመለከታቸው ወገኖችን ያሳተፈ የምክክር ስብሰባ ማካሄድ ይገኝበታል።

በዚሁ መሠረት በሐረሪ ክልል በወረዳና በክልል ደረጃ ጎብረተሰቡና የሚመለከታቸው ወገኖችን ያሳተፈ የምክክር ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል። የስብሰባው ግኝቶችም ዝርዝር ሪፖርት በጽሁፍ ተጠናቅሮ ለሚመለከታቸው አካላት ተሰራጭቷል።

በፌደራል ደረጃም በቅርቡ ተመሳሳይ የምክክር ስብሰባ ይካሄዳል። በወረዳና በክልል የተካሄዱ ምክክሮችና ግኝቶች ለፌደራል ምክክር መነሻና ለስኬቱም ጠቃሚ መረጃዎችን በማበርከት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ። በመሆኑም የክልሉ ምክክር ስብሰባ ሂደትና ግኝቶች አስመልክቶ ለፌዴራል ምክክር ታሣታፊዎች በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ እንዲያስችል ይህን አጭር ሪፖርት ማዘጋጀት አስፈልጎል።

ሪፖርት በክልሉ የተካሄዱ የምክክር ሂደት፣ በአፈፃፀም ያገጠሙ ችግሮችና የተገኙ ተሞክሮዎችን ሲዳሰስ በዋነኛነትም በምክክር የተገኙ ግኝቶች በተለይም የክልሉ ድህነት ገጽታ፣ መንስኤ፣ ባለፉት ዓመታት ድህነትን ለመቀነስ የተደረጉ ጥረቶችና ወደፊትም ድህነትን ለመቀነስ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች በአጭሩ ይቃኛል።

CGRDA

2. የሐረሪ ክልል የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅትና ሂደት አጭር ሪፖርት

የብሔራዊ ድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት አካል የሆነዉ የሐረሪ ክልል ምክክር ስብሰባ ዝግጅት ነሐሴ 23 ቀን 1993 ዓ.ም የዝግጅቱ አስተባባሪ አስፈፃሚና ድጋፍ ሰጪ አካላት የስትሪንግ፣ የቴክኒክ ኮሚቴ እና ሴክሬተሪያት በማዋቀር እንቅስቃሴዉን በይፋ ጀመረ።

እንቅስቃሴን በማጠናከርም በወረዳና በክልል ደረጃ የምክክር ስብሰባዉን ለማካሄድ ተፈላጊ ቅድመ ዝግጅት ተግባራትን በማጠናቀቅ በቅድሚያ የወረዳ ምክክሩን በክልሉ የገጠር እና የሐረር ከተማ የምክክር ስብሰባ መድረኮች አማካይነት ከጥቅምት 30 እስከ ህዳር 3 ቀን 1994 ዓ.ም ሲያጠናቀቅ በቀጣይም የክልል ምክክሩን ከጥር 29 እስከ የካቲት 1 ቀን 1994 ዓ.ም በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል።

እነዚህን የምክክር ስብሰባዎች ለማስፈፀም የተከናወኑ አብይ ቅድመ ዝግጅት ተግባራት፣ የስብሰባዉ ሂደትና የገጠሙ ችግሮች እንዲሁም የተገኙ ተሞክሮዎች በአጭሩ እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

2.1 ቅድመ ዝግጅት ተግባራት

2.1.0 የቴክኒክ ኮሚቴ ስልጠና

የስትራቴጂዉን ዝግጅት ለማሳካት በቅድሚያ ከተለያዩ ሴክተር ቢሮዎች የተዉጣጡ 13 ከፍተኛ ባለሙያዎችን በአባልነት ላቀፈ ለቴክኒክ ኮሚቴ በፌዴራል የተዘጋጀ የ3 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል።

ኮሚቴዉ በፌዴራል የተዘጋጀዉን የአፈፃፀም ማዕቀፍ ከክልሉ ተጨባጭና ልዩ ሁኔታዎች ጋር ያጣጣመ የአፈፃፀም ስልትና የድርጊት መርሃ-ግብር ቀርፆ እንቅስቃሴዉን መርቷል።

2.1.1 የምክክር ወረዳ መረጣ

ሀገሪቱን እንደሚወክሉ ታምኖባቸዉ የምክክር ስብሰባዉ እንዲካሄድባቸዉ ከተመረጡት 116 ወረዳዎች መሀል 2 በሐረሪ ክልል መሆኑ ይታወቃል። በዚሁ መሰረት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታና የምክክር ስብሰባዉ ዓላማና ተፈላጊ ዉጤት እንደሚያስገኝ የታመነበት ክልሉን በገጠር እና በሐረር ከተማ የከፈለ 2 የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት የምክክር ስብሰባዉ እንዲካሄድ ተደርጓል።

CCRDA

2.1.2 የምክክር ስብሰባ መሪዎችና ራፖርተሮች መረጣና ስልጠና

ብቁ የስብሰባ መሪዎችና ራፖርተሮች መምረጥ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ የፌዴራል ማዕቀፍ መመዘኛን ያሚሉ በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸዉ ገለልተኛና የመንግስት ተሿሚ ያልሆኑ በትምህርት ደረጃቸዉ ዲፕሎምና ከዚያም በላይ ያጠናቀቁ 4 የስብሰባ መሪዎች /2 ለወረዳ እና 2 ለክልል/ እና 6 ራፖርተሮች /4 ለወረዳና 2 ለክልል/ ሲመረጡ ብቃታቸዉን ለማሳደግም እንዲረዳ በፌዴራል የተዘጋጀ የ3 ቀናት ስልጠና ተከታትለዋል::

2.1.3 ግንዛቤ ማስጨበጥ

የክልሉ ህብረተሰብ ስለስትራቴጂዉ በቂ ግንዛቤና መረጃ ኖሮት ለዝግጅቱ የሚጠበቅበትን አስተዋፃኦ ማበርከት እንዲችል የወረዳ ምክክሩ ከመካሄዱ በፊት ለ95 የህብረተሰብ ተወካዮች እንዲሁም ለ57 የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት የግንዛቤ ማስጨበጫ አዉደ-ጥናት ተካሂዷል:: በተጨማሪም በፌዴራል የተዘጋጀ 3 የዉይይት ሰነዶችና በራሪ ወረቀቶች፤ በኢንተር አፍሪካ ግሩፕ የተዘጋጀ መፅሄቶች እንዲሁም ለክልል ምክክር የተዘጋጀ ሪፖርቶች ተሰራጭተዋል::

በዚህም የህብረተሰብ ተወካዮች ከአካባቢያቸዉ ህብረተሰብ ጋር በመወያየት ፍላጎቱና ለዝግጅት ጠቃሚ መረጃ በማበርከት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል::

2.1.4 የምክክር ስብሰባ ተሳታፊዎች መረጣ

የክልሉ ምክክር ስብሰባ ተፈላጊዉ ዉጤት ማስገኘት እንዲችል ኅብረተሰቡን በአግባቡ የሚወክሉ ተሳታፊዎች መምረጥ የሚያስችል በፌዴራል የተዘጋጀዉ ማዕቀፍ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ያጣጣመ መመዘኛ መሰረት ተሳታፊዎች እንዲመረጡ ተደርጎል:: ይህም በዝርዝር ሲታይ

የወረዳ ተሳታፊ መረጣ መመዘኛ የድህነት ሁኔታና የህዝብ ብዛት መሰረት ያደረገ ሆኖ ፆታ፣ ዕድሜ፣ የሥራ ሁኔታ፣ በቀላሉ ለአደጋ መጋለጥ የሃብት ሁኔታ እና የደህዉን ኅብረተሰብ ፍላጎትና ህሳብ ለመግለፀ በቂ ችሎታ መኖሩ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በየቀበሌዉ የህብረተሰብ ተወካዮች አማካይነት ተመርጠዋል:: መንግሥትና፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራትም ባላቸዉ የድህነት ተዛምዶ እንቅስቃሴና ግንኙነት መሠረት አድርጓል::

በዚህ መሠረት ለወረዳ ምክክር የተሳተፉት በድምሩ 66 የህብረተሰብ ተወካይ ሲሆኑ ከዚህም ዉስጥ /ገጠር 33 እና ከተማ 33/ ፆታዊ ስብጥራቸዉ 36 ወንድ 30 ሴቶች ናቸዉ:: እንዲሁም በአስረጂነት 15 የመንግሥት መ/ቤቶች እና በታዛቢነት 20 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበራት ተወካዮች በስብሰባዉ ላይ ተገኝተዋል::

CGRDA

በተጨማሪም 3 ክቡር የፌዴራል ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት እና 2 ከፌዴራል ሴክሬተሪያት የስብሰባ ሂደቱን ተከታትለዋል።

በክልል ምክክር ስብሰባ በጠቅላላዉ 194 ተሳታፊዎች ተገኝተዋል። የተሳታፊዎች ስብጥር 36 ከህብረተሰብ፣ 30 ከፍተኛ ዉሳኔ ሰጪ፣ 74 የመንግሥት መ/ቤቶች፣ 23 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት፣ 12 የአገር ሽማግሌዎች፣ 5 የግል ባለሃብቶች፣ 4 የሐይማኖት ተጠሪዎች፣ 4 ከብዙሃን መገናኛ 3 በቀላሉ ለአደጋ ከተጋለጡ ህብረተሰብ ክፍሎች እና 3 ታዋቂ ምሁራን ተካፍለዋል። በተጨማሪም 4 የአለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች /UNDP, IDA, EU, Inter Africa Group/ እንዲሁም ከፌዴራል ሴክሬተሪያት 2 በድምሩ 6 ተወካዮች የስብሰባዉን ሂደት ተከታትለዋል።

2.2 የምክክር ስብሰባ ሂደት

የምክክር ስብሰባ ምዕላተ ጉባኤ መምላቱ ሲረጋገጥ የአካባቢዉ ባህላዊ ሥነ-ሥርዓት በመከተል ስብሰባዎቹ ሲጀመሩ በቅድሚያ የመክፈቻ ንግግር በታዋቂ ግለሰቦች፣ ስለስትራቴጂ አጭር ማብራሪያ፣ እስካሁን የተከናወኑ ተግባራት እንዲሁም የወረዳ ምክክር ግኝት ሪፖርት ቀርቧል።

በመቀጠልም የፌዴራል አፈፃፀም ማዕቀፍ እና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ በምክክሩ የሚጠበቀዉን ዉጤት ለማስገኘት ቀደም ተከተልና ሥርዓት የጠበቀ ዝርዝር የዉይይት አጀንዳ በተሳታፊዎች ሙሉ ድምፅ በማፀደቅ ዝርዝር ዉይይት ተካሄዷል።

የወረዳም ሆነ የክልል ምክክር ስብሰባ ቋንቋ አማረኛ ቢሆንም አማረኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑ ተሳታፊዎች ሀሳባቸዉን ለመግለፅ ሆነ ስብሰባዉን ለመከታተል እንዲችሉ በሐረሪና በኦሮሞኛ ቋንቋዎች አግባብ ያለዉ የትርጉም አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጎል።

የዉይይቱ ሂደት በአጀንዳዉ መሰረት ተሣታፊዎች ዴሞክራሲያዊ መብታቸዉን በመጠቀም በነፃ ማንኛዉንም ሀሳብ እንዲስተናገድ እንዲንሸራሸር እንደአስፈላጊነቱም መረጃና ማብራሪያ በአስረጂ መ/ቤቶች በኩል በመሰጠቱ አብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ የጋራ መተማመንና መግባባት ላይ ተደርሷል።

አልፎ አልፎ በስብሰባ ሂደት የተፈጠሩ የሀሳብ ልዩነቶች ለማስወገድ ተሳታፊዎች በመረጧቸዉ በቀጥታ ድምፅን በመስጠት እንዲሁም ወደፊት ድህነት ለመቀነስ ሊወሰዱ የሚገባቸዉ እርምጃዎች ተብለዉ በተሳታፊዎች የተዘረዘሩትን ቀደም-ተከተል ለማስያዝ እንዲረዳ በግል የሚሞላ የቀደም-ተከተል ማስያዣ ሠንጠረዥ አማካይነት የእያንዳንዱ ተሳታፊ ሀሳብ በማሰባሰብ አልባት እንዲያገኝ ተደርጓል።

CCRDA

የወረዳ ምክክር ተሳታፊዎች የድህነት ገፅታ፣ መንስኤና መፍትሄዎች ከግል ህይወት ልምድና ገጠመኞች እስከ ክልልና ብሄራዊ ጉዳዮች የዳሰሰ የደህዉ አመለካከትና ፍላጎት ጎልቶ የተንፀባረቀበት ደማቅና የነቃ ተሳትፎ ያልተለየዉ ዝርዝር ሰፊና ጥልቅ ዉይይት ተካሄዷል::

የክልል ምክክር ጎብረተሰቡ በወረዳ የመከረባቸዉ ግኝቶች ላይ ተመሥርቶ የግኝቱ ተጨባጭነት የማረጋገጥ፣ የበለጠ የማዳበርና ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በማከል ክልላዊ ቅርጽ ማስያዝ ከተለያዩ ብሄራዊ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲ ጋር ማጣጣምና ማዳበር ላይ ያተኮረ ነበር::

በክልሉ የተካሄዱ የምክክር ስብሰባ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ በድምጽና በምስል ሲቀረጽ ሂደቱና ግኝቶቹ በተገቢዉ ሁኔታ በጽሁፍ ተጠናቅሮ ለሚመለከታቸዉ አካላት ተሰራጭቷል::

2.3 በአፈፃፀም ሂደት የገጠሙ ችግሮችና የተገኙ ተሞክሮዎች

በክልሉ የተካሄዱ የምክክር ስብሰባዎች ለማስፈፀም በተደረገው ጥረት የገጠሙ ችግሮች መሀል የበጀትና የጊዜ እጥረት በዋንኛነት ይጠቀሳሉ:: እነዚህም

- ለምክክሩ ያማረ ውጤት ቁልፍ የሆኑት የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበት ለተዘጋጁት ሥልጠናዎች/ የአሰልጣኞች፣ የስብሰባ መሪዎችና ራፖርተሮች/ እና ለስብሰባዉ ቅድመ-ዝግጅት እንዲሁም ድህነት ሰፊ ጥልቅና ውስብስብ ከመሆኑ አንፃር አሁን ከተገኘዉ ውጤት የበለጠና የተሻለ ለማስገኘት በተሳታፊዎች ሊነሱ የሚችሉ አሁን ከቀረቡት ሀሳቦች የበለጡትን ለማስተናገድ ለምክክሩ ስብሰባው የተሰጠው ጊዜ አጭር መሆኑ
- እንዲሁም ለማስፈጸሚያ የተመደበው በጀት አነስተኛ በመሆኑ በክልሉ አቅም ለማብቃቃት ጥረት ቢደረግም በወጪ ርዕስ ሲደለደል የክልሉ ተጨባጭ ሁኔታና የሥራ መጠን ጋር ባለመጣጣሙ በአፈፃፀም ሂደት ችግሮች አስከትሏል::

እነዚህን ችግሮች አቅም በፈቀደ መጠን በክልሉ አቅም ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል::

ምክክሩን በማስፈፀም ሂደት በርካታ ተመክሮዎች ተገኝተዋል:: ከእነዚህም ተሞክሮዎች በቀጣይነት ለሚዘጋጀዉ ተመሳሳይ ዝግጅቶች ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገቡ የሚታመንባቸው::

* ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የምክክር ስብሰባ ወረዳዎችና ተሳታፊዎች ብዛት 116 እና ሆኖ ቢወሰንም የተሻለ ዉጤት ለማስገኘት ጎብረተሰቡና የሚመለከታቸዉ ወገኖች በአግባቡ እንዲያሳትፍ ብዛቱ ቢሻሻል

CCRDA

* የስትራቴጂዉ ዝግጅት ሰፊና ቀጣይነት ያለዉ በመሆኑ ቀልጣፋና ያማረ ዉጤት ለማስገኘት የዝግጅቱን ሂደት የሚመራ፣ የሚያስተባብርና የሚያስፈፅም ከኮሚቴ ይልቅ ተቋማዊ አደረጃጀት ቢከተል
* በአይነቱ ልዩና ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደዉ ምክክር ጎብረተሰቡ ለልማትና የራሱን ችግር በራሱ ጥረት ለመፍታት ፍላጎትና ተነሳሽነት ያለዉ መሆኑን በተግባራዊ እንቅስቃሴዉ ያስመስከረበት እንዲሁም ተዳማጭነት ማግኘቱን ያረጋገጠበት በመሆኑ በቀጣይ በተመሳሳይ ዝግጅትም ሆነ ስትራቴጂዉን በማስፈፀም፣ በመከታተልና በመገምገም ሂደት ጅምር ተሳትፎን የበለጠ ለማጎልበት ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ መሆኑ በቂ ግንዛቤ ተገኝቷል።

በመጨረሻም የክልል ምክክር ስብሰባ ዋና ዋና ግኝቶች በ4 አብይ ርዕሶች ተከፍሎ እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

3. የሐረሪ ክልል ምክክር ስብሰባ ዋና ዋና ግኝቶች

3.1 የክልሉ የድህነት ገፅታ/ሁኔታ

ተሳታፊዎች የክልሉ ወቅታዊና ያለፉ አመታት የድህነት ሁኔታ ከ21 ያላነሱ አመልካቶችን በመጠቀም ሲገመግሙ ለድህነት የበለጠ የተጋለጡ የጎብረተሰብ ክፍሎችንም ለይተዋል።

የግምገማዉ ዉጤት መሰረት በክልሉ ድህነት እጅግ ተንሰራፍቶ የሚገኝ እና ደረጃዉ ይለያይ እንጂ አብዛኛዉ ጎብረተሰብ በድህነት ኑሮ ዉስጥ እንደሚገኝ የጋራ ድምዳሜ ላይ ተደርሶል።

በለፉት 5 አመታት እየተባባሱ ከሄዱት የድህነት ኑሮ አመልካቾች መሀል ዋና ዋናዎቹ

1. የምግብ ፍጆታ
   - ☆ በገጠር የተመጣጠነ ምግብ እጥትና የምግብ ተረጂ ጎብረተሰብ እጅግ መጨመሩ (ከገጠር ነዋሪ 61-7% ለረሃብ አደጋ በተጋለጠ አካባቢ ይኖራል።)
   - ☆ በከተማ የምግብ ሽቀጥ ዋጋ መናርና አብዛኛዉ ገቢ ለዚሁ ማዋሉ
   - ☆ በምግብ እጥት ሳቢያ የሞቱ፣ ጤናቸዉ የታወከና የተሰደደ ጎብረተሰብ መበራከቱ

2. የመጠጥ ዉኃ
   - ☆ በገጠር የንፁህ ዉኃ ሽፋን ከ3% ወደ 18% ቢሻሻልም በቂ አለመሆኑ
     - ○ ከዉኃ ፍለጋ ከ2-3 ሰዓት በአግር እንደሚጋዙ

CCRDA

☆ በከተማ የንፁህ ዉኃ ሽፋን መቀነሱ

- ያለዉ አቅርቦት 25% ብቻ ይሸፍናል
- አስተማማኝ አለመሆኑ

3. መጠለያ
   ☆ የኪራይ ዋጋ መናር
   ☆ የቀበሌ ቤቶች መፈራረስ በተለይ ባህላዊ ቤቶች
   ☆ በረንዳ አዳሪና የላስቲክ ቤቶች መበራከት

4. ጤና ሽፋኑ የተሻሻለ ቢሆንም
   ☆ በቀላሉ በተላላፊና በወረርሽኝ የሚጠቃ ጎብረተሰብ መበራከቱን
   ☆ የጤና አገልግሎት ጥራት ማነስ
   ☆ HIV/ኤድስ ስርጭትና ጥቃት መባባስ
   - 30% የሆስፒታል አልጋ በHIV/ኤድስ ተጠቂዎች መያዙን
   - ወላጅ አልባ ህፃናት መበራከት

5. ትምህርት ሽፋኑ ቢሻሻልም
   ☆ ትምህርት የማይከታተሉ ደሀ ህፃናት መበራከት
   ☆ የትምህርት ጥራት ማነስ
   ☆ ደጋሚና የሚያቋርጡ ተማሪዎች መበራከት
6. ኤነርጂ በተለይ የማገዶ እጥረት
7. ሥራ አጥ መበራከት
8. ገቢ ማነስ (ኑሮን ለመደገፍ አለመቻል)
9. ማህበራዊ ቀዉስ መበራከት (ወንጀል፣ ወልዶ መጣል፣ ሴትኛ አዳሪነት፣ ጎዳና ተዳዳሪነት ለማኝ ----- ወዘተ)
10. የመንገድና ትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋንና ብቃት ማነስ
    ☆ የመኪና መንገድ በቂ አገልግሎት አለመሰጠት
    ☆ የነዳጅና የትራንስፖርት ዋጋ መናር
    ☆ የትራፊክ አደጋ መበራከት
11. የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ አደጋ መባባስ
    ☆ ደንና ቁጥቋጦ መመናመን
    ☆ ለም አፈር የገፅና የምድረ ገፅ ዉኃ መመናመን
    ☆ የአየር ንብረት ለዉጥ

CCRDA

☆ ረሃብና ድርቅ መስፋፋት

☆ የጎርፍ አደጋ መባባስ

☆ HIV በሽታ መስፋፋት

☆ ተላላፊና ወረርሽኝ መስፋፋት

12. በሴቶችና በህፃናት የሚተዳደሩ ቤተሰቦች መበራከት፡
13. የኢኮኖሚ ጥገኛ መበራከት፡
14. የህዝብ ብዛት /ዕድገት መጨመር
15. ህገ-ወጥ ንግድ መስፋፋት
16. የፍትህ መራዘምና መጋዳል
17. ባህላዊና ታሪካዊ ቅርፃ ቅርፅ ላይ የሚደርስ ጉዳት መባባስ
18. የአካባቢ ብክለትና የዕዳት ጉድለት መባባስ
19. የህብረተሰብ ሞራልና ሥነ-ልቦና መላሸቅ
20. ገበሬዎች በዕዳ መዘፈቅ ናቸዉ::

መሻሻል ከታየባቸዉ ፀጥታ፣ ሰላም፣ ትምህርት እና ጤና አገልግሎት ሽፋን እና በገጠር የመጠጥ ዉሃ ሽፋን ናቸዉ::

3.2 የድህነት መንስኤና አባባሽ ምክንያቶች

➢ ገጠር- ቀዳሚው፡- የእርሻ ምርት የምግብ እህል፣ የነዋይ ሰብል/ጫት፣ ሎዝ፣ አትክልትና ፍራፍሬ

ቀጣዩ እንስሳትና የእንስሳት ምርት ተዋፅኦ

የመጨረሻው እንጨት ፣ ከሰል፣ ድንጋይ፣ አሸዋ ሸክላ የቀን ጉልበት እና የኮንትሮባንድ ዕቃ ማስተላለፍ

➢ በከተማ- የመንግሥት ሠራተኛ፣ ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርት፣ የቤት ውስጥና ሌሎች አገልግሎቶች እና ግብርና እንደቅደም ተከተላቸው የጎብረተሰቡ የገቢ ምንጮች ናቸው::

ጎብረተሰቡ ከእነዚህ ምንጮች የሚያገኘው ገቢ በተሳታፊዎች ዕይታ

- ገቢው አነስተኛ በመሆኑ ኑሮውን ለመደገፍ በቂ አለመሆናቸው
- ከጠቅላላው ገቢ የሴቶች ድርሻ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ
- ከመንግሥትና የፋብሪካ ሠራተኞች በቀር ሌሎቹ አስተማማኝ ሥራና ገቢ አለመሆኑ
- በተመሳሳይ የሥራ መስክ ከግል ይልቅ የመንግሥት ክፍያ የተሻለ መሆኑ

CCRDA

- ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙት በከተማ ጥቂት በህገ-ወጥ ንግድ የተሰማሩና ባለሀብቶች በገጠርም በንግድ የተሰማሩ እና መስኖ ጫት የሚያለሙ ገበሬዎች እንደሆኑ ተጠቅሷል::

በክልሉ የድህነት መንስኤ፣ አባባሽ ምክንያቶችና ውጤት እርስ በርስ የተቆራኙና ተለዋዋጭ ሆኖ ደረጃቸው በጊዜ፣ በአካባቢና በጎብረተሰብ የሚለያዩ መሆናቸውን በመገንዘብ በክልሉ ገጠርና ከተማ የድህነት መንስኤዎችና አባባሽ ምክንያቶች ዉስጥ ዋና ዋናዎቹ

1. ድህነት በክልሉ የረዥም ጊዜ ድምር /ክምችት ውጤት መሆኑ
2. የገቢ ማነስ፣ ምርትና ምርታማነት ማሽቆልቆልና ኢንቨስትመንትና ቁጠባ ውሱንነት
3. በቂ የሥራ ዕድል አለመኖር በተለያዩ መፈናቀል እና በራስ ጥረት የሥራ ዕድል ለመፍጠር የተደረገ ጥረት አናሳነት
4. የህዝብ ብዛት /ዕድገት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር በተለይም የህዝብ ፍልሰት
5. የኑሮ ዉድነት መባባስ የገንዘብ መግዛት አቅም ማነስና የምርት አገልግሎት ዋጋ መኖር
6. የመኖሪያ አካባቢ ብክለትና የፅዳት ጉድለት መባባስ
7. የተፈጥሮና ሰዉ-ሰራሽ አደጋዎች መባባስ በተለይም ድርቅ፣ HIV/ኤድስ ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታ....
8. የመንግሥት የልማት ትኩረትና እንቅስቃሴ አጥጋቢ አለመሆን በተለይም
   - የኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎቶች ሽፋን፣ ጥራትና ውጤት አናሳነት
     - ትምህርት
     - ጤና
     - መንገድ
     - ፍትህ
     - ሌሎች
   - የጎብረተሰብ ተሳትፎ አናሳነት
   - ለልማትና ለጎብረተሰብ ተሳትፎ አመቺ የአስተዳራዊ አደረጃጀትና የተቀናጀ ልማት አመራር፣ አፈፃፀምና ክትትል ሥርዓት አለመዘርጋት
   - የልማት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ሀብት በሙሉ አቅም በሚገባ ለመጠቀም አለመቻል
     - የሰው ኃይልና የውስጥ አደረጃጀት አለመሟላት
     - የልማት ወጪ ፍላጎትና ገቢ አለመመጣጠን
     - ለከተማ የተሰጠ ትኩረት አናሳነት

CCRDA

9. የኅብረተሰቡ ልማዳዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ግላዊ ባህሪና አመለካከት የተፈለገውን ያህል አለመሻሻል
    - ለሥራና ለልማት ያለ አመለካከት አለመለወጥ
    - ከአቅም ጋር የተመጣጠነ ወጪና የቁጠባ ባህል አለመዳበር
    - ለአጉል ሱስ ተገዥነት፣ ጎጂ ልማዳዊና ባህላዊ ድርጊቶች አለመወገድ
    - ኅብረተሰብን ለልማት ለማነሳሳትና ለማንቀሳቀስ የሚያስችል አደረጃጀት አለመኖር
10. አነስተኛ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት አለመስፋፋት እና ኅብረተሰቡ በኅ/ሥ/ማ አለመደራጀት
11. የኤነርጂና የማገዶ አቅርቦትና አጠቃቀም ቴክኖሎጂ አለመሻሻል
12. በገጠር የግብርና ምርትና ምርታማነት ማሽቆልቆል
    - የአየር ንብረት መዛባትና ድርቅ መስፋፋት
    - የመሬት ይዞታ አስተዳደርና አጠቃቀም ችግሮች መባባስ የእርሻ መሬት እና የነፍሰ-ወከፍ የገበሬ ይዞታ ማነስ
    - መስኖ አለመስፋፋትና ውሃን በቁጠባና በሚገባ የመጠቀም ባህል አለመዳበር
    - የተሻሻሉ የግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅርቦት ስርጭትና አጠቃቀም የተፈለገውን ያህል አለመሻሻል
    - የግብርና ኤክስቴንሽንና ሌሎች የልማት አገልግሎቶች ሽፋንና ጥራት አናሳነት
    - የግብርና ምርት አሰባሰብ ፣ አከመቻቸትና አያያዝ አለመሻሻል
    - የግብርና ሥራ ወቅቱን ጠብቆ አለመከናወን
        - የሥራ ባህል አለመለወጥ
        - የእርሻ መሣሪያና የማረሻ በሬ እጦት
        - የመረጃ እጦት
13. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ደን፣ ቁጥቋጦ፣ ለም አፈር፣ የገፀና የከርሰ-ምድር ውሃ መመናመን
14. የኢንፎርማል ሴክተር አለመስፋፋትና ኢንቨስትመንት ውሱንነት
15. የሐረር ከተማ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር በጊዜያዊም ሆነ በዘላቂነት አለመፈታት
16. በከተማ የአገልግሎት ብቃትና ጥራት እንዲሁም ምርትና ምርታማነት መቀነስ
    - መሬት የማግኘት ችግር/ ቢሮአክራሲያዊ አሠራር አለመሻሻል/
    - የህገ-ወጥ ንግድ መስፋፋት
    - ኢንፎርማል ሴክተርና ኢንቨስትመንት የሚያስፋፉና የሚያጠናክሩ ምቹ ፖሊሲዎች አለመኖር

CCRDA

ይገኛል። በገጠርም በተለያዩ ቀበሌዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ያደረጉ የውሃ አቅርቦት ግንባታ ተከናውኗል።

- <u>በግብርና ልማት ዘርፍም፡-</u> የግብርና ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ ያተኮረ ሆኖ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሽፋን ማሳደግ፣ ገበሬዎችን በተለያዩ ሙያ ማሰልጠን፣ የተሻሻለ የምርት ግብአት አቅርቦትና ስርጭት፣ የሰብል ጥበቃና የእንስሳት ጤና አጠባበቅ እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። ለዚሁም የግብርና ልማት ተቋማት ግንባታ፣ የመሣሪያና የሰለጠነ-ባለሙያ ማሟላት ተግባራት ተፈጽመዋል።
- <u>በማህበራዊ ዘርፍም፡-</u> በተፈጥሮና በሰዉ-ሰራሽ አደጋ ምክንያት ለተጎዱ ቤተሰቦች የምግብ እርዳታ፣ ለሴቶች ለወጣቶችና ለወላጅ አልባ ህፃናት የሙያ ስልጠና፣ የማቴሪያልና የብድር አገልግሎት ድጋፍ ተሰጥቷል። እንዲሁም ለቅርጽ ሀብቶች ጥገና ሲደረግ በቤተሰብ ምጣኔ ረገድ ለሴቶችና ለእናቶች የተለያዩ አገልግሎቶች ተሰጥተዋል።

የምክክር ተሳታፊዎች የተከናወኑ ተግባራትን በዝርዝር ገምግመዋል። የግምገማዉ ዉጤት ሲጠቃለልም

- የተከናወኑት ተግባራት ከችግሩ ስፋት አንፃር ሲታዩ በቂ አለመሆናቸዉን፣
- በመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተተገበሩ እንጂ ጎብረተሰቡን አለማሣተፋቸዉን፣
- የአገልግሎት ሽፋናቸዉ ከጤናና ከ1ኛ ደረጃ ትምህርት በቀር ሌሎቹ ሽፈንና የጥራት ደረጃቸዉ ዝቅተኛ መሆኑን፣
- የደህዉን ጎብረተሰብ ዋና ችግሮች በማቃለል በኩል ያበረከቱት አስተዋያኦ አነስተኛ መሆኑን በተሳታፊዎች ተገልጾል። ከገጠሙ ዋንኛ ችግሮች መሃል
  - ✓ ለክልሉ የተመደበዉ በጀት በአብዛኛዉ ለሐረር ከተማ መጠጥ ዉኃ በማዋሉ ለሌሎች ሊዉል ይችል የነበረዉ በጀት መሻማቱ፣
  - ✓ ለከተማ የተሰጠዉ ትኩረት አናሳ መሆኑ፣
  - ✓ የክልሉን ችግሮችና ሀብት ላይ የተመሠረተ ስትራተጂ ዕቅድ ተዘጋጅቶና ለማስፈፀም የሁሉንም አካላት ያቀናጀ ጥረት አለመደረጉ፣
  - ✓ በተለይም ድህነትን ለመቅረፍ የተሰጠ ትኩረት አናሳ መሆኑ እና
  - ✓ በአደረጃጀትና በአቅም አናሳነት ሳቢያ በአፈፃፀማቸዉ ችግር የገጠሙአቸዉ እንደነበሩ ተገልጿል።

3.4 ወደፊት በክልሉ ድህነትን ለመቀነስ በቀጣይነት መወሰድ የሚገባቸዉ እርምጃዎች

CCRDA

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሊወሰዱ የሚገባቸዉ እርምጃዎች

ተ.ቁ	መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች	በጊዜ ላይ ተወያዩ ህዝብ የሰጠዉ ድምፅ በመቶኛ		ቅደም-ተከተል
		አጭር ጊዜ	ረዥም ጊዜ	
1.	በክልሉ እጅግ የተከማቸዉን የሥራ አጥ ለመቀነስም ሆነ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንፎርማል ሴክተርን ለማስፋፋትና ለማሳደግ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን መዉሰድ፤	79%	21%	3
2.	በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት የሚያስችሉ እርምጃዎችን መዉሰድ፤	55%	45%	6
3.	የክልሉ ቁልፍ ችግር የሆነዉን የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ የተጀመረዉን ሥራ በማጠናከር ተግባራዊ ማድረግ፤	93%	7%	1
4.	የህገ-ወጥ ንግድ ህጋዊ ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ማድረግና የኮትሮባንድ ንግድን ደረጃ በደረጃ ማስወገድ፤	72%	28%	4
5.	የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ በአግሮ ኢኮሎጂ ላይ እንዲያተኩር፤ የተሻሻሉ ግብዓቶች አቅርቦትና ስርጭት ወቅቱን የጠበቀ እንዲሆን፤ ለመስኖ ልማት ትኩረት መስጠት፤ የግብርና ምርምርና ጥናትን ማጠናከር፤ እንዲሁም ለከተማ ግብርና ተስማሚ የሆነ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፤	67%	33%	5
6.	አነስተኛ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ማስፋፋት፤ ለሴቶች ልዩ የብድር አገልግሎት ማቅረብ፤	84%	16%	2

በመሠረተ ልማትና በሌሎች ተመሳሳይ መስክ መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች

ተ.ቁ	መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች	በጊዜ ላይ ተወያዩ ህዝብ የሰጠዉ ድምፅ በመቶኛ		ቅደም-ተከተል
		አጭር ጊዜ	ረዥም ጊዜ	
1.	የመኖሪያ ቤት ግንባታ ከከተማዉ ማስተር ፕላን ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲሄድ፤ ህገ-ወጥ የጨረታ ቤቶች ግንባታ ለመግታት የሚያስችል ተገቢ እርምጃ መዉሰድ፤	64%	36%	2
2.	የመገበያያ እና የመዝናኛ ስፍራዎች ተከልለዉ ሕብረተሰቡ ኑሮዉን በዘመናዊ መንገድ ለመምራት እንዲችልና ከልዩ ልዩ አደጋዎች ራስን ለመከላከል የሚያስችለዉ የከተማ ቦታ አጠቃቀም ፕላን ማዘጋጀትና በሥራ ላይ ማዋል፤	37%	63%	6
3.	የገጠሩን ህብረተሰብ የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ የመንገድ ሥራና ጥገናን በስፋት ማከናወን፤	62%	38%	3
4.	አማራጭ የኃይል ምንጭ ለማጎልበት የሚረዳ የልማት ዕቅድ መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፤	52%	48%	4
5.	ለገጠር መምህራን እና ለልማት ጣቢያ ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት መስራት፤	68%	32%	1
6.	ያለአግባብ የተወረሱ ቤቶች ለባለቤቶቹ በመመለስ በግል ዘርፍ የቤት አቅርቦትን ችግር ለማሻሻል የሚያስችል ፕሮግራም መቅረፅና ማስፈፀም፤	40%	60%	5

CCRDA

በክልሉ ባህላዊና ልማዳዊ ተፅዕኖዎችን ለማቃለል መወሰድ የሚገባቸዉ እርምጃዎች

ተ.ቁ	መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች	በጊዜ ላይ ተወያዩ ህዝብ የሰጠዉ ድምፅ በመቶኛ		ቅደም-ተከተል
		አጭር ጊዜ	ረዥም ጊዜ	
1.	ህብረተሰቡ የሚጠቀምባቸዉ ጎጂ ባህላዊ ግርዛት፣ እንጥል መቁረጥ፣ ጉሮሮ ማስቧጠጥ... ወዘተ ችግሮችን ለመቅረፍ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የባህሪይ ለዉጥ ማምጣት፣	72%	28%	2
2.	ሰቆቶችና በህፃናት ላይ የስነ-ልቦናና የአካል ጉዳት የሚያደርሱ ድብደባ፣ አስገድዶ መድፈር... ወዘተ ችግሮችን ለመቅረፍ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ የስነ-ወሲብና የፆታ ትምህርት በት/ቤቶች እንዲሰጥ እንዲሁም አጥፊዎች በህግ እንዲቀጡ ማድረግ፣	83%	17%	1
3.	በጤናም ሆነ በኢኮኖሚ ላይ ጉዳት እያደረሱ ያሉ አጓጉል ሱሶች ጫት፣ ሺሻ፣ ሐሺሽ፣ አልኮል መጠጥ ወዘተ ለመቀነስ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን መዉሰድ፣	61%	39%	6
4.	ህብረተሰቡ ለማህበራዊ ጉዳዮች ማስፈፀሚያ እየተገለገለባቸዉ የሚገኙት ተቋማት ዕድር፣ ሰንበቴ፣ ዕቁብ፣ አፎቻ... ወዘተ በልማት ላይ እንዲሳተፉ ጥረት ማድረግ፣	64%	36%	5
5.	ወጣቱ ትዉልድ የህዝብ፣ የሥራ ፍቅርና አክብሮት ያለዉ እንዲሆን የባህሪ ለዉጥ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣	65%	35%	4
6.	ህብረተሰቡ ስለ ልማትና ሥራ ያለዉን አመለካከትና ባህሪ ለመለወጥ ተገቢ እርምጃ መዉሰድ፣	70%	30%	3
7.	ለጋብቻ ምስረታ ቀላልና ብኩንነት የማይታይበት የጋብቻ ሥርዓት እንዲዳብር ማድረግ፣	64%	36%	5

CCRDA

በክልሉ የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ችግሮችን ለማቃለል መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች

ተ.ቁ	መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች	በጊዜ ላይ ተወያዩ ህዝብ የሰጠዉ ድምፅ በመቶኛ		ቅደም-ተከተል
		አጭር ጊዜ	ረዥም ጊዜ	
1.	HIV ኤድስን ለመከላከል የተጀመረዉን ጥረት የበለጠ ማጠናከር፣ በሥነ-ተዋልዶ ረገድም የምክር አገልግሎቱን ማስፋፋት፣	91%	9%	1
2.	የቅድመ-ጋብቻ የኤድስ ምርመራ እንዲደረግ ግፊት ማድረግ፣	82%	18%	2
3.	የቱሪስት መስህብና የዓለም ቅርጽ ሃብት የሆነዉን የጀጎል ግንብ፣ በጀጎል ዉስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶች በተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ችግሮች ሳቢያ ከሚደርስባቸዉ አደጋ ለመከላከልና ለትዉልድ ቅርፅን ለማቆየት የሚያስችሉ ተገቢ የቅርፅ ሀብት ጥበቃ እርምጃዎች መዉሰድ፣	64%	36%	4
4.	የመሬት መሸርሸርና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መዉሰድ፣	81%	19%	3
5.	የህዝብ ፍልሰትን የሚቀንሱ ተገቢ እርምጃዎች መዉሰድ፣	56%	44%	5

CCRDA

ድህነትን ለመቀነስ በአቅም ግንባታ መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች

ተ.ቁ	የአቅም ግንባታ እርምጃዎች	ቅደም-ተከተል
1.	ህብረተሰቡን የሚያሳትፉ የቀበሌና የወረዳ መስተዳድር ማደራጀት እና ዲሞክራሲያዊ ባህል የሚዳብርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤	1
2.	በክልሉ ካለዉ ከፍተኛ የልማት ችግር በተለይም ከመጠጥ ዉሃ ችግር አንፃር እንዲሁም ክልሉ ካለዉ ስትራቴጂክ አቀማመጥ በህዝብ ፍልሰትና ሌሎች ምክንያቶች በክልሉ ኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ጫና በመኖሩ ብሔራዊ የበጀት ድልድሉ ይህን ያገናዘበ እንዲሆን ጥረት ማድረግ	5
3.	ለወጣቱ ትዉልድ ሥራ ለመፍጠር የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት፤ ለሴቶች ስልጠና ልዩ ትኩረት መስጠት፤	2
4.	የግብርናን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በቂ ባለሙያዎችን ማፍራት እና ገበሬዉን ማሰልጠን፤	9
5.	የግብርናን እንዲሁም የአነስተኛ የሥራ መስኮችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ የአምራቾች እና የአገልግሎት ሰጪ ህብረት ሥራ ማህበራትን ለማስፋፋትና ለማሳደግ የሚያስችል መንግሥታዊ ተቋም ማቋቋም እና ተገቢዉን አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል፤	11
6.	የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማደራጀትና አገልግሎቱንም ማስፋፋት፤	4
7.	ገበሬዎችን በተለያዩ የግብርና ሙያዎች ማሰልጠንና የሰርቶ ማሳያ ጣቢያዎችን ማደረጃት	10
8.	ልዩ ልዩ የግብርና ቴክኖሎጂ በተለይም የድህረ ምርት አያያዝና የአነስተኛ መስኖ ስራዎች ለማስፋፊያ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠርና ተገቢዉን አገልግሎት መስጠት	11
9.	በክልሉ ዉስጥ ያሉትን የምርትና የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት የዉስጥ ድርጅት ማሟላት፤ የማኔጅመንትን የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋትና ማጠናከር	6
10.	የአገር ዉስጥ ገቢ አመዳደብና አሰባሰብን በተመለከተ በመንግሥት ሠራተኛዉ፤ በገበሬዉ እና በነጋዴዉ ህብረተሰብ መህከል ሚዛናዊ እና አግባብ ያለዉ አሠራር መዘርጋት፤	8
11.	ሙስናን ለመቀነስና ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መዉሰድ፤	3
12	የክልሉን ኅብረተሰብ ለልማት እንዲነሳሳ፤ እንዲንቀሳቀስ ለማስቻል ግንዛቤዉን ለማሳደግ በቂ መረጃና ተከታታይነት ያለዉ ትምህርት ማሰራጨት፤ ክልላዊ የመገናኛ ብዙሃን ማደረጃትና አገልግሎት መሰጠት፤	7
13	በክልሉ እየተንሰራፋ የመጣዉን ማህበራዊ ቀዉስ አቅም በፈቀደ መጠን ለመቅረፍ በተለይም ወላጅ አልባና አሳዳጊ ያጡ ህፃናት፤ ጣሪ ያጡ አዛዉንት፤ አቅመ ደካሞች እና የአዕምሮና የአካል ጉዳተኞችን ለመደገፍ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠርና አገልግሎት መስጠት፤	12
14	የብሄራዊና ክልላዊ የአካባቢ ፖሊሲን ለማስፈፀም በተለይም ብዛሃን ህይወት በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ ጥንታዊ ባህላዊና ልማዳዊ አካባቢ በቀል ዕዉቀቶች፤ ተግባራትና ፈጠራዎችን የሚያሰባስብ በሥራ ላይ የሚዉልበትን ሁኔታ የሚፈትሽና የሚጠብቅ አደረጃጀት መፍጠር፤	13
15	መንግስት ለኅብረተሰቡ የሚሰጠዉ አገልግሎት ሽፋን ጥራትና ብቃት ደረጃን ለማሳደግ የሚያስችል የመንግስት ሰራተኛ የሥራ ተነሳሽነትና ትጋት ችሎታ ዉጤት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ፤ የምዘና፤ የምደባና ክትትል ሥርዓት ማደራጀትና መተግበር እንዲሁም በየጊዜዉ ብቃቱን እንዲያሻሽል የአጭርና የረዥም ጊዜ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ስልጠናና ጉብኝት ተጠቃሚ እንዲሆን ማመቻቸትና መተግበር።	11

CCRDA

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

Poverty Reduction Strategy Paper

Draft Report of the District Consultations

In the

SOMALI NATIONAL REGIONAL STATE

CCRDA

CONTENTS

1. Introduction 3
1.1 Social and Economic Status of SNRS 3
1.2 The Process of District Level Consultation 5
1.3 Composition of the Consultation participants 5
1.4 General Process of The Meetings and the Problems encountered 5
1.5 The agendas for the consultation 6

2. Poverty definition, expression and perception (at community level) 7
2.1 Definition of poverty 7
2.2 Expressions of poverty 7
2.3 Consequences of poverty 8
2.4 Coping mechanisms to poverty situation 8

3.0 The poverty situation over the last five years. 9
3.1 Changes in basic needs for the family over the past five years 9
3.2 Timely provision of basic needs and changes over the last five years 9
3.3 Vulnerability to drought within society 9

4. Causes of poverty within the region 10
4.1 Causes of poverty 10
4.2 Livelihoods of the society 10
4.3 Problems associated with production in the region 11
4.4 Effect of traditional practices of livelihoods 11
4.5 Natural and man made disasters in the district 11

5. The efforts made to minimize poverty levels over the last five years 13
5.1 The efforts of society, and public organizations 13
5.2 Government departments 13
5.3 Non governmental organizations 15

6. Actions to be taken to reduce poverty situation in the district 16
6.1 Ensuring food security 16
6.2 Income generating schemes 16
6.3 Improvement of basic services and disaster prevention 17
6.4 Future directions for emphasis by development agencies 17

CCRDA

1. Introduction

1.1 Social and Economic Status of SNRS

Position, size and population

The Somali National Regional State is in Eastern and south east Ethiopia. It border the Republic of Djibouti in the north, the Republic of Somalia in the East and the Republic of Kenya is the extreme south. Within Ethiopia it borders the Afar regional state in the north, and it shares a long border with the Oromia region in the west. The Somali National Region State is estimated to be 340,000 square kilometres in size (BoPED, 1999). It is divided into nine Zones, and these are further divided into 52 districts.

Based on the Ethiopian National Census, The Somali National Regional State has a population estimated in the year 2000 at 4 million people. The majority of this population (85%) is found in the rural areas, with the other rest in the urban areas.

Economic status

The economy of the Somali National Regional State is based mainly on its renewable natural resources, particularly its livestock, crop and forest resources.

Livestock populations in SNRS

Species	Number
Cattle	3,746,000
Camels	2,032,000
Goats	8,547,000
Sheep	9,053,000
Donkeys	213,000

CORDA

Both livestock and agricultural resources are utilized in traditional method through the years, droughts, wars, and the large-scale population movements coupled by influx of refugees. Man-made or natural disasters contributed significantly to environmental degradation and depletion of natural resources, leading to poor crop and livestock production.

The main source of income for rural population is livestock raising, which constitute 40% of the total income, while crop production constituted 26%. Trade 14%, and gift or obtained free 7%. For urban population, trade is the main source of income (36%), followed by gift or obtained free (17%).

Literacy

Illiteracy rates are very high all over the Somali region. Of the total population in the age of 7 years and above 71% are illiterate, and only 10% can read and write. More over, the illiteracy rates are very high in rural areas (90% females illiterate, and 74% males illiterate), while urban illiteracy is 42% (54% for females and 30% males) (Investment, 2000).

Health

Health service in the region is very limited, while health manpower is in short supply. Movement of pastoralists from place to place constantly imposes difficultly for the health facilities to reach and serve them. In 1999 there were 4 Hospitals, 10 health centres and 48 doctors, 3 pharmacists, 119 nurses, 200 health assistants, and 40 laboratory technicians.

Water availability

The availability of water is very scarce in the region in some areas animal move up to 50km to get water. During dry seasons rural people get water either by digging holes in to the sands or dried river beds, or fetch it from far away places. But, in general the inhabitants of the region do not have an access to clean and adequate potable water, bore holes, river intakes serve to a limited number of people. Although a lot of efforts has been done to improve the availability of clean water to both human being and livestock, still the gap is very wide.

Transport and communications

With regard to transportation and communications, there are 1,629 km of all weather roads and 2,844 km of dry weather roads. How ever, most of the roads are in bad condition, journeys take a long time hindering marketing of goods and increasing costs.

Automatic /digital telephone services are available in Jijiga and Gode. Several towns have semi-automatic telephone services. In addition to this twenty-three towns have radio communications, and 12 towns have postal services.

Housing and shelter

Mobile housing units in 1997 made up 42% of all housing, whereas only 18% the housing units were improvised. More over, 82% of the housing units in urban centres had no toilet facilities; and 97% of the toilet facilities are dry pits, mostly shared (Central Statistical Authority, 1998).

Energy

Unfortunately, traditional forms of energy contribute to about 99% of the total energy supply in the region. Firewood alone accounts for 82%, followed by charcoal (12%). This extensive use of bio-fuels contributes to deforestation and subsequent loss of top soil through increased erosion. Eleven towns in the region have electricity, and eleven more towns are recommended for electrification in the near future.

Banking and Insurance service

Banking and insurance services are in their infant stage in the region. Commercial bank of Ethiopia has branches in Jijiga, Gode, D/bur, Kebridahar and Moyale,two private bank namely Wegagen and Awash bank operate in Jijiga town. However the majority of the towns in the region have no access to bank services, moreover, the development bank of Ethiopia, has no branch in the region. This poor bank service resulted the use of value-less Somali shillings in the transaction in most of region, and this creates inflation and instability of the economy as whole, currently there are four insurance companies which have either branch or contact offices in Jijiga and few clients, like contractors, and government agencies are using them.

CCRDA

Conclusion

Therefore, based on the socio-economic situation of the community living in the region gives a greet weight to under take community consultation in order to get valuable information for the development of strategies and plans to reduce poverty and improve the living standard of the people. As a result of this as implemented in the other parts of the country, district level consultation started in this region on 5th megabit 1994 and expected to complete on 15th megabit 1994.

1.2 The Process of District Level Consultation

To overcome disaster and natural calamities, it is imperative that the community has adequate access to all basic services, in which the community should be fully participating. It is important that public security is maintained, especially in the remote rural areas. Financial institutions like banks and insurance agencies should be established within all the districts. The community should be enlightened to assume ownership of, and rights over, public services dedicated to the society, so that they should therefore guard vigilantly their proper utilization and maintenance.

6.4 Future directions for emphasis by development agencies

To enhance sustainable development, emphasis should be given to:

- Development efforts should be integrated, co-ordinated and appropriate to the area and population concerned.
- Quality of education at all levels within the society needs to be enhanced: community education and awareness of development, capacity building of government employees, provision of adequate training institution from primary to tertiary levels.
- Participation by local communities in all development efforts leads to greater success rates, ownership by eventual beneficiaries and proper maintenance of facilities
- All development effort depends on just leadership and good governance: a necessary condition for sustainable development is an accountable and transparent public service.

CCRDA

የኢትዮጵያ ምክክር
በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት

አጭር ሪፖርት

CCRDA

ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር
አዲስ አበባ
የካቲት 1994

I. ማጠቃለያ፣

መንግሥት ዋናውን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት መጀመሩን ነሐሴ ወር 1993 በጊዮን ሆቴል በተካሄደው ሕዝባዊ አውደ ጥናት ላይ ይፋ አድርጓል። የሰነዱንም ዝግጅት በዕቅድ ለመምራት መርሃ ግብር የተቀረፀ ሲሆን፤ በመርሃ ግብሩ ላይ የተመለከቱት ዝርዝር ተግባራት በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት መከናወናቸውን የሚከታተሉና የሚያስተባብሩ ኮሚቴዎች በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ ተቋቁመዋል። በተሟላ መልክ ሰነዱን ለማዘጋጀት የሚከናወኑት ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

1. በኢትዮጵያ የድህነት ሁኔታ ላይ ዝርዝር ጥናት ማካሄድ፣
2. በኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ላይ ከህዝቡና ሌሎች ከሚመለከታቸው የልማት አጋሮች ጋር ምክክር ማካሄድ፣
3. በሴክተር ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ላይ እስከአሁን የተደረጉ ጥናቶችን መረጃዎች ማሰባሰብና መገምገም፣
4. የኢኮኖሚ እድገትና ድህነት ቁርኝት ጥናት ማካሄድ
5. የHIV/AIDS መከላከያና መቆጣጠሪያ ስትራቴጂ ማዘጋጀት
6. በስትራቴጂው ላይ ለተመሠረቱ ፕሮግራሞች የማክሮ ኢኮኖሚና ወጪ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣
7. የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውጤት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት፣

በድህነት ሁኔታ ላይ የሚካሄደው ዝርዝር ጥናት በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በኢኮኖሚ እድገትና ድህነት ቁርኝት ላይ የሚደረገው ጥናት በመካሄድ ላይ ነው። በሴክተር ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ላይ በቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት መረጃዎች እየተሰባሰቡ ይገኛሉ። የHIV/AIDS ስትራቴጂ ቀረጻ በብሔራዊ የኤድስ ካውንስል ሴክሬታሪያት እየተሰራ ሲሆን፤ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋትና የማክሮ ኢኮኖሚና ወጪ ማዕቀፍ ዝግጅትም በቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት እየተከናወነ ነው።

በመርሃ ግብሩ መሠረት ምክክር ለማካሄድ የታቀደው በወረዳ፣ በክልልና በፌዴራል ደረጃ ነው። በዚህም መሠረት በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች አዲስ

CCRDA

አበባ መስተዳድርና ድሬዳዋ ካውንስልን ጨምሮ በወረዳ ደረጃ ምክክር ተካሂዷል። በክልል ደረጃም በሁሉም ክልሎች ምክክር ተካሂዷል።

II. <u>የወረዳ ምክክር</u>

የመጀመሪያውን ምክክር ከሰነዱ ዋናው ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይ ደህው ሕብረተሰብ ጋር ማድረጉ አስፈላጊ ነበር። በዚህም መሠረት ካለው ውስን ጊዜ፣ ገንዘብና አቅም አንጻር በሀገሪቱ በሚመረጡ 116 ናሙና ወረዳዎችና በእያንዳንዱ ወረዳ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላሉ ተብለው ከሚመረጡ 50 ሰዎች ጋር ምክክር ለማድረግ ዕቅድ ተያዘ። በሁሉም ክልሎች በሚገኙ 117 ወረዳዎች ላይ ከ6000 ሕዝብ ጋር በኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ላይ ምክክር ተካሂዷል። ምክክሩም በተሳካ ሁኔታ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የተገኘውም ውጤት መንግሥት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ ድህነትን ለመቅረፍ ለሚያከናውናቸው የልማት ጥረቶች መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው። ምክክሩን አለም አቀፍ ድርጅቶች የታዘቡት ሲሆን፣ በምክክሩ ላይ የታየው የህብረተሰቡ ተሳትፎ ግልጽና ዲሞክራቲክ እንደነበር ምስክርነት ሰጥተዋል።

ይህንን ውጤት ለማስመዝገብ ጊዜ፣ ጉልበት፣ ሙያዊ ክህሎትና ከፍተኛ የማስተባበር ብቃት የጠየቁ በርካታ ሥራወች ተከናውነዋል። እነዚህም ሥራዎች የተከናወኑት በወረዳ ምክክር መሪዎች፣ በክልል ቴክኒክ ኮሚቴና ሴክሬታርያት አባላትና በፌዴራል የቴክኒክ ኮሚቴና የድህነት ጽ/ቤት አባላት ነው። በአጠቃላይ ከወረዳ እስከ ፌዴራል ድረስ ለዚህ ሥራ የተመደቡት ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ያሳዩት የሥራ ተነሳሽነትና ኃላፊነት የመወጣት ብቃት የሚደነቅ ነው። በተለይ በወረዳ ምክክር ላይ ህዝቡ ያሳየው ተሳትፎ ግልጽ፣ ተገቢና ሚዛናዊ ነበር።

የወረዳ ምክክርን የተሳካ ለማድረግ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው ቅድመ የወረዳ ምክክር ስራዎች በዕቅድ የተከናወኑ ሲሆን፣ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

CCRDA

2.1 ድርጅታዊ መዋቅር መዘርጋት

በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅትን በአግባቡ ለማስተባበር የሚያስችል መዋቅር መዘርጋት መከናወን ያለበት ግንባር ቀደም ተግባር ነበር። በሀገር አቀፍ ደረጃ ሚኒስትሮች አባል የሆኑበት አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ከተለያዩ የሚኒስቴር መ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያቀፈ ብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴና የዕለት ተዕለት ስራውን የሚከታተል የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት ተቋቁሟል። በክልል ደረጃም በተዋረድ ተመሳሳይ መዋቅር ተዘረጋ። በዚህ ከፌዴራል እስከ ክልል በተዘረጋው መዋቅር አማካኝነት ነው የወረዳ ምክክርን ስኬታማ ያደረጉት ቅድመ የወረዳ ምክክር ሥራዎች የተከናወኑት። በተለይ በፌዴራልና በክልል መካከል ቅርብ የሥራ ግንኙነት ለመፍጠር በመቻሉ፣ በቴክኒክ ኮሚቴና የድህነት ጽ/ቤት ውስጥ የተመደቡት ባለሙያዎች ለሥራው ትኩረት ሰጥተው በሙሉ አቅማቸው በመንቀሳቀሳቸው ከወረዳ ምክክር የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት አንዱ ምክንያት ሆኗል።

2.2 ለክልል ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ሥልጠና መስጠት

ሁሉም የክልል ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ በደብረዘይት የስራ አመራር ኢንስቲትዮት በሶስት ዙርና በየዙሩ ሶስት ቀን የቆየ ስልጠና ተሰጥቷል። ሥልጠናውም ያተኮረው ሀገሪቱ በምታዘጋጀው የድህነት ቅነሳ ሰነድ ላይ ሲሆን፣ ሌሎች ከድህነት ጋር የሚያያዙ ጽሑፎም ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል። በዚህ ስልጠና ላይ የክልሎችን ቀጣይ ተግባር የሚገልጽ መርሃ ግብር ለመቅረጽ የተቻለ ሲሆን፣ በተጨማሪ በፌዴራል ጽ/ቤት በተዘጋጀው ረቂቅ የወረዳ ምክክር መመሪያ ላይ ጥልቀት ያለው ውይይት ተደርጓል። ሥልጠናው ግንዛቤ ከመፍጠር ባሻገር፣ የክልሎችን ተጨባጭ ሁኔታ ያንፀባረቀና የወረዳ ምክክር ለማካሄድ የሚያስችሉ ጉዳዮች ከተሳታፊዎች ለማግኘት እንዲቻል አድርጓል።

CCRDA

2.3 የወረዳ ምክክር መመሪያ ማዘጋጀት

በወረዳ ደረጃ የሚካሄደው ምክክር ግልጽ ዕይታና የጋራ ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ በሁሉም ክልሎች አንድ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲካሄድና ከምክክሩም የሚጠበቀው ውጤት በሚፈለገው ዓይነትና መጠን እንዲገኝ ለማስቻል በቅድሚያ የወረዳ ምክክር መመሪያ ተዘጋጅቷል። ይህም መመሪያ በወረዳ ምክክር ላይ ከመዋሉ በፊት፣ የፌዴራልና የክልል ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት እንዲተቹት ተደርጓል። ለወረዳ ምክክር መሪዎች በተደረገው ስልጠና ላይ መመሪያው መሠረታዊ ዶክመንት ነበር። የወረዳ ምክክር መሪዎችም መመሪያውን መሠረት በማድረግ፣ የወረዳቸውን የምክክር አጀንዳ፣ ፕሮግራምና የስብሰባ ሂደት አመራር ለማዘጋጀት ችለዋል። መመሪያው በአጠቃላይ በሀገሪቱ ውስጥ የተካሄደው የወረዳ ምክክር የተሳካ እንዲሆንና የተጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

2.4 የክልሎችን የምክክር ወረዳ ድርሻ መወሰን

ሀገሪቱ ካላት ጠቅላላ ወረዳ ውስጥ 25 በመቶ (116) የሚገመተውን በምክክሩ ለመሸፈን መታቀዱ የሚያመለክተው ውክልናው ከፍተኛ እንደሆነ፣ ምክክሩን በስፋት ለማካሄድ መታቀዱና በአጠቃላይ ምክክሩ ከፍተኛ ግምት እንደተሰጠው ነው።

116 ወረዳዎችን ለየክልሉ ለማከፋፈል የተወሰዱት መመዘኛዎች የሕዝብ ብዛት፣ ክልሎች ያሏቸው የወረዳዎች ብዛት፣ የግብርና ቀጠና (Agro-ecological zone) መለያየትና የከተማ ሁኔታ ናቸው። በዚህም መሠረት ኦሮሚያ 34፣ አማራ 23፣ ደቡብ 18፣ ትግራይ 8፣ ሶማሊ 9፣ አዲስ አበባ 7፣ አፋር 5፣ ቤኒሻንጉል 4፣ ጋምቤላ 4፣ ሐረሪ 2፣ ድሬዳዋ 2 የምክክር ወረዳዎች እንዲደርሳቸው ተደርጐ ተከፋፍሏል።

CCRDA

2.5 ወካይ የክልል ምክክር ወረዳዎች መምረጥ

በየክልሉ ምክክር የሚካሄድባቸውን ወረዳዎች ብዛት ከመወሰኑ ባሻገር ሌላው ቁልፍ ተግባር፣ ክልሉን በሚገባ የሚወክሉ ወረዳዎችን መምረጡ ነው። በዚህ ረገድ እያንዳንዱ ክልል ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚሄዱ መመዘኛዎች በማውጣት ክልሉን የሚወክሉ ወረዳዎች መርጠዋል። ወካይ ወረዳዎችን በመምረጥ ረገድ ክልሎች የተጠቀሙበት መመዘኛዎች እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል።

2.5.1 በቂ ዝናብ የሚያገኙ እህል አምራቾች
2.5.2 ዝናብ አጠር እህል አምራቾች
2.5.3 በተደጋጋሚ ለድርቅ የተጋለጡ
2.5.4 አርብቶ አደር አካባቢ
2.5.5 ለውጪ ንግድ የሚሆኑ ምርት አምራቾች
2.5.6 የሕዝብ ጥግግት
2.5.7 የግብርና ቀጠና (ቆላ፣ ደጋ፣ ወይናደጋ)
2.5.8 በምግብ ራስን መቻል (ትርፍ አምራች)
2.5.9 በምግብ ራስን አለመቻል (ትርፍ አምራች ያልሆኑ)
2.5.10 የልማት ደረጃ ልዩነት
2.5.11 ልዩ ባህሪ ያላቸው ወረዳዎች (ጠረፍ ወረዳዎች፣ ለኢንቬስትመንት አመቺ የሆኑ፣ ስደተኞች አካባቢ)
2.5.12 የብሔር ብሔረሰቦች ተዋጽኦ
2.5.13 ለመሠረተ ልማት አቅርቦት ያላቸው
2.5.14 በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የተጎዱ

2.6 ወካይ የምክክር ወረዳ ተሳታፊዎችን መምረጥ

በተመረጡት ወካይ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩትን ሕዝብ የሚወክሉ ሃምሳ የምክክር ተሳታፊዎችን መምረጥ ሌላው ተግባር ነበር። የተሳታፊዎች ጥንቅርን በተመለከተ 60 ከመቶ ከነዋሪው፣ 20 በመቶ መንግስታዊ ከሆኑ ድርጅቶችና ቀሪው 20 በመቶ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራትን እንዲወክሉ ተደርጓል። በዚህ ረገድ በአብዛኛው ክልል በቅድሚያ የተከናወነው ስራ፣ የቅስቀሳ ሴሚናር በማካሄድ ሕዝቡ ግንዛቤ

CCRDA

እንዲጨብጥ ማድረግ ነው። በመቀጠልም የክልል ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የወረዳ ምክክርን ለመምራት ከተመረጡ ሰዎች ጋር በመሆን፣ የወረዳውን ሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት መሪዎች፣ የጐሳ መሪዎችና እንዲሁም ሕብረተሰቡን በማማከር የወረዳውን ሕዝብ ይወክላሉ የተባሉ 50 ተሳታፊዎች እንዲመረጡ ተደርጓል። የሴቶች ተሳትፎ ጉልህ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ በተሳታፊዎች መረጣ ወቅት ትኩረት ተሰጥቶታል። በዚህም መሠረት ሴቶች እስከ 30 ከመቶ ድርሻ እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል። በብዙ የምክክር ወረዳዎች እንደታየው ሴቶች ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረጋቸው የሚታወቅ ነው።

2.7 <u>የወረዳ ምክክር መሪዎች መምረጥ</u>

የወረዳ ምክክርን በአግባቡ በመምራት፣ ከምክክሩ የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት፣ ምክክሩን በሰብሳቢነት ሊመሩ የሚችሉና በምክክሩ ሂደት የተነሱ ጉዳዮችን ሊዘግቡ የሚችሉ ሰዎችን መምረጥ ሌላው ቅድመ የወረዳ ምክክር ተግባር ነው። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ የምክክር ወረዳዎች አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዘጋቢዎች እንዲኖራቸው በመወሰን፣ የእነዚህም ሰዎች አመራረጥ የሚከተሉትን መመዘኛዎች መሠረት ያደረገ ነበር።

- በሕብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸው
- በአካባቢው ረዥም ጊዜ የኖሩ
- ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ነጻ የሆኑ
- የአካባቢውን ቋንቋ የሚናገሩ
- ስለአካባቢው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በቂ ግንዛቤ ያላቸው
- ስብሰባን በመምራት፣ ቃለ ጉባዔ በመያዝና ሪፖርት በማጠናቀር ልምድ ያላቸው።

2.8 <u>የወረዳ ምክክር መሪዎች ስልጠና ማካሄድ</u>

ለተመረጡት የወረዳ ምክክር መሪዎች የሶስት ቀናት ስልጠና በየክልሉ ተሰጥቷል። ስልጠናው የተሰጠው በድህነት ጽንሰ ሀሳብ፣ በሀገሪቱ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ላይ ጭምር ሲሆን፣ ያተኮረው

CGRDA

ግን ከወረዳ ምክክር የሚጠበቀውን ውጤት በአግባቡ ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ነበር:: በዚህም መሠረት በስብሰባ ሂደት አመራር፣ የወረዳ ምክክር አጀንዳ ቀረጻ፣ የወረዳ ምክክር ፕሮግራም ዝግጅትና የወረዳ ምክክር ቃለ ጉባዔ አያያዝና ሪፖርት ጥንቅር ላይ ጊዜ፣ ሙያዊ ብቃትና ጉልበት የጠየቀ ስልጠና ለወረዳ ምክክር መሪዎች ተሰጥቷል::

የወረዳ ምክክር በአግባቡ ተካሂዶ፣ የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት የወረዳ ምክክር መሪዎች ሚና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነበር:: ስለዚህ የወረዳ ምክክር መሪዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት ሊወጡ የሚያስችላቸው ክህሎት ሶስት ቀን በሚቆይ ስልጠና መስጠት ይቻላል ለማለት አያስደፍርም:: ሆኖም ይህንን ክፍተት በመዝጋት የሚፈለገውን ብቃት ለመፍጠር ስልጠናው ሙያዊ ብቃትና ከፍተኛ ልምድ ባላቸው አሰልጣኞች እንዲሰጥ ተደርጎ ምክክሩን ስኬታማ ለማድረግ ተችሏል::

III. የክልል ምክክር

ከጥር 29 እስከ የካቲት 11 ቀን 1994 ባሉት ጊዜያት ውስጥ የክልል ምክክር በዘጠኝ ክልሎች፣ እንዲሁም በአፋር ከየካቲት 30 እስከ መጋቢት 2 ቀን 1994 ተካሂዷል:: በአጠቃላይ ከ2000 ያላነሰ ሕዝብ የክልል ምክክርን ተሳትፈዋል:: በየክልሉ የሚካሄደው ምክክርን ስኬታማ ለማድረግ በቅድሚያ የሚከተሉት ሁለት መሠረታዊ ስራዎች ተከናውነዋል::

3.1 የክልል ምክክር ማዕቀፍ ማዘጋጀት

በየክልሉ የሚካሄደው ምክክር አንድ ወጥ እንዲሆን፣ ግልጽ አላማ ላይ እንዲመሠረትና በሁሉም የሚመለከተው የክልል አካላት ላይ የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር፣ ከምክክሩ የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ በቅድሚያ የክልል ምክክር ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል:: ይህ ማዕቀፍ በፌዴራልና በክልል የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል::

CCRDA

3.2 ለክልል ምክክር መሪዎች ስልጠና መስጠት

በደብረዘይት ስራ አመራር ኢንስቲትዮት ለክልል ምክክር መሪዎችና የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል። ጥር 6 እና 7 ቀን 1994 በተካሄደው በዚህ ስልጠና ላይ ከአፋር በስተቀር ሁሉም ክልሎች ተካፍለዋል።

ስልጠናው ያተኮረው በፌዴራል ጽ/ቤት የተዘጋጀው የክልል ምክክር ማዕቀፍ ላይ ውይይት በማድረግ፣ ከክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማዕቀፉ እንዲገናዘብ ማድረጉ ላይ ነበር። በዚህም መሠረት በማዕቀፉ ላይ ጥልቀት ያለው ውይይት በማድረግ፣ ከየክልሉ የመጡት ተሳታፊዎች ማዕቀፉ የክልላቸውን ሁኔታ እንዲያንፀባርቅ በሰጡት ማስተካከያ መሠረት የመጨረሻው ኮፒ ወጥቷል።

IV. የወረዳ ምክክር አንኳር ግኝቶች

4.1 የድህነት ምንነት?

በአብዛኛው የወረዳ ምክክር ተሳታፊዎች አመለካከት፣ ድህነት ማለት ለመኖር የሚያስፈልጉ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች ያለሚሟላት ወይም ጨርሶ ማጣት ነው። የድህነት መገለጫዎች ናቸው ተብለው በህብረተሰቡ ከተነሱት ዋናዎቹ የምግብ ማጣት፣ የጤና ችግር፣ መጠለያና ልብስ ማጣት፣ የእርሻ መሬት አለመኖር ወይም እጥረት፣ ስራ አጥነትና የስራ መስክ ውስንነት፣ የጎዳና ተዳዳሪነት፣ ዝሙትነትና ልመና መስፋፋት ናቸው። የድህነት ሁኔታን በተመለከተ በአብዛኛው ተሳታፊዎች አመለካከት እየተባባሰ እንደሆነ ሲገለጽ፣ ኑሮን ለማሻሻል ጥረት ቢያደርጉም ፍጹም ከድህነት መላቀቅ እንዳልቻሉ ገልፀዋል።

4.2 የድህነት መንስኤዎችና እያባባሱ ያሉ ምክንያቶች

በሁሉም የምክክር ወረዳዎች ለድህነት መንስኤ ናቸው ተብለው የተገለጹት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊና ባህላዊ ይዘት አላቸው። ድህነትን ለመቀነስ በሁሉም ዘርፍ መረባረብ እንደሚያስፈልግ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። ጎጂ ባህሎችን ማስወገድ ለድህነት ቅነሳ ከፍተኛ ሚና ስላለው፣ ህብረተሰቡ ራሱን አደራጅቶ መንቀሳቀስ እንዳለበት

CCRDA

በተለይ የእድሜ ባለፀጋ የሆኑ አዛውንት ተሳታፊዎች አሳስበዋል። ከዚህ በታች ለማመልከት የተሞከረው በአብዛኛው ተሳታፊዎች የተነሱትን ዋና ዋና የድህነት ምክንያቶች በገጠርና በከተማ በመለየት ነው።

ገጠር

- የአመታዊ፣ የቋሚ ሰብልና የእንስሳት ምርታማነት ዝቅተኛ መሆን፣
- የመሬት ጥበት። ይህም እያደገ በመጣው የሕዝብ ቁጥር እድገት መባባስ፣
- የኤድስ መስፋፋት
- ውስን ገቢን በአግባቡ አለመጠቀምና የቁጠባ ባህል አለመዳበር፣
- የንጹህ ውሃ እጥረት። በዚህም ምክንያት ሕብረተሰቡ ለተለያዩ የውሃ ወለድ በሽታዎች በመጠቃት ጤናው መታወኩ፣ እንዲሁም ሴቶችና ሕጻናት በውሃ ፍለጋ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ማጥፋት፣
- በመጠንና በጥራት ዝቅተኛ የሆነ የጤናና የትምህት አገልግሎት። በዚህም ምክንያት በቀላሉ ሊወገዱ በሚችሉ በሽታዎች (ወባ፣ ታይፎይድ፣ ማጅራት ገትር) ህብረተሰቡ እየተጠቃ መሆኑ፣
- የገበያ ችግር። በዚህም ምክንያት ገበሬው ላመረተው ምርት ተገቢውን ዋጋ አለማግኘት፣
- የቤተሰብ ቁጥር መብዛትና በቤተሰብ ውስጥ የጥገኛው ቁጥር ከፍተኛ መሆን፣
- ስራ አጥነት። በተለይ በገጠሩ ከግብርና ውጪ አማራጭ የስራ መስኮች ፍጹም ውስን መሆን፣
- ቢሮክራሲና ፖሊሲን በአግባቡ አለመተግበር፣
- በቂ የመንገድ አገልግሎት አለመኖር። ይህም ግብዓትና ምርትን በአግባቡ ለማጓጓዝ ማነቆ መሆን፣
- የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ አለመጠቀምና አለመንከባከብ። ይህም ለአፈር ለምነትና ለድርቅ መባባስ አንዱ ምክንያት መሆን

ከተማ

- በአብዛኛው ከተማ ተሳታፊዎች እንደተገለጸው ዋና ዋና የድህነት ምክንያቶች ሥራ አጥነት፣ የጤናና የትምህርት አገልግሎት በጥራትም ሆነ በመጠን ዝቅተኛ መሆን፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ

CCRDA

መስፋፋት፣ ጎጂ ባህሎች፣ በቤተሰብ ውስጥ የጥገኛ ቁጥር ከፍተኛ መሆንና የቤተሰብ ምጣኔ አለመስፋፋት ናቸው::

<u>ለድህነት መባባስ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊና የግል ባህሪያት</u>

የኢትዮጵያ ድህነት አስከፊ ደረጃ ላይ በደረሰበት ሁኔታ ሊቀረፉ የሚችሉ በርካታ ጎጂ ባህሎች እያባባሱት ይገኛሉ:: ወደፊት በሀገሪቱ ትርጉም ባለው መልክ ድህነትን ለመቀነስ፣ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል:: ድህነትን ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶችንና የሚገኙትን ውጤቶች በአግባቡ በመጠቀም ለበለጠ ትግል አቅምን ለመገንባት፣ ጎጂ ባህልን ማስወገድ ቀላል ግምት ሊሰጠው አይገባም::

በአብዛኛው ተሳታፊዎች ድህነትን ያባብሳሉ ተብለው የተጠቀሱት ጎጂ ባህሎች የሚከተሉት ናቸው::

- የጥሎሽ ክፍያና የሰርግ ዝግጅት:: በሬን ከመሸጥ ጀምሮ ያለውን ውስን ሀብት እስከሚሟጠጥ ድረስ፣
- የቀብርና የሀዘን ስርዓት መንዛዛት፣
- ድርብ ጋብቻ፣
- ሱሰኝነት /ስካር/፣
- ስራ መናቅ፣
- የሴቶች ጠለፋ፣
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣
- የሴቶች የስራ ጫና፣
- የባዕድ አምልኮ፣
- ልመናና የተረጂነት ስሜት፣
- ሀይማኖታዊ የበዓላት ቀናትን ምክንያት በማድረግ አለመስራትና መደገስ፣

4.3 <u>አስተዳደራዊ ችግሮች</u>

- የወረዳም ሆነ የቀበሌ አስተዳደር አካላት ሙያዊ ብቃት ዝቅተኛ መሆን፣
- ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመዳበር፣

CCRDA

- በልማትም ሆነ በፀጥታ ችግሮች ላይ ወቅታዊና ፍትሐዊ ውሳኔ አለማግኘት፣
- የቅንጅት ስራ አለመኖር
- ተደጋጋሚ የአስተዳደራዊ መዋቅር ለውጥ፣
- የክትትልና የግምገማ ስርዓት በሁሉም የልማት መስክ አናሳ መሆን፣
- መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያካሂዱት ፕሮግራም ሕዝቡን በየደረጃው በበቂ ሁኔታ ያሳተፈ አለመሆን፣
- የፍትሕ መዛባትና መጓተት፣
- ባለሙያን በአግባቡ አለመጠቀምና ከፍተኛ የባለሙያ ፍልሰት መኖር
- የልማትና የፖለቲካ ስራ መቀላቀልና መጋጨት፣
- ራስ ወዳድነት

4.4 <u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች</u>

- የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ
- የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ
- የኤድስ ስርጭትን መግታት
- የስራ ዕድሎችን መፍጠር:: በተለይ በገጠሩ አካባቢ ከግብርና ውጪ የሆኑ የስራ መስኮችን ማስፋፋት::
- የሴቶች የስራ ጫናን የሚቀንሱ ፕሮግራሞች ማካሄድ
- ጎጂ ባህሎችን በማስወገድ ገቢን በአግባቡ መጠቀምና የቁጠባ ባህልን ማዳበር
- ሕብረተሰቡን መሠረት ያደረገ ዘለቄታነት ያለው ሰፊ የአካባቢና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራዎች ማካሄድ
- የተረጂነት አመለካከትን በማስወገድ የራስ መተማመን በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እንዲሰርጽ ማድረግ
- የጤናና የትምህርት ተቋማትን በሰው ኃይልና በማቴሪያል ማደራጀትና የአገልግሎቱን ጥራት ማሻሻል፣
- የብድር አገልግሎት ማስፋፋት:: ከዚህም ጋር አበረታች የሆነ የብድር አሰጣጥና አከፋፈል ስርዓት መዘርጋት፣
- የስነ ተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞችን ማስፋፋት
- መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያካሂዱት ፕሮግራም የሕብረተሰቡን ፍላጎት ያንፀባረቀና ዘለቄታዊነት

CCRDA

እንዲኖረው ለማድረግ ከቀረጻ እስከ ክትትልና ግምገማ ድረስ በቅድሚያ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ እንዲሆን ማድረግ::

- በወረዳና በክልል ደረጃ የሚንቀሳቀሱ የልማት ኃይሎች በቅንጅት እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስልት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፣

4.5 <u>ለድህነት የተጋለጡ የህብረተሰቡ ክፍሎች</u>

- ሚሪ የሌላቸው አረጋውያን፣
- በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት፣
- ባሎቻቸው በጦርነት የሞቱባቸው ሴቶች፣
- የጎዳና ተዳዳሪዎች፣
- ከገጠር ወደ ከተማ ፈልሰው የመጡ ሰዎች፣

4.6 ማጠቃለያ

ከወረዳና ክልል ምክክር ሂደት በተገኘው መረጃ መሠረት የሚከተሉት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ወይም ጉዳዮች የተጠናከረ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ መገንዘብ ተችሏል::

- ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ
- የግብርና ምርታማነትን በሁሉም የምርት ዓይነቶች ማሳደግ
- የትምህርትና የጤና አገልግሎትን በመጠንና በጥራት ማሻሻል
- የመንገድ ሥራን ማስፋፋት
- የውሃ አገልግሎትን ማጠናከር
- የአነስተኛ ብድር አገልግሎትን ማስፋፋት
- የሥነ ተዋልዶ ፕሮግራምን ማጠናከር
- ጎጂ ባህሎችን ማስወገድ
- መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የልማት እቅዶች አፈጻጸም አስተዳደርን ማሻሻል
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ልማትን ማጠናከር
- ኤች.አይ.ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር

CCRDA

የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት

የትግራዩ የክልል ምክክር ሰነድ ሪፖርት

CCRDA

የፌደራልና ሲኦ/ልማት ቢሮ
መጋቢት 1994
መቐሌ፣

የትግራይ ክልል ማህበረ - ኢኮኖሚ ገፅታ

የትግራይ ብሄራዊ ክልል ከኢትዮጵያ አንዱ ሲሆን በሰሜን ከኤርትራ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በምዕራብ ከሱዳንና በደቡብ ከአማራ ብሄራዊ ክልል ጋር ይዋሰናል።

ክልሉ ሶስት አስተዳደራዊ እርከኖች አሉት። እነሱም የክልል፣ የወረዳና የጣብያ /የቀበሌ/ መስተዳድሮች ተብለው ይለያሉ። በእነዚህም የመስተዳድር እርከኖች ውስጥ፡-

- 6 ዞኖች
- 47 ወረዳዎች/12 የከተማና 35 የገጠር ወረዳዎች/
- 620 ጣብያ/የቀበሌ/ 92 የከተማና 528 የገጠር ጣብያዎች/ ይገኛሉ።

ክልሉ 53638 ስኳር ኪ/ሜትር ስፋት እንዳለው ሲገመት በ1994 ዓ/ም ብክልሉ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው የህዝብ ብዛት አሰፋፈር በዞን ሲቀመጥ የሚከተለው ምስል ይኖረዋል።

ተ ቁ	ዞን	የ1994 የህዝብ ብዛት ግምት	ስፋት በስኳር ኪ/ሜ	አሰፋፈር
1	ምዕራባዊ	906544	27355	33.2
2	ደቡባዊ	904425	10567	81.2
3	ማእከላዊ	1161464	10352	112.2
4	ምስራቃዊ	727231	5363.8	135.5
5	መቀሌ	141433	--	344.3
6	ትግራይ	3901000	53638	72.7

ከዚህ ከላይ ከተጠቀሰው የክልሉ የመሬት ስፋት ውስጥ 28 በመቶ የሚሆነው ብቻ ለእርሻ ሊውል የሚችል ሲሆን ከዚህም ውስጥ ወደ 19 ከመቶ የሚሆነው ብቻ ነው ስራ ላይ እየዋለ ያለው። ከአንድ በመቶ በታች የሚሆነው ደግሞ በደን የተሸፈነ መሆኑ ይገመታል።

CCRDA

የክልሉ መልከአ ምድር ተራራማና ወጣ ገባ የበዛበት ነው። የባህር ወለል ከፍታውም ከ600 ሜትር /ሑመራ አከባቢ/ እስከ 3935 ሜትር /ማይጨው አከባቢ የሚገኘው ዕበት ተራራ/ ይሆናል። ይህ የከፍታ መለያየት የክልሉን የአየር ጠባይ የተለያየ እንዲሆን አስገድዶታል። በዚህም መሰረት ከፍተኛው የሙቀት መጠን እስከ 40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የሚደርስ ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ እስከ 5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይደርሳል። ክልሉ የሚያገኘው ዓመታዊ የዝናብ መጠንም ከ300 -- 1000 ሚ/ሜትር እንደሚደርስ ይገመታል። በክልሉ ያለው ዝናብ መሰረታዊ ጠባዮች የሚከተሉት ናቸው።

- ዘግይቶ የመጀመር
- ቶሎ የማቋረጥ
- በሁሉም ቦታዎች ያልተመጣጠነ መሆኑ
- በኣጭር ጊዜ ከፍተኛ ዝናብ ይጥላል። በዚህም ምክንያት
  - የሰብሎች ምርትና ምርታማነት ይቀንሳል
  - የኣፈር መሸርሸር ያስከትላል
  - የመሬት እርጥበት ይቀንሳል

በ1994 ዓ/ም ትንበያ መሰረት 3.901 ሚልዮን ህዝብ በክልሉ እንደሚኖር ይገመታል። ከዚህ የህዝብ ብዛት ውስጥ 49.2 በመቶ ወንዶችና ቀሪው 50.8 በመቶ ሴቶች ናቸው። 82.5 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ህዝብ በገጠር የሚኖርና ኑሮውም በአብዛኛው በዝናብ ውኃ በሚለማው የግብርና /Rain fed agriculture/ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ የተመሰረተ ነው ቀሪው 17.5 በመቶ ደግሞ በከተማ የሚኖር ሆኖ በተለያዩ የንግድ ስራዎችና በመንግስት በሰራተኛነት የሚተዳደር ይሆናል።

የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የእድገት ደረጃን ለመለካት ከ1987 -- 1991 ዓ/ም ያለውን የክልሉን አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት /RGDP/ ግመታ ጥናት ተካሂዶ ነበር። ከዚሁ ጥናት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው

- በ1987 ዓ/ም የክልሉ አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት ብር 2.9 ቢልዮን የነበረው
- በ1991 ዓ/ም የክልሉ አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት ብር 3.3 ቢልዮን ደርሷል።
- ይህም በየዓመቱ በአማካይ የ6.7 በመቶ እድገት ማሳየቱን ያመለክታል።

በተመሳሳይ መልኩ የነብስ ወከፍ ገቢም ተጠንቷል። የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተውም

CCRDA

- በ1987 ዓ/ም የክልሉ የነብስወከፍ ገቢ መጠብ ብር 830 የነበረው
- በ1991 ዓ/ም የክልሉ የነብስወከፍ ገቢ ብር 926 ደርሷል::
- ይህም በአማካይ በየዓመቱ የ2.9 በመቶ እድገት እንዳሳየ ያመለክታል::

ይህ የሚያሳየው አሁንም ከድህነት መስመር በታች የሚኖር የህዝብ ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ነው:: የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በ1991 ዓ/ም ያካሄደው ጥናት እንደሚያመለክተው ከትግራይ ክለለ ህዝብ ውስጥ 57:9 በመቶ የሚሆነው ከድህነት መስመር በታች እንደሚኖርና ከሁሉም ክልሎች ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ ይገኛል:: ይህንን ለማቃለልም መንግስት ከህዝብ፣ ከመያዶችና የግል ባለሃብቶች ጋር በመተባበር ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችለው ስትራተጂ ለመንደፍ በሂደት ላይ ይገኛል::

በድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ዝግጅት ሂደት ሰነዱ የሁሉም የልማት ሃይሎች ሃሳብ ያካተተ እንዲሆን ለማድረግ በወረዳ፣ በክልልና በፌዴራል የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው እየተካሄዱ ይገኛሉ:: በትግራይ ክልልም የወረዳ ምክክር በስምንት ወረዳዎች ከታህሳስ 19 -- ጥር 4/1994ዓ/ም የተጠቃለለ ሲሆን የካቲት 2 -- 3/1994 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ ደግሞ የክልል ምክክር ተከሂዷል:: በሁለቱም የምክክር መድረኮች የተገኙ ተሳታፊዎች ብዛትና ዓይነት በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል::

ተ.ቁ	ዝርዝር	በወረዳ ምክክር	በክልል ምክክር	ጠቅላላ
1	የገበሬ ተወካዮች	209	--	209
2	የሃይማኖት መሪዎች	18	--	18
3	የመንግስት ሰራተኞች	92	117	209
4	ከመያዶች	9	13	22
5	ከህዝባዊ ማህበራት	77	17	94
	ድምር	402	147	549

ከወረዳና ከክልል ምክክሮች በተገኙት ውጤቶች በመንተራስም የክልሉ የድህነት ሁኔታ፣ በክልሉ የድህነት መንስኤዎች፣ በክልሉ የድህነትን ሁኔታ ለማቃለል በሁሉም የልማት ሃይሎች የተወሰዱ እርምጃዎች፣ ለወደፊቱ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችና የድህነት ማቃለያ ስትራተጂው ተግባራዊ ለማድረግ መወሰድ ያለባቸው ታሳቢዎች ያጠቃለለ አጭር ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል::

CCRDA

የክልሉ የድህነት መገለጫዎች

ድህነት ማለት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ማለትም ምግብ፣ ልብስ፣ መጠሊያና ከእነዚህ ጋር አብረው የሚሄዱ የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ መሰረታዊ የጤና አገልግሎቶችና ትምህርት፣ የመኖሪያ ቤት ወዘተ አለመሟላት ማለት ነው:: በክልሉ የድህነት መገለጫዎችም የሚከተሉት ናቸው::

- አማካይ የመኖር እድሜ/Life expectancy/ አጭር ነው:: የክልሉ አማካይ የመኖር እድሜ ለሁለቱ ፆታዎች 50 ዓመት/በሃገር አቀፍ ደረጃ 52 ዓመት/ ሲሆን ለወንዶች 48 ዓመት፣ ለሴቶች 51 ዓመት ነው::
- የህፃናትና እናቶች መታመምና መሞት መጠን መብዛት/High rate of morbidity & mortality/ ሌላው የድህነት መገለጫ ነው:: የቅድመና ድህረ ወሊድ የጤና አገልግሎት ተጠቃመሚ ሴተቶች ቀ4ጥር በጣም አነስተኛ ነው:: ከ90 በመቶ በላይ ሴቶች ያለምንም የጤና ባለሙያ እገዛ በቤታቸው የሚወልዱ ናቸው:: በዚህም ምክንያት ለተለያዩ የወሊድ ችግሮች የሚጋለጡ ሴቶች ቡዙ ናቸው:: የህፃናት ጠ ንነትም ቢሆን ከእናቶቹ የተለየ አይደለም:: በክልሉ ከሚወለዱት 1000 ህፃናት ውስጥ 104ቱ የመጀመሪያ ዓመታቸው ሳያከብሩ፣ 169ቱ ደግሞ አምስተኛ ዓመታቸው ሳያከብሩ እንደሚሞቱ ጥናቶች ያመለክታሉ::
- የማእከላይ ስታትስቲክስ ባለስልጣን በ1987 ዓ/ም ያካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት መሰረት የክልሉ ምጣኔ-ወሊድ/Fertility rate/ 5.4 በመቶ ሆኖ ይኸውም በከተማ 4.2 በመቶ፣ በገጠር 5.6 በመቶ ነው:: ይህም ከፌደራሉ ምጣኔ-ወሊድ/4 በመቶ/ ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ ነው:: ምጣኔ ወሊድ በበዛ ቁጥር ደግሞ ለጤና ችግር የሚጋለጡ የሴቶች ቁጥር ስለሚጨምር የቤተሰብ የህክምና ይጨምራል:: በተጨማሪም ሴቶች በልማት ስራ ሊያውሉት የነበረው ጊዜ ይቀንስባቸዋል:: እነዚህ ሁኔታዎች የቤተሰብ ገቢ እንዲቀንስና ከዛም አልፎ ለድህነት ሊጋለጡ ይችላሉ::
- ትግራይ ለረሃብና ለስደት መጋለጥ አይሎ የሚታይበት ክልል ነው:: በክልሉ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው የህዝብ ብዛት ውስጥ አንድ ሶስተኛ የሚሆነው የምግብ እህል እጥረት ስለሚያጋጥመው በየዓመቱ ከመንግስት/ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች/ የእህል እርዳታ ይጠብቃል:: ካልሆነ ህይወታቸው በአደጋ ላይ ይወድቃል:: ይህንን መሰል ችግር አይሎ የሚታየው ዝናብ አጠርና የአፈር ለምነት ከመጠን በላይ የተጓደለባቸውና በዚህም ምክንያት የምግብ ዋስትና የሌላቸው ተብለው በተፈረጁት 16 ወረዳዎች የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው::

CCRDA

- ስራ ማጣትም እያየለ በመምጣት ላይ ያለ የድህነት ሁኔታ አመላካች ነው:: በክልሉ መስራት ከሚችለው ህዝብ ውስጥ 6.5 ፐርሰንት ስራአጥ መሆኑ የማእከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን በ1991 ዓ/ም ባካሄደው ጥናት አረጋግጦታል:: በዚህ ላይ ከኤርትራ ጋር በተካሄደው ጦርነት ምክንያት የተፈናቀሉና በገጠሩ አከባቢ የሚታረስ መሬት የማግኘት እድል ያላጋጠማቸው ሰዎች ሰደመሩ በክልሉ የስራ አጡ ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል መገመት አያዳግትም::
- የመሃይምነት መስፋፋትና የአከባቢ ንፅህና መጓደልም ዓይነተኛ የክልሉ ድህነት መግለጫዎች ናቸው:: አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከጠቅላላ ሴቶች 77 በመቶና ከጨቅላላ ወንዶች 65 በመቶ ያልተማሩ መሆናቸው የስታትስቲክስ ባለስልጣን በቅርቡ ያወጣው ጥናት ያመለክታል:: በአንደኛ ደረጃ መማር ከሚገባቸው ከ10ሩ 7.2 እንደሚማሩ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ 20.5 በመቶ ብቻ የመማር እድል እንዳጋጠማቸው ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ:: ያልየማረ ህዝብ ስለ የአከባቢ ንፅህና አጠባበቅ ዘዴዎች ቡዙም እውቀት ስለማይኖረው መጓደላቸው አይቀሬ ነው::

<u>በክልሉ የድህነት መንስኤዎች</u>

በክልሉ ለድህነት መስፋፋት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ምክንያቶች እንደየባህርያቸው ተፈርጀው ሲቀርቡ የሚከተሉት ይመስላሉ::

1. <u>ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች</u>

   የድሃ ጎብረተሰብ ኑሮ በአብዛኛው የሚመሰረተው በተፈጥሮና አከባቢውን መሰረት ያደረገ ነው:: በመሆኑም የህዝቡ ቁጥር እየጨመረ በመጣ ቁጥር በአከባቢው የሚገኘውን የተፈጥሮ ሃብት በተፋጠነ ሁኔታ እየተራቆ ፣ መሄዱ የግድ ይሆናል:: ይህም ድህነት እየተስፋፋ እንዲሄድ ያስገድደዋል:: ድህነትን ከሚያባብሱ ተፈጥሮአዊ ክስተትች መካከል የሚከተሉት ይገኝበታል::

   - ተደጋጋሚ ድርቅ
   - ወቅቱ ያልጠበቀ ዝናብ
   - የሚፈለገው መጠን ዝናብ አለማግኘት
   - የደን መመናመን
   - በቀጣይነት የለም አፈር መሸርሸር

CCRDA

- የማገዶ እንጨት እጥረት በመኖሩ የአፈርን ለምነት ሊያዳብሩ የሚችሉ ተረፈ ምርት /ቅጠላቅጠል፣ የገለባና የአገዳ ሰብሎች ትራፊ/ እና ኩበት ለማገዶነት መጠቀም
- የእርጥበት መቀነስ

2. <u>ፖለቲካዊ ምክንያቶች</u>

በዚህ ስር የተጠቀሱ ምክንያቶች የኣስፈላጊ ፖሊሲዎች መውጣትና በተግባር ላይ ማዋል፣ ህዝቡ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ማድረግ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል:: በዚሁ መስክ የተያዙ ችግሮች

- የፈፃሚ አካላት አቅም ማነስ
- በፈፃሚ አካላት በኩል ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር
- የወጡ ፖሊሲዎች ያለባቸው የአፈፃፀም ችግር
- የእርሻ መሬት በገበሬ እጅ የሚቆይበት ጊዜ የሚጠቁም ፖሊሲ አለመኖር
- ተፈጥረንና አከባቢን ለመንከባከብ የወጡት ፖሊሲዎች በህዝቡ ዘንድ አለመታወቃቸው
- ጦርነቶች

<u>3. ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች</u>

ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች ተብለው የተፈረጁት

- የኅብረተሰቡን ጉልበት፣ ልምድና እውቀት ለኢኮኖሚ ልማት ስራዎች በቀጣይነት አለመጠቀም
- በአከባቢው ለሚመረቱ ሰብሎች /የቅባት እህሎች/ በቂ ገበያ ማጣት
- የብድር አገልግሎት የሚሰጡና ሰለ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም የምክር አገዕልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች አለመስፋፋት
- ላለው ጉልበት በቂ ገበያ አለማግኘት
- ትምህርት እንደሚፈለገው አለመስፋፋቱና እድሚያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናን የትምህርት እድል አለማግኘታቸው::

CCRDA

- የተሰሩ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በቀጣይነት አገልግሎታቸው እንዲሰጡ አለማስቻል
- የመኖሪያ ቤት ችግር
- ለኃላቀር ባህሎችና ልምዶች መገዛት
- የቁጠባ ባህል አለመዳበር
- ስራአጥነት
- ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴዎች በገበሬው ዘንደ በስፋት አለመጠቀም
- የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሽታ መስፋፋት
- የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት በበቂ አለማዳረስ
- የኤሌክትሪክ፣ የስልክና የፖስታ አገልግሎቶች አለማዳረስ
- አምራች በሆኑ ወረዳዎች የመኪና መንገድ አለመስፋፋት

<u>እስከአሁን ድህነትን ለመቀነስ የተወሰዱ እርምጃዎች</u>

በክልሉ ድህነትን ለመቀነስ በመንግስት፣ በመያዶችና በህዝቡ ጥረት የሚከተሉትን አበይት ስራዎች ተከናውኗል።

- ከደርግ ውድቀት ማግስት ጀምሮ የወደሙትን የመሰረተ ልማት አውታሮች መልሶ ለመገንባት የሚያግዝ የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ተነድፎ በስራ ላይ እንዲውል ጥረት ተደርገዋል።
- ገጠርን ማእከል ያደረገ ሁለገብ የልማት ስትራተጂ ተነድፎ ተግባራዊ እንዲሆን ተሞክሯል።
- ገበሬው ከተለያዩ ዘመናዊ የእርሻ አሰራር ዘዴዎችጋር ለማስተዋወቅና ከየአከባቢው የአግሮ ኢኮሎጂያዊና የእርጥበት ሁኔታ ጋር በማዛመድ እንዲጠቀምባቸው የሚያስችሉት ስልጠናወችና የማስተዋወቅ ስራዎች ተካሂዷል።
- የሴቶችን ችግር ለማቃለል የሚያግዙ መጠነኛ እንቅስቃሴዎች ተካሂዷል።
- የግል ኢንቨስተሮችን ለማበረታታት የመጀመሪያ ደረጃ ስራዎች ተሰርቷል።
- የመኖሪያ ቤቶች እጥረት ለማቃለል ጥረቶች ተደርጓል።
- የትምህርት፣ የጤናና የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ በከተማና በገጠር ለማዳረስ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በተጨማሪም ከተሞች የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የስልክና የፖስታ ኣገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል። የዋና መንገዶች

CCRDA

ጥገናና አዳዲስ የገጠር መንገዶች ስራ ተከናውኗል። እያንዳንዲ ወረዳም ከዞንና ከክልል ጋር የመገናኘት እድል ተፈጥሮለታል።

<u>ሰመደፊቱ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች</u>

ድህነትን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ እንዲቻል ትክክለኛና ከክልሉ ተጠባጭ የድህነት ሁኔታ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መፍትሄዎች መስቀመጥና መተግበር አስፈላ ነው። እነዚህ የድህነት ማቃለያና ማስወገጃ መፍትሄዎች በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ሶሚተገበሩ ተብለው ቢለዩ ለአፈፃፀም አመቺነት ይኖራቸዋልና በዛ መልኩ ተለይተው ቀርቧል።

1. <u>በአጭር ጊዜ ሊከናወኑ የሚገባቸው</u>

- መንግስት ግልፅና ወደ ተግባር ሊያሸጋግረው የሚችል የተፈጥሮና አከባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ማውጣት አለበት። የአጠባብቅና የአጠቃቀም ህግ እንዲወጣለትም ያስፈልጋል።
- የግል ደን ተከላን ማበረታታት
- በጥናት ላይ በመመስረት የገበሬ የመሬት ይዞታ ጊዜ ከ20 ዓመት በላይ የሚሆንበትን መንገድ ማፈላለግ
- የባዮ ጋዝ አጠቃቀም ማስተዋወቅና ማስፋፋት
- በጥናት ላይ በመመስረት ከየአከባቢው አግሮ ኢኮሎጂ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ የዛፍ ዓይነቶች መትከል
- መተኪያ የሌላቸው ተፈጥሮአዊ አከባቢዎች መንከባከብ
- ተከታታይነት ያለው የአፈርና ውኃ ጥበቃ ስራን በሰፊው ማካሄድ
- ቶሎ ሊደርሱ የሚችሉ የአዝርእት ዓይነቶች መጠቀም
- በአመራርና አሰራር ያለው ችግር መፍታት
- የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና ደንቦች ህዝቡ እንዲያውቃቸው ማድረግ
- የአመራር አካላት አቅም በቀጣይነት ማሳደግ
- የአከባቢ ሰላምና መረጋጋት በአስተማማኝነት ማስፈን

CCRDA

2. <u>በመካከለኛ ጊዜ የሚፈፀሙ</u>

- ስለ ተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅና አጠቃቀም በሚመለከት የኅብረተሰቡን ግንዛቤ በቀጣይነት መሳደግ
- ከተሞች የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ
- በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያግዙ ፓኬጆች ማዘጋጀትና መተግበር
- የመሰረተ ልማት አውታሮችን /ትምህርት፣ ጤና፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የመንገድ፣ የስልክና የፖስታ አገልግሎቶች/ ማዳረስ
- ገበሬዎች በግላቸው የተለያዩ ዛፎችና ፍራፍሬዎች ተክለው እንዲጠቀሙ መበረታታት
- በአከባቢው ለሚመረቱ ምርቶች በቂ ገበያ እንዲያገኙ ማመቻቸት

3. <u>በረዥም ጊዜ ሊሰሩ የሚገባቸው</u>

- በከተማም ሆነ በገጠር ነዳጅ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ
- አሁን ያለው ልቅ የሆነ የእንስሳት የግጦሽ አጠቃቀም በተወሰነ የግጦሽ አጠ ቃቀም መተካት
- ኅብረተሰቡ ከኋላቀር አስተሳሰቦች፣ ልምዶችና ባህሎች እንዲላቀቅ ማስተማርና የግንዛቤ ለውጥ ማምጣት
- ኅብረተሰቡ የቁጠባ ባህል እንዲያዳብር ማገዝ
- ህዝቡ የተሻለ የአመጋገብ ስርአት እንዲከተል ማስተማር
- ኅብረተሰቡ የኤድስን በሽታ አስከፊነት በመገንዘብ እንዲከላከለው የግንዛቤ ለውጥ እንዲያመጣ በቀጣይነት ማስተማር

<u>የድህነት ቅነሳ ስትራተጂው ተግባራዊ ለማድረግ</u>
<u>መወሰድ ያለባቸው ታሳቢዎች</u>

የድህነት ቅነሳ ስትራተጂው ወደ ተግባር ሲሸጋገር ብቻ ነው በድህነት ሁኔታ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ሊመዘገብ የሚችለው:: ይህ ደግሞ ለመንግስት ብቻ የሚተው ኃላፊነት አይደለም:: የድህነትን ጫና ለመቀነስም ሆነ ለማጥፋት

CCRDA

የሁሉም የልማት ኃይሎች/መንግስት፣ ህዝብ፣ መያዶች፣ የግል ባለሃብቶች/ የተቀናጀ እንቅስቃሴ እንደሚያስፈልግ እሙን ነው:: እዚህ ላይ እንደ ዋነኛ የመንግስት ሃላፊነት ተደርጎ የሚወሰደው የልማት ኃይሎቹን ዓቅም ማሳደግ፣ ለተሳትፎአቸው የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠርና ቅንጅቱን መምራት ይሆናል:: ስለሆነም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት እንዲደረግ እንላለን

- በድህነት የሚጠቁ የጎብረተሰብ ክፍሎች ፕሮፋይል ማዘጋጀትና ለይቶ ማውጣት
- የእያንዳንዱ አከባቢ እምቅ ሃብት /Potential resources/ የሚያሳይ ካርታ መዘጋጀት ይኖርበታል::
- ስራዎች ከእያንዳንዲ የልማት ኃይል ዓቅም አኳያ ተለይተው ቢቀመጡ በአፈፃፀም ወቅት ከሚፈለገው በላይ ሪሶርስ በአንድ አከባቢ መደራረብ እንዳይከሰት ይረዳል:: ለምሳሌ መንግስት ዴሞክራሲያዊ አሰራርን በማስፈን፣ ሰላምና መረጋጋትን በማስፈን፣ በትላልቅ የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ የአስፈፃሚ አካላትን ዓቅም ግንባታና በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ቢያተኩርና ሌሎቹ ዓውደ ስራዎች ለቀሪዎቹ የልማት ኃይሎች ቢተውላቸው ይመረጣል::
- የስትራተጂው አፈፃፀም የሚከታተልና በየጊዜው እየገመገመ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚያስተባብር አካል ቢኖረው ይመረጥ ነበር:: ይሁን'ንጂ ካለው የሰው ኃይልና የገንዘብ አቅም አኳያ የሚቻል አይመስልም:: በትንሹ ቢሆንም ግን በአንድ አስፈፃሚ አካል ስር አንድ አስተባባሪ አካል /Coordinating unit/ መሰየሙ ለኢንፎርሜሽን ቅብብሎሽ ስለሚያግዝ የሚገባውን ያህል ትኩረት ማግኘት አለበት::
- የእርዳታ እህልን አሰጣጥ በነፃ መሆኑ ጉዳት እያደረሰ ያለ ይመስለናል:: ምክንያቱ በህዝቡ ዘንድ የተረጂነት መንፈስ እንዲጎለብት አስችሎታልና:: ስለዚህ የህዝቡን የመስራት ዓቅም እየተገመገመ መስራት የሚችለው ሰርቶ እንዲወስደው ቢደረግ ለልማት ስራው መፋጠን ያግዛል:: በተጨማሪም "ሰርቸ ያገኘሁት ነው" የሚለውን መንፈስ በጎብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርፅ ይረዳል:: ከዛም አልፎ ስራን የመውደድና የመፍጠር ዓቅሙ ያጎለብትለታል::
- እርዳታ ሰጪ አካላት/በተለይም የዓለም ባንክና የገንዘብ ድርጅቶች/ ድህነትን ለመቀነስና ከአገራችን ለማጥፋት ፍላጎቱ ካላቸው ለስትራተጂው መተግበር የሚያስፈልገውን ፋይናንሳዊ ሪሶርስ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠ

CCRDA

በቅባቸዋል። የአገሪቱ ዕዳ በመሰረዝ ለዕዳ መክፈያ ሊውል የነበረው በድህነት ማቃለያ ስትራተጂው ማስፈፀሚያ እንዲውል አበዳሪ መንግስታትን ማግባባት አንዱ ከድርጅቶቹ የሚጠበቅ ተግባር ሲሆን ካለምንም ፖለቲካዊ ቅድመ ሁኔታ ተጨማሪ እርዳታና ብድር በመስጠት እንዲተባበሩ ይጠበቃል። ይህ የፋይናንስ ሪሶርሰ ከተገኘ /ሎሎቹ ፋክተሮች እንደተሟሉ በመውሰድ/ ድህነትን በአስተማማኝነት ከአገራችን ለማጥፋት ይቻላል።

CCRDA